የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
ADDIS ABABA

ብሔራዊ የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ

ኧ.ኤ.አ ከ 2021– 2024

ብሔራዊ
የዲጂታል ክፍያ
ስትራቴጂ

እ.ኤ.አ.አ 2021– 2024

መቅድም

አገራችን ኢትዮጵያ ዓለምአቀፍ የዲጂታል ሽግግር አካል በመሆን እ.ኤ.አ በ2025 የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂን ሙሉ በሙሉ ለመተግበር በቁርጠኝነት በመስራት ላይ ትገኛለች፡ ፡ በዚህ ወሳኝ የሽግግር ጊዜ (ከ2021-2024) የሚተገበር የብሔራዊ የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂን በማዘጋጀት በስትራቴጂው በግልጽ እንደተቀመጠው አካታችና በኃላፊነት ስሜት የሚተገበር የዲጂታል ክፍያ ስነምህዳር መገንባት ለኢትዮጵያ ህዝብና ኢኮኖሚ እጅግ በጣም አስፈላጊ እና አስቻይ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

የዲጂታል ክፍያ አማራጮችን መተግበር ግልጽነትና ውጤታማነትን ከማስፈን፣ የሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንጻር፣ የፋይናንስ አካታችነትና ሁሉን አቀፍ እድገት ከማምጣት አኳያ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል፡፡ በጥሬ ገንዘብ መጠቀምን በመተው ወደ ዲጂታል አማራጭ መሄድ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት ያግዛል፣ የህዝቦችን የኑሮ ሁኔታ በማሻሻል አጋጣሚዎችን ይፈጥራል፡፡

በኢትዮጵያ ለዲጂታል ክፍያ ጠንካራ መሠረት ለመጣል የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተቋማት በቅንጅትና መሪ ተዋናይ በመሆን ከልማት አጋሮች ጋር በመተባበር ትልቅ ሥራ ተሰርቷል ፡፡ በዚህም ባለፉት ስድስት ዓመታት (እ.ኤ.አ ከ2014-2019) የዲጂታል ግብይት በሁለትና በሶስት እጥፍ እድገት አሳይቷል፡፡ በሞባይል የሚፈጸም ግብይት ከፍተኛውን ዕድገት በማምጣት በተጠቀሰው ጊዜ የ214 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡

እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ የዲጂታይዜሽን ጉዞ ገና በጅምር ላይ የሚገኝ ነው፡፡ በሌሎች አገራት እንደታየው በርካታ ተግዳሮቶች ወደፊት ይጠብቁናል፡፡ እነኝህን ተግዳሮቶች ለመሻገር ግልጽ የሆነ ስትራቴጂክ ራዕይ፣ በተጨማሪም ይህንን ራዕይ ለመደገፍ የሚያግዝ ስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀት ዕቅዱን ውጤታማ በሆነ አግባብ መተግበር ያስፈልጋል፡፡

ውጤታማና በኃላፊነት ስሜት የሚተገበር የዲጂታል ክፍያ ስነምህዳር በመፍጠር ሂደት የዚህ ብሔራዊ የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ዓላማ የሚሆነው ከፋይናንስ አካታችነት አንጻር ያለውን የጾታ ልዩነት ክፍተት ለመሙላት ማገዝ እንዲሁም የሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ከብሔራዊ የጾታ እኩልነት አንጻር ማጎልበት ነው፡፡

በቁልፍ ባለድርሻ አካላት መካከል የሚደረግ ውጤታማ ትብብር በሁሉም ረገድ ለስኬት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚመለከታቸውን ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በስፋትና በጥልቀት በማማከር ብሔራዊ ስትራቴጂው እንዲዘጋጅ አድርጓል፡፡ በዚህ ረገድ ሃሳባቸውን ላካፈሉና ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው በምክክር ዝግጅቶች ላይ ለተሳተፉ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በራሴ ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በነዚህ የምክክር መድረኮች ላይ የተገኙ ግብዓቶች ስትራቴጂውን በመቅረጽ የአገራችን የዲጂታል ክፍያ ፍላጎት ለማሟላት፣ ያለንን የዲጂታል አቅም ከማውጣት አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ይህንን ስትራቴጂ ሙሉ ለሙሉ ለመተግበር ቁርጠኞች መሆናችንን እየገለጽኩ በቀጣይ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት ለመስራት ያለንን ዝግጁነት አረጋግጣለሁ፡፡በተጨማሪም በዚህ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት ያለመታከት የሰሩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባለሙያዎችና ድጋፍ ላደረጉ አካላት በሙሉ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከሰትን ተከትሎ ዲጂታል ክፍያን የኢትዮጵያ ህዝብ በስፋት እንዲጠቀም በጋራ ርብርብ ለማድረግ፣ በፍጥነትና ውጤታማ በሆነ አግባብ ለመተግበር ትክክለኛው ጊዜ ላይ እንገኛለን፡፡

አዲሱ የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂያችን ኢትዮጵያ ወደ ጠንካራና በይበልጥ አካታች ወደሆነ ኢኮኖሚ በምታደርገው ጉዞ ሊያጋጥሙን የሚችሉ ተግዳሮቶችን በመፍታት ረገድ ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ እምነቴ ነው፡፡

ዐቢይ አሕመድ አሊ (ዶ/ር)
ጠቅላይ ሚኒስትር
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ይህ ሰነድ የኢትዮጵያ ዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ሰነድ ሲሆን በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ተዋቅሮ ቀርቧል፡-ስትራቲጂካዊ አውድ፣ የስትራቴጂ ማዕቀፍ፣ እንዲሁም የትግበራ ማዕቀፍን ይዟል፡፡

የዋና አውድ ክፍል ለአንባቢዎች አገራዊ መነሻ /Baseline/፣ ዓለማቀፍ መልካም ተሞክሮዎችንና በኢትዮጵያ የዲጂታል ክፍያ ከባቢ ሁኔታ ያጋጠሙ ቁልፍ ተግዳሮቶችን አስመልክቶ ግንዛቤ ይሰጣል፡፡

የስትራቴጂ ማዕቀፍ ክፍል የስትራቴጂውን ራዕይ፣ ራዕዩን ለማሳካት የሚያግዙ ስትራቴጂያዊ ምሰሶዎች፣ ለስትራቴጂው ስኬት መሰረት ሆነው የሚያገለግሉ ቁልፍ አስቻይ ሁኔታዎችን ይዳስሳል፡፡ እያንዳንዱ ስትራቴጂክ ምሰሶ አገራዊ መነሻዎችን፣ ተግዳሮቶችን፣ ዓለማቀፍ መልካም ተሞክሮዎችንና የሚተገበሩ ስትራቴጂክ ተግባራትን በማካተት በጥልቀት ይዳስሳል፡፡ የትግበራ ማዕቀፍን አስመልክቶ በተከታይ ክፍል ቀርቧል፡፡

የትግበራ ማዕቀፍ ክፍል ጥቅል የትግበራ እቅድ፣ የአስተዳደር መዋቅር እና የስትራቴጂውን ጥቅሞች ለማሳካት የሚያግዙ የክትትልና ግምገማ ስርአቶችን አካቶ ይዟል፡፡

የምስል ማዉጫ 7
አጠቃላይ 8

ሀ. ስትራቴጂካዊ ዐዉድ 10

ለ. ብሔራዊ ዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ማዕቀፍ 22
ለ1. ስትራቴጂክ ራዕይ 23
ለ2. ስትራቴጂክ ምሰሶዎች 24

ለ2.1. ስትራቴጂክ ምሰሶ 1፡ አስተማማኝ፣ አካታችና ተናባቢ መሰረተ ልማት መገንባት 24

ለ2.1.1. የአገልግሎት መስጫ አማራጮችን ቁጥር ማሳደግ 31

ተግባር 1፡ ከገንዘብ መክፈያ ማሽንና የክፍያ ነቁጥ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ቴክኒካዊ ግሮችን መረዳት 33

ተግባር 2፡ የገንዘብ መክፈያ ማሽንና የክፍያ ነቁጥ አገልግሎት መስጫዎችን ቁጥር ማስፋት 34

ተግባር 3፡ የወኪል አገልግሎትን ለማስፋፋት የቢዝነስ ተሞክሮዎችን መከለስ 36

ተግባር 4፡ የቴሌኮም ተደራሽነትን በኔትወርክ ሽፋንና በአገልግሎት መሣሪያዎች አቅርቦት 38

ለ2.1.2. ተናባቢነት 39

ተግባር 5፡ ለኤሌክትሮኒክ የገንዘብ ዝውውር የሚያገለግል በቴክኖሎጂ የታገዘ የማጣሪያ መሰረተ ልማት 40

ተግባር 6፡ በሁሉም ተዋንያንና የክፍያ መንገዶች ተናባቢነትን ማሳደግ 41

ተግባር 7፡ የክፍያ ጌትወይ ማበልጸግ 42

ተግባር 8፡ ቅፅበታዊክፍያ / Real Time Payment-RTP/ አማራጭን መተግበር 43

ተግባር 9፡ የባንክ የክፍያ መሳሪያዎች ተመሳሳይና ወጥ እንዲሆኑ ማስቻል 44

ለ2.2. ስትራቴጂያዊ ምሰሶ 2፡ አካታች ውጤታማ የዲጂታል የክፍያ አሰራሮችን መተግበር........45

ለ2.2.1. እየሰፋ የሚሄድ አገልግሎትን መዘርጋት........54

ተግባር 10፡ የመንግስትንና የመንግስት ኢንተርፕራይዝ ክፍያዎችንና የሚሰበሰቡ ገቢዎችን ዲጂታይዝ ማድረግ........54

ተግባር 11፡ የማህበራዊ ዋስትናና ሰብዓዊ ድጋፎችን ዲጂታይዝ ማድረግ........56

ተግባር 12፡ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የሚደረጉ ከቱሪዝም ጋር የተያያዙ ዝውውሮችን ዲጂታይዝ ማድረግ........57

ተግባር 13፡ በግብርና ዘርፍ ያሉ ክፍያዎችን ዲጂታይዝ ማድረግ........58

ተግባር 14፡ ድንበር ተሻጋሪ የሐዋላ አገልግሎትን ዲጂታይዝ ማድረግ........59

ለ2.2.2. ማበረታቻዎች........59

ተግባር 15፡ ለገንዘብ ተቋማት ጥሬ ገንዘብ ላይ ክፍያ መተግበር........60

ተግባር 16፡ በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ዝውውሮች ላይ ገደብ መጣል........60

ተግባር 17፡ በኤሌክትሮኒክስ ክፍያ ለሚከናወኑ የግብር ማዘዋዎች ማበረታቻዎችን ማድረግ........61

ለ2.2.3 የግንዛቤ መፍጠሪያና ማስተማሪያ መርሃ-ግብሮች........62

ተግባር 18፡ ዲጂታል የክፍያ አማራጮችን በተመለከተ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን መፍጠር........62

ተግባር 19፡ የዲጂታል ክፍያ መጠቀሚያ ሁናቴን መሰረት የደረገ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን መቅረጽ........63

ለ2.2.4 አካታችነት........64

ተግባር 20፡ ፆታን መሰረት ያደረገ መረጃን በመሰብሰብ ሃላፊነት ያለባቸዉና ዓለምአቀፍ ዉሳኔ ሰጪ አካላትን ማሳወቅ........65

ተግባር 21፡ ከፋይናንስ አገልግሎቶች የተገለሉትን የህብረተሰብ ክፍሎችን ያማከለ አገልግሎቶችንና መፍተሔዎችን ማስጀመር........66

ተግባር 22፡ አገልግሎቶችን በበርካታ የቋንቋ አማራጮች ማቅረብን ማበረታታት........67

ለ2.3. ስትራቴጂያዊ ምሰሶ 3፡ ጠንካራና ወጥ የሆነ የሕግ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ መገንባት 67

ለ2.3.1. የቁጥጥር አቅም 72

ተግባር 23፡ የህግ ድንጋጌዎችን ማጠናከርና የቁጥጥር አቅምን ማጎልበት 72

ለ2.3.2. ሪፎርም 73

ተግባር 24፡ አዲሱን የወኪል አጠቃቀም መመሪያን አተገባበር መከታተል 73

ተግባር 25፡ የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ባንክ ያልሆኑ የፋይናንስ ተቋማት ተሳትፎን መከታተል 74

ተግባር 26፡ አዲሱን የደንበኛህን እወቅ ህግ ተግባራዊነት መከታተል 76

ተግባር 27፡ የፋይናንስ ደንበኞችን ጥበቃ ማጠናከር 77

ተግባር 28፡ የሳይበር ደህንነትን ማጠናከር 78

ተግባር 29፡ እልክትሮኒክስ ደረሰኞችን በክፍያ ማረጋገጫነት መቀበል የሚያስችል ህግ ማዉጣት 78

ለ2.4. ስትራቴጂያዊ ምሰሶ 4፡ ለአዳዲስ ፈጠራ አስቻይ ከባባዊ ሁኔታ መፍጠር 79

ለ2.4.1. አዳዲስ ተዋንያን 81

ተግባር 30፡ የቴክኖሎጂን ተግባርና ሃላፊነት ግልፅ ማድረግ 82

ተግባር 31፡ የፊነቴክ ዓለምአቀፍ ሀብቶችን ተደራሽነትን ማስፋት 82

ለ2.4.2. ማዕቀፍ 83

ተግባር 32፡ ስጋቶችን በአግባቡ በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚያስችል የፈጠራና ቴክኖሎጂ ልማት ማዕቀፍ መፍጠር 84

ለ3. አስቻይ ሁኔታዎች 85

አስቻይ 1፡ ወጭ ቆጣቢ አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ የክፍያ ሥርዓት ለመገንባት ሊኖር የሚገባ ቁርጠኝነት 86

አስቻይ 2፡ በዲጅታል ክፍያ ከባቢ ላይ አቅም ለመገንባት ቅድሚያ መስጠት እና መወዕለነዋይን ማስፈሰስ 87

አስቻይ 3፡ ከ ብሔራዊ የልማት ሪፎረሞችና ፖሊሲዎች ጋር ንቁ እና ቀጣይት ያለዉ ትብብርን ማረጋገጥ 87

አስቻይ 4፡ የተሟላ የአስተዳደር የትግበራ እቅድ በማዘጋጀት ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያዎችን በመጠቀም ክንውንን መከታተል 89

ሐ. የአተገባበር ማዕቀፍ 90

ሐ1. የትግበራ ዕቅድ 91

ሐ2. አስተዳደራዊ መዋቅር 94

ሐ3. የክትትል ዕቅድ 95

የቃላትና ሀረጎች ፍቺ 96

ማጣቀሻ 98

የምስል ማውጫ

ምስል 1፡ የኢትዮጵያ ፤ ቻይና፤ ህንድ እና ኬኒያ ሀገራት ንፅፅራዊ ዕይታ 13
ምስል 2፡ የዲጂታል ፋይናንስ አካታችነት ከዘላቂ የልማት ግቦች ጋር ያለው ቁርኝነት 17
ምስል 3፡ ዉስጣዊ ፤ ዉጫዊ እዲሁም እየተካሔዱ ካሉ ሪፎረሞች ጋር ያለዉ ቁርኝት 21
ምስል 4፡ የብሔራዊ ዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ማዕቀፍ....23
ምስል 5፡ በክፍያ መፈጸሚያ መሳሪያዎች መካከል ያለ ተናባቢነት 26
ምስል 6፡ ተነጻጻሪ ዕየታ ፡ የኤ.ቲ.ኤም ዕድገት (2014–2017) ከ . ዲጂታል ክፍያ ድርሻ (2017)....28
ምስል 7፡ የክፍያ መፈጸሚያ መሳሪያዎች ተደራሽነት 32
ምስል 8፡ ለ ትራነዛክሽኖች ስኬታማ ላለመሆን ተደጋጋሚ ምክኒያቶች....34
ምስል 9፡ በወኪል የተከነወነ ግብይት/ትራንዛክሽን....37
ምስል 10፡ የዲጂታል ክፍያ ተጠቃሚዎች ሥርዓቱን የመቀበል ምጣኔ ከባቢያዊ መረጃ 46
ምስል 11፡ የኢ-ታክስ ማብራሪያ 47
ምስል 12፡ ገላጭ ምሳሌ፡ የምርታማነት ሴፍቲኔት ፕሮግራም 47
ምስል 13፡ ዲጂታል ክፍያ በ አይነት 48
ምስል 14፡ የዲጂታል ክፍያ ሞዴሎች 70
ምስል 15፡ እያንዳነዱ ሞዴል ከ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ሁኔታ ጋር ያለዉ ቁርኝነት....74
ምስል 16፡ የድረጊት መረሀግብር ቅድመ ተከተል....92
ምስል 17፡ የድረጊቶች መተግበሪያ የጊዜ ማዕቀፍ....93
ምስል 18፡ አስተደደራዊ መዋቅር....94

አጠቃላይ

ኢትዮጵያ ለህዝቦቿ ተጠቃሚነት የላቀ አቅም መፍጠር የሚያስችል ብሔራዊ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን በማካሄድ ላይ ትገኛለች፡፡ ይህ እ.ኤ.አ ከ2021 እስከ 2024 ድረስ የሚዘልቅ የሦስት ዓመት ብሔራዊ የዲጅታል-ክፍያ ስትራቴጂ የዚሁ ለውጥ ጉዞ ዋነኛ አካል ነው፡፡ ይህ ስትራቴጂ ሰነድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ[1] የክፍያ ስነ-ምህዳሩን በማዘመን ውስን የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ያለውና የፋይናንስ አካታችነቱ የጎለበተ ኢኮኖሚ ለመፍጠር ፍኖተ ካርታ በመሆን ያገለግላል፡፡ ብሔራዊ የዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሃገሪቱን የችርቻሮ /አነስተኛ ዋጋ ያላቸው/ የክፍያ ዘዴዎችን ለማዘመን ባስቀመጠው እቅድ ዋነኛ አካል ነው፡፡

ዲጅታል ክፍያ ሰፊ፣ ውስብስብና ባለብዙ አውድ አጀንዳ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ዲጅታል ክፍያን ለማሳደግ በተለያዩ ሴክተሮችና የኢኮኖሚ አውታሮች የሚገኙ ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎና የተቀናጀ ጥረት ይጠይቃል፡፡ ይህንን ታሳቢ በማድረግ ይህ ብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ በክፍያ ስነ-ምህዳሩ ውስጥ ተዋናይ የሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር ሰፊ ውይይትና ምክክር በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡

የብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ራዕይ፡- ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ተወዳዳሪ፣ ወጭ ቆጣቢ፣ በፈጠራ የታገዘና ሃላፊነቱን በአግባቡ የሚወጣ የክፍያ ከባቢያዊ ሁኔታ በመገንባት ውስን ጥሬ ገንዘብን የሚጠቀምና የፋይናንስ አካታችነትን የተላበሰ ኢኮኖሚ እንዲኖር ማገዝ ነዉ፡፡

ይህ ብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ አራት ዋና ዋና ምሰሶዎችን ታሳቢ አድርጓል፡-

- ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አካታችና ተናባቢ መሰረተ ልማት መገንባት፣
- የዲጂታል ክፍያ አገልግሎትን መተግበር፣
- ወጥነት ያለውና ሁሉን አቀፍ (ውጤታማ) የህግ ድንጋጌዎችና የክትትልና ቁጥጥር ማእቀፍ ማዘጋጀት፣
- ለአዳዲስ ግኝቶችና ፈጠራዎች አስቻይ ከባቢን መፍጠር ናቸው፡፡

ከላይ ለተዘረዘሩት አራት ምሰሶዎች ዝርዝር የድርጊት ስትራቴጂዎችና የትግበራ እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ እነዚህ የድርጊት ስትራቴጂዎች ቅድሚያ ሊፈቱ የሚገባቸውን ተግዳሮቶች በመለየት የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡ በተጨማሪም የድርጊት ስትራቴጂው የኢትዮጵያን የክፍያ ሴክተር ወቅታዊ ደረጃ እንዲሁም ዓለማቀፍ የስኬት ተሞክሮዎችን ታሳቢ ተደርጎ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

በተጨማሪም የብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂው አራት አስቻይ ሁኔታዎችን በመለየት ከላይ ከተገለጹት ምሰሶዎች ጋር በማቀናጀት ለስትራቴጂው መደላድል /መሰረት/ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ እነዚህ አስቻይ ሁኔታዎች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡

- አስተማማኝ፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ውጤታማ አገርአቀፍ የክፍያ ስርዓትን ለመገንባት ያለው ቁርጠኝነት፣
- በዲጂታል ክፍያ ከባቢያዊ ሁኔታ ላይ የአቅም ግንባታ ስራዎች ለማከናወን ቅድሚያ ትኩረት መሰጠቱና አስፈላጊውን ሃብት መመደቡ፣
- ከአገሪቱ የልማት እድገት ሪፎርም ስራዎችና ፖሊሲዎች ጋር ቀጣይነት ያለው ቅንጅትና መናበብ እንዲኖር መደረጉ፤ እንዲሁም፣
- ውጤታማ የአስተዳደርና የትግበራ እቅድ ግንባታና ቁልፍ የአፈጻጸም መለኪያዎችን በማዘጋጀት አፈጻጸምን መለካት የሚያግዝ አሰራር መኖሩ ናቸው፡፡

ይህ ብሔራዊ የዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ከኢትዮጵያ መንግስት ሁሉን አቀፍ የሪፎርም አጀንዳ ጋር እንዲጣጣም ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡ የኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ ሪፎርም ስትራቴጂና የዚሁ አካል በሆነው ዲጅታል የፋይናንስ አገልግሎት ስትራቴጂ ዋና አካል ተደርጎም ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም ባለድርሻ አካላት፣ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተዋናዮች የሚጠበቅባቸውን ድርሻ በማበርከት ለኢትዮጵያ የክፍያ ስነ-ምህዳር እድገት እገዛ እንዲያደርጉ ለማስቻል እንደዋና አቅጣጫ ጠቋሚ ሆኖ ያገለግላል (World Bank Group 2020a)፡፡

ይህ ብሔራዊ የዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ወደ ዲጂታል አሰራር በማሸጋገር የፋይናንስ አካታችነትን ለማረጋገጥ፣ የስራ እድል ለመፍጠር፣ የሴቶችን የኢኮኖሚ ተሳትፎ ለማሳደግ ከሚካሄዱ የሪፎርም[2] ተግባራት ጋር በቅንጅት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ለዚህም ኢትዮጵያ ያስቀመጠችው አካታች የኢኮኖሚ እድገት፣ የላቀ ብልጽግና እንዲሁም የተሻለ የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ ግብ ለማሳካት ያግዛል፡፡

በዓለምአቀፍ ደረጃ የተከሰተው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ የዲጂታል ክፍያን አስፈላጊነት ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በሌሎች አገራት እንደታየው ዲጅታል ክፍያ የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመከላከል እንደ ዋነኛ መሳሪያ አገልግሏል፡፡ ዲጅታል ክፍያ የሰዎችን መቀራረብ በመቀነስና የጥሬ ገንዘብ ልውውጥን በማስቀረት አስተማማኝ፣ ፈጣንና ወጭ ቆጣቢ ክፍያ እንዲኖር ያስችላል (Goodwin-Groen 2020)፡፡ ዓለምአቀፍ ተሞክሮዎችን መነሻ በማድረግ የኢትዮጵያ መንግስት የዚህን ስትራቴጂ አንዳንድ ጉዳዮች መተግበር ጀምሯል፡፡ በዚህም እስካሁን ባለው ሁኔታ የዲጂታል ስርዓት ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጣባቸው በሚችሉና በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት የተፈጠሩ አስቸኳይ የጤና፣ ማህበራዊ እገዛ እና የኢኮኖሚ ፍላጎቶችን ማሟላት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም ስትራቴጂው ከዚህ የአጭር ጊዜ ጥቅም ባሻገር የዲጂታል ሽግግሩ ጠንካራ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ሚዛናዊ ማህበረሰብና ዘላቂ የተፈጥሮ ከባቢን ለመገንባት የሚቻልበትን አግባብ ከዓለምአቀፍ ግንዛቤ አንጻር ያስቀምጣል፡፡ በዚህም ኢትዮጵያ ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት የምታደርገውን ጉዞ ለማሳለጥ ዋነኛ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ሀ.

ስትራቴጂካዊ ዐውድ

መነሻ

ኢትዮጵያ ለመካከለኛው ምስራቅ አገራትና ለአካባቢው ገበያ ቅርበት ባለው የአፍሪካ ቀንድ ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ ያላት አገር ነች፡፡ የህዝብ ቁጥር 109 ሚሊዮን አካባቢ (World Bank Group 2020b) ሲሆን በአፍሪካ ሁለተኛዋ ባለብዙ ህዝብ እና በቀጠናው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት የምታስመዘግብ አገር ነች፡፡ ከ2010 እስከ 2018 በነበሩ ዓመታት ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ አጠቃላይ አገራዊ ምርት 10.7 በመቶ እድገት አስመዝግባለች፡፡ ይህም እድገት ከሰሃራ በታች ባሉ አገራት አማካይ እድገት 0.1 በመቶ እንዲሁም ዓለምአቀፍ አማካይ እድገት 2.2 በመቶ ጋር ሲነጻጸር እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህ የኢኮኖሚ እድገት እንደተጠበቀ ሆኖ በአገር ውስጥ ምርት /GDP/ ኢትዮጵያ አሁንም ዝቅተኛ ገቢ ደረጃ ካላቸው አገሮች ትመደባለች (World Bank Group 2020c)፡፡ አመታዊ የነብስ ወከፍ ገቢዋ 777 የአሜሪካ ዶላር ሲሆን ይህም ከሰሃራ በታች ካሉ አገራት አማካይ ገቢ 1,586 የአሜሪካ ዶላር እንዲሁም ከዓለማቀፍ አማካይ የነብስ ወከፍ ገቢ 11,312 የአሜሪካ ዶላር በእጅጉ ያነሰ ነው (World Bank Group 2020c)፡፡ ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2025 ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለመድረስ አመታዊ የነብስ ወከፍ ገቢዋንም ከ 1,026 ወደ 3,995 ለማድረስ ግብ አስቀምጣ በመንቀሳቀስ ላይ ትገኛለች፡፡

ዘመናዊና ውጤታማ የፋይናንስ ስርዓት መኖር የተረጋጋና አካታች የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት ቁልፍ አስቻይ መሳሪያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አዳጊ ኢኮኖሚ ባላቸው አገራት የዲጅታል ክፍያ ማደግ አመታዊ አገራዊ ምርትን ለማሳደግ እስከ 3 በመቶ ያክል ድርሻ ይኖረዋል (Massi et al. 2019)፡፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የዲጅታል ክፍያ ስርዓትን ለማሳደግ የተግባር እንቅስቃሴ ማድረግ ጀምራለች፡፡ ለዚህም የመሰረተ ልማት ማሟላት፣ የዲጂታል ክፍያ መተግበርን ማበረታታት፣ የህግ ድንጋጌዎችን የመከለስ እንዲሁም ፈጠራን የማበረታታት ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

- በኢትዮጵያ የክፍያ ስርዓት ሥር-ነቀል ለውጥ በማምጣት ወደ ዘመናዊነት የተሸጋገረው እ.ኤ.አ በ2011 የኢትዮጵያ አውቶሜትድ ትራንስፈር ሲስተም / EATS/ መተግበር ጀምሮ ነው (World Bank Group 2020a)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በ2016 የብሄራዊ ስዊች/ተናባቢ ስርዓት/ አገልግሎት መጀመር ለዲጅታል ክፍያ ተናባቢነት እንዲኖር በማስቻል ረገድ ቀዳሚ እመርታ የታየበት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ኢ.ት.ስዊች ሙሉ ለሙሉ ትግበራው ሲጠናቀቅ ለዲጂታል ክፍያ አገልግሎት እንደ ዋና ማእከል ሆኖ የሚያገለግል ይሆናል፡፡
- እንደ ግሎባል ፊንዴክስ (Demirgüç-Kunt et al. 2018) የመረጃ ቋት እ.ኤ.አ በ 2014 በኢትዮጵያ 22 በመቶ የሚሆኑ አባዎራዎች በመደበኛ የፋይናንስ ተቋማት ሂሳብ መክፈታቸው ተገምቷል፡፡ ይህ አሃዝ ከፍተኛ እድገት በማሳየት እ.ኤ.አ በ2017 የ 13 በመቶ ጭማሪ በማሳየት 35 በመቶ ደርሷል፡፡
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቅርብ ጊዜ የክፍያ መሳሪያ አቅራቢዎች እንዲሁም ወኪል መጠቀምን በሚመለከት የወጡ መመሪያዎች[3] ለአነስተኛ ክፍያዎች የሚጠቅም ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታና የድንጋጌ የህግ ማእቀፍ እንደሚፈጥር ይታመናል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ሌሎች የክፍያንና ከክፍያ ጋር የተገናኙ አገልግሎቶችን የሚገድቡ ድንጋጌዎች በክለሳ ላይ ይገኛሉ፡፡
- ኢትዮጵያ በዲጂታል ክፍያ ዘርፍ ለሚደረጉ የፈጠራ ስራዎች አስቻይ ከባቢን ለመፍጠር አስፈላጊውን መደላድል ፈጥራለች፡፡ ዲጅታል ቦርሳን ጨምሮ ሌሎች የዲጅታል ክፍያ መተግበሪያ የፈጠራ እድገት የሃገሪቱን የዲጅታል ክፍያ ትግበራ ለማሻሻል አግዟል፡፡

ምንም እንኳን ከላይ የተዘረዘሩት ተግባራት የኢትዮጵያን ዲጂታል ክፍያ ከባቢያዊ ሁኔታ ያሳደጉ ቢሆንም ዓለማቀፍ ደረጃዎች ላይ ለመድረስ ቀሪ ተጨማሪ ጥረቶችን ይጠይቃል፡፡ የኢትዮጵያ ዲጂታል ክፍያ ከባቢያዊ ሁኔታ ከቀጠናዊ እና ዓለማቀፍ ተሞክሮዎች ጋር ለማነጻጸር ከኬንያ፣ ቻይና እና ህንድ ጋር ያለው ንጽጽር በሚከተለው ስዕል ተመላክቷል፡፡

ምስል1: የኢትዮጵያ ፤ ቻይና፤ ህንድ እና ኬኒያ ሀገራት ንፅፅራዊ ዕይታ[4]



ዓለማቀፍ መልካም ተሞክሮዎች

የቴክኖሎጅና ዲጅታል የንግድ ሥራ እድገትን ተከትሎ የተጠቃሚነት ፍላጎት መጨመር ከዚህም ባለፈ ፈጣን፣ የላቀ ደህንነት፣ ግልጽነት ያለው እና ውጤታማ የክፍያ ስርዓትን አስፈላጊነት በእጅጉ እንዲጨምር አድርጓል፡፡ በዓለማችን በአሁኑ ሰዓት ፖሊሲ አውጭ አካላት የጥሬ ገንዘብ ግብይትን ለመቀነስ የሚያግዙ የፖሊሲ አማራጮችን በአንጻሩ ደግሞ የዲጂታል ክፍያ ዘዴዎችን ማላመድ እና እንዲጨምሩ ለማድረግ የሚያግዙ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡

ዲጂታል ክፍያ ሲባል በዲጂታል መገናኛ መንገዶች አማካኝነት የሚተገበሩ የክፍያ መፈጸሚያ መሳሪያዎችን በመጠቀም ዋጋ/ገንዘብ/ ማስተላለፍ ማለት ነው (Better Than Cash Alliance 2020a)፡፡ ነባሩ የዲጂታል ክፍያ አሰራር በአመዛኙ በባንኮች የሚመራ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ግን በፋይናንስ ከባቢ ሁኔታው ውስጥ የፋይናንስ ቴክኖሎጂ ፈጠራዎች (ፊንቴክ) እንዲሁም የተንቀሳቃሽ /ሞባይል/ ገንዘብ ኦፕሬተሮች የፋይናንስ ከባቢ ሁኔታውን በመለወጥ በፋይናንስ ቴክኖሎጂ እንዲሁም የኤሌክትሮኒክ ገንዘብ አቅራቢዎች የታገዙ ተዋናዮች እንዲካተቱ አድርጓል፡፡

ዲጂታል ክፍያዎች በመላዉ ዓለም በጥቅም ላይ በመዋል ላይ የሚገኙት፡-

- ፍጥነትንና ውጤታማነትን በመጨመር ወጭን ለመቀነስ፣
- ተጠያቂነትንና ክትትልን በመጨመር ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሁም ግልጽነት ያለው አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ፣
- የበርካታ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ተደራሽነት እውን በማድረግ የፋይናንስ አካታችነትን ለማሳደግ፣
- ሴቶች በፋይናንስ ጉዳዮቻቸው ላይ የበለጠ የቁጥጥር አቅም እንዲኖራቸው በማድረግ የኢኮኖሚ ተሳትፏቸውን ለማጎልበት ሁነኛ መሳሪያ በመሆናቸው ነው፡፡

በዓለማቀፍ ደረጃ የተገኙ መልካም ምሳሌዎችን /ተሞክሮዎችን/ ዋቢ በማድረግ የዲጂታል ክፍያ አማራጮችን ማላመድ የፋይናንስ አካታችነትን የሚያረጋግጥ እድገት ከማምጣት አኳያ የሚያስገኛቸው ጥቅሞች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡-

ቀልጣፋና ወጭ ቆጣቢ

በጥሬ ገንዘብ የሚፈጸም ክፍያ በባንክ ወይንም በቼክ ገቢ የሚደረግ ገንዘብ ተጠቃሚዎች /ተገልጋዮች/ በአካል ወደ ባንክ ቅርንጫፍ ወይንም አገልግሎት ሰጭ ተቋም (በአገልግሎት መስጫ ሰዓት ብቻ) መሄድን ይጠይቃል፡፡ ሆኖም ግን ዲጂታል የክፍያ አማራጮች ተጠቃሚዎች ባሉበት ቦታ ሆነው በሚመቻቸው መንገድ ክፍያ እንዲፈጽሙ በማስቻል ለዚሁ የሚባክን ጊዜን ይቆጥባል፡፡ ዲጂታል ክፍያ የከፋይና ተከፋይ የቦታ ርቀት ሳይገድበው በፍጥነት ክፍያን ለመፈጸም ያስችላል፡፡ ይህም ሆኖ ግን እንደ አጣዳፊ የጤና ሁኔታና የተፈጥሮ አደጋ በመሳሰሉ ጊዜ የማይሰጡ ሁኔታዎች ክፍያዎች በቅፅበት /ሪል ታይም/ እንዲሆኑ ለማድረግ መስራት ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም ከርቀት ቦታ በዲጂታል መንገድ የሚፈጸሙ ክፍያዎች በአካል ለመጓጓዝ ወይንም ለፖስታ አገልግሎት /መላኪያ/ የሚወጡ ወጭዎችን በማስቀረት ረገድ ለተጠቃሚዎች አማራጭ የሚሰጡ ሲሆን በባንኮችና በንግድ ተቋማት በኩል ቅርንጫፎችን ለመክፈትና ለማንቀሳቀስ የሚወጣ ወጭን በማስቀረት ረገድ ከፍተኛ ጥቅም ይኖረዋል፡፡

ከጥሬ ገንዘብ ወደ ዲጂታል ክፍያ የሚደረግ ሽግግር በመንግስት ደረጃ ከፍተኛ የሆነ የረጅም ጊዜ የወጭ ቅነሳ ጥቅምን ያስገኛል፡፡ በኒጀር ለማኅበራዊ ዋስትና ፕሮግራም የሚፈጸም ክፍያ በተንቀሳቃሽ ስልክ አማካኝነት እንዲፈጸም በመደረጉ ገንዘብ ለማስተላለፍ የሚወጣ ወጭ በጥሬ ገንዘብ ሲከፈል ከነበረውን በ 20 በመቶ ቀንሷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የሜክሲኮ መንግስት ከ 1997 ጀምሮ የዲጅታል ክፍያ ዘዴን ተግባራዊ ማድረግ በመጀመሩ የማህበራዊ ዋስትና፣ የጡረታ አበል እንዲሁም የቀን አበል /ምንዳ/ ክፍያ አመታዊ ወጭ በ 3.3 በመቶ ወይንም በ1.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር አካባቢ መቆጠብ ችሏል፡፡

ግምቶች እንደሚያመለክቱት በህንድ በመንግስት የሚፈጸሙ ክፍያዎችን በማዘመን ወደ ዲጂታል ክፍያ መሸጋገሩ ለዚሁ ተግባር የሚውል ወጭ እንዲሁም በመጭበርበር የሚባክን ሃብት በዓመት 22.4 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማዳን ተችሏል፡፡ በብራዚል የቦልሳ ፋሚሊያ ፕሮግራም ዲጂታል ክፍያን በመጀመሩ አጠቃላይ ከክፍያ ጋር የተያያዙ ወጭዎቹን ከነበሩበት 14.7 በመቶ ወደ 2.6 በመቶ (ከአጠቃላይ ክፍያ) ማውረድ ተችሏል (World Bank et al. 2014):: ይህ ብቻ ሳይሆን ከምቹነት የሚመነጭ ከፍተኛ ጥቅም ያስገኛል (ለምሳሌ የጊዜ ቁጠባ፣ የመጓጓዣ ወጭ መቀነስ) እንዲሁም የአገልግሎት ክፍያ ዝቅተኛ መሆን ተጨማሪ ጥቅም ነው፡፡ ምንም እንኳን የዲጂታል ክፍያ አቅራቢዎች የአገልግሎት ክፍያ የሚያስከፍሉ ቢሆንም በአንዳንድ ባንኮች ጥሬ ገንዘብ ለማስቀመጥ ከሚጣል ክፍያ ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ነው (HSBC UK Bank 2019; KCB Bank 2019; Siam Commercial Bank 2019; Grupo Financiero Banorte 2019; Massi et al. 2019)፡፡

ከላይ የተገለጸው ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲጂታል ክፍያ ከጥሬ ገንዘብ ክፍያ ርካሽ አማራጭ የማይሆንበት አጋጣሚ መኖሩን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ይህም የሚሆነው ከዲጅታል ክፍያ የሚገኙ ጥቅሞችና ወጭዎች በተለያዩ ተዋናዮች /ባለድርሻ አካላት/ ዘንድ በእኩል መጠን የተከፋፈለ ባለመሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ የደመወዝ ወይንም የጡረታ አበል ተከፋዮች በወኪሎች በኩል የአገልግሎት ክፍያ ከፍለው ገንዘብ ወጭ ከማድረግ ይልቅ ክፍያቸውን በጥሬ ገንዘብ በአካል መቀበልን ሊመርጡ ይችላሉ፡፡ በእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች መንግስት የዲጂታል ክፍያን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ህብረተሰቡን በማበረታታት ሚናውን ሊወጣ ይገባል፡፡ ለደህንነት ሥጋት መንስኤ የሆነዉንና ጥሬ ገንዘብን በብዛት መጠቀምን ለመቀነስ እንዲቻል በተወሰኑ አካባቢዎችና ዘርፎች የዲጂታል ክፍያዎችን ለመጠቀም የሚጣሉ የአገልግሎት ክፍያዎች ይደጎማሉ፡፡

በዓለማቀፍ ደረጃ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ስርጭትን ለመከላከል የሚደረገው ጥረት ዲጂታል ክፍያን ከማበረታታት እንዲሁም የጥሬ ገንዘብ ግብይትን ከመቀነስ አንጻር ተጨማሪ እድሎችን ፈጥሯል፡፡ ለምሳሌ በኬንያ የሞባይልና ኤሌክትሮኒክ ባንኪንግ አገልግሎት ክፍያዎችን በመቀነስ አንዳንዴም ጨርሶ በማስቀረት የጥሬ ገንዘብ አገልግሎትን የመቀነስ ስትራቴጂ ስራ ላይ ውሏል፡፡

አስተማማኝነት እና ግልጽነት

አስፈላጊ የጥንቃቄና የመከላከል ተግባራት እስከተከናወኑ ድረስ ምንም እንኳን የበይነ መረብ ጥቃቶችና ዲጂታል ማጭበርበር ቢኖሩም ዲጂታል ክፍያ ከጥሬ ገንዘብ በተሻለ ደህንነቱ የተጠበቀ የክፍያ አማራጭ ነው፡፡ ግብይቶች /ክፍያዎች/ ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል፣ “ምን ይዘሃል?” - (የክፍያ ካርድ/ተንቀሳቃሽ ስልክ)፣ “ምን ታውቃለህ?”- (የይለፍ ቃል/ሚስጥራዊ ጥያቄዎች) እና “ማን ነህ?” - (የአሻራ/የፊት ገጽታ መለየት) የሚሉ የማጣራት /የማረጋገጥ/ ብቃቶችን እንዲያሟሉ ይደረጋል፡፡ ተጨማሪ እርምጃዎች እንደ ባለ ሁለት ደረጃ /2FA/ ጥምር ማረጋገጫዎች ለምሳሌ የክፍያ ካርድ (ምን ይዘሃል?) እንዲሁም የግል መለያ ቁጥር /PIN/ (ምን ታውቃለህ?) መጠቀም ያሉትን ያካትታል፡፡ በተንቀሳቃሽ ስልክ መተግበሪያ ላይ ያሉ እንደ የማለፊያ ቁጥር፣ የግል መለያ ቁጥር /PIN/ እና ሌሎችም የደህንነት ብቃቶች የላቀ የደህንነት እርምጃ አካል ናቸዉ፡፡

በንግድ ባንኮች ጥቅም ላይ የሚውሉ አብዛኛዎቹ መተግበሪያዎች በባንክ ሂሳቡ ውስጥ በመግባት ወይንም የጥሪ ማእከላትን በማነጋገር በክፍያ ነቁጥ ወይንም ከተንቀሳቃሽ ስልክ መተግበሪያ የሚመጡ የክፍያ ትዕዛዞችን ለማገድ የሚያስችል የ24/7 የማያቋርጥ አገልግሎት መዕከል አማራጭ አላቸው፡፡ በጥሬ ገንዘብ ግብይት ወቅት ግን ካለው ባህሪ አንጻር ይህንን ማድረግ እጅግ አስቸጋሪ /የማይቻል/ ነው፡፡ የዲጂታል ክፍያ ተጠቃሚነት በጨመረ ቁጥር የገንዘብ ስርቆት መጠን በዚያው መጠን እንደሚቀንስ በተለያዩ አገራት ተረጋግጧል (Mai 2016; Boorstin 2017)፡፡

የዲጂታል ክፍያ ማደግ በመደበኛ የፋይናንስ ስርዓት ውስጥ የሚኖረውን የገንዘብ ዝውውር እንዲጨምር በማድረግ ህገ-ወጥ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በአገራዊ ገቢ ላይ የሚያሳርፈውን ተጽእኖ ለመቀነስ ያግዛል፡፡ በመደበኛ የፋይናንስ ስርዓት የሚደረግ የገንዘብ እንቅስቃሴ የክፍያዎችን ግልጽነት እንዲጨምር በማድረግ የገቢ መስሪያ ቤቶች የገንዘብ እንቅስቃሴዎችን ባግባቡ መከታተል እንዲችሉ ያግዛል፡፡ በህገወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን የመሳሰሉ የፋይናንስ ወንጀሎችን በቀላሉ ለመከታተልና ለመለየትም ያስችላል፡፡

የፋይናንስ አካታችነት

መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዲጂታል ክፍያ ወጭን ከመቀነስና ግብይትን ምቹ ከማድረግ በተጨማሪ ተፈላጊዉን መስፈርት የሚያሟሉ ተጠቃሚዎችን ቁጥር በማሳደግ የፋይናንስ አካታችነት እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ የባንክ ሂሳብ ያላቸው ደንበኞች ዲጂታል ክፍያን በተደጋጋሚ እንዲጠቀሙ ማድረግ ቁጠባን ያበረታታል፡፡ ይህም ሁኔታ የተረጋጋ የፋይናንስ ከባቢያዊ ሁኔታ እንዲኖር በማድረግ ድህነትን ለመቀነስ የሚደረገውን ጥረት ያግዛል፡፡ በተጨማሪም ጠረፋማና ገጠራማ አካባቢ የሚገኙ ተጠቃሚዎች በብድር፣ በቁጠባ እና በመሳሰሉት መልክ ለፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆኑ በማስቻል ድህነትን ለመቀነስና የኢኮኖሚ ተሳትፏቸው እንዲጎለብት ያደርጋል፡፡

ዲጂታል ክፍያ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎችን በአውቶማቲክ ቁጠባ ስርዓት ውስጥ እንዲታቀፉ በማድረግ በጊዜ ሰሌዳ የሚላክ አጭር የጽሁፍ መልእክት ቁጠባን እንዲያስታውሱ በማድረግ፣ ቁጠባቸውን ሳስተጓጉሉ ተጠቃሚዎች ማንቂያዎችን በመላክ እና ለመቆጠብ እንቅፋት የሚሆኑ የስነ ልቦና ማነቆዎችን ለመፍታት የሚያግዙ ስልቶችን ለመጠቀም ያስችላል (World Bank Group 2020f; International Monetary Fund 2020; Massi et al. 2019)፡፡ በኬንያ ኤም ፔሳን የመሰሉ ዲጅታል ፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢዎች በአገሪቱ የመደበኛ የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ቁጥር በ 2006 ከነበረበት 27 በመቶ በሶስት እጥፍ በማሳደግ በ 2015 ወደ 75 በመቶ እንዲደርስ አድርገዋል (International Telecommunications Union Media Centre 2019)፡፡

ዲጂታል ክፍያ ግለሰቦች፣ የንግድ ድርጅቶችና የፋይናንስ ተቋማት ተጋላጭነታቸውን መቀነስ እንዲችሉ ያግዛል፡፡ ዲጂታል ክፍያን መሰረት አድርጎ የሚፈጠር የኤሌክትሮኒክ አውታረ መረብ አንድ ቤተሰብ የፋይናንስ ማህበረሰባዊ ትስስሩን እንዲያሰፋ ያግዛል፡፡ ይህም ሁኔታ በድንገት ሊፈጠር የሚችል የገንዘብ እጦትን ለመቅረፍ የሚያስችል ተደራሽነት እንዲኖር ያግዛል፡፡ በኬንያና በኡጋንዳ እንደታየው የሞባይል ገንዘብ መኖርና ሥራ ላይ መዋል ተጠቃሚዎች የሚያጋጥማቸውን ድንገተኛ የፋይናንስ ኩነቶችን በተሻለ ሁኔታ ለመምራት እድል ሰጥቷል (World Bank et al. 2014)፡፡ በተጨማሪም የፋይናንስ ተቋማት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ደንበኞችን የብድር የኋላ ታሪክና የፋይናንስ መረጃ እንዲያገኙ በማስቻል የብድር አሰጣጥ ውሳኔያቸው በተሰላ ተጋላጭነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን አስችሏቸዋል፡፡ የመረጃ በበቂ ሁኔታ መኖር የፋይናንስ ተቋማትን እንዲሁም የመድን ሰጭ ኩባንያዎችን የስጋት ተጋላጭነት ከመቀነስ አኳያ የመተማመን ስሜት በማጎልበት ዕድሉ ላልነበራቸዉና መስፈርቱን ለሚያሟሉ ሰዎች የብድር አቅርቦት እንዲጨምር እድል ይፈጥራል ፡፡

ዲጂታል የፋይናንስ አካታችነትን በሃላፊነት ስሜት እንዲሁም ዘላቂነት ባለውና ባግባቡ በሚመራ ከባቢያዊ ሁኔታ ውስጥ መፈጸም እድገትን ማሳለጥ ብቻ ሳይሆን ለ 2030 የተቀመጡ የዘላቂ ልማት ግቦችን በተፋጠነ መልኩ ለማሳካት ያግዛል፡፡ ይህንን የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ በተሳካ ሁኔታ መተግበር ኢትዮጵያ ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት ለምታደርገው ጥረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ እንደ ቤተር ዛን ካሽ አሊያንስ የ2018 ህትመት አካታች የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከ 17 ዘላቂ የልማት ግቦች ውስጥ 13ቱን ለማሳካት ያግዛል (Better Than Cash Alliance 2018)፡፡ የዚህ ዝርዝር ሁኔታ በሚከተለው ምስል ተመላክቷል፡፡

ምስል 2: የዲጂታል ፋይናንስ አካታችነት ከ ዘላቂ የልማት ግቦች ጋር ያለዉ ቁርኝነት

1 ድህነትን ማጥፋት

ቁጠባን በማበረታት,፤ ለመንግስት ገንዘብን ለሚፈለግበት ቦታ በቀላሉ እዲደርስ ይረዳል እዲዉምንግድን በማቀላጠፍ ወጪ ቆጣቢ የፊይናንስ አገልግሎት እዲኖር ያስችላል

2 ረሀብን ማጥፋት

ለአርሶአደሮች ቸብድርና የፋይናንስ አገልግሎት አዲዳረስ በማድረግ ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ ማህበራዊ ገንዘብ መላላኪያ እዲኖር ያስችላል፡፡

3 ጤናማነትና ደህንነት

ቤተሰቦችን ላልተጠበቀ የጤና ወጪ እዲዘጋጁ በማድረግ አነስተኛ የጤና ዋስትና ተመጣጣኝ እዲሆን የስችላል፡፡ እዲሁም አስተማማኝ ና የበለጠ ገቢ እዲኖራቸዉ ያደርጋል፡፡

4 ጥራት ያለዉ ትምህርት

አማራጭ ምርቶችን በማበረታታት፤ ለመምህራን ድህንነቱ የተጠበቀ፤ ፈጣንና አስተማማኝ የደሞዝ አከፋፈል እዲኖር በማስቻል ወላጆች የትምህርት ወጪን በአግባቡ እዲያስተዳድሩ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ከትምህርት ዘርፍ የሚገኘዉን የጥሬ ገንዘብ ፍሰትን በማቀላጠፍ መንግስትን ዘላቂ የንግድ አሰራሮች አረዲቀርጽ ጸጸስችለዋል፡፡

5 የፆታ እኩልነት

ሴቶች ገንዘብን የበለጠ እዲቆጣጠሩ የስችላል, እዲሁም የንግድ ባለብት ሴቶች ንግዳቸዉን/ስራቸዉን/ በበለጠ, እዲረዱት ያስችላል፡፡ በተጨማሪም ፖሊሲ አዉጪዎች ለሴቶች ተስማሚ የሆነ ፖሊሲና ዲጂታል ምርቶችን እዲያወጡ ያስችላል፡፡

6 ንፁህ ዉሃና ንፅህና

የክዋኔ ወጪን በመቀነስና አስተማማኝ የጥሬ ገንዘብ ፍሰትን በመፍጠር ደህንነቱ የተጠበቀና ዘላቂ የዉሃ ልምምድ እዲኖር የስችላል፡፡

7 ተመጣጣኝና ንፁህ ኢነርጂ

ወደ ወጪቆጣቢ ቅድመ ክፍያ ወይም መፍትሔ እደተገኘ መክፈል በበማስቻል የኢነርጂ ተደራሽነትን ያስፋፋል፡፡

8 የተመቸ ስራና ዕድገት

ለሰራተኞች ቀጥታ የፊይናንስ አካታችነትን በመፍጠር ሰራተኞች ጥሬ ገንዘብ በመያዝ የሚያወጡትን ወጪ እዲቀንስ የስችላል፡፡

9 ኢደስተሪ፤ፈጠራና መሰረተ ልማት

ጥቃቅን ፤አነስተኛና መካክለኛ ኢነተረፕራይዞች የክፍያ ታሪካቸዉንና የብድር ዉጤታቸዉን እዲገነቡ ይረዳቸዋል፡፡ እዲሁም በስራቸዉ ዉጤታማ እዲሆን፤ ከደሞዝካፍያ ጋር በተያያዘ ከሰራተኞቻቸዉ ጋር የሚከሰትን ልዩነቶችን ያስቀርላቸዋል፤ የሰራተኛ ህግን እዲያከብሩና መጭበርበርን የቀንስላቸዋል፡፡

10 አዱሎን መቀነስ

ምርታማነትንና ገቢን በመጨመር፤የገንዘብ መላኪያን ወጪ በመቀነስ የገጠሩ ህብረተሰብ ወጪን በተሸለ መንገድ እዲያስተዳድር የስችላል

11 ዘላቂ ከተሞችና ህብረተሰብ

ግዜን፤ ወጪንና ብክነትን ይቀንሳል; አነስተኛ የቤት ብድር እዲኖር ያስችላል; ተለዋዋጭ/ምቹነ,/ና ዉጤታማ የተጠራቀመ ዋጋ እዲኖር የደርገላ፡፡እዲሁም በህብረተሰብ ዉስጥመጋራትን ጠስፋፋል፡፡ s

13 አየርንብረት ጥበቃ

ተጠቃሚዎችን የካርቦን አሻራን እዲቀንሱ በማበረታታት ደሀ ቤተሰቦችን በአየር ለዉጥ ምክኒያት ከሚመጣ ኣደጋ በመከላከል ምቹ የአየር ንብረት መወዕለነዋይን የበረታታል

16 ሰላም፤ፍትህና ጠንካራ ተቀማት

የመዛግብትን ኦዲት መደረግና ግልጸኘነትን ይፈጥራል፡፡ ለመንግስት የገንዘብ ማስተላለፍን ወጪን በመቀነስ መደበኛ ኢኮኖሚ እዲኖር ረረደርጋል

SUSTAINABLE DEVELOPMENT GOALS

የሴቶች የኢኮኖሚ ተሳትፎ

የዲጂታል ክፍያዎችን መተግበር አይነተኛ አስተዋጽኦ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ማሳደግ መቻሉ ነው፡፡ ዲጂታል ክፍያ ሴቶች በግላቸዉ በመረጡት መንገድ ገንዘብን መላክና መቀበል እንዲችሉ ያግዛቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ሌሎች የቤተሰብ አባላት ሴቶች ገንዘባቸውን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ጫና በሚያሳድሩበት የማህበረሰብ ባህል ባለበት ሁኔታ የተሻለ አማራጭ እንዲያገኙ ያስችላል፡፡ ከሰሃራ በታች ባሉ አገራት የዲጂታል ክፍያ መተግበር የሴቶችን የኢኮኖሚ ነጻነት ከማረጋገጥ፣ የኢኮኖሚ ተሳትፎ ከማሳደግ እንዲሁም እንደ ቁጠባ ያሉ የፋይናንስ ምርቶችንና አገልግሎቶችን በስፋት ከመጠቀም አንጻር በጎ ተጽእኖ መፍጠሩን ለማረጋገጥ ተችሏል (World Bank et al. 2014)፡፡

በዓለም ላይ ያሉ አገራት የዲጂታል ክፍያ ስርዓትን አስፈላጊነትና ጥቅም እየተገነዘቡ በመጡበት በዚህ ሰዓት ሌሎች በርካታ አገራት ከበይነ መረብና የሞባይል ባንክ እንዲሁም የካርድ ክፍያ ተሻግረው በመሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡ የፋይናንስ ቴክኖሎጂ አቅራቢዎች (ፊንቴክ) የዓለምን የፋይናንስ ገበያ በበለጠ ፈጠራ እየቀየሩት ሲሆን በዘርፉ ለፈጠራ ያለው ምቹ ሁኔታ ለውጡ በፍጥነትና በማያቋርጥ ሁኔታ እንደሚቀጥል አመላካች ነው፡፡ ባንክ ፎር ኢንተርናሽናል ሴትልመንት በ2019 ባደረገው ጥናት በጥናቱ ከተሳተፉ የ63 አገራት ማዕከላዊ ባንኮች መካከል 70 በመቶ የሚሆኑት ዲጂታል ገንዘብን በሚመለከት የዝግጅት ስራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ማዕከላዊ ባንኮች በፍጥነት ከሚለዋወጠው የፋይናንስ ስነ-ምህዳር አንጻር እራሳቸውን የማላመድ ስትራቴጂ እየተከተሉ መሆኑን አመላካች ነው (Bank for International Settlements 2019)፡፡ በስዊድን የባንክ የጥሬ ገንዘብ የወረቀት ኖቶችን እና ሳንቲሞችን በኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ ለመቀየር የሚያስችል ውይይት ተደርጓል፡፡ ክሪፕቶከረንሲና ያልተማከለ ክፍያ ከቢትኮይን መምጣት ጀምሮ ዓለማቀፍ የመነጋገሪያ ርዕስ ሆኗል፡፡ ፌስቡክ እና የመሳሰሉ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች የራሳቸውን ክሪፕቶከረንሲ ለመጀመር መዘጋጀታቸውን ተከትሎ ዓለምአቀፍ ትኩረት ስቧል፡፡ በመጨረሻም የዲጂታል ክፍያዎች በተሟላ ሁኔታ መተግበርና ጥቅም ላይ መዋል ለኢትዮጵያ ህዝብና ኢኮኖሚ የበለጠ እድል ይከፍታል፡፡

ተግዳሮቶች

በኢትዮጵያ ዲጂታል ክፍያን በተሟላ ሁኔታ ለመተግበር ያሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች በአራት ምድብ ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ እነኚህም:- የመሠረተ ልማት፣ የመተግበር፣ የህግ ማዕቀፍ እና የፈጠራ ተግዳሮቶች ናቸዉ፡፡

መሰረተ ልማት፡- የመሰረተ ልማት ተግዳሮቶች አገር አቀፍ የመሰረተ ልማት ወስንነቶችና በክፍያ መፈፀሚያ ማሽኖች መካከል ያለው የተናባቢነት ሁኔታ ውስን መሆንን የተመለከቱ ናቸው፡፡ በማደግ ላይ ያለ መሰረተ ልማትና አስተማማኝነቱ ውስን የሆነ የቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌክትሪክ አገልግሎት በመኖሩ ለምሳሌ የኤሌክትሪክ መቆራረጥ፣ ዲጂታል ክፍያን ለመተግበር በተለይም በገጠር አካባቢ እንቅፋት ፈጥሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከፊል ተናባቢነት የክፍያ ከባቢ ሁኔታን ብሎም የፋይናንስ አካታችነት ዉጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡

ዲጂታል ክፍያን ማላመድ፡- ዲጅታል ክፍያን ሊያስጠቅሙ የሚችሉ አስቻይ ሁኔታዎች ዉስን መሆናቸዉ ዲጅታል ክፍያን ለመተግበር እንቅፋት ሆኗል፡፡ የተጠቃሚዎች ፍላጎት አናሳ በመሆኑ በህዝብ ተቋማትም ሆነ በግሉ ዘርፍ ለሚደረጉ ግብይቶች ህብረተሰቡ በጥሬ ገንዘብ መጠቀምን በመምረጡ ዲጅታል ክፍያ ሊያድግ አልቻለም[5]። ከአቅርቦት አንጻር ሲታይ የፍላጎት አናሳ መሆንን ተከትሎ ዲጂታል ክፍያን ለማሳደግ የሚያበረታታ የንግድ ሁኔታ የለም፡፡ ዲጅታል ክፍያ እንግዳ /አዲስ/ መሆኑን ተከትሎ የህብረተሰቡ አመኔታ ዝቅተኛ ነው፡፡

የህግ ማዕቀፍ፡- ባህላዊ /ተለምዷዊ/ ባልሆኑ የባንክ አሰራሮች በተለይም አነስተኛ ወጪ ያላቸዉ እንደ ወኪልና ሞባይል ባንኪንግ ለመሳሰሉ የአነስተኛ ክፍያ መንገዶች የህግ ማእቀፎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ፣ በቅርቡም ሁለት አዳዲስ የህግ መመሪያዎች ወጥተዋል[6]፡፡ በመሆኑም እነዚህ መመሪያዎች ባግባቡ መተግበራቸውን ለማረጋገጥ በቅርበት ክትትል በማድረግ የሚጠበቅባቸውን ውጤት ማምጣታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

የፈጠራ ከባቢ ሁኔታ፡- በቴክኖሎጂ የሚታገዙ የፋይናንስ አገልግሎቶች የፈጠራ ከባቢ ሁኔታ ለዓለምአቀፍ እውቀቶች፣ ሃብት እና የፋይናንስ ድጋፍ ተጠቃሚ ለመሆን ሊያግዙ ይችላሉ፡፡

ቀጥሎ የሚቀርበው የስትራቴጂ ማዕቀፍ ክፍል ከላይ የተለዩትን ተግዳሮቶች ለመፍታት ያለመ ነው፡፡

ከቁልፍ የሪፎርም ተግባራት ጋር ያለው መጣጣም

በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎችን የሚያካትት አገርአቀፍ ሪፎርሞችን በማካሄድ ላይ ትገኛለች፡፡ ይህንን ስትራቴጂ ጨምሮ በመካሄድ ላይ የሚገኙ የሪፎርም ተግባራት ተደምረው አገር በቀል የሪፎርም አጀንዳውንና[7] ከ 2020 እስከ 2030 የሚዘልቀውን የ 10 ዓመት ብሄራዊ የእድገት እቅድን [8]ለማሳካት ያግዛሉ፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚመራቸው የሪፎርም ተግባራት መካከል ሊኖር ከሚገባው ውስጣዊ መጣጣም ባሻገር የዚህ ስትራቴጂ ዝግጅት ከሰባት ቁልፍ ውጫዊ /ሀገራዊ/ የሪፎርም ተግባራት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ እነዚህም በሁለት ምድቦች ተከፍለዋል፣

- ብሔራዊ የዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂን ለሪፎርም ስኬታቸው እንደ ዋነኛ አስቻይ ስትራቴጂ የሚወሰዱ፡- ብሔራዊ የዲጅታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ እና የ10 ዓመት አገራዊ የእድገት እቅድ፣
- ከብሔራዊ የዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ጋር የተቆራኙ ስትራቴጂዎች፡- አገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም አጀንዳ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ ሪፎርም ፕሮግራም፣ የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አዋጅ[9] ፣ ብሔራዊ የዲጂታል መታወቂያ ፕሮግራም፣ የንግድ ስራ አመችነት ሪፎርም፡፡ እነዚህ የተዘረዘሩት በሙሉ ከብሔራዊ የዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ጋር ቁርኝት ያላቸው ሲሆን በትግበራ ወቅት ቀጣይነት ያለው መጣጣምና ቅንጅት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡

ምስል 3: ስትራቴጂው በመካሄድ ላይ ከሚገኙ ሪፎርሞች ጋር ያለዉ ቁርኝት

ብሔራዊ የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ

ዉስጣዊ ቁርኝነት

የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ

የፋይናንስ አካጀታችነት ስትራቴጂ

የፋይናንስ ዘርፍ ሪፎርም

በቅርብ ከጸደቁ መመሪያዎች
- የክፍያ ሰነድ አዉጪዎች መመሪያ
- የወኪል ባነክ አገልግሎት መመሪያ

በረቂቅ ደረጃ ካሉ መመሪያዎች
- የክፍያ ስረዓት ኦፕሬተሮች መመሪያ
- የደንበኞች ጥበቃ መመሪያ
- የባንክ ዘርፍ የበየነመረብ ደህንነት መመሪያ

ዉጫዊ ቁርኝነት

ምድብ 1: ከ አስፈላጊ/አስቸከይ/ና ተፈጻሚ ዕቅዶች ጋራ ያለዉ ቁርኝነት

ገንዘብ ሚኒስቴር
ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም አጀንዳ

የኢትዮጲያ ኮሚኒከሽን ባለስልጣን
የቴልኮምኒኬሽን ሴክተር/ዘርፍ/ ሪፎርም

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚነሰቴር
ኤሌክተሮኒስ ተራነዛክሽን አዋጅ

የሰላም ሚነስቴር
ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ፕሮግራም

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
የንግድ አሰራር ቅልጥፍና ሪፎርም

ምድብ 2: ለብሔራዊ ዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ እንደ ወሳኝ መሰረት የተወሰዱ ሪፎረሞች

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚነሰቴር
ብሔራዊ ዲጂታል ትራነስፎረሜሽን ስትራቴጂ

የፕላንና ልማት ኮሚሽን
10-አመት ብሔራዊ መሪ እቅድ

ከላይ በምስል 3 እንደተመለከተው እነዚህ የሪፎርም ሥራዎች በተለያዩ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና መንግስታዊ ተቋማት የሚተገበሩና በተለያየ የትግበራ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ በተለያዩ ተቋማት የሚተገበሩ የሪፎርም ሥራዎች ስፋትና ጥልቀት በዚህ ስትራቴጂ ትግበራ ላይ የሚፈጥሩት ተግዳሮትና መልካም አጋጣሚ በመኖሩ የትብብር መስኮችንና ሊያጋጥሙ የሚችሉ መደራረቦችን በጥልቀት መገምገም ያስፈልጋል፡ ፡ ይህ ስትራቴጂ በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ የእድገት ጉዞ አንድ አካል መሆኑን ለማረጋገጥ ሲባል ከተጠቀሱት የሪፎርም ተግባራት ጋር ያለውን ቁርኝት ለማረጋገጥና ለማጣጣም እንዲቻል በጥልቀት ተገምግሟል፡፡ ዝርዝሩ በአስቻይ 3፡ እየተተገበሩ ካሉ አገርአቀፍ የእድገት ሪፎርም ሥራዎችና ፖሊሲዎች ጋር የሚኖርን ቅንጅት ማረጋገጥ በሚለው ክፍል ይቀርባል፡፡

ከ.

ብሔራዊ ዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ማዕቀፍ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ማዕቀፍ ራዕይ፣ ራዕዩን ለማሳካት የሚያግዙ ስትራቴጂክ ምሰሶዎችና እንደ መደላድል የሚያገለግሉ ቁልፍ አስቻይ ሁኔታዎችን ያካተተ ነው፡፡

ለ1. ስትራቴጂክ ራዕይ

ከላይ በምስል 4 እንደተመለከተው የብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ራዕይ፡- ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ተወዳዳሪ፣ ወጭ ቆጣቢ፣ በፈጠራ የታገዘና ሃላፊነቱን በአግባቡ የሚወጣ የክፍያ ከባቢያዊ ሁኔታ በመገንባት ውስን ጥሬ ገንዘብን የሚጠቀምና የፋይናንስ አካታችነትን የተላበሰ ኢኮኖሚን ማገዝ ነዉ፡፡

- ደህንነቱ የተጠበቀ፡- ደህንነቱ የተጠበቀ ክፍያ እና ደንበኞቹን መከላከል የሚያስችል፣
- ተወዳዳሪ፡- ዲጅታል ክፍያን ለመተግበር እና በዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ የክፍያ ስርአቶችን ለማቅረብ ማበረታቻዎችን መፍጠር፣
- ወጭ ቆጣቢ፡- ጤናማ ፈጣንና በአግባቡ የሚሰራ የክፍያ ከባቢ ሁኔታን መፍጠር፣
- በፈጠራ የታገዘ፡- ለተገልጋዮች ምቹና ተጨማሪ ወጭ ቆጣቢ የግብይት አማራጮች እንዲኖሩ ማስቻል፣
- በሃላፊነት ስሜት የሚንቀሳቀስ፡- የዲጅታል ክፍያ አገልግሎትን ከማግኘትም ሆነ ከመጠቀም አንጻር አመኔታና በራስ መተማመን እንዲኖር ማስቻል፣
- አነስተኛ ጥሬ ገንዘብ መጠቀም[10]፡- የበለጠ ተደራሽ፣ አስተማማኝና ግልጽነት ወዳለው የክፍያ ከባቢያዊ ሁኔታ መድረስ፣
- አካታች፡- ሁሉንም ዜጋ ተጠቃሚ ማድረግ፡፡

ይህ የብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ራዕይ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ተጠቃሚ የሚያደርግ የክፍያ ከባቢ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስፈልገውን ወሳኝ ለውጥ (ተለምዷዊ አሰራሮችን በመረበሽ) ስልታዊና እመርታዊ በሆነ መንገድ ለመግለጽ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ መንግስት በሁሉም ረገድ የተሻለ ሊባል የሚችል የላቀ አፈጻጸም ማስመዝገብ የሚችል ዓለማቀፍ የክፍያ ከባቢያዊ ሁኔታን ለመገንባት ያለውን ቁርጠኝነት ያጠናክራል፡፡

ራዕዩ በአገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም አጀንዳና የ10 ዓመት አገራዊ የእድገት እቅድ[11] ላይ ከተቀመጡት አገራዊ ትልሞች ጋር የሚጣጣም ነው፡፡ የሪፎርም አጀንዳው ውጤታማ የፋይናንስ ገበያ በመገንባት ፈጣንና አካታች የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥን ለሚቀጥሉት 10 ዓመታት እንደ አንድ ዋነኛ የልማት ግብ ለይቷል፡፡ በመሆኑም ይህ ስትራቴጂ የዲጂታል ክፍያ ከባቢ ሁኔታን በማበልጸግ የተቀመጠውን ብሔራዊ ራዕይ ለማሳካትና አገሪቱን በብልጽግና ጎዳና ላይ ማራመድን ዓላማ አድርጓል፡፡

ምስል 4: የብሔራዊ ዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ማዕቀፍ

ራዕይ

1 ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ተወዳዳሪ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ በፈጠራ የታገዘና ሃላፊነቱን በአግባቡ የሚወጣ የክፍያ ከባቢያዊ ሁኔታ በመገንባት ዉስን የጥሬ ገንዘብን የሚጠቀምና የፋይናንስ አካታችነትን የተላበሰ ኢኮኖሚን ማገዝ ነዉ፡፡

ስትራቴጂክ ምሰሶዎች

2	3	4	5
አስተማማኝ፣ አካታችና ተናባቢ መሰረተ ልማት መገንባት	ዲጂታል ክፍያን በመተግበር አካታችነቱን ማረጋገጥ	ሁሉን አቀፍና ዉጤታማ የህግ ድንጋጌዎችና የክትትልና ቁጥጥር ማዕቀፍ እዲኖረ ማስቻል	ለአዳዲስ ግኝቶችና ፈጠራዎች ከባቢ ሁኔታ እንዲኖር ማድረግ

አስቻይ ሁኔታዎችS

6 አስተማማኝ፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ዉጤታማ አገርአቀፍ የክፍያ ስርዓትን ለመገንባት ያለዉ ቁርጠኝነት

7 በዲጂታል ክፍያ ከባቢያዊ ሁኔታ ላይ የአቅም ግንባታ ስራዎች ለማከናወን ቅድሚያ ትኩረት መስጠቱና አስፈላጊዉን ሃብት መመደብ

8 ከአገሪቱ የልማት እድገት ሪፎርም ስራዎችና ፖሊሲዎች ጋር ቀጣይነት ያለዉ ቅንጅትና መናበብ እዲኖር ማድረግ

9 ዉጤታማ የአስተዳደርና የትግበራ እቅድ ግንባታና ቁልፍ የአፈጻጸም መለኪየዎችን በማዘጋጀት አፈጻጸምን መለካት የሚያግዝ አሰራር ማኖር

ለ2. ስትራቴጂክ ምሰሶዎች

የብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ራዕይን ለማሳካት አራት ስትራቴጂ ምሰሶዎች ተለይተዋል፡፡ እነዚህ ምሰሶዎች ራዕዩን ከማሳካት አንጻር አስፈላጊውን ጥንካሬ በመስጠት ያግዛሉ፡፡

- ስትራቴጂክ ምሰሶ 1፡ አስተማማኝ፣ አካታችና ተናባቢ መሰረተ ልማት መገንባት፣
- ስትራቴጂክ ምሰሶ 2፡ ዲጂታል ክፍያን በመተግበር አካታችነቱን ማረጋገጥ፣
- ስትራቴጂክ ምሰሶ 3፡ ጠንካራ (ውጤታማ) እና ወጥነት ያለዉ የህግ ድንጋጌዎችና የክትትልና ቁጥጥር ማዕቀፍ መገንባት፣
- ስትራቴጂክ ምሰሶ 4፡ ለአዳዲስ ግኝቶችና ፈጠራዎች አስቻይ ከባቢ እንዲኖር ማድረግ፣

ለ2.1.ስትራቴጂያዊ ምሰሶ 1፡ አስተማማኝ፣ አካታችና ተናባቢ መሰረተ ልማት መገንባት

መነሻና ቁልፍ ተግዳሮቶች

በኢትዮጵያ ለዲጂታል ክፍያ እድገት አስፈላጊ የሆኑ የመሰረተ ልማት ሁኔታዎች ሊያድጉና ሊሻሻሉ ይገባል፡፡ በኢትዮጵያ የተንቀሳቃሽ ስልክ ተጠቃሚዎች ቁጥር 40 በመቶ ሲሆን የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ቁጥር ደግሞ 19 በመቶ ነው፡፡ በአንጻሩ ከሰሃራ በታች የሚገኙ አገራት አማካይ የተንቀሳቃሽ ስልክ 86 በመቶ እንዲሁም የኢንተርኔት 26 በመቶ ተጠቃሚዎች አሉ (World Bank Group 2020c; GSMA 2020; International Telecommunications Union 2020) ፡፡

> "ዓለም ዲጂታል እየሆነች ነው፤ እኛም የዚሁ አካል መሆን ይገባናል"
> በስትራቴጂው ዝግጅት ወቅት ባለድርሻ አካላት ከተናገሩት፣

በኢትዮጵያ የፋይናንስ አገልግሎት መሰረተ ልማት በፍጥነት እያደገ ነው፣ ነገር ግን የስርጭት መጠኑ አሁንም ከሰሃራ በታች ካሉ አገራት ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው፡፡ በኢትዮጵያ 18 ባንኮችና 35 የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት 109 ሚሊዮን ለሚሆን ህዝብ አገልግሎት ይሰጣሉ አብዛኞቹ ቅርንጫፎችም በከተሞች አካባቢ የሚገኙ ናቸው፡፡ የባንክ ቅርንጫፍ የነብስ ወከፍ ስርጭት በ2004 ከነበረበት 0.8 ለ100000 ሰዎች በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመር በ 2019 4.7 ለ 100000 ሰዎች ደርሷል፡፡ ይህም ሆኖ ግን ከሰሃራ

በታች ካሉ አገራት አማካይ 5.2 ለ 100000 ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው (International Monetary Fund 2020; World Bank Group 2019)[12] ፡፡ የሞባይል ገንዘብ ወኪል ስርጭት በኢትዮጵያ ገና በጅምር ላይ የሚገኝ ሲሆን በ2019 ብዛታቸው 13000 አካባቢ ነው[13]፡፡ በአንጻሩ በ2018 በጋና 400,000፣ በኬንያ 206,000 እንዲሁም በሩዋንዳ 110,000 የሞባይል ገንዘብ ወኪሎች ይገኛሉ (International Monetary Fund 2020)፡፡

የኢትዮጵያ የክፍያ ስርዓት ዘመናዊነት የጀመረው በ2011 የኢትዮጵያ አውቶሜትድ ትራንስፈር ሲስተም /EATS/ መተግበርን ተከትሎ ነው (World Bank Group 2020a)፡፡ የዲጂታል ክፍያ ተናባቢነት መሰረተ ልማት ኢትስዊች ከተመሰረተ ከአምስት አመታት በኋላ በ2016 ሥራ ጀምሯል፡፡ ኢትስዊች ውጤታማ፣ አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ የኤሌክትሮኒክ ክፍያ መሰረተ ልማት ማቅረብን አላማው አድርጎ በሁሉም የመንግስትና የግል ባንኮች የድርሻ መዋጮ ባለቤትነት የተቋቋመ የስዊች መሰረተ ልማት ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ ስድስት ባንኮች በቀጥታ በኢትስዊች በኩል የሚጠቀሙ ሲሆን ሌሎች ስድስት ባንኮች የራሳቸው ስዊች አላቸው ቀሪዎቹ ስድስት ባንኮች ደግሞ በጋራ ባቋቋሙት ፕሪሚየር ስዊች የተሰኘ ስዊች በኩል ይጠቀማሉ[14]፡፡ ይህም ሆኖ ግን ሁሉም ስዊቾች ብሔራዊ ስዊች ከሆነው ኢትስዊች ጋር እንዲገናኙ ይደረጋል፡፡ ማይክሮፋይናንስ ተቋማት እንዲሁም ሁሉም የተፈቀደላቸው የፋይናንስ ተቋማት በቅርቡ ኢትስዊችን እንደሚቀላቀሉ ይጠበቃል፡፡ የኢትስዊች አባልነት በሁለት አይነት መንገድ ሲሆን ቀጥታ ተሳታፊነት (በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የክፍያና ማወራረጃ ሂሳብ ላላቸው) እንዲሁም በተዘዋዋሪ ተሳታፊነት በንግድ ባንኮች በኩል (በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የክፍያና ማወራረጃ ሂሳብ ለሌላቸው)፡፡

እስካሁን ባለው ሁኔታ የገንዘብ መክፈያ ማሽኖች / ATM/ ተናባቢነት የተተገበረ ሲሆን ሌሎች የክፍያ መንገዶች ተናባቢነት በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድ ጠቃሚ እርምጃዎች በ2020 እንደሚወሰዱ ይጠበቃል፡፡

- ኤሌክትሮኒክስ የገንዘብ ዝውውር :- (ከአንድ ባንክ ሂሳብ ወደ ሌላ ባንክ የሚገኝ ሂሳብ)[15]:- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በአሁኑ ሰዓት ከአንድ ባንክ ሂሳብ ወደ ሌላ ባንክ ሂሳብ የሚደረግ የገንዘብ ዝውውርን በሙከራ ትግበራ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ አገልግሎት በቀጣይ ወራት ሙሉ ለሙሉ እንደሚተገበር ይጠበቃል፡፡
- የክፍያ ነቁጥ ተናባቢነት፡- ኢትስዊች የክፍያ ነቁጥ ተናባቢነትን በአገር ውስጥና ዓለማቀፍ የክፍያ ካርድ ኔትዎትኮች የሙከራ ትግበራ በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ አገልግሎት በቀጣይ ወራት ሙሉ ለሙሉ እንደሚተገበርና አገልግሎት እንደሚጀምር ይጠበቃል፡፡
- ሌሎች የክፍያ መንገዶች ተናባቢነትን ማስፋት፡- የክፍያ ነቁጥ ተናባቢነት ትግበራን ተከትሎ የኤሌክትሮኒክ ባንኪንግና የሞባይል ዋሌት ተናባቢነትን ለመተግበር እቅድ የተቀመጠ ሲሆን ትግበራው በሞባይል ዋሌት የሚጀምር ይሆናል፡፡

ከተናባቢነት ተግዳሮት ባሻገር በሁሉም የክፍያ መንገዶች ላይ ተጠቃሚዎች ተደጋጋሚ የቴክኒክ ችግሮች መኖራቸውን ይገልጻሉ[16]፡፡ ይህ ሁኔታ በሚከተለው ምስል 5 ቀርቧል፡፡

ምስል 5: በክፍያ መፈጸሚያ መሳሪያዎች መካከል ያለ ተናባቢነት

	ኤ.ቲ.ኤም	የክፍያ ነቁጥ	ኢ- ባንኪንግ	የሞባይል ገንዘብ
መጠቀሚያ ምክኒያቶች	✓ የባንክ ሂሳባችን ካለበት ባንክ ኤ.ቲ.ኤም ጥሬገንዘብ ማዉጣት ✓ ከሌላ ባነክ ኤ.ቲ.ኤም ጥሬ ገንዘብ ማዉጣት ✓ ተመሳሳይ ባነከ ዉስጥ ባሉ ሂሳቦች መካከል ገንዘብ ማስተላለፍ ✓ በተለያዩ ባነኮች ባሉ ሂሳቦች መካከል ገንዘብ ማስተላለፍ ✓ በተመሳሳይ ባነከ ዉስጥ ያለን ቀሪ ሂሳብ ማወቅ ✓ በተለያዩ ባነከ ዉስጥ ያለን ቀሪ ሂሳብ ማወቅ	✓ በተመሳሳይ ባንክ የዴቢት ወይም ክሬዲት ካረድ እና የክፍያ ነቁጥ ክፍያን መፈጸም × በተመሳሳይ ባንክ የዴቢት ወይም ክሬዲት ካረድ እና የክፍያ ነቁጥ ክፍያን መፈጸም	○ በዲጂታል አማካኝነት ገንዘብ ከመደበኛ ሂሳብ ወደ ሞባይል ገንዘብ ማስተላለለፍ ✓ በተመሳሳሰይ ባንከ ዉስጥ ባሉ ሂሳቦች መካከል ገንዘብን ማስተላለፈ × በተለያዩ ባንኮች ዉስጥ ባሉ ሂሳቦች መካከል ገንዘብን ማስተላለፈ	✓ በ ሞባይል ገንዘብ ኣማከኘነት በተመሳሳሰይ ባነክ ዉሥጥ ላለ አገልግሎለትተ ሰጪ/ቸርቻሪ ሂሳብ ክፍያን መፈጸም × በ ሞባይል ገንዘብ ኣማከኘነት በተለያየ ባነክ ዉሥጥ ላለ አገልግሎለትተ ሰጪ/ቸርቻሪ ሂሳብ ክፍያን መፈጸም
የተጠቃሚዎች ዕይታ	ብዙዉን ጊዜ ኤ.ቲ.ኤም ካገልግሎት ዉጪ መሆን ተደጋጋሚ የአገልግሎት ክፍያ መክፈል እዲዉም መክፍያ ደረሰኝ መቀበል	ብዙዉን ጊዜ የክፍያ ነቁጥ ካገልግሎት ዉጪ መሆን/በቴሌኮም ወይም በሲስተም ጉዳዮች ተደጋጋሚ የአገልግሎት ክፍያ መክፈል	አገልግሎለቱ 24/7 ያለማግኘት ወይም ብዙዉን ጊዜ አገልግሎለት ያለመስጠት ብዙዉን ጊዜ ቀሪ ሂሳብን በትክክል ለለለመግለጽ እና የባንክ ማረጋገጫን መሻቱ	በሞባይ ገንዘብ በሚከፈል ክፍያ የሚገኝ ኢ- ደረሰኝ ጠቀባይነት የለመኖር(ምሳሌ, ከክፍያ ጋር ተያይዞ ለሚኖር አለመግባባት መፍቻ ሆኖ አለማገልገል)

✓ ሙሉ በሙሉ ተናባቢየሆነ ○ የተወሰነ ተናባቢት ያለዉ × ሙሉ ለሙሉ ተናባቢ ያልሆነ

ሰፋ ባለ ዕይታ፣ አገርአቀፍ የመሰረተ ልማት ተግዳሮቶች በፋይናንስ አገልግሎትና ዲጂታል ክፍያ መሰረተ ልማቶች ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ ያሳድራሉ፡፡ በተለይም አስተማማኝ የኔትዎርክ ሽፋን አለመኖር፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽነት ውስን መሆን፣ የተማከለ ብሔራዊ መለያ (መታወቂያ) ስርዓት አለመኖር በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

የኔትዎርክ ሽፋን

በኢትዮጵያ የኢንተርኔት መልክአ ምድራዊ ሽፋን 86 በመቶ የሚሆነው የ2G፣ 85 በመቶ የ 3G እና 70 በመቶ የ4G ነው (GSMA 2020)፡፡ ይህም ሆኖ 19 በመቶ ብቻ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ትርጉም ባለው ሁኔታ ኢንተርኔትን ይጠቀማሉ፡፡ ደካማ የቀጥተኛ (Real time) ግንኙነትና አስተማማኝነት፣ ዝቅተኛ የዲጂታል ግንዛቤ (እውቀት)፣ እንዲሁም ከፍተኛ የአገልግሎት ክፍያ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎቱን እንዳይጠቀሙ ምክንያት ሆኗል[17]፡፡ መሰረተ ልማትን በማጎልበት አስተማማኝ የኢንተርኔት ግንኙነት በሰፊ መልክአ ምድር እንዲኖር ማድረግ ዲጂታል ክፍያ፣ ኢንተርኔትን ጨምሮ በመተግበሪያ የሚሰሩ የባንክ አገልግሎቶች፣ ቅጽበታዊ (Real time) ክፍያዎች እንዲሁም የገንዘብ መክፈያ ማሽኖች /ATM/ እና የክፍያ ነቁጥ /POS/ መሳሪያዎች የኔትዎርክ ግንኙነትን አስተማማኝ ለማድረግ አስቻይ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

በቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ የሚደረገው ሪፎርም

በአገልግሎት ጥራትና ተደራሽነት ላይ ትርጉም ያለው እድገት እንደሚያመጣ ይጠበቃል፡፡ ኢትዮ ቴሌኮምን በከፊል ወደ ግል ይዞታ ለማዛወርና በሂደቱም ለሁለት ተጨማሪ ኦፕሬተሮች ፈቃድ ለመስጠት የተወሰነው ውሳኔ በቴሌኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማት ዘርፍ የሚደረገውን ኢንቨስትመንት እንደሚያሳድገው ይጠበቃል፡፡ በተያያዘም በዘርፉ በጥራትና ውጤታማነት ረገድ የሚኖረው ውድድር ይጨምራል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከገንዘብ ሚኒስቴር፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ እንዲሁም ከኢትዮጵያ የኮሙኒኬሽን ባለስልጣን ጋር በቅርበትና በትብብር በመስራት የሞባይል ኔትዎርክ ኦፕሬተሮች /MNOs/ በፋይናንስ ስነ-ምህዳሩ ውስጥ ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና ለመወሰን እንዲሁም ከቴሌኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማት እድገት መስፈርቶች ጋር እንዲጣጣም በማድረግ የዲጂታል ክፍያ ስነ ምህዳሩን ቀጣይነት ያረጋግጣል፡፡

የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽነት

ምንም እንኳን የኢትዮጵያ መንግስት በኤሌክትሪክ ኃይል ዘርፍ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ላይ የሚገኝ ቢሆንም በኢትዮጵያ ለኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽ የሆኑት ዜጎች 44 ከመቶ ብቻ ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ባህላዊ የባንክ መሰረተ ልማት (የገንዘብ መክፈያ ማሽን፣ የክፍያ ነቁጥና ሌሎችም) እና ባህላዊ ያልሆኑ የባንክ መሰረተ ልማት (ሞባይል ገንዘብ)[18] መስፋፋትና አስተማማኝነት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ በሌሎች ከሰሃራ በታች ባሉ አካባቢዎች በሞባይል ገንዘብ የሚሰሩ pay-as-you-go ከግሪድ ውጭ ያሉ አማራጮች በገጠር አካባቢ ለሚኖሩ ዜጎች የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽነት አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ይህ የኤሌክትሪክ ተደራሽነት አዎንታዊ ኡደትን በመፍጠር እንደ ራውተር ያሉ የግንኙነት መሳሪያዎች ኃይል እንዲያገኙ ወይንም ተንቀሳቃሽ ስልኮች ኃይል እንዲሞሉ አስችሏል፡፡ ይህንን በተመለከተ ከውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት መስራትን ይጠይቃል፡፡

የዜግነት መታወቂያ ስርዓት

የተማከለ ብሔራዊ የመለያ (መታወቂያ) ስርዓት አለመኖር የፋይናንስ ሴክተሩ ወጭን በሚቀንስ አግባብ አዳዲስ ደንበኞችን የመቀበል አቅሙ ውስን እንዲሆን አድርጎታል፡፡ የሰላም ሚኒስቴር በጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ እገዛ ብሔራዊ የመለያ (መታወቂያ) ሰነድ በማዘጋጀት ላይ ነው፡፡ ትግበራው ደረጃ በደረጃ የሚካሄድ ሲሆን በሚቀጥሉት ስድስት አመታት በአገራቀፍ ደረጃ ሙሉ ለሙሉ የሚዳረስ ይሆናል፡፡ የዜጎች ብሄራዊ መታወቂያ ስርዓት መኖር ወጭ ቆጣቢ በሆነ መንገድ የደንበኛህን እወቅ /KYC/ ፕሮግራምን ለማከናዎን ያግዛል፡፡ ወጭ ቆጣቢ የደንበኛህን እወቅ /KYC/ ስርዓት አለመሟላት የፋይናንስ ምርቶችን በስፋት ለመጠቀም ገዳቢ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ብሔራዊ የዜግነት መታወቂያ በኢትዮጵያ ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ የሚገባ ፕሮግራም ነው፡፡ በመሆኑም ከሰላም ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት መስራትና ከዚህ ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ዓለም አቀፍ መልካም ተሞክሮዎች

ለዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ትግበራ መሰረተ-ልማት ረገድ ያሉ መልካም ተሞክሮዎች ከተደራሽነት፣ ከተናባቢነት (interoperability) እንዲሁም ከሰፊው የመሠረተ ልማት እንደ ብሔራዊ የዲጂታል መለያ መታወቂያ ሥርዓት አንጻር የዓለምአቀፍ ተሞክሮዎች ተዳስሰዋል፡፡

የተደራሽነት ነጥቦች (Access Points)

ከምስል 6 መገንዘብ እንደሚቻለው በዓለምአቀፍ ደረጃ የባህላዊ የባንክ ሥርዓት መሰረተ-ልማት (ለምሳሌ የገንዘብ መክፈያ ማሽን) ቁጥር በተለይም ዲጂታል ክፍያን በከፍተኛ ሁኔታ በሚጠቀሙ አገራት እያሽቆለቆለ መምጣቱን እንመለከታለን፡፡ በብራዚል፣ ስዊድንና ዩናይትድ ኪንግደም ከፍተኛ ደረጃ የዲጂታል ክፍያ ቢኖራቸዉም የጥሬ ገንዘብ ዝውውርና አጠቃቀም በከፍተኛ ሁኔታ እየቀነሰ ይገኛል፣ እንዲሁም በነዚህ ሀገራት የገንዘብ መክፈያ ማሽን ቁጥር እየቀነሰ መጥቷል (World Bank Group 2020d; International Monetary Fundn 2020)፡ ፡ ይህ ለውጥ ሊመጣ የቻለው የዲጂታል የክፍያ ሥርዓት መሰረተ-ልማት በማደጉ፣ በቀን 24 ሰዓትና ሁሉንም ቀናት ክፍያ መፈጸም የሚቻልባቸው የክፍያ ነቁጥ (POS) አማራጮች፣ የሞባይል የክፍያ ነቁጥን (M-POS) ጨምሮ መፈጠራቸውና የተንቀሳቃሽ ስልኮች መተግበሪያዎች በአማራጭነት መቅረባቸው ነው፡፡ በዲጂታል ክፍያ ሥርዓት ዕድገት ውስጥ አስተማማኝና ፈጣን የኢንተርኔት አገልግሎት መሰረተ-ልማት ዕድገት ወሳኝ ድርሻ ተጫውቷል፡፡

ምስል 6: ተነጻጻሪ ዕየታ ፡ የኤ.ቲ.ኤም ዕድገት (2014–2017) ከ . ዲጂታል ክፍያ ድርሻ (2017)



እንደ ገንዘብ መክፈያ ማሽን ያሉ ጠንካራ የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጭ ማድረጊያ መሰረተ-ልማት ኔትወርክ ትስስር ለዲጂታል ክፍያ እድገት ገፊና ወሳኝ መነሻ ምክንያት መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በሌሎች አገራት በተለይም በናይጄሪያ፣ በህንድና በባንግላዴሽ ማዕከላዊ ባንኮች እንደታየዉ የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጭ ማድረጊያ መሰረተ-ልማት ኔትወርክ በከተሞችና ገጠር አካባቢዎች በሚገኙ የገንዘብ መክፈያ ማሽን እንዲሁም የቅርንጫፎችን ስርጭት የማመጣጠን ሥራ ሰርተዋል (India Brand Equity Federation 2011; State Bank of Pakistan 2007; Remo 2012; World Bank 2012)፡፡

ለነጋዴ ግብይት ክፍያዎች የክፍያ ነቁዋን የሚተኩ በዋጋ ተመጣጣኝና ምቹ የክፍያ አማራጮች ለምሳሌ የሞባይል የክፍያ ነቁጥ እና ፈጣን ምላሽ መለያ (QR Codes) የመሳሰሉት መሰረተ-ልማቶች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ሞባይል የክፍያ ነቁጥ(M-PoS)፣ ስማርት/ ዘመናዊ/ የክፍያ ነቁጥ አሰራር ሲሆን ከስማርት ስልኮች ወይም ታብሌት ጋር በመገኛኘት ክፍያዎችን ለመፈጸም የሚያስችል ሲሆን የደንበኞችን መረጃ ለመከታተልና ለማስተዳደር ያግዛል፡፡ ሞባይል የክፍያ ነቁዋን ስራ ላይ ማዋል ከተለመደው ባህላዊ የክፍያ ነቁጥ ጋር ሲነጻጸር ዋጋው ያነሰ ነው(Square 2018; SmartPay 2018)፡፡ ፈጣን ምላሽ መለያ (QR ኮድ) የምንላቸው የባር ኮድ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ምስሎች ሲሆኑ በነጋዴው የክፍያ ቦታ በመቀመጥ በተጠቃሚዎች ሞባይል ስልክ የሚገኙ መረጃዎችን ለመጠቀም በማገበብና እንደ ግብዓት በመጠቀም የክፍያ ትዛዞችን ለማነሳሳት ያገለግላሉ ፡፡ QR ኮዶች ነጋዴው የአገልግሎት ክፍያ ለአቅራቢዎች ብቻ በመፈጸም አገልግሎት የሚያገኝበት ሲሆን ምስል ብቻ ስለሚፈለግ ከሞባይል ስልክ ውጪ የሚያስፈልግ ተጨማሪ መሳሪያ የለም፡፡ ነጋዴው ለጥገና የሚከፍለው ተጨማሪ ወጪም የለበትም፡፡

በቻይና ዊ ቻት ፔይ (WeChat Pay) እና አሊ ፔይ (Alipay) በዚሁ የQR ኮዶች አማካኝነት ከፍተኛ ግብይት የሚፈጸምበት ሲሆን በተለይም በሱፐር ማርኬቶችና በምግብ ቤቶች በሰፊው ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በህንድ QR ኮዶችን ለትንንሽ ግብይቶች በመጠቀም የዲጂታል የክፍያ ሥርዓት እንዲስፋፋ በሰፊው ተሰርቷል፡፡ እነዚህን አዳዲስ አማራጮችን በመጠቀም የዲጂታል የክፍያ ሥርዓት እንዲያድግ የስማርት ስልኮችና ፈጣን የኢንተርኔት አገልግሎት ማደግ ትልቅ ሚና አለው፡፡ ጋና በቅርቡ አገር አቀፍ የ QR ኮድ የክፍያ ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መስፋፋትን ለመቆጣጠር ተጠቅማበታለች፡፡ በስማርት ስልኮች አማካኝነት የሚፈጸመው ይህ የክፍያ ሥርዓት የተለያዩ ባንኮችና የሞባይል ኔትወርክ አቅራቢዎች በቅንጅት የሚያቀርቡትና ከአንዱ ባንክ እንዲሁም የሞባይል ኔትወርክ ወደሌላው ክፍያዎችን መፈጸም የሚያስችል የተናበበ አሰራር ነው (Joy Online 2020)፡፡

ተናባቢነት

ተናባቢነት ለስኬታማ እና አካታች ዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ስነ ምህዳር እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ አብዛኞቹ የዓለም አገራት የክፍያ ሥርዓቱን በሚከተለዉ መልኩ የሚያቀናጅ ብሔራዊ ስዊች አስፈላጊነትን እዉቅና ሰተዋል፡-

- በገንዘብ መክፈያ ማሽኖች፣ በክፍያ ነቁጥ፣ የኤሌክትሮኒክስ ክፍያዎች እና ሌሎችም ተናባቢነት እንዲኖር ማስቻል
- ባንኮች እንዲተሳሰሩ እጅግ አመቺ መሰረተ-ልማትን በመፍጠር፣
- በቀን ለ 24 ሰዓት በሳምንት ለ7ቀን ክፍያዎችን በቅጽበት (real time) ለመፈጸም ያስችላል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ሶስት ነገሮችን በዉጤታማነት ማግኘት የዲጂታል የክፍያ ሥርዓትን በመተግበር ረገድ መሰረት የሚጥል ሲሆን፣ አስተማማኝ፤ ውጤታማና የተሳለጠ የንግድ ልዉዉጥ እንዲኖር ያግዛል፡፡

Consultative Group to Assist the Poor (CGAP) የተባለው ቡድን (Garcia Arabehety etal. 2016) ተናባቢነትን አስመልክተው ባደረገው ጥናት የክፍያ ሥርዓት በሁሉም ስርዓቶች ተናበው መስራት፣ ሰዎች ክፍያዎችን ከየትኛውም አማራጭ መቀበል እንዲሁም መላክ መቻላቸው ፈጣንና ዋጋው ተመጣጣኝ አገልግሎት እንዲያገኙ በማስቻል ለተገልጋዩ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ነው፡፡ የፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢዎች ከዚህ ከፍተኛ ቁጥር ካለው ግብይት የሚገኘውን አዲስ የቢዝነስ ዕድሎች ለመጠቀም በበጎ መልኩ ተቀብለውታል፡፡ ፖሊሲ አውጪዎችም የፋይናንስ አካታችነትን በማረጋገጥ ረገድ ከአንዱ ስርዓት ወደሌላው ስረዓት መስራት የሚያስችሉ ተናባቢ አሰራሮችን በመዘርጋት ዜጎች በፋይናንስ ስርዓቱ በመካተት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ትኩረት አድርገዋል[19]፡፡

የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ተናባቢነትን ማስፋፋት (የተለያዩ የሞባይል ዋሌት አገልግሎት ሰጭዎች ሲኖሩ) የፋይናንስ ተደራሽነትን በማረጋገጥ ዜጎች የፋይናንስ ስርዓቱ ውስጥ ተካታች እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ በኬንያ ፋይናንሻል ሴክተር ዲፕኒንግ (Financial Sector Deepening, FSD Kenya) እንደተገለጸው፣ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ባላቸውና ኢመደበኛ ቢዝነስ ለሚሰሩ ዜጎች በገበያ ውስጥ ያለውን ወጪ ይቀንሳል፡፡ ስኬታማ ነው የሚባለውና በፋይናንስ ስርዓቶች መካከል ያለው እርስ በርስ ተናቦ መስራት መቻል (interoperability) ጥሩ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰደው የታንዛንያ ተሞክሮ ነው፡፡ እ.ኤ.አ. በ2014 የተጀመረው ይህ አሰራር በአሁኑ ወቅት 30% ከግለሰብ ወደ ግለሰብ ያለውን ግብይት ለመሸፈን አስችሏል (Mburu 2018)፡፡

ተናባቢ የክፍያ ስርዓትን ለማስፋት በተቻለ መጠን ለተጠቃሚዎች ወጪው ዝቅተኛ መሆን አለበት፡፡ ለዚህም ደግሞ በስዊች አቅራቢዎች፣ በክፍያ ስርዓቱ እንዲሁም በክፍያ አገልግሎት አቅራቢዎች የአገልግሎት ክፍያ መዋቅሩ ላይ በመስራት ለተጠቃሚዎች የኢኮኖሚ ማበረታቻ በመፍጠር ይህንን ተናባቢ አሰራር ማበረታታት የአገልግሎት አቅራቢዎችም አገልግሎቱን ከማስፋት የሚገኘውን ጥቅም መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን መዋቅር በመዘርጋት ሂደት ውስጥ አራት መሰረታዊ

የአገልግሎት ክፍያዎችን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ CGAP እነዚህን አራት የአገልሎት ክፍያ አይነቶች በሚከተለው መንገድ ይተነተናል (Niehaus & Cook 2018)፡፡

- የአሰራር ሥርዓት ክፍያዎች (Scheme fees) ፡ ለአገልግሎቱ አቅራቢዎች በጋራ ስምምነት ተናባቢነትን ለማስፈን በሚፈጸመው ስምምነት ውስጥ ለሚኖራቸው ተሳትፎና አባልነት የሚከፈሉ ክፍያዎች ሲሆኑ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ኢትዮ-ፔይ፣ ማስተር ካርድና ቪዛ ይካተታሉ፡፡
- የስዊች ክፍያዎች (Switch fees)፡ ክፍያን የማሸጋገር (የራውቲንግ) አገልግሎት ለሚያቀርቡ ማዕከላዊ የቴክኖሎጂ አቅራቢዎች የሚከፈል የስዊች ክፍያ ሲሆን በዚህ ውስጥ ኢት-ስዊች ተጠቃሽ ነው፡፡
- የዝውውር እና ልውውጥ ክፍያዎች (Interchange and interpay fees)፡ ለተናባቢ አገልግሎት አቅራቢዎች የሚከፈል ክፍያ ሲሆን ከአንዱ የገንዘብ መክፈያ ማሽን ኔትወርክ አገልግሎት የሌላውን ኔትወርክ አገልግሎት ለማግኘት የሚከፈል ክፍያ ነው፡፡
- የአገልግሎት ተጠቃሚዎች ክፍያዎች (End-user fees) ፡ ደንበኞች የተናባቢ አገልግሎት ለማግኘት የሚከፍሉት ክፍያ ሲሆን በአሰራር ስርአት፣ በሲዊችና በአገልግሎት አቅራቢዎች የሚወሰዱ የኢኮኖሚ ውሳኔዎች ተጠቃሚው ጋር ቀጥተኛ ተጽእኖ ይፈጥራሉ፡፡

የክፍያ ጌትወይ በዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ውስጥ አስፈላጊ ከሆኑት ሁኔታዎች አንዱ ነው፡፡ የክፍያ ጌትወይ (Payment gateway) የሶስተኛ ወገን ሶፍትዌር ሲሆን የደንበኞች የባንክ አካውንት ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ከሌሎች የክፍያ አማራጮች ጋር (ኔት ባንኪንግ፣ የክሬዲት ካርድ፣ ዴቢት ካርድና የተቀናጀ የክፍያ ኢንተርፌስ፣ ከሞባይል ዋሌት) ጋር በማገናኘት ገንዘብ ለማስተላለፍ የሚያገለግል ነው፡፡ በክፍያ ሂደት ውስጥ የደንበኛውን ዝርዝር መረጃዎች የሚጣሩበት፣ በአካውንት ውስጥ በቂ ስንቅ መኖሩ የሚረጋገጥበትና የክፍያ ሁኔታው የሚከናወንበት ሲሆን በባንኮች፣ በድረ-ገጾችና በመተግበሪያዎች መካከል የመረጃ ልውውጥ ይደረግበታል፡፡ ይህም በአብዛኛው በኢንተርኔት የሚፈጸም ግዥ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ የክፍያ ጌትወይ ከስዊች መሰረተ-ልማት ጋር የሚናበብና የሚቀናጅ ነው፡፡ የክፍያ ጌትወይ የክፍያ ጥያቄ መረጃዎችን ከሰበሰበ በኋላ ግብይቱን ወደ ስዊች ይመራል፣ በቀጣይም ግብይቱ ወደሚመለከተው ባንክ ወይም የክፍያ አገልግሎት አቅራቢ ማረጋገጫ ይጠይቅበታል፡፡

የክፍያ ጌትወይ ለበይነ መረብ ግብይት ወሳኝ ሲሆን የክፍያ መተግበሪያዎችን በማቀናጀት በኩልም ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ በዚህ ረገድ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደመልካም ተሞክሮ የሚወሰደው የሲንጋፖሩ Network for Electronic Transfers (NETS)[20] ነው፡፡ በሲንጋፖር የባንኩ ማህበረሰብ በመቀናጀት የክፍያ መሰረተ-ልማትን ለደንበኞች፣ ለነጋዴዎችና ለባንኮች በጋራ ለማድረስ የተካሄደ እንቅስቃሴ ውጤት ነው፡ ፡ በመላው ሲንጋፖር ተግባራዊ በተደረገው በዚህ አሰራር 40 ሺህ የክፍያ ነቁጥ መሳሪያዎች እንዲሁም 55ሺህ የQR ኮዶች የሚናበቡበት የክፍያ ስርዓት መሰረተ-ልማት ተዘርግቷል፡፡ በቤልጅየም ባንኮች በመቀናጀት Inter bank Standards Association Belgium (ISABEL) በፈጠሩት ትብብር የጋራ ኔትወርክ፣ የአገልግሎት አቅርቦትና የደንበኞች ሶፍትዌር በመፍጠራቸው ይጠቀሳሉ፡፡ በ ISABEL ሁለት የክፍያ ጌትወይ የተፈጠረ ሲሆን ከፍተኛ መጠን ያላቸውን ግብይቶችን ለማከናወን አስችሏል (Gulati and Srivastava 2007)፡፡

የዲጂታል መለያ መታወቂያ መሰረተ-ልማት

በተለያየ ደረጃ የሚከናወን የደንበኛህን እወቅ መርሃ-ግብር አገራት በብሔራዊ መለያ (መታወቂያ) እጦት በኩል ያለውን ክፍተት ለመሙላት ተጠቅመውበታል፡ ፡ ፋይናንሻል አክሽን ታስክ ፎርስ (The National Action Task Force) (2020) የፋይናንስ አካታችነትን በማረጋገጥ ሂደት የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን ለመፍታት የደንበኛን ዝርዝር መረጃ ጥናት በማከናወን ሂደት የስጋት መጠንን ግምት ውስጥ ያስገባ ሂደትን እንዲከተሉ ይመክራል፡፡ ሜክሲኮ በመደበኛው የፋይናንስ ስርዓት ውስጥ መካተት ያልቻሉትንና ብሔራዊ መለያ መታወቂያ የሌላቸው ዜጎች የሚስተናገዱበትን በተለያየ ደረጃ የሚከናወን የደንበኛን እወቅ ሂደትን በመተግበር የፋይናንስ አካታችነትን ለማረጋገጥ ሰርታለች (Faz and Dias 2011)፡፡ ይህ በተለያየ ደረጃ የሚከናወን የደንበኛን እወቅ ሥርዓት ብሔራዊ መለያ መታወቂያ ለሌላቸው ደንበኞች ውስን አገልግሎቶችን ብቻ እንዲያገኙ ሲያደርግ ብሔራዊ መለያ መታወቂያ ላላቸው ዜጎች ግን ሁሉን አቀፍ አገልግሎት ማለትም ዓለም አቀፍ ዝውውርና የብድር አገልግሎቶችን ጭምር እንዲያገኙ አድርገዋል፡፡ በአፍሪካም በተለይም በናይጄሪያ ምንም እንኳ ብሔራዊ መለያ መታወቂያ አሰራር ሥርዓት የተዘረጋ ቢሆንም መለያ ካርድ ላልደረሳቸው ዜጎች በተለያየ ደረጃ በሚከናወን የደንበኛን እወቅ አሰራር አማካኝነት ዜጎች ለፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነት እንዲያገኙ ተደርጓል (Alliance for Financial Inclusion 2019)፡፡

ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች

አስተማማኝና ተናባቢ የሆነ መሰረተ-ልማትን ለመዘርጋት ሁለት ክፍል ያላቸው ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች ተነድፈዋል፡፡ በሁለት ክፍል ከተዘረዘሩት ስትራቴጂካዊ እርምጃዎች ውስጥ ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ ዘጠኝ ስትራቴጂያዊ ተግባራት የመሰረተ-ልማት መሻሻልን እንደሚያግዙ ታምኖበታል፡፡ ሁለቱ የስትራቴጂካዊ እርምጃ ክፍሎች፡-

- የዲጂታል መሰረተ-ልማት የአገልግሎት መስጫ አማራጮችን ቁጥር ማሳደግ፣
- በሁሉም የክፍያ መንገዶች መካከል ተናባቢነትን ማረጋገጥ (ለምሳሌ፣ የክፍያ ነቁጥ፣ የገንዘብ መክፈያ ማሽን፣ ኢ-ባንኪንግ፣ ሞባይል)፡፡

ይህም በተከታዮቹ ዝርዝር ተግባራት መታገዝ ይኖርበታል፡፡

የአገልግሎት መስጫ አማራጮችን ቁጥር ማሳደግ (Access Points)

- ተግባር 1፡ ከገንዘብ መክፈያ ማሽንና የክፍያ ነቁጥ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ቴክኒካዊ ችግሮችን መፍታት
- ተግባር 2፡ የገንዘብ መክፈያ ማሽንና የክፍያ ነቁጥ አገልግሎት መስጫዎችን ቁጥር ማስፋት
- ተግባር 3፡ የወኪል አገልግሎትን ለማስፋፋት የቢዝነስ ተሞክሮዎችን መከለስ
- ተግባር 4፡ የቴሌኮም ተደራሽነትን በኔትወርክ ሽፋንና በአገልግሎት መሣሪያዎች አቅርቦት ረገድ ማሳደግ

ተናባቢነት

- ተግባር 5፡ ለኤሌክትሮኒክ የገንዘብ ዝውውር የሚያገለግል በቴክኖሎጂ የታገዘ የገንዘብ ማጣሪያ መሰረተ ልማት /Automated Clearing House (ACH)/ ማቋቋም
- ተግባር 6፡ በሁሉም ተዋንያንና የክፍያ መንገዶች ተናባቢነትን ማሳደግ
- ተግባር 7፡ የክፍያ ጌትወይ ማበልጸግ
- ተግባር 8፡ የሪልታይም /RTP/ ክፍያ አማራጭን መተግበር
- ተግባር 9፡ የባንክ የክፍያ መሳሪያዎች ተመሳሳይና ወጥ እንዲሆኑ ማስቻል

ለ2.1.1 የአገልግሎት መስጫ አማራጮች

በተለምዶ የፋይናንስ ዘርፉ ለደንበኞች አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ የመሰረተ-ልማት አማራጮች (የባንክ ቅርንጫፎች፣ የገንዘብ መክፈያ ማሽን፣ የክፍያ ነቁጥ መሳሪያዎች) ላይ የመተማመን ሁኔታ ይታያል፡፡ የወኪል ባንክ አገልግሎትና የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት አማራጮች መስፋፋት እንዲሁም የሌሎች ወጪ ቆጣቢ አሰራሮች መከሰት ለማሳያም የሞባይል የክፍያ ነቁጥ መምጣት የነበረውን አሰራር በመቀየር የፋይናንስ ተቋማት ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ አገልግሎታቸውን ለማድረስ እንደሚችሉ ማሳያ ሆኗል፡፡ የአዲሱ አማራጭ ሞዴል መምጣት የባንኮችን ትኩረት ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ እንዲሆን በማድረግ ለፋይናንስ ተደራሽነት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ አስችሏቸዋል፡፡

ከምስል 7 መረዳት እንደሚቻለው በኢትዮጵያ የባህላዊ የክፍያ አገልግሎት መስጫ (የገንዘብ መክፈያ ማሽን፣ የክፍያ ነቁጥ) እና ባህላዊ ባልሆኑ (የወኪል) አገልግሎት መስጫ አማራጮች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ በማሳደግ ረገድ ትልቅ እመርታ ታይቷል፡፡ በኢትዮጵያ የአገልግሎት መስጫ አማራጮችን ቁጥር በማሳደግ ረገድ በተለይም ከከተሞች ውጭ ባሉ አካባቢዎች የወኪል ባንክ አገልግሎት ሰጭዎችን እና የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማትን በመጠቀም ለማሳደግ ተችሏል፡፡ ይህም ሆኖ ግን አሁንም የበለጠ ለመስራት እድሎች አሉ፡፡

እድገቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የባንክ ቅርንጫፎች፣ የገንዘብ መክፈያ ማሽንና የክፍያ ነቁጥ መሳሪያዎች በአብዛኛው በከተሞች አካባቢ የሚገኙ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ደንበኞች ከገንዘብ መክፈያ ማሽንና የክፍያ ነቁጥ መሳሪያዎች አጠቃቀም ጋር ተያይዞ በሚያነሱት ተደጋጋሚ ቅሬታዎች የተነሳ የዲጂታል ክፍያ አማራጮችን ለማሳደግ የሚደረገው ጥረት ላይ በአጠቃላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳርፏል፡፡

የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት ማላመድን በማሳደግ ሂደት ውስጥ የገንዘብ ገቢና ወጭ ማድረጊያ (Cash-in Cash-outs) መሰረተ-ልማቶች በገጠርና በከተማ ማስፋፋት ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ በከተሞች አካባቢ የገንዘብ መክፈያ ማሽኖች ቁጥር መጨመር ገንዘብን ገቢና ወጭ ለማድረግ በወኪሎች ቁጥር ማደግ እየታገዘ ትልቅ ሚና መጫወት የሚችል መሰረተ-ልማት ሲሆን፣ በገጠር አካባቢዎች ደግሞ የወኪል አገልግሎቶች በዋናነት ገንዘብ ገቢ እና ወጭ ለማድረግ አማራጭ መሰረተ-ልማት ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ይህም የደንበኞችን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ከግምት የሚያስገባና ባለው የመሰረተ-ልማት አማራጭ ላይ የሚመሰረት ነው፡፡

ምስል 7: የክፍያ መፈጸሚያ መሳሪያዎች ተደራሽነት[21]

ምንጭ: የክፍያና ሒሳብ ማወራረጃ ሥረዓት ዳይርክቶሬት ብሔራዊ ባንክ



ተግባር 1፡ ከገንዘብ መክፈያ ማሽንና የክፍያ ነቁጥ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ቴክኒካዊ ችግሮችን መፍታት

በዲጂታል ክፍያ አማራጮች የደንበኞች ቀጣይነት ያለዉ አዎንታዊ የአገልግሎት ተሞክሮ በክፍያ ስነ-ምህዳሩ ላይ የተጠቃሚዎች እምነት እንዲጎለብት ያግዛል፡፡ ተለምዷዊ በሆነዉ በባንክ ስርዓት የሚካሄደው የግብይት ስኬት መጠን 85% ነው (EthSwitch 2019)፡፡ ደንበኞች በአገልግሎት ሂደቱ አሉታዊ ተሞክሮ ካላቸው አገልግሎቱን በመተግበር ረገድ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ አሁን ካሉት የዲጂታል ክፍያ አማራጮች (የገንዘብ መክፈያ ማሽን እና የክፍያ ነቁጥ) ጋር ተያይዞ የሚነሱትን ቅሬታዎች መፍታት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

በምስል 8 እንደምንመለከተው ተገልጋዮች የገንዘብ መክፈያ ማሽን እና የክፍያ ነቁጥ ሲጠቀሙ ገንዘብ ከሂሳባቸው በተደጋጋሚ ተቀናሽ እንደሚደረግ፣ ገንዘብ ወጭ ለማድረግ የገንዘብ መክፈያ ማሽኖች በቂ ገንዘብ የሌላቸው መሆን እንዲሁም የገንዘብ መክፈያ ማሽኖች እና የክፍያ ነቁጥ መሣሪያዎች ብዙ ጊዜ ከአገልግሎት ውጭ መሆን እንደችግር አንስተዋል፡፡ በተጨማሪም ተገልጋዮች ቅሬታ አቅርበው ገንዘብ ለማስመለስ ያለው ሂደት ውስብስብና ጊዜ የሚወስድ መሆኑ ተነስቷል፡፡ ባጠቃላይ ተጠቃሚዎች ጥሬገንዘብ ከባንክ ቅርንጫፍ አውጥተው ለክፍያ መጠቀምን እንደሚመርጡ ገልጸዋል፡፡

"በካርድ መገልገልን በተመለከተ ተስፋ ቆርጫለሁ - ከምቹነቱ አስቸጋሪነቱ ይበዛል፡፡"

በስትራቴጂው ዝግጅት ከባለድርሻ አካላት አስተያየት የተወሰደ

ኢትስዊች በአሁኑ ጊዜ የሩብ ዓመት መጽሄት በማዘጋጀት አሃዛዊ መረጃዎችን ያቀርባል፡፡ በዚህም በገንዘብ መክፈያ ማሽን ተሞክረው ያልተሳኩ ክፍያዎችን በተመለከተ ምክንያቶችንና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ይጠቁማል[23]፡፡ ይሄው ተመሳሳይ አሃዛዊ መረጃ ትግበራው ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ ለክፍያ ነቁጥ ግብይቶችም የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

እነዚህ የቴክኒክ ችግሮችን ለመፍታት ትርጉም ያለው ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ በተለይም በባንኮች በኩል ተጠባባቂ መሰረተ ልማቶችን ማዘጋጀት እና የክፍያ ስርዓታቸውን በትኩረት መከታተል ይገባቸዋል፡፡ (ላልተሳኩ የክፍያ ሙከራዎች ተገቢውን ክትትል የማያደርጉ አገልግሎት አቅራቢዎች ዋነኛው ምክንያት ናቸው)፡፡ አሃዛዊ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የተገልጋዮችን ግንዛቤ ለማጎልበት ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራበት ይገባል (ላልተሳኩ የክፍያ ሙከራዎች በሁለተኛ ደረጃ በምክንያትነት የሚነሳው የተገልጋዮች የአጠቃቀም ችግር ነው)፡፡

በተጨማሪም የተሟላ የደንበኞች የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት በመፍጠር በጊዜ ሰሌዳ የተገደበ የመፍትሄ አሰጣጥ መኖር በክፍያ ስርዓቱ ላይ አመኔታ እንዲጎለብት ያግዛል፡፡ እጅግ የተዋጣለት የቅሬታ አፈታት ሥርዓት አጥፊዎች የሚቀጡበትና ተገልጋዮች የሚካሱበት እንዲሁም በተገልጋዮች የሚቀርቡ ሃሰተኛ ቅሬታዎችና የማጭበርበር ሙከራዎችን በማስረጃ አስደግፎ የማሳመን ሃላፊነት በባንኮች ላይ እንዲሆን የሚያደርግ ነው፡፡ ኢትስዊች የቅሬታ አፈታት ስርዓት ያለው ሲሆን በጊዜ ሰሌዳ የተገደበ ቅሬታን የማጣራትና ደንበኞችን የመካስ አሰራር አለው፡፡ ሆኖም ግን ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች የማስፈጸም አቅሙ ከዓለማቀፍ ተሞክሮ አንጻር ሊቃኝና ሊሻሻል ይገባል[24]፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ ሃሳቦች

- ከኢትስዊች ጋር በመተባበር የሩብ ዓመት የግብይት መረጃ መጽሄት ማዘጋጀትን ማስቀጠል እንዲሁም ወደ ሌሎች የክፍያ መንገዶች (ለምሳሌ የክፍያ ነቁጥ) ማስፋት፣
- ከኢትስዊች እና ባንኮች ጋር በመተባበር በሪፖርት የተለዩ ግኝቶች ላይ እንዲሁም በሚወሰዱ እርምጃዎች እና የክትትል እቅድ ላይ በየሩብ ዓመት የምክክር መድረክ ማዘጋጀት፣
- ከኢትስዊች እና ባንኮች ጋር በመተባበር የቅሬታ አፈታት ስርዓትን መከለስ፣ እንዲሁም የማስፈጸሚያ መሳሪያዎችን ከዓለማቀፍ ተሞክሮዎች አንጻር ማካተት፣
- ከኢትስዊች እና ከባንኮች ጋር በመተባበር ተጠባባቂ መሰረተ ልማት በሁሉም ባንኮች በሚቋቋምበት ሁኔታ ላይ እቅድ ማዘጋጀት፣

የዚህ ተግባር ውጤታማነት በተግባር 18 ላይ የተመረኮዘ ነው፤ ዲጂታል መሰረተ ልማቶችን ማዕከል ያደረገ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብር ማካሄድ፣

ምስል 8: ለ ትራነዛክሽኖች ስኬታማ ላለመሆን ተደጋጋሚ ምክኒያቶች[22]

ተግባር 2፡ የገንዘብ መክፈያ ማሽንና የክፍያ ነቁጥ አገልግሎት መስጫዎችን ቁጥር ማስፋት

የባንክ ቅርንጫፎች፣ የገንዘብ መክፈያ ማሽኖችና የክፍያ ነቁጥ መሣሪያዎች የፋይናንስ አካታችነትን ለማረጋገጥ ወሳኝ የአገልግሎት መስጫዎች ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ወደ 47 በመቶ የሚጠጉ የገንዘብ መክፈያ ማሽኖች፣ ወደ 77 በመቶ የሚጠጉ የክፍያ ነቁጥ መሳሪያዎች በዋና ከተማዋ አዲስ አበባ የሚገኙ ሲሆን አብዛኛዎቹም በባንክ ቅርንጫፎች አቅራቢያ የተተከሉ ናቸው[25]፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ህዝብ ብዛት ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ 3.1 በመቶ እንደሚሆን ይገመታል[26]፡፡ የገንዘብ መክፈያ ማሽኖችና የክፍያ ነቁጥ መሳሪያዎች እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ የባንክ ቅርንጫፎች በዚሁ አካባቢ የተከማቹ መሆኑ ስርጭቱ ያልተመጣጠነ መሆኑን ያሳያል፡፡

ባንኮች ለገንዘብ መክፈያ ማሽን እና ለክፍያ ነቁጥ መሳሪያ ግዥ የሚያወጡት መወዕለንዋይ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ሆኖም ግን በአሁኑ ጊዜ ያለው የባንኮች ሪፖርት እንደሚያሳየው በመጣው መወዕለንዋይ ላይ የሚገኘው ትርፍ በጣም ዝቅተኛ ወይንም ከዜሮ በታች ነው፡፡ ለገንዘብ መክፈያ ማሽኖች በያንዳንዱ ግብይት የአገልግሎት ክፍያ የሚጣል ሲሆን በክፍያ ነቁጥ የሚሰጥ አገልግሎት ግን ከአገልግሎት ክፍያ ነፃ በአንዳንድ ሁኔታዎችም በግብይት የገንዘብ መጠን ላይ የማበረታቻ ቅናሽ ይደረጋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ የገንዘብ መክፈያ ማሽኖችና የክፍያ ነቁጥ መሳሪያዎች በባንኮች ባለቤትነት የተያዙ ናቸው፡፡ ይህም ሲባል የመሳሪያዎቹ አስተዳደርም ሆነ የጥገና ወጭዎች የባንኮች ሃላፊነት ነው፡፡ ሦስተኛ ወገን የአገልግሎት አቅራቢዎች - ባለ ቡናማ - ምልክት (brown-label) የሚመደቡ (የአገልግሎት መስጠት ፈቃድ በባንኮች ባለቤትነት ሆኖ የፋይናንስ አገልግሎት ሰጭ ባልሆኑ ድርጅቶች የንብረት ባለቤትነትና አስተዳደር ስር ያሉ) አሰራር የተፈቀደ ሲሆን ባለ ነጭ - ምልክት (white-label) የሚመደቡ (የአገልግሎት መስጠት ፈቃድም ሆነ የንብረት ባለቤትነትና አስተዳደራቸው የፋይናንስ አገልግሎት ሰጭ ባልሆኑ ድርጅቶች የተያዙ) አሰራር የተፈቀደ አይደለም፡፡ በሌሎች አገራት ባለ ነጭ - ምልክት የገንዘብ መክፈያ ማሽኖችና የክፍያ ነቁጥ መሳሪያዎች የአገልግሎቶች አማራጭ በማቅረብ የዚህን መሰረተ ልማት መስፋፋት ያግዛሉ፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባለ ቡናማ - ምልክት የሶስተኛ ወገን አገልግሎት አቅራቢዎችን እንደ አማራጭ ተጠቅሞ የገንዘብ መክፈያ ማሽኖችና የክፍያ ነቁጥ መሳሪያዎች አገልግሎች መስጫ ማዕከላትን ማስፋፋት የሚቻልበትን እድል በክፍያ ስርዓት ኦፕሬተሮች መመሪያ ፈጥሯል፡፡ ይህ አማራጭ ሦስተኛ ወገን አገልግሎት አቅራቢዎች ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በገንዘብ አስተዳደር ላይ በሚደረግ የአገልግሎት ስምምነት (service-level agreement) በመፈጸም የገንዘብ መክፈያ ማሽኖችና የክፍያ ነቁጥ መሳሪያዎችን በባለቤትነት ይዘው እንዲያስተዳድሩ ያስችላቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ የፋይናንስ ተቋማት በቁልፍ ተልእኳቸው ላይ እንዲያተኩሩ የሚያግዝ ሲሆን በተጓዳኝ የክፍያ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማስፋት ያግዛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ እንደ ተንቀሳቃሽ የክፍያ ነቁጥ ያሉ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መሰረተ ልማቶች እንዲፈጠሩ ማበረታታት በንግዱ ማህበረሰብ ዘንድ ዲጂታል ስነ ምህዳሩ በስፋት እንዲተገበር ለማድረግ ይጠቅማል፡፡ በኢትስዊች በኩል የተንቀሳቃሽ የክፍያ ነቁጥ በኢትዮጵያ ለማስጀመር የተያዘው እቅድ ትርጉም ያለው የተጠቃሚነት ፍላጎት መኖሩን በመለየት የሚካሄድ ሲሆን አገልግሎቱ ከመጀመሩ በፊት የሚያስገኘው ጥቅም ባግባቡ መፈተሽ ይኖርበታል፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ ሃሳቦች

- ማዕቀፉን ባግባቡ በመከለስ ባለ ቡናማ - ምልክት እና ነጭ ምልክት የገንዘብ መክፈያ ማሽኖችና የክፍያ ነቁጥ አገልግሎቶችን መፍቀድ፣
- ከኢትስዊችና ፊንቴኮች ጋር በመተባበር የተንቀሳቃሽ የክፍያ ነቁጥ አገልግሎት ለመጀመር ያለውን የተጠቃሚዎች ፍላጎትና የኢኮኖሚ አዋጭነት ለመለየት የሚያስችል ትንተናና ግምገማ ማካሄድ፣
- ከኢትስዊችና ባንኮች ጋር በመተባበር አዲስ የገንዘብ መክፈያ ማሽኖችና የክፍያ ነቁጥ መሰረተ ልማት የሚያስፈልጋቸውና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ አካባቢዎችን በመለየት የማስፋፊያ እቅድ ማዘጋጀት፣
- የዚህ ተግባር ስኬት በተግባር 6 ላይ የተመረኮዘ ነው፣ ተግባር 6፡ ለሁሉም ተዋንያንና የክፍያ መንገዶች ተናባቢነትን ማሳደግ፣ እና ተግባር 30 የፊንቴኮችን ተግባርና ሃላፊነት መወሰን፣

ተግባር 3፡ የወኪል አገልግሎትን ለማስፋፋት የቢዝነስ ተሞክሮዎችን መከለስ

የወኪል ባንክ በባህላዊ የፋይናንስ አገልግሎት መሰረተ ልማት ውስጥ ጠቃሚ የአገልግሎት መስጫ ማዕከል ነው፡፡ ለፋይናንስ ዘርፉ የባንክ ቅርንጫፎችን ከማቋቋም ይልቅ ባነሰ የመሰረተ ልማትና የሰው ሃይል ወጭ በወኪሎች በመጠቀም ክልላዊ ተደራሽነትን በከፍተኛ ሁኔታ ለማስፋት አማራጭ ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ከባንኮች በሚያገኙት የኮሚሽን ክፍያ ተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ከመሆኑ ባሻገር ወደነሱ የሚመጡ ተገልጋዮች በመጨመር በሽያጭ መጠናቸው ላይ በጎ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡

የወኪል ባንኪንግ አገልግሎት በአንጻራዊነት ለኢትዮጵያ አዲስ ክስተት ነው፡፡ ከስር በምስል 9 እንደተመለከተው የወኪል ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ ይገኛል፡፡ ሆኖም ግን በወኪሎች በኩል የሚፈጸም ግብይት ቁጥር በአንጻሩ ዝቅተኛ ነው፡፡ ለዚህም በባንኮችና በተጠቃሚዎች በኩል ደካማ የቢዝነስ/የንግድ/ ተሞክሮዎች መኖራቸው በምክንያትነት ይነሳል፡፡

በአሁኑ ወቅት ካለው የቢዝነስ ፍላጎት ተግዳሮት ተብለው ሪፖርት ከተደረጉት መካከል:-

- የመጠቀሚያ አስቻዮች፡ ወኪሎች በአብዛኛው ገንዘብ ገቢና ወጭ ለማድረግ ያገለግላሉ፡፡ ሆኖም ግን ከባህላዊ የአገልግሎት መስጫ ቦታዎች ጋር ተጠጋግተው የሚገኙ በመሆኑ እንዲሁም ለመብራት፣ ውሃ፣ ስልክና የመሳሰሉት የአገልግሎት ክፍያዎች ቢኖሩም የተገደቡ መሆናቸው፡፡
- የአገልግሎት ክፍያ፡ ከባህላዊ ክፍያ መሰረተ ልማቶች ጋር ሲነጻጸር ወኪሎች በያንዳንዱ ግብይት የሚያስከፍሉት የአገልግሎት ዋጋ ከፍተኛ ነው፡፡
- ቅድመ ሁኔታዎች የወኪል ፈቃድ ለማግኘት የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ ከወንጀል ሪከርድ ነጻ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ፣ እና ሌሎችን ለማግኘት አስቸጋሪ በመሆናቸው ይገድባሉ፡፡
- ወኪል መቅጠር፡ ለባንኮች ወኪሎችን መመልመልና በውክልና እንዲሰሩ ማድረግ ቀላል ተግባር አይደለም፡፡ ምክንያቱም ወኪሎች በዚህ አገልግሎት የሚያገኙት ገቢ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

በተጨማሪም ሴቶችን ማዕከል ያደረገ የቢዝነስ ጉዳይ በመፍጠር የዲጂታል ክፍያን ለመጠቀም ብሎም የፋይናንስ አካታችነትን ለመጨመር ያግዛል፡፡ GSMA እና ሌሎች ያቀረቡት ማስረጃ እንደሚያሳየው (Lindsey & Wilson 2019; Aakanksha 2016) የሴት ወኪሎችን መጠቀም በርካታ ወንድና ሴት ደንበኞችን ለማግኘትና ለማjየት ያግዛል፡፡ በተጨማሪም ግማሽ የሚሆኑት የደንበኛ መሰረት ሴቶች በመሆናቸው እነሱን መሳብ ያስችላል (Ryan 2019)፡፡

የወኪል ባንኪንግን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችና የህግ ማዕቀፍ በስትራቴጂ ምሰሶ 3፤ ሁሉን አቀፍ (ውጤታማ) የህግ ድንጋጌዎችና የክትትልና ቁጥጥር ማዕቀፍ እንዲኖር ማስቻል ላይ ተገልጸዋል፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ ሃሳቦች

- ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በመተባበር የተከለሰ የቢዝነስ ጉዳዮች በማዘጋጀት የወኪል ባንኪንግ በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ የሚያግዙ ስትራቴጂዎች ማዘጋጀት:-
  - የአገልግሎት ክፍያ፣
  - ሊሟሉ የሚገባቸው ሁኔታዎች (ከወንጀል ነጻ መሆንን የሚያረጋግጥ ሰነድ)፣
  - ወኪል የመቅጠር ሂደቶች፣
  - ሴት ወኪሎች፣
- ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በመተባበር የወኪል አገልግሎት መስጫ ማእከላትን እድገት በየጊዜው መከታተል፡፡

የዚህ ተግባር ስኬት በስትራቴጂ ምሰሶ 3 በተዘረዘሩ ተግባራት ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ በተለይም ተግባር 24፡ አዲሱን የወኪል አጠቃቀም መመሪያ ትግበራ መከታተል፡፡ እንዲሁም ተግባር 25፡ ባንክ ያልሆኑ የፋይናንስ ተቋማት በሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ያላቸውን ተሳትፎ መቆጣጠር፡፡

ምስል 9: በወኪል የተከነወነ ግብይት/ትራንዛክሽን

ምንጭ: የክፍያና ሒሳብ ማወራረጃ ሥረዓት ዳይርክቶሬት ብሔራዊ ባንክ



ተግባር 4፡ የቴሌኮም ተደራሽነትን በኔትወርክ ሽፋንና በአገልግሎት መሣሪያዎች አቅርቦት ማሳደግ

አስተማማኝና ሁሉንም አካባቢ የሚያዳርስ የቴሌኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማት መኖር ዲጂታል ክፍያን ለማሳደግ ወሳኝ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የቴሌኮሙኒኬሽን ሴክተር ዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት በሚያግዝ አግባብ ሪፎርም እየተደረገ ይገኛል፡፡ ሪፎርሙ የቴሌኮሙኒኬሽን ኢንዱስትሪው ከፍተኛ የመሰረተ ልማት እድገት እንዲያመጣ ይጠበቃል፡፡ የመሰረተ ልማት እድገቱ ከፋይናንስ ሴክተሩ የአገልግሎት ፍላጎት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ግብዓቶች ሊቀርቡ ይገባል፡፡

የመንግስት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ማዕቀፍን በመጠቀም የቴሌኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማት ግንባታው የዲጂታል ክፍያ ከባቢ ሁኔታን ፍላጎት በሚያረጋግጥ አግባብ እንዲመራ ይደረጋል፡፡ ይህም በተለይ የሞባይል ኔትዎርክ ኦፐሬተሮች የፋይናንስ አዋጭነት በማይኖራቸው የገጠር አካባቢዎች መሰረተ ልማትን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የቴሌኮሙኒኬሽን ሴክተር ፖሊሲዎችን ከሚያዘጋጀው የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እንዲሁም ለማልማትና ተወዳዳሪ ግዥን ለማዘጋጀት ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የሚሰራ ይሆናል፡፡ እነዚህ የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በሞባይል ኔትዎርክ ኦፕሬተሮች እና በመንግስት የማህበረሰብ አገልግሎት ግዴታ ማዕቀፍ መሰረት ፋይናንስ ይደረጋሉ፡፡ ይህም በቅርቡ በተረቀቀው የመንግስት ድርጅቶች አዋጅ[27] ላይ ተወስኗል፡፡

የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትዎርክ ትስስር ከማደጉ በተጨማሪ የተንቀሳቃሽ ስልክ ተደራሽነት ለዘመናዊና ተደራሽ የፋይናንስ አገልግሎቶች እንደ ሞባይል ዋሌትና ሞባይል ባንኪንግ የመሳሰሉት ጠቃሚ አስቻይ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

በኢትዮጵያ የሞባይል ስልኮች (ስማርት የሆኑና ያልሆኑ) ተደራሽነት ሽፋን በ 2020 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት 32 በመቶ ደርሷል[28]፡፡ ብሔራዊ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ አካታች የሞባይል ስልክ ተደራሽነትን፣ የሃገር ውስጥ የስልክ መገጣጠሚያ ተቋማትን ለመከላከል በሚል በወጣው ፖሊሲ ምክንያት በቀላሉ ለመግዛት አስቸጋሪ የሆነ ዋጋ እንዲኖራቸው መደረጉን እንደ ዋና ተግዳሮት ተወስዷል፡፡ የሞባይል ስልኮች ተደራሽነትን ለማስፋት የብሔራዊ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂው በገንዘብ ሚኒስቴር የሚመራ ፕሮጀክት በመቅረጽ የሞባይል ስልክ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ የሚያግዝ የገበያ ማበረታቻ መስጠትን ታሳቢ አድርጓል፡፡

ኢትዮጵያ ዲጂታል ክፍያን ለማሳደግ በምታደርገው ጥረት የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትዎርክ መሰረተ ልማት እና የሞባይል ስልክ ተደራሽነትን ማስፋፋት አስፈላጊ ነው፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው የውሳኔ ሃሳቦች

- ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና የገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትዎርክ መሰረተ ልማትን የማህበረሰብ አገልግሎት ግዴታ ማዕቀፍን በመጠቀም ማስፋፋት፣
- ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና የገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የሞባይል ስልክ ተደራሽነትና የመግዛት አቅምን የገበያ ማበረታቻ በመጠቀም ማሳደግ፣

ለ2.1.2. ተናባቢነት

የዲጂታል ክፍያ አገልግሎት በሚፈለገው ደረጃ እንዲያድግ ከተፈለገ በከፋይና ተከፋይ መካከል ተናባቢነት ሊኖር ይገባል፡፡ የስነ ምህዳር፣ የወኪሎችና የተገልጋዮች ተናባቢነት፤ ተዛማጅነት ያላቸው ቢሆም በሃሳብ ደረጃ እራሳቸውን ችለው ይቆማሉ፡፡ CGAP በዚህ ዙሪያ ባካሄደው የምርምር ጥናት (Tarazi & Kumar 2012) እነዚህ ሶስት የተለያየ ይዘት ያላቸው የተናባቢነት አይነቶች እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

- የስነ ምህዳር ተናባቢነት፡- በተለያዩ አገልግሎት አቅራቢዎች መካከል የሚኖር የክፍያ ግብይት ተናባቢነት እንዲኖር ማስቻል፣
- ወኪል (ብቸኛ ያልሆነ)፡- አንድ ወኪል ለተለያዩ አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሰራ ማስቻል፣
- የደንበኞች ተናባቢነት፡- አንድ ደንበኛ በተመሳሳይ ኔትዎርክ የሚገኙ ስልኮችን ባለው ሲም ካርድ ማግኘት ሲችል እንዲሁም በርካታ ሂሳቦችን በአንድ ሲም ካርድ እንዲጠቀም ማስቻል ነው፡፡

ይህ የስትራቴጂው ክፍል የስነምህዳር ተናባቢነትን ይዳስሳል፡፡ ተናባቢነት አመች፣ ፈጣንና እንከን የለሽ ግብይት በክፍያ ከባቢ ሁኔታው ውስጥ የሚገኙ የክፍያ አገልግሎት አቅራቢዎች መካከል እንዲኖር ያስችላል፡ ፡ በተጨማሪም ፈጠራን በማፋጠን በስነምህዳሩ ውስጥ ጥብቅ ግንኙነት እንዲኖር በማገዝ አካታችነትን ያጎለብታል፡፡

በኢትዮጵያ የዲጂታል ክፍያ መሰረተ ልማት ተናባቢነት በማደግ ላይ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የኢትዮጵያ አውቶሜትድ ትራንስፈር ሲስተም /EATS/ በመተግበር የተቀናጀ የገንዘብ ዝውውርና ማወራረጃ ሥርዓት እንዲኖር አስችሏል፡፡ ሁሉም ባንኮች በዚህ ስርዓት ውስጥ ተሳታፊ ናቸው የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትም ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ በተናጠል የሚወራረዱ ቅጽበታዊ ክፍያዎች (Real time gross settlement /RTGS/) ስርዓት ሙሉ ለሙሉ የተተገበረ ሲሆን በማወራረጃ ስርዓቱ ውስጥ በጎ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከባንኮች ጋር በመቀናጀት የብሔራዊ ክፍያ ስዊች /ኢትስዊች/ የበለጠ በማሳደግ በባንኮች መካከል እንዲሁም በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት መካከል የሚደረግ ክፍያን ሙሉ ለሙሉ ተናባቢ እንዲሆን ለማስቻል እየተሰራ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ስርዓቱ የሚያገለግለው በገንዘብ መክፈያ ማሽኖች በኩል የሚፈጸሙ ክፍያዎችን ተናባቢ ለማድረግ ብቻ ነው፡፡

በአሁኑ ሰዓት ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ተናባቢነትን ማረጋገጥ ሲሆን በመቀጠል የትኩረት አቅጣጫው የተናባቢነት መዋቅሮችን የበለጠ በማጎልበት በቅጽበት የሚከፈሉ (Real time) ክፍያዎችን በቀን ለ24 ሰዓት በሳምንት ለ7ቀናት እንዲኖሩ ማስቻል ነው፡፡ ፈጣን ክፍያዎች ወይንም አፋጣኝ የገንዘብ ማጣራት መኖር የዲጂታል ክፍያ ከጥሬ ገንዘብ ግብይት ጋር በሚወዳደሩበት ሥርዓት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ተግባር 5፡ ለኤሌክትሮኒክ የገንዘብ ዝውውር የሚያገለግል በቴክኖሎጂ የታገዘ የማጣሪያ መሰረተ ልማት ማስፋት

ዘመናዊ ዲጂታል የማጣሪያና ማወራረጃ ስርዓት ለዲጂታል ክፍያ ከባቢ ሁኔታ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የክፍያ ስርዓት በኢትዮጵያ ወደ ዘመናዊነት የተሸጋገረው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የኢትዮጵያ አውቶሜትድ ትራንስፈር ሲስተምን /EATS/ በ2011 መጀመሩን ተከትሎ ነው (World Bank Group 2020a)፡፡ ይህ የክፍያ ስርዓት ሪል ታይም ግሮስ ሴትልመንት /RTGS/ እና አውቶሜትድ ክሊሪንግ ሀውስ /ACH/ ሁለት ቁልፍ ክፍሎች አሉት፡፡

- RTGS - ገንዘብን ወይም ፈንድን በኤሌክትሮኒክ መንገድ የማስተላለፍ ሂደት ሲሆን ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውና አስቸኳይ የሆኑ ክፍያዎችን ከአንዱ ባንክ ወደ ሌላ ባንክ ወዲያውኑና በተናጠል ለማስተላለፍ የሚያገለግል ነው፡፡ በባንኮች መካከል የሚኖረው ሂሳብን የማወራረድ ስራ የቀኑን የሂሳብ መዝጊያ ጊዜ ሳይጠብቅ ወዲያውኑ ዝውውሩ በተፈጸመበት ሰዓት የሚከናወን ነው፡፡
- ACH ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ነገር ግን የገንዘብ መጠናቸው አነስተኛ የሆኑ ክፍያዎች በፋይናንስ ተቋማት መካከል በኤሌክትሮኒክስ መንገድ የሚጣሩበት ስርዓት ነው፡፡

በአሁን ሰዓት ACH ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኘው በቼክ ለሚከናወኑ ክፍያዎች ነው፡፡ ለጊዜው በስራ ላይ ያሉት ቼኮች ወጥነት ያላቸው ባለመሆናቸው የማወራረድ ስራው የሚከናወነው ቼኮች ወደ ስርዓቱ በገቡ ከሁለት ቀናት በኋላ (T+2) ነው፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቼኮች ወጥነት እንዲኖራቸው ለማስቻል ስራዎችን እየሰራ የሚገኝ ሲሆን ይህም የማጣራት ሂደቱን የሚያሻሽለው ይሆናል፡፡

ACH አነስተኛ መጠን ያላቸውን ክፍያዎች (የኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ዝውውሮችን) ታሳቢ ተደርጎ የተዘረጋ ስርዓት ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን ሙሉ ለሙሉ በስራ ላይ አልዋለም፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይህ ስርዓት የኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ዝውውሮችን ማጣራት ስራ ለማስጀመር ትግበራውን እ.ኤ.አ. በ2021 መጨረሻ ለማጠናቀቅ እቅድ ይዟል፡፡ ከመነሻው የማወራረድ ስራው ከ አንድ ቀን በኋላ (T+1) በመሆን እንዲጀመርና በሂደት ወደ በእለቱ (T+0) እንዲሆን ታሳቢ ያደረገ ነዉ፡፡ በ ACH በአንድ ቀን የሚከናወነው ከፍተኛ የዝውውር ጣሪያ መጠን በባንኮች እንደሚወሰን ይጠበቃል፡፡

የ ACH ተግባራዊ መደረግ በዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ውስጥ የመጠቀም አስቻይ ሁኔታ ለመፍጠር ወሳኝ መሰረት የሚጥል ነው፡፡ ስርዓቱ ለግሉም ሆነ ለመንግስት ሴክተሮች የክፍያ ሥርዓት ውስጥ ውጤታማ፣ ተናባቢና ወጪ ቆጣቢ የክፍያ አገልግሎት እንዲኖር በማስቻል መንግስት፣ የንግዱ ማህበረሰብና ግለሰቦች የቼክ እና የጥሬ ገንዘብ ዝውውርን በማስቀረት የኤሌክትሮኒክ ክፍያዎች እንዲጠቀሙ ያስችላል፡፡ በፋይናንስ ዘርፉ ውስጥም ትብብርን በመፍጠር ተቋማቱ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የማድረግ ድርሻ አለው፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- ከባንኮች ጋር በጋራ በመተባበር አነስተኛ መጠን ባላቸው ክፍያዎች ACHን በተሟላ ሁኔታ በመተግበር ክፍያዎችን በፍጥነት ለማከናወን ማስቻል፣

የዚህ ምክረ-ሃሳብ ትግበራ ስኬት በተግባር 9 ላይ የተመረኮዘ ነው፡ የባንክ የክፍያ መሳሪያዎች ተመሳሳይና ወጥ እንዲሆኑ ማስቻል፡፡

ተግባር 6፡ በሁሉም ተዋንያንና የክፍያ መንገዶች ተናባቢነትን ማሳደግ

ሙሉ ለሙሉ ተናባቢ የሆነ አገራዊ ስዊች ለኢትዮጵያ የዲጂታል ክፍያ ከባቢ ሁኔታ የግድ አስፈላጊ ነው፡ ፡ በአሁኑ ወቅት ባንኮች ብቻ የኢትስዊች አባል ሲሆኑ ብቸኛ ተናባቢ የሆነው ሥርዓትም የገንዘብ መክፈያ ማሽን አገልግሎት ነው፡፡ ኢትስዊች ሌሎች በፋይናንስ ዘርፉ ውስጥ ያሉ ተዋንያን ተሳታፊ እንዲሆኑ እቅድ ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን ሁሉም የክፍያ አማራጮች ማለትም የክፍያ ነቁጥ፣ በኢ-ባንኪንግና በሞባይል ዋሌት ተናባቢ ሥርዓትን መፍጠርን ያካትታል፡፡ የክፍያ ነቁጥ ተናባቢ እንዲሆን በተወሰኑና አዲስ አበባ ላይ በሚገኙ ነጋዴዎች ላይ የሙከራ ትግበራ የተጀመረ ሲሆን እ.ኤ.አ. በ2021 መጨረሻ ሙሉ ትግበራ ለመጀመር እየተሰራ ነው፡፡

የክፍያ ነቁጥ ተናባቢነት ትግበራ ውጤታማነትን ተከትሎ በቀጣይ የሞባይል ዋሌት እና የኢ-ባንኪንግ የተናባቢነት ትግበራ በቅደም ተከተል ተግባራዊ እንደሚደረግ ይጠበቃል፡፡ ሁሉም የክፍያ ዘርፉ ተዋንያን በኢትስዊች አባልነት የሚካተቱበትን ሁኔታ መፍጠርና በሁሉም የክፍያ መንገዶች መካከል ተናባቢነትን ማምጣት የዲጂታል የክፍያ ሥርዓትን በኢትዮጵያ በተሳካ መልኩ ለመተግበር ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡ ማስፋፋቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የሞባይል ዋሌት ተናባቢነትን ማረጋገጥ በእጅጉ ወሳኝ ነው፡፡ የሞባይል ዋሌትን ተናባቢነት ለመፍጠር የሚያስፈልጉ መሰረተ-ልማቶችን መዘርጋት በአገሪቱ ያሉ ተግዳሮቶችን በቶሎ እልባት ለመስጠትና በቀጣናው ካሉ ቀዳሚ አገራት መሳ ለመሳ ለማደግ ያግዛል፡፡

ተመጣጣኝና የሆነ የአገልግሎት ክፍያ መዋቅር በአገልግሎቱ አቅራቢዎች መካከል እንዲፈጠር ማድረግ አገልግሎቱ በተጠቃሚዎች ዘንድ በቶሎ እንዲለመድ በማድረግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የግብይት መጠን እንዲኖር ያግዛል፡፡ በዚህም የስርዓትና የስዊች ወጪ በእያንዳንዱ ግብይት እንዲቀንስም ያስችላል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ኢትስዊች የአገልግሎት ክፍያዎችን የሚያሰላው በእያንዳንዱ ግብይት ሲሆን ከአባል ባንኮች ጋር በመቀናጀት የአገልግሎት ክፍያ መዋቅርንና የክፍያ ስርዓትን ደረጃ ይወስናል፡፡ ለትግበራው ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይሁንታ ማግኘት ይጠበቅበታል፡፡ የተናባቢነት መጠኑ በተቋማትና በክፍያ ሥርዓቶች መካከል እያደገ ሲመጣ ተመጣጣኝና ተቀራራቢ የሆነ የአገልግሎት ክፍያ መዋቅር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- ከኢትስዊች ጋር በመተባበር የኢትስዊች የተናባቢነት ትግበራ ዕቅድን ቅደም ተከተል መወሰንና ማስፈጸም፣
- ከኢት-ስዊች ጋር በመተባበር ተመጣጣኝ የሆነ የአገልግሎት ክፍያ መዋቅር በተቋማት መካከል እንዲፈጠር በማድረግ ተገልጋዮች በዝቅተኛ ዋጋ የዲጂታል ክፍያ አገልግሎቱን እንዲያገኙ ማድረግና የፋይናንስ ተቋማት ዲጂታል ክፍያ አገልግሎቱን እንዲያቀርቡ ማበረታታት፣

ተግባር 7፡ የክፍያ ጌትዌይ ማበልጸግ

በኦንላይንና በተቀናጀ መተግበሪያ ለሚከናወኑ ክፍያዎች የክፍያ ጌትዌይ በጣም ወሳኝ የዲጂታል የክፍያ መሰረተ ልማት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ምንም ዓይነት የክፍያ ጌትዌይ የለም፡፡

በአሁኑ ወቅት በመንግስትና በግሉ ዘርፍ የተጀመሩ የዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ፕሮግራሞች ተግባራዊ እንዲሆኑ የክፍያ ጌትዌይ መተግበር ወሳኝነት አለው፡፡ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በጋራ በመሆን እያበለጸጉት የሚገኝ ብሔራዊ የቢዝነስ ፖርታል[29] ተገልጋዮች ኦንላይን ክፍያዎችን መፈጸም እንዲችሉ የክፍያ ጌትዌይ እጅግ በፍጥነት መጀመር እንዳለበት አንዱ አመላካች ምክንያት ሆኗል፡፡ ሌሎች በመንግስት የተጀመሩ ፕሮግራሞች ለምሳሌ በትራንስፖርት ሚኒስቴር በኩል የተሽከርካሪ ምርመራና የትራፊክ ቲኬት ክፍያዎች፣ የገቢዎች ሚኒስቴር የኢ-ታክስ ክፍያዎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተጀመሩ የአገልግሎት ክፍያዎችን ለመሰብሰብ የክፍያ ጌትዌይ ላይ በእጅጉ የሚመሰረቱ ናቸው፡፡

በክፍያ ከባቢ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ባለድርሻዎችና ተዋናዮች የራሳቸው የሆነ የክፍያ አማራጮችንና አገልግሎቶችን ይዘው ብቅ ያሉ ቢሆንም ለትግበራቸው በእጅጉ የሚያግዘውና የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት ከባቢ ሁኔታ አስቻይ በመሆን የሚያገለግለው የክፍያ ጌትዌይ ነው፡፡ የክፍያ ጌትዌይ አለመኖር ነጋዴዎችና ተገልጋዮች ዲጂታል ክፍያን በስፋት ለመጠቀም እንደ ገዳቢ ሁኔታ ተወስዷል፡፡ አንዳንድ የግል ኩባንያዎች የክፍያ ጌትዌይ እስከሚሟላ ድረስ ዲጂታል ክፍያን ላለመጠቀም የወሰኑ ሲሆን ክፍያን ሰብስቦ ወደራሳቸው ቋት ለማስገባት ከተለያዩ ባንኮች ጋር በመስራት ከመድከም ይልቅ ጥሬ ገንዘብን መጠቀም የተመቸ እንደሆነ ይገልጻሉ[30]፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- ከኢትስዊች ጋር በመተባበር የክፍያ ጌትወይን ለመተግበር የወጣውን ዕቅድ መከለስና ማፋጠን

ተግባር 8፡ ቅጽበታዊ ክፍያ / Real Time Payment-RTP/ አማራጭን መተግበር

የቅጽበታዊ ክፍያዎች በሌላ አጠራራቸው ፈጣን ክፍያዎች የገንዘብ መጠናቸው አነስተኛና የድግግሞሽ መጠናቸው ከፍተኛ የሆኑ ክፍያዎች ናቸው፡፡

በመደበኛ የቅጽበታዊ /RTP/ ሥርዓት ውስጥ አራት ቁልፍ ሂደቶች በፍጥነት ይከናወናሉ፡-

- ግብይቱን ማጽደቅ (በሂሳብ ውስጥ በቂ ስንቅ መኖሩን በማረጋገጥ)፣
- ለግብይቱ አስፈላጊውን ገንዘብ በፍጥነት ማቅረብ፣
- በፋይናንስ ተቋማት መካከል ያለን ያልተከፈለ ሂሳብ በፍጥነት ማወራረድ፣
- ማረጋገጫ: ተከፋይ ገንዘቡን ይቀበላል፣ ከፋይ የግብይቱን ሁኔታ የሚገልጽ ማረጋገጫ ይሰጠዋል፡፡
- ይህ ፈጣን የገንዘብ ዝውውር እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ዲጂታል ክፍያ ከጥሬ ገንዘብ ግብይት ጋር በቀጥታ በሚወዳደርበት ሁኔታ በተለይ ጠቃሚ አሰራር ነው፡፡

የችርቻሮ/አነስተኛ/ ቅጽበታዊ ክፍያ /Retail RTP/ በኢትዮጵያ ውስጥ የለም፡፡ ነገርግን ኢትስዊች ተናባቢ ሥርዓቶች ለማስፋፋት ከያዘው እቅድ ጋር በሞባይል የሚፈጸሙ ግብይቶች፣ ከካርድ ወደ ካርድ በሚደረጉ ክፍያዎችና ከካርድ ወደ ባንክ ሂሳብ በሚደረጉ ዝውውሮች ላይ ለመተግበር ፍላጎት አለው፡፡ ይህም ተገልጋዮች ፈጣንና ደህንነቱ የተጠበቀ ክፍያ ተደራሽ እንዲሆኑ በማስቻል ከዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ጋር እንዲተዋወቁና እንዲላመዱ በማድረግ ከክፍያ ሥርዓቱ የሚገኘውን ፍሬ እንዲጠቀሙ ያበረታታል፡፡

የቅጽበታዊ ክፍያ /RTP/ መተግበር በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ውስጥ እንደ ትራንስፖርት መጋራት (ride-sharing)፣ እቃና አገልግሎትን ማድረስ /ዴሊቨሪ/፣ ኢ-ኮሜርስና ሌሎችም ባሉ አካባቢዎች የላቀ ፈጠራ እንዲኖር ያስችላል፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- ከኢትስዊች ጋር በመሆን የችርቻሮ/ አነስተኛ/ ቅጽበታዊ ክፍያ /RTP/ ሥርዓትን መተግበር፣

የዚህ ተግባር ስኬት በተግባር 6 ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በሁሉም ተዋንያንና የክፍያ መንገዶች ተናባቢነትን ማሳደግ፡፡

ተግባር 9፡ የባንክ የክፍያ መሳሪያዎች ተመሳሳይና ወጥ እንዲሆኑ ማስቻል

በፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ ወጥነት ያለው /Standard/ አሰራርና አገልግሎት መኖር በዘርፉ ተዋንያን ዘንድ ተመሳሳይ ቋንቋና ግንዛቤ ለመፍጠር በእጅጉ አስፈላጊ ነው (ለምሳሌ ለብድር የመረጃ ቋት የተለየ መለያ መስጠት)፣ በርካታ ተዋናዮችን በሚያሳትፉ አገልግሎቶች ወጥነት ያለው አሰራር ባግባቡ የተቃኘ ህብር ለመፍጠር ያግዛል (ለምሳሌ በባንኮች መካከል ያለውን ግብይት ማወራረድ)፣ እንዲሁም ለተገልጋዮች የአገልግሎት ጥራት ደረጃ እና ስምም መሆንን በግልጽ ማስቀመጥ (ለምሳሌ ከኮርፖሬት ደንበኞች የሂሳብ ሥርዓት ጋር ሂሳብን ማስታረቅ)፡፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ ያለው ወጥ አሰራር /ስታንዳርድ/ ከሚጠበቀው በታች ሲሆን የክፍያ ሥርዓት መሰረተ ልማት እንዳይጎለብት የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ተጠቃሚዎች ተከታዮቹን ያነሳሉ፡-

- የባንክ ሂሳብ መግለጫ፣ ወጥነት የሌለው የባንክ የሂሳብ መግለጫ ኩባንያዎች የባንክ ክፍያቸውንና ግብይታቸውን ከሂሳብ አያያዝና ኦዲት ስርዓታቸው ጋር በቀላሉ ለማስታረቅ እንዲቸገሩ አድርጓል፡፡
- ዝውውሮች፣ ወጥነት የሌላቸው የገንዘብ ማስተላለፊያ ቅጾች ተገልጋዮች ተጨማሪ የማስማማት ስራዎችን እንዲሰሩ ያስገድዳሉ፡፡ በተለይም ድርጅቶች የሰራተኞችን ደመወዝ ክፍያ ለመፈጸም፡፡
- ቼክ፣ ሁለት ስታንዳርዶች በስራ ላይ የዋሉ ሲሆን (ለድርጅቶችና ለግለሰቦች) የክንውን ሂደቱ ሁሉም ባንኮች ስርዓቱን እንዲተገብሩ ይጠይቃል፤ ይህ ደግሞ ተጨማሪ ወጪዎችንና ውጤታማ ያልሆነ አሰራርን ይፈጥራል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዓለም ደረጃ ወረቀት አልባ ግብይት በዲጂታል ክፍያ ምክንያት እያደገ በመምጣቱ፣ በዓለማቀፍ የክፍያ ከባቢ ሁኔታ የቼክ አገልግሎት እየቀረ መምጣቱን እንዲሁም ወደመቆም እየሄደ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ቁልፍ የባንክ የክፍያ መሳሪያዎችን ወጥነት ያላቸውና ተመሳሳይ እንዲሆኑ ማድረግ ውጤታማ የክፍያ ከባቢያዊ ሁኔታን ለመፍጠር ወሳኝ እርምጃ ነው፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- ከባንኮችና ከደንበኞች ጋር በመተባበር ወጥነት ኖሯቸው ሊዘጋጁ የሚገባቸውን ቁልፍ ጉዳዮች መለየት፣
- ዓለም አቀፍ መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመር ወጥ የሆኑ የክፍያ መሳሪያዎችን ለመተግበር የሚያግዙ ዝርዝር መመሪያዎችን (Standardization guidelines) ማዘጋጀት፡፡

ለ2.2. ስትራቴጂያዊ ምሰሶ 2፡ አካታች ውጤታማ የዲጂታል የክፍያ አሰራሮችን መተግበር

መነሻና ቁልፍ ተግዳሮቶች

ዲጂታል ክፍያ እንዲተገበር ከፍላጎትና ከአቅርቦት እይታ አንጻር መሰራት ያለባቸው በርካታ ስራዎች አሉ፡፡ ከፍላጎት አንጻር ህብረተሰቡ ማለትም የመንግስትና የግል ዘርፉ ክፍያዎችን ለመፈጸም አሁንም ጥሬ ገንዘብ ይዘው መንቀሳቀሳቸው አልቀረም፡፡ ከአቅርቦት አንጻር ውስን የሆነ ፍላጎት በመኖሩ አጥጋቢ የሆነ የዲጂታል ክፍያ የሚያስችል ሁኔታ አልጎለበተም፡፡ ፍላጎትና አቅርቦት የተሳሰሩ በመሆናቸው ይህንኑ ተደጋጋሚ ዑደት ለመቀየር ግብ አስቀምጦ መስራት ይገባል፡፡

"በፌስታል ብር ይዘን እስከመቼ?" ከስትራቴጂ የባለድርሻ አካላት ምክክር የተወሰደ ፣

እንደ ዓለም ባንክ ሪፖርት እ.ኤ.አ. በ2017 በኢትዮጵያ የዴቢት ካርድ ተጠቃሚ ቁጥር 4በመቶ ሲሆን (ከሰሃራ በታች ባሉ አገራት የነበረው አሃዝ 18በመቶ ነበር) ከ1በመቶ በታች የሆኑት ደግሞ የክሬዲት ካርድ ነበራቸው (ከሰሃራ በታች ባሉ አገራት የንጽጽር አሃዙ 3በመቶ) ነው፡፡ የዲጂታል ክፍያ የሚጠቀሙ ተገልጋዮች ቁጥር ደግሞ 12በመቶ (ከሰሃራ በታች ባሉ አገራት ያለው የተጠቃሚ ቁጥር ደግሞ በንጽጽር ሲታይ 34በመቶ) ሆኗል (World Bank Group 2020d)፡፡ (ከታች የቀረበውን ምስል 9 ይመልከቱ)

በኢትዮጵያ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ከ90በመቶ በላይ የሚሆነው የችርቻሮ ግብይት የሚካሄደው በጥሬ ገንዘብ እንደሆነ ይገመታል[31]፡፡ ከጥቂት ግብይቶች ውጪ ዝቅተኛም ሆነ ከፍተኛ የክፍያ መጠን ያላቸው ግብይቶች የሚከናወኑት በጥሬ ገንዘብ ነው፡፡ የጥሬ ገንዘብ ክፍያ ማዘዣ (ሲ.ፒ.ኦ) እና ቼክ በአንዳንድ ግብይቶች በግሉም ሆነ በመንግስት ዘርፎች እንደ አማራጭ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን በተለይም ከፍተኛ የዋጋ መጠን ባላቸው እንደ ቤትና መኪና ግዢ ላይ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ የመንግስትና የግል ዘርፍ የኮርፖሬት የደመወዝ ክፍያዎች እንዲሁም የጡረታ ክፍያዎች በኤሌክትሮኒክ መንገድ የከፋዩ ድርጅትና የተጠቃሚው ባንክ ሂሳብ ተመሳሳይ ከሆነ የሚተላለፍ ሲሆን የመንግስት ተቋማት፣ ለጋሾች፣ የግል ዘርፍ ተጠቃሚዎች የድርጅቱ ባንክ ሂሳብ ባለበት ባንክ ሂሳብ እንዲከፍቱ በማድረግ በኤሌክትሮኒክስ መንገድ የደመወዝ ክፍያዎችን ያስተላልፋሉ (ለማሳያም የመንግስት ሰራተኞች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አገልግሎቱን ያገኛሉ)፡፡ የሞባይል መገንዘብ በኢትዮጵያ አዲስ ጽንሰ-ሃሳብ ሲሆን ብዙዎች የሞባይል የአየር ሰዓት ለመሙላት የሚጠቀሙበት አገልግሎት ነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት የዲጂታል ክፍያ በአገሪቱ እንዲጀመርና ስር እንዲሰድ ከፍተኛ ቁርጠኝነት አለው፡፡ የክፍያ ስርዓቱን ዲጂታል በማድረግ ውስጥ ትልቅ ድርሻ አለው ተብሎ የሚወሰደው ሁሉም የመንግስት ዝውውሮችና ግብይቶች ዲጂታል እንዲሆኑ ማድረግ ሥርዓቱን በማስለመድ ረገድ መሰረት ይጥላል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን በመንግስትና በለጋሾች የተጀመሩ ሁለት የዲጂታል ክፍያ ማሳያዎች በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡ ማሳያዎቹ በምስል 11 እና 12 ቀርበዋል፡፡ ቢሆንም ሌሎች በርካታ ስኬታማ ማሳያዎችን በመምሳሌነት በማንሳት የክፍያ ሥርዓቱ ስር እንዲሰድ የሚደረገውን ጥረት ማገዝ ይገባል፡፡

ምስል 10፡ የዲጂታል ክፍያ ተጠቃሚዎች ሥርዓቱን የመቀበል ምጣኔ ከባቢያዊ መረጃ

ምንጭ፡ ዓለም ባንክ (2020d)



ምስል 11፡ የኢ-ታክስ ማብራሪያ

በገቢዎች ሚኒስቴር የተተገበረውና ታክስ ከፋዩ ማህበረሰብ በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ታክስ የሚያሳውቅበትና ክፍያ የሚፈጽምበት ሥርዓት ታክስ ከፋዩ ከታክስ ማሳወቅና ክፍያ ጋር ተያይዞ ሲያባክን የነበረውን ጊዜና ወጪ የሚቆጥብ አሰራር ነው፡፡ ሥርዓቱ የገቢዎች ሚኒስቴርን ከቢል አግሪጌተር፣ ከንግድ ባንኮችና ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጋር የሚያስተሳስር ነው፡፡ ይህ የኢ-ታክስ ሥርዓት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ተነሳሽነት የተጀመረና በአሁኑ ወቅት ከ3,000 በላይ ታክስ ከፋዮች ግብራቸውን በዚሁ መንገድ ተመዝግበው ግብራቸውን የሚያሳውቁበትና ክፍያ የሚፈጽሙበት አሰራር ነው፡፡ ይህ ሥርዓት ሊያስተናግድ የሚችለው 10,000 ታክስ ከፋዮችን ሲሆን ትኩረት ያደረገዉም ከፍተኛ ግብር ከፋዮችን ብቻ ሲሆን ሌሎች አነስተኛ ግብር ከፋዮችን ሊያስተናግድ የሚችል ሞባይልን መሰረት ያደረገ የክፍያ ሥርዓት በትግበራ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

አሁን ያለው ሥርዓት የሚሰራው በተከታዩ መንገድ ነው፡፡

1. ታክስ ከፋዮች በገቢዎች ሚኒስቴር የኢ-ፋይሊንግ ሥርዓት ውስጥ በመመዝገብ በሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የኢ-ታክስ ፋይል ይከፍታሉ፣
2. በገቢዎች ሚኒስቴር በኦንላይን በተዘረጋው አሰራር (platform) ታክስ ከፋዮች ታክሳቸውን ያሳውቃሉ፣
3. ታክስ ከፋዮች የሚጠበቅባቸውን የታክስ መጠን ክፍያ በኦንላይን የባንክ አገልግሎት ባሉበት ሆነው ያከናውናሉ (ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተጀመረ ሲሆን አሁን ወደ ሌሎች የንግድ ባንኮች እየሰፋ ይገኛል)፣
4. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ክፍያውን ማጣራት ሲያደርግ የገቢዎች ሚኒስቴር በበኩሉ መረጃዎችን ከብሔራዊ ባንክ በተላከዉ መረጃ መሰረት ያስተካክላል፡፡

ምስል 12፡ ገላጭ ምሳሌ፡ የምርታማነት ሴፍቲኔት ፕሮግራም

የዲጂታል ድጋፍ ክፍያዎች (ከመንግስት ለግለሰብ ተጠቃሚዎች የሚከናወን Government to Person- G2P)

የግብርና ሚኒስቴር በዘረጋውና ለድርቅ ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በቀጥታ የሚደረግ የፋይናንስ ድጋፍ ሲሆን የምርታማነት ሴፍቲኔት ፕሮግራም[32] በሚል የሚታወቅ ፕሮግራም ነው፡፡ ፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ከሚገኙ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትና ከፊንቴክ ኩባንያዎች (Fintechs) ጋር በመሆን (MOSS ICT and Belcash) በሞባይል ገንዘብ አገልግሎት የሚከናወን ሲሆን የገጠሩን ህብረተሰብ በሞባይል አማካኝነት ያሉ አማራጮችን በመጠቀም የተሻለ ውጤት ለማግኘት ታስቦ የሚከናወን አሰራር ነው፡፡ በ380 ወረዳዎች ከሚገኙ 8 ሚሊዮን የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ውስጥ 30በመቶ ለሚሆኑት (2.6 ሚሊዮን) ተጠቃሚዎች ክፍያዎች የሚከናወኑት በሞባይል ስልካቸው አማካኝነት በሚከናወን ዲጂታል የከፍያ ሥርዓት ነው፤ በዚህ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት በዓመት የሚከፈለው የገንዘብ መጠን ብር4 ቢሊዮን እንደሚሆን ይገመታል፡፡

አሁን ያለው ሥርዓት የሚሰራው በሚከተፈለው መንገድ ነው፡፡

1. የግብርና ሚኒስቴር በሚያወጣው የምዝገባ መርሃ-ግብር መሰረት ተጠቃሚዎች በሚኖሩበት አካባቢ በመገኘት ለሞባይል ገንዘብ አገልግሎት በሞባይል ስልካቸው አማካኝነት ይመዘገባሉ፤ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ስለ አጠቃቀሙ ስልጠና ይሰጣሉ፡፡
2. የግብርና ሚኒስቴር በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት አማካኝነት በየወሩ ክፍያዎችን ይፈጽማል፡፡
3. የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ክፍያዎችን ለተጠቃሚዎች የሚፈጽሙ ሲሆን ተጠቃሚዎች በተንቀሳቃሽ ስልካቸው አማካኝነት ክፍያ መፈጸሙን ማሳወቂያ መልዕክት ይደርሳቸዋል፡፡
4. ተጠቃሚዎች በአቅራቢያቸው ከሚገኙ ወኪሎች ጥሬ ገንዘብ ማውጣት ወይም ከሞባይል ስልካቸው ክፍያዎች ለሌሎች መፈጸም ይችላሉ፡፡

በቀጣይ በዚህ የዲጂታል የክፍያ ፕሮግራም ሁሉንም ተጠቃሚዎች ሙሉ ለሙሉ ለማካተት የታቀደ ሲሆን በዚህ መንገድ በዓመት የሚከናወነው የክፍያ መጠንም 10 ቢሊዮን ብር ይሆናል፡፡ የተጠቃሚዎች የክህሎት ውስንነት፣ የተንቀሳቃሽ ስልክ ለመግዛት የአቅም ውስንነት መኖርና የወኪል አገልግሎት ኔትወርክ ትስስር ደካማ መሆን ፕሮግራሙ ከገጠሙት ተግዳሮቶች ውስጥ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ያሉትን የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት በማሳደግ የዲጂታል ግብይቶችን ለማሳደግ ዕድሎች እንዳሉ የቀረቡት ሁኔታዎች ማሳያ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምሳሌዎቹ ሥርዓቱን ለመጠቀም ትልቅ አቅም እንዳለ ያሳያሉ፡፡

በአሁን ወቅት በኢትዮጵያ የሚከናወኑ የዲጂታል ግብይቶች በአራት ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ፡፡

- የገንዘብ መክፈያ ማሽን ግብይቶች፡ ጥሬ ገንዘብ ማውጣት፣ ክፍያዎችን ማስተላለፍና ቀሪ ሂሳብ ማወቅ፣
- የክፍያ ነቁጦች ግብይቶች፡ በዴቢት ወይም በክሬዲት ካርድ የግብይት ክፍያዎችን መፈጸም፣
- የሞባይል ባንኪንግ ግብይቶች፡ የሞባይል ገንዘብን በመጠቀም ክፍያዎችን መፈጸም፣
- የኢንተርኔት ባንኪንግ ግብይቶች፡ የባንክ ድረ-ገጾችን በመጠቀም ክፍያዎችን ኦንላይን መፈጸም ናቸው፡፡

በምስል 13 በተቀመጠው መሰረት በኢትዮጵያ በአሁን ወቅት ያለው በእነዚህ ግብይቶች የመጠቀም ቁጥር እየጨመረ ቢሆንም አሁንም ከዚህ የበለጠ አሃዙን ለማሳደግ ብዙ ዕድሎች አሉ፡፡ በገንዘብ መክፈያ ማሽን የሚከናወነው የጥሬ ገንዘብ ዝውውር 64በመቶ ሲሆን ከፍተኛውን ድርሻ ይዟል (EthSwitch Steering Committee 2019)፡፡ በክፍያ ነቁጦች የሚከናወኑ ዝውውሮችም ዕድገት በማሳየት ላይ ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን 40በመቶ የሚሆኑት የክፍያ ነቁጥ መሣሪያዎች የሚገኙት በባንኮች ቅርንጫፎች በመሆኑ የነጋዴ ግብይት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሳይሆኑ ቅርንጫፎቹ ጥሬ ገንዘብ ለመክፈል የሚጠቀሙባቸው ናቸው[33]፡፡

ምስል 13: ዲጂታል ክፍያ በአይነት

ምንጭ፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ



በኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፉ የሚያቀርባቸው አገልግሎቶች ትርፍን ታሳቢ አድርገው የሚቀርቡ አይደሉም፡፡ ጥሬ ገንዘብ ማስገባትና ማውጣት (CICO- Cash-in Cash-out) ለባንኮች እንደቢዝነስ የሚወሰድ ስራ አይደለም፡፡ በአሁን ሰዓት በዲጂታል መንገድም ሆነ በጥሬ ገንዘብ የሚከናወኑ ዝውውሮች የአገልግሎት ወይም የኮሚሽን ክፍያ የሌላቸው ወይንም በጣም አነስተኛ ክፍያ የሚከፈልባቸው ናቸው፡፡ በተጨማሪም ተገልጋዮችን ሊያበረታቱ የሚችሉ የተወሰኑ ዝውውሮች (የጥሬ ገንዘብና የዲጂታል) ምንም ዓይነት የዋጋ ስትራቴጂ የላቸውም፡፡ አበረታችና ፈጠራ የታከለበት የንግድ አሰራር በዲጂታል አገልግሎት አቅራቢዎች በኩል አለመኖሩ በተገልጋዩ ዘንድ አሁንም ጥሬ ገንዘብን እንዲጠቀምና የዲጂታል ክፍያ አገልግሎትን ለመጠቀም አስገዳጅ ፍላጎት እንዳይፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡

አሁን ባለው የኢትዮጵያ የፋይናንስ አገልግሎት ስርጭት ሁኔታ አገልግሎቱ በአብዛኛው በከተሞች የተወሰነ ሲሆን በዋነኛነት መካከለኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በሚኖሩበት አካባቢ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ከ35-75በመቶ የሚሆነው የፋይናንስ አገልግሎት መሰረተ-ልማት በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኝ ነው[34]፡፡ ሰፊ የጂኦግራፊ ሽፋንን መድረስ የፋይናንስ ተደራሽነትን በአገሪቱ በማረጋገጥ ረገድ በእጅጉ ወሳኝ ነው፡፡ በክልሎች መካከል ያሉ ለምሳሌ የቋንቋ፣ የጂኦግራፊያዊ መሰረተ-ልማት መለያየትና የህዝብ አሰፋፈር ሁኔታ የፋይናንስ አካታችነትን በአገር አቀፍ ደረጃ ከማረጋገጥ አንፃር ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ሁኔታዎች ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለፋይናንስ አካታችነት ቅድሚያ በመስጠት እ.ኤ.አ. በ2017 ብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ[35] አውጥቷል፡፡ ለዚህ ተብሎ በተቋቋመው ሴክሬታሪያት አማካይነት ሥነ-ምህዳሩን በማስፋት ረገድ ለትግበራው በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ዓለም አቀፍ መልካም ተሞክሮዎች

ዲጂታል ክፍያን ለመተግበርና ስር እንዲሰድ ከማድረግ አኳያ ዲጂታል ክፍያን የሚያስጠቅሙ አገልግሎቶችን እያሰፉ በመሄድ (Scalable use cases)፣ ማበረታቻዎችን በማቅረብና፣ የግንዛቤ መፍጠሪያ መርሃ-ግብሮችን በመዘርጋት እና አካታችነትን በማስፋት ረገድ ያሉ ዓለም አቀፍ መልካም ተሞክሮዎች ተለይተዋል፡፡

እየሰፋ የሚሄድ አገልግሎት በመዘርጋት ረገድ ያሉ ተሞክሮዎች (Scalable use cases)

ዲጂታል የክፍያ ሥርዓትን መተግበርና ስር እንዲሰድ ማድረግ እየሰፋ የሚሄድ አገልግሎቶችን መለየትንና የተለየ የክፍያ ስርዓትን ማስረፅን ይጠይቃል፡፡ በአገር ዉስጥ መደበኛ ባልሆነ ኢኮኖሚ የስራ እድል በሚፈጠርበት አከባቢ ብዙ በጥሬ ገንዘብና በሳንቲም ላይ የተመሰረተ የገንዘብ ዝዉውር ነዉ የሚስተዋለዉ፡፡ እንደ አንጎላ፣ ሜክሲኮና ኬንያ የመሳሰሉት ሀገራት እነዚህን መደበኛ ያልሆኑ ዘርፎችን የሞባይል ገንዘብ ዝውውር ተጠቃሚ በማድረግ ኢ-መደበኛ ከሆነ የኢኮኖሚ ዘርፍ ወደ መደበኛ የፋይናንስ ዘርፉ ውስጥ እንዲካተቱ አድርገዋል (Eschenbacher & Irrera 2019)፡፡ ተጨማሪ መረጃዎችና ትንተናዎች እደሚያሳዩት በዓለም አቀፍ ደረጃ ሞባይል ገንዘብ ጥቅም ላይ በመዋሉ ምክንያት ድብቅ/ኢ- መደበኛ//shadow/ ኢኮኖሚ በ 2.4 በመቶ ቀንሷል[36]፡፡ የዲጂታል ክፍያዎች እዲተገበሩ በማድረግ ረገድ ሌላው ትልቅ ድርሻ ያለው የመንግስት ክፍያዎችን በዲጂታል መንገድ እንዲፈጸሙ ማድረግ ነው፤ በተለይም የመንግስት ስራ የመፍጠርና የመቅጠር ድርሻ ትልቅ በሆነባቸው አገራት ብዙ ቁጥር ያለው ህዝብ ወደ ዲጂታል ክፍያ ስርዓቱ እንዲገባ በማድረግ ድርሻው የጎላ ነው፡፡ በሌላ መልኩ መንግስት የሚሰጣቸው የማህበራዊ ዋስትና ድጋፎችም በዲጂታል ክፍያ ሥርዓት እንዲፈጸሙ ማድረግ ለዲጂታል ክፍያ መተግበር ትልቅ ድርሻ አላቸዉ፡፡

ድንበር ተሻጋሪ የሐዋላ ክፍያዎችም በዲጂታል ክፍያ እንዲከናወኑ ተደርገዋል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአዲሱ የዲጂታል ክፍያ ቴክኖሎጂ ከውጭ አገር የሚላኩ የክፍያ አማራጮች ቀደም ሲል የነበረውን ተወዳዳሪ ያልሆነ፣ የማይመቸዉንና ብዙ ወጪ የሚጠይቀውን አሰራር እየተገዳደረው ይገኛል፡፡ ይህ

አዲስ ሞዴል የጊዜና የገንዘብ ወጪን ከመቀነሱም ባሻገር ለላኪውም ሆነ ለተቀባዩ በቀላሉ ተደራሽ የሆነ አገልግሎት ነው፡፡ የእነኚህን አዳዲስ የዓለም አቀፍ የሐዋላ ዝውውሮች አሰራር በተመለከተ ያሉ ዋና ዋና የዲጂታል ሞዴሎች የሚከተሉትን ያካትታል (Alliance for Financial Inclusion 2018)፡፡

- የሞባይል ገንዘብን መሰረት ያደረገ፡ በሞባይል ገንዘብ ወይም በሞባይል ሂሳብ ድንበር ተሻጋሪ የገንዘብ ዝውውሮች እንዲከናወኑ የሚያስችል ነዉ፡፡ የሞባይል ገንዘብ ሂሳቦች ከላኪውና ከተቀባዩ ጫፍ በሁለቱም በኩል መጠቀም ይቻላል፡፡ ይህ የአሰራር ስርዓት በምዕራብ አፍሪካ፣ በምስራቅ አፍሪካ፣ በደቡብ ምስራቅ እስያ እና በፓስፊክ በሰፊው የተተገበረ ነው፡፡ በምዕራብ አፍሪካ ካሉት የገንዘብ መክፈያ ማሽን፣ የሞባይል ገንዘብ[37] እና ኦሬንጅ ገንዘብ[38] በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡
- በኦንላይንና በኢንተርኔት አማካኝነት፡ ደንበኞች በባንክ ሂሳባቸው፣ በዴቢት ካርድ፣ በክሬዲት ካርድ እና በሌሎች አማራጮች አማካኝነት የኦንላይን የሃዋላ ዘዴን በመጠቀም ገንዘብ ማስተላለፍ የሚችሉበት ነው፡፡ የሐዋላ ተቀባዮች በተለያዩ አማራጮች (በሞባይል ገንዘብ፣ ወደ ባንክ ሂሳብ ቀጥታ ገቢ በማድረግ፣ የአየር ሰዓት በመሙላትና ጥሬ ገንዘብ ወጪ በማድረግ) ክፍያዎችን ያገኛሉ፡ ፡ ይህንን ከሚያከናውኑ ኩባንያዎች ውስጥ ዎርልድ ሬሚት[39] እና ሹም[40] ተጠቃሽ ናቸው፡፡
- ኦንላይን አቻ ላቻ የሚደረጉ ዝውውሮች (Online peer-to-peer)፡ እነኝህ የኦንላይን ምህዳሮች በሁለት የተለያዩ ሀገራት የሚገኙ ገንዘብ ላኪዎች ድንበር ተሻጋሪ ገንዘብ ሳያስፈልግ እንዲገናኙ ያስችላሉ፡ ፡ ድንበር ተሻጋሪ የገንዘብ ዝዉውር አነስተኛ በመሆኑ ገንዘቡን ለማስተላለፍ የሚወጣዉም ወጪ አነስተኛ ነዉ፡ ፡ ይህ ሙሉ በሙሉ ኦንላይን በመሆኑ የጥሬ ገንዘብ ቅብብሎሽ አይኖረውም፡፡ በመሆኑም ግብይቶች የሚፈፀሙት በባንክ ሂሳብ፣ በክፍያ ካርድ ወይም በውስን አቅራቢዎች የሚቀርብ የዝግ የሞባይል ገንዘብ ነው፡፡ ለዚህም፡- ትራንስፈር ዋይዝ እና ከረንሲ ፌይር ተጠቃሽ ምሳሌዎች ናቸዉ፡፡
- በቢትኮይንና በብሎክቼይን የሚከናወኑ ዝውውሮች፡ የገንዘብ ዝውውርን በቢትኮይን ወይም በሌሎች የብሎክቼይን አሰራሮች ማስተላለፊያ መንገድ ነው፡፡ ዝውውሮች የሚከናወኑት በላኪና ተቀባይ አገራት ገንዘብ ሲሆን ድንበር ተሻጋሪ ዝውውሮች ግን የሚፈጸሙት በቢትኮይን ወይም በሌሎች የክሪፕቶከረንሲዎች ነው፡፡ ለዚህም፡- አብራ እና ቢትፔሳ በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡
- በቢትኮይንና በብሎክ ቼይን የሚከናወኑ ዝውውሮች፡ የገንዘብ ዝውውርን በቢትኮይን ወይም በሌሎች የብሎክ ቼይን አሰራሮች ማስተላለፊያ ነው፡፡ ዝውውሮች የሚከናወኑት በላኪና ተቀባይ አገራት ገንዘብ ሲሆን ነገር ግን ድንበር ተሻጋሪ ዝውውሮች ግን በቢትኮይን ወይም በሌሎች የክርፕቶከረንሲዎች ነው፡፡ Abra[43] እና BitPesa[44] በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን አንድ ወይም ከዚያ በላይ ያሉ የሐዋላ የድንበር ተሻጋሪ ዝውውር አማራጮችን ለእያንዳንዱ ኢኮኖሚ በጥንቃቄ መተግበር መፍትሄ ነዉ፡፡

ማበረታቻዎች

የዲጂታል የክፍያ ሥርዓት የበለጠ እንዲተገበርና ስር እንዲሰድ ማዕከላዊ ባንኮችና መንግስት ተገልጋዮች በምን መልክ ቢበረታቱ አገልግሎቱን ሊጠቀሙ እንደሚችሉ፣ ነጋዴዎች ምን ቢደረግ ክፍያዎችን በዚህ መልኩ ሊቀበሉ እንደሚችሉ፣ የንግድ ባንኮችና የፋጠራ ባለቤቶች እንዴት ቢደገፉ እና ቢጎለብቱ በዘርፉ ላይ የበለጠ ተሳታፊ እንደሚሆኑና መዋዕለ ንዋያቸውን ሊያፈሱ እንደሚችሉ አማራጮችን ማጤን ያስፈልጋል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተተገበረ ያለዉ ተሞክሮ የሚያሳየው በጥሬ ገንዘብ የሚደረግ ግብይትን ዋጋ የሚያሳጣና የማያበረታታ አሰራር

መከተልን ነው፡፡ ስዊድንን ጨምሮ አንዳንድ አገራት የጥሬ ገንዘብ አያያዝን ስራ ለትርፍ ለተቋቋሙ ድርጅቶች ማስተላለፋቸዉ የንግድ ባንኮችንና የደንበኞችን የጥሬ ገንዘብ አያያዝ የተዛመደ ወጪ አንሯል (Knowledge@Wharton 2018)፡፡ በህንድና በብራዚል ተገልጋዮች ለንግድ ባንኮች የሚፈጽሙት የዝውውር አገልግሎት ክፍያ እጅግ አነስተኛ መሆን የሞባይል ባንኪንግ ከጥሬ ገንዘብና ከፊትለፊት ባንኪንግ በእጅጉ ርካሽ ነዉ፡፡ (State Bank of India 2020; Banco do Brasil 2019)፡፡

ሌሎች አገራት በበኩላቸዉ የክፍያ ነቁጦችን አጠቃቀምና ትግበራ ለማበረታታት የተለያዩ እርምጃዎችን ወስደዋል፡፡ ለነጋዴዎች የሚደረገው ማበረታቻ የክፍያ ሥርዓቱ እንዲተገበር ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገ ሲሆን በታይላንድ ነጋዴዎች በዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ክፍያዎችን በመቀበላቸው የታክስ ክፍያ የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል (Bank of Thailand 2017)፡፡ ህንድ በበኩሏ ለእያንዳንዱ ዝውውር 0.5 በመቶ ክፍያ በመሸፈን የትግበራውን ወጪ ደጉማለች ፡፡ በደቡብ ኮሪያ በክሬዲት ካርድ ለሚደረግ ሽያጭ ነጋዴዎች የታክስ እፎይታ እንዲያገኙ ሲደረግ (WalletBuddy 2017) በኡራጓይም ከዲጂታል ዝውውሮች (ከ22 እስከ 18 በመቶ) የሽያጭ ታክስ ተመላሽ ተደርጎ ለክፍያ ነቁጥ መሰረተ ልማት ድጎማ ዉሏል (Moneytrans 2018)፡፡

በደቡብ ኮሪያ ሸማቾች ክፍያዎችን በዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ሲፈጽሙ ከከፈሉት ዋጋ ተመላሽ እንዲያገኙ በማድረግ ሸማች-ተኮር ፖሊሲ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ሌሎች የመንግሥት አካላት ደግሞ በዲጂታል መንገድ ለሚደረጉ ዝውውሮች ተጠቃሚዎችና ነጋዴዎች የተለያዩ ማበረታቻዎችን እንዲያገኙ የተለያዩ አሰራሮችን ያስተዋውቃሉ፣ ቅናሽ ይሰጣሉ፣ የአገልግሎት ክፍያ መጠንን ይቆጣጠራሉ፡፡ ለማሳያም በናይጄሪያ በካርድ ለሚደረጉ ግብይቶች የዝውውር ክፍያ 0.75 በመቶ እና ከዚያ በታች እንዲሆን በተቆጣጣሪው አካል ተወስኗል፡፡ በሞሮኮም የዝውውር የአገልግሎት ክፍያ ከ1 በመቶ በታች እንዲሆን ተደንግጓል (Yoco 2019)፡፡

የግንዛቤ መፍጠሪያና የማስተማሪያ መርሃ-ግብሮች

የፋይናንስ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ዲጂታል ለማድረግ የሚሰራውን ስራ ለማገዝ የፋይናንስ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓትን የተመለከቱ የግንዛቤ መፍጠሪያና ማስተማሪያ መርሃ-ግብሮች ዓለም አቀፍ የፖሊሲ አውጪዎች አጀንዳ ሆነዋል (OECD 2018)፡፡ የቡድን 20 አገራት በዲጂታል አካታችነት ከፍተኛ እርከን መርህ እንደሚያሳየው የዲጂታል እና የፋይናንስ የግንዛቤ መፍጠሪያና ማስተማሪያ መርሃ-ግብሮችን ማስፋፋት በጣም ወሳኝ መሆኑን ይገልጻል (Global Partnership for Financial Inclusion 2016)፡፡ ትኩረቱም በዘርፉ የተለዩ ባህሪያትን በመለየት፣ ያለውን ጠቀሜታና ከዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ጋር ተያይዘው ያሉ አደጋዎችን በማሳየት፣ የአገልግሎት ማግኛ አማራጭ ዘዴዎችን በመዘርዘር፣ ምን እንደሚመስሉ በመመዘንና በማስፋፋት እንዲሁም ዘርፉን የበለጠ በማስተዋወቅ ተጠያቂነትና ትርፋማ የሆነ የዲጂታይዜሽን ሂደትን በማጎልበት ተገልጋዮች በአገልግሎቱ ላይ እምነት እንዲያሳድሩ በማድረግ በፋይናንስ አገልግሎት ውስጥ ተካታች የሆኑትንና ያልሆኑትን መድረስ እንደሆነ ይዘረዝራል፡፡

የእስያ ልማት ባንክ (2019) የዲጂታል ፋይናንስ የግንዛቤ መፍጠሪያና ማስተማሪያ መርሃ-ግብር አራት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ መርሃ-ግብሩ በእነዚህ የፋይናንስ ክህሎት ማስተማሪያ ነጥቦች ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸው ያስቀምጣሉ፡፡

1. የዲጂታል ፋይናንስ ምርቶችና አገልግሎት እውቀት ፤ የሚያካትተውም ክፍያዎችን፣ የሃብት አስተዳደር (Asset Management)፣ አማራጭ ፋይናንስ (Alternative Finance) እና ሌሎች ኢንተርኔትን መሰረት ያደረጉ አገልግሎቶች፣
2. ከዲጂታል የፋይናንስ አገልግሎት ጋር የተያያዙ አደጋዎች፣ እነዚህም ማስገር /phishing/, ማጥፋት /pharming/, ስለላን መሰረት ያደረጉ /spywar/, ሲም ካርድ መቀያየር /SIM Card Swapping/, መግለጥ/Profiling/ እና መጥለፍ/hacking/፣

3. ከፋይናንስ ጋር የተያያዙ አደጋዎችን የመቆጣጠሪያ መንገዶች፣ ይህም ተጠቃሚዎች የመተግበሪያ መሳሪያዎችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው፣ በሁለተኛ ተራ ቁጥር ላይ ከተጠቀሱ አደጋዎች እንዴት ራሳቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው ከዚህ ውስጥ የይለፍ የሚስጥር ቁጥራቸውን (PIN) እና ሌሎች የግል መረጃቸውን እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው፣
4. የተገልጋዮች መብቶችንና በተራ ቁጥር 2 የተዘረዘሩት አደጋዎች ሲያጋጥሟቸው ምን ህጋዊ ቅድመ-ሁኔታዎችን መከተል እንዳለባቸው ማካተት አለበት፡፡

አካታችነት

የዓለም ኢኮኖሚ የጾታዊ እኩልነትን በፋይናንስ አገልግሎት ውስጥ አካታች ማድረግ የፋይናንስ አካታችነትን በማረጋገጥ ውስጥ እጅግ ወሳኝ ሚና እንዳለው ከግምት በማስገባት በየጊዜው ልዩ ትኩረት እየተሰጠው የሚገኝ ጉዳይ ሆኗል፡፡ እንግሊዝና ሜክሲኮ በዚህ ረገድ ብዙ ርቀት በመጓዝ የሚጠቀሱ ሲሆን፣ ሴቶች በፋይናንስ አገልግሎቱ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ የተለያዩ እርምጃዎችን ወስደዋል፡፡ ይህም ፆታን መሰረት ያደረገ መረጃን በመሰብሰብ፣ መረጃ መሰረት ያደረገ ዕይታን በማበልፀግ በኢኮኖሚ ዉሥጥ የሴቶችን ተሳትፎን መጨመር እና የገበያ ጥናትን በመጠቀም ለሴቶች ተስማሚ የሆኑ ምርቶችን ማበልፀግ፡፡. እነዚህ እርምጃዎች በዲጂታል ክፍያዎች ሴቶችን ተሳታፊ የማድረግ አስፈላጊነትን ያሳዩ ሆነዋል፡፡

ሜክሲኮ ፆታን መሰረት ያደረገ መረጃን የፋይናንስ ሪፎርም ህግንና ብሔራዊ የጾታ እኩልነት ፕሮግራም ስታወጣ እንደግብዓት ተጠቅማበታለች፡፡ ከዚህ ባሻገር መረጃው ሴቶች ከፋይናንስ አገልግሎት የሚርቁበትን ምክንያት በተለይም በሀገር ውስጥ ስራና መደበኛ ባልሆኑ የንግድ ዘርፎች መሰማራታቸው ለዚሁ አስተዋጽኦ ማድረጉን ለይታበታለች፡፡ በእንግሊዝ፣ በባንግላዴሽና በሜክሲኮ ሴት የቢዝነስ ባለቤቶች ላይ ፋይናንስ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ምን እንደሆነ ጠቃሚ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች ሴቶች በየትኞቹ ዘርፎች ላይ መደገፍ እንዳለባቸው ለመለየት አግዘዋል፣ ባንኮችና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት መረጃውን በመውሰድ አገልግሎታቸውን እንዴት ጾታ ባማከለ መንገድ ለማድረስ እንደሚችሉ አግዟቸዋል፡፡ እንግሊዝ ባለፉት 10 ዓመታት ጾታን ያማከለና ፍትሃዊ አገልግሎት ለመስጠት መረጃውን ተጠቅማበታለች፡፡ ሜክሲኮ በጾታ ላይ ያለውን የፋይናንስ አካታችነት ክፍተት እ.ኤ.አ. በ2001 ከነበረበት 12.2 በመቶ እ.ኤ.አ በ2017 ወደ 2.9 በመቶ ዝቅ አድርጋለች፡፡

ስትራቴጂካዊ እርምጃዎች

የተገልጋዮችን አመኔታ ለማግኘትና የዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ስር እንዲሰድ አራት ክፍሎች ያሉት ስትራቴጂካዊ እርምጃዎች ተነድፈዋል፡፡ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ከተቀመጡት ስትራቴጂካዊ እርምጃዎች ውስጥ 11ዱ ስትራቴጂካዊ እርምጃዎች የአቅርቦትና የፍላጎት ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት ቅድሚያ ተሰጥቷቸው በኢትዮጵያ ቢተገበሩ አገልግሎቱ እንዲለመድና ስር እንዲሰድ ትልቅ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡

- እየሰፋ የሚሄድ አገልግሎትን መዘርጋት አገልግሎቱ እንዲተገበርና ስር እንዲሰድ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡
- ተጠቃሚዎች ወደ ዲጂታል የክፍያ ሥርዓት እንዲመጡ ማበረታዎችን መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- ለተገልጋዮች የግንዛቤ መፍጠሪያና ማስተማሪያ መርሃ-ግብሮችን በማዘጋጀት ማስተማር ይገባል፡፡
- አካታችነትን ማበረታታትና መደገፍ ይገባል፡፡

ይህ ተግባር በዝርዝር ተግባራት ሊደገፍ ይገባል

እየሰፋ የሚሄድ አገልግሎትን መዘርጋት

ተግባር 10፡ የመንግስትና በመንግስት ስር ያሉ ኢንተርፕራይዞችን ክፍያና ገቢ አሰባሰብ ዲጂታይዝ ማድረግ

ተግባር 11፡ የማህበራዊ ዋስትናና ሰብዓዊ ድጋፎችን ዲጂታይዝ ማድረግ

ተግባር 12፡ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የሚደረጉ ከቱሪዝም ጋር የተያያዙ ዝውውሮችን ዲጂታይዝ ማድረግ

ተግባር 13፡ የግብርና ዘርፍ ክፍያዎችን ዲጂታይዝ ማድረግ

ተግባር 14፡ ድንበር ተሻጋሪ የሐዋላ ገንዘብ መላኪያን ዲጂታይዝ ማድረግ

ማበረታቻዎች

ተግባር 15፡ የፋይናንስ ተቋማት ለጥሬ ገንዘብ አያያዝ እንዲያስከፍሉ ማድረግ

ተግባር 16፡ በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ግብይቶች ላይ ገደብ መጣል

ተግባር 17፡ታክስ የሚደረጉ ሆነዉ በኤሌክትሮኒክስ ለሚከናወኑ ግብይቶች ማበረታቻዎችን ማድረግ

የግንዛቤ መፍጠሪያና መስተማሪያ መርሃ-ግብሮች

ተግባር 18፡ ዲጂታል የክፍያ መተግበሪያዎችን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን መፍጠር

ተግባር 19፡ የዲጂታል ክፍያ አጠቃቀምን መሰረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን መቅረጽ

ኣካታችነት

ተግባር 20፡ ፆታን መሰረት ያደረገ መረጃን በመሰብሰብ የሚመለከታቸዉንና ዓለምአቀፍ ዉሳኔ ሰጪ አካላትን ማሳወቅ

ተግባር 21፡ ከፋይናንስ አገልግሎቶች የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያማከለ አገልግሎቶችንና መፍትሔዎችን ማስጀመር

ተግባር 22፡ ባለብዙ ቋንቋ አገልግሎቶች እንዲኖሩ ማበረታታት

ለ2.2.1 እየሰፋ የሚሄድ አገልግሎትን መዘርጋት

ዝውውሮች በሶስት ዋና ዋና መንገዶች ሊቀመጡ ይችላሉ፡፡ የግለሰብ (Person)፣ የንግድ (Business) እና የመንግስት (Government) ናቸው፡፡ የዲጂታል ግብይት እንዲተገበር እና ስር እንዲሰድ እነዚህን ሶስት የዝውውር ዓይነቶች ለማስፋት የሚያስችሉ አገልግሎቶች ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል፡፡ ትንንሽ የዝውውር ዋጋ ያላቸው ነገር ግን ቶሎ ቶሎ የሚከናወኑ ክፍያዎችን በተመጣጣኝ ወጪ ለማቅረብ በሚያስቸሉ አማራጮች ላይ ትኩረት በማድረግ መስራት የዲጂታል ክፍያ በወጥነት እንዲተገበርና ሥር እንዲሰድ የሚደረገውን ጥረት ለማፋጠን ያግዛል፡፡ በጊዜ ሂደት የተገልጋዮችን አመኔታ ለማትረፍ የሚያስችል ሲሆን ወደ ሌሎች የዲጂታል ክፍያ አማራጮች በማምራት በአነስተኛ ወጪ ሽግግሩን ለማረጋገጥ ያግዛል፡፡

በኢትዮጵያ ያለውን ተሞክሮ በርካታ ማሳያዎችን በማስቀመጥ መግለጽ ይቻላል፡፡ በብሔራዊ የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ቅድሚያ ከሚተገበሩ ተግባራት መካከል የመንግስት ክፍያዎችን፣ ለህብረተሰብ የሚለቀቁ ክፍያዎችን፣ የሃዋላ ክፍያዎችንና መንግስት በስፋት የሚተገብራቸዉ የልማት ሴክተሮችን እንደ ግብርና እና ቱሪዝም ዲጂታል ማድረግ ይገኙበታል፡፡

ለተለዩት ደንበኞች የዲጂታል ክፍያ አገልግሎቶች የተገልጋዮች የገበያ ጥናት በማድረግ የግለሰብ ተጠቃሚ ተኮር አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት አገልግሎቱ እንዲለመድ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ በተጨማሪም በእያንዳንዱ አገልግሎት ላይ ለተጠቃሚዎች የግንዛቤ መፍጠሪያና ማስተማሪያ መርሃ-ግብሮችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ Better Than Cash Alliance (2016) እንዳስቀመጠው "የተገልጋዩን ፍላጎት መሰረት አድርጎ የሚቀረጽ የዲጂታል የክፍያ ሥርዓት የተገልጋዩን የመጠቀም ፍላጎትና አቅም የሚያጎለብት ሲሆን የሚነሱ የደንበኞች ቅሬታዎችን ይቀንሳል፡፡" ሲል Responsible Digital Payments Guidelines በሚለው ሰነድ ያስቀምጣል፡፡

ተግባር 10፡ የመንግስትንና የመንግስት ኢንተርፕራይዝ ክፍያዎችንና የሚሰበሰቡ ገቢዎችን ዲጂታይዝ ማድረግ

የመንግስት ክፍያዎችና ገቢ አሰባሰቦች በኮምፒዉተር እንዲተሳሰሩ /አዉቶሜት/ ማድረግና ወደ ዲጂታል አሰራር መቀየር ዉስን ጥሬ ገንዘብ የሚጠቀም ማህበረሰብን ለመፍጠር መሰረት እንደሚጥል ይጠበቃል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት በስሩ ባሉ የመንግስት አካላት፣ ተቋማትና በመንግስት የልማት ድርጅቶች /SOEs/ አማካኝነት በኢኮኖሚዉ ውስጥ የማይተካ ሚና ይጫወታል፡፡ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት ይዞታ ስር ያሉት ኢንተርፕራይዞች ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ የመንግስትና የመንግስት የልማት ድርጅቶች /SOEs/ ዝውውሮች ላይ ክፍያ ለመፈጸምም ሆነ ለመቀበል ትኩረት ማድረግ አገልግሎቱ እንዲለመድና ስር እንዲሰድ ድርሻው የጎላ በመሆኑ ተደጋጋሚነት ያላቸው (high-frequency) ክፍያዎች ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ በፋይናንስ ዘርፉ ሪፎርም የዳሰሳ ጥናት የተካተተ ነው፡፡

ዝውውሮቹ ከፍተኛ ድርሻ የሚይዙና በተለያየ መንገድ ተዘርዝረው ሊቀመጡ የሚችሉ ናቸው፡፡

- ከመንግስት ለግለሰብ (G2P)፡ የሚፈጸሙ የደመወዝና የጡረታ ክፍያዎች፣
- ከግለሰብ ለመንግስት (P2G)፡ የሚፈጸሙ የግለሰብ የታክስ ክፍያዎች፣
- ከመንግስት ለንግድ ተቋም/ለአቅራቢ (G2B)፡ የሚፈጸሙ ክፍያዎች፣

- ከንግድ ተቋም ለመንግስት (B2G)፡ የሚፈጸሙ ከፍተኛ መጠን ያላቸው የኩባንያ የታክስ ክፍያዎች፣
- ከንግድ ተቋም ለግለሰብ (B2P)፡ የሚፈጸሙ የደመወዝ ክፍያዎች /SOE wages/፣
- ከግለሰብ ለንግድ ተቋም (P2B)፡ የሚፈጸሙ የአገልግሎት የአየር ትኬት ክፍያዎች፣

ከላይ የተዘረዘሩት አንዳንዶቹ ክፍያዎች በዲጂታል የክፍያ ሥርዓት አማራጮች ውስጥ በአሁኑ ሰዓት እየተካተቱ የሚገኙ ናቸው፡፡ በተለይም

- የደመወዝና የጡረታ ክፍያዎች ፡ በከተሞች አካባቢ መንግስት የኤሌክትሮኒክስ የማስተላለፊያ መንገዶችን በመጠቀም ደመወዝና የጡረታ ክፍያዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡
- የድርጅትና የግለሰብ የታክስ ክፍያዎች፡ የገቢዎች ሚኒስቴር ተግባራዊ ባደረገው የኢ-ታክስ የኤሌክትሮኒክስ የታክስ ክፍያ ሥርዓት የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና ሌሎች የንግድ ባንኮች በበይነ መረብ መተግበሪያ አሰራር ተቀናጅተው በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ወደ 3000 የሚጠጉ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ለአገልግሎቱ ተመዝግበዋል፡፡ በተጨማሪም የገቢዎች ሚኒስቴር መካከለኛና አነስተኛ ግብር ከፋዮች በሞባይል ስልካቸው አማካኝነት የታክስ ክፍያ መፈጸም እንዲችሉ እየሰራ ይገኛል[45]፡፡
- የአገልግሎትና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ክፍያዎች፡ በዲጂታል የአገልግሎት ክፍያ አማካኝነት ደንበኞች የአየር ሰዓት መሙላትና የውሃ ቢል የአገልግሎት ክፍያን መፈጸም ይችላሉ፡ ፡ የአዲስ አበባ ውኃና ፍሳሽ ባለስልጣን ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በመተባበር በሲቢኢ-ብር የሞባይል ዋሌት የዲጂታል አገልግሎት አማካኝነት የሚከናወን ነው፡ ፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ደንበኞቹ ወደ ትኬት ቢሮዎቹ ሳይመጡ ካሉበት ሆነው በኦንላይን በድረ-ገጽ ወይም የአየር መንገዱን መተግበሪያ በመጠቀም በዲጂታል አማራጮች የበረራ ትኬታቸውን እንዲቆርጡና ክፍያ እንዲፈጽሙ አሰራር ዘርግቷል፣ በዚህ መንገድ አገልግሎቱን የሚያገኙ ደንበኞቹን ለማበረታታትም ቅናሽ ይሰጣል፡፡

ነገር ግን አሁንም ሰፊ ስራ ይጠይቃል፡፡ ለመንግስት ክፍያዎችና ገቢ አሰባሰብ አማራጮችን መንደፍ፣ በፋይናንስ ሚኒስቴር ክፍያዎችን በኮምፒዉተር ማስተሳሰር /አዉቶሜት/ ማድረግ፣ አንድ ወጥ የግምጃቤት ሂሳብን መተግበር፣ የፌዴራልና የክልላዊ መንግስታት ሥርዓቶችን አውቶሜት ማድረግ፣ የመንግስትንና የቢል ክፍያዎችን በግል ዘርፍ አግሪጌተሮች በኩል መሰብሰብ እና በይበልጥ የጎለበተ የመንግስት የኢ-መተግበሪያ መፍጠር ይገባል (World Bank Group 2020a)፡፡

ይሄ በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ተግባር ሲሆን የቁልፍ ባለድርሻ አካላትን ትብብር የሚጠይቅ፣ ዝርዝር የመነሻ ጥናት የሚያስፈልገው፣አካታች የሆነ ዕቅድ ሊወጣለት የሚገባ እና የደረጃ በደረጃ ትግበራ የሚጠይቅ ነው፡፡ ትግበራው በበጀት ቁጥጥር ላይ ትልቅ ለውጥ የሚያመጣ፣ ሁለንተናዊ የወጭ ቁጠባን የሚያመጣና የፋይናንስ ተካታችነትን የሚያረጋግጥ ይሆናል፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- ከገቢዎችና ከፋይናንስ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ከመንግስትና ወደ መንግስት የሚከናወኑ ክፍያዎችንና የገንዘብ ፍሰትን ብዛትና መጠን በስድስት መደቦች መተንበይና ማሳየት፣
- ከገቢዎችና ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር አሁን ያለውን ዝርዝር የአቅም ሁኔታ የሚያሳይ ዳሰሳ ማድረግ፣ ባለው የአሰራር ስፋትና ገደብ እንዲሁም የሚፈልጉ ለውጦችን መለየት እንዲሁም የሚያስፈልጉ የፋይናንስና የቴክኒክ ሃብቶችን መለየት፣
- በሂደት የሚከናወኑ የተለያዩ የዲጂታል አማራጮችን በመጠቀም የሚከናወኑ ዝውውሮችን ዕቅድ ማዘጋጀት

የዚህ ተግባር ስኬታማነት በተግባር 6 በሚወሰዱ ተግባራት ላይ የተወሰነ ነው፡፡ ይሄውም ተናባቢ የሆኑ መሰረተ ልማቶችን በማሳደግ ተጠቃሚዎች ወደ ባንክ መሄድ ሳያስፈልጋቸው የመንግስት ክፍያዎችን በሞባይል ዋሌትና በኤሌክትሮኒክ ክፍያ አማካይነት መፈጸም ሲችሉ ነው፡፡

ተግባር 11፡ የማህበራዊ ዋስትናና ሰብዓዊ ድጋፎችን ዲጂታይዝ ማድረግ

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የልማት ድርጅቶች ብዙ ጊዜ ለተጠቃሚዎች የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ይታወቃል፡፡ በጥሬ ገንዘብ እንዲህ ዓይነት ድጋፎችን ከመስጠት ጋር የተያያዙ የደህንነት ስጋቶችና የቁጥጥር ችግሮች አሉ፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የእርዳታና ሰብዓዊ ድጋፍ ክፍያዎችን ወደ ዲጂታል የክፍያ አማራጮች የማሻገር አዝማሚያ ይታያል (Nkamgang Bemo etal. 2017; GSMA 2019a; MasterCard 2016; Aid & International Development Forum 2016)፡፡ በኢትዮጵያ የማህበራዊ ዋስትናና የሰብአዊ ድጋፍ ክፍያዎችን ወደ ዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ቅድሚያ ሰጥቶ ማምጣት ከሚያስገኘዉ ቀጥተኛ ጠቀሜታዎች መካከል ውጤታማነትና ቅንጅት፣ ግልጽነት፣ ተጠያቂነትና ደህንነት ይጠቀሳሉ፡፡ በተዘዋዋሪም ለሰፊው የፋይናንስ ተደራሽነት አጀንዳ የራሱን አስተዋጽኦ በማበርከት ከፋይናንስ ተደራሽነት ርቀው የሚገኙትን የህብረተሰብ ክፍሎች ለማካተት የዲጂታል ክፍያዎች ለምሳሌ የሞባይል ዋሌት ድርሻ አለው፣ ለዲጂታል ዝውውርም በር ከፋች ሂደት ሊሆን ይችላል፡፡ የዲጂታል ክፍያ ለተጠቃሚዎች በሚፈጽሙ የሰብአዊ ድጋፍ አድራጊ ድርጅቶች መካከል ውጤታማ የሆነ ቅንጅትና ትብብር ለመፍጠር ከተቻለ የመንግስትን ግቦች በመደገፍ ረገድ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

በኢትዮጵያ በጥሬ ገንዘብ ሲደረጉ የነበሩ ድጋፎች በከፊል ወደ ዲጂታል የክፍያ አማራጮች እየመጡ ነው፡፡ በተለይም የግብርና ሚኒስቴር ከለጋሽ ድርጅቶች ፣ ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትና የፋይናንስ አገልግሎት ከማይሰጡ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የሚፈጽመው የPSNP የሞባይል ገንዘብ ክፍያ ተጠቃሽ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር የዲጂታል ክፍያ አማራጮች መንግስት ኮቪድ-19ን የመሰለ ወረርሽኝና ሌሎች ቀውሶች ሲከሰቱ በተሻለ መንገድ ምላሽ ለመስጠትና ዝግጁ ለመሆን ያስችለዋል፡፡

ይሄው ተግባር ለጋሽ ካልሆኑ ሌሎች የመንግስት ተቋማት ለሚፈጸሙ የማህበራዊ ድጋፍ ፕሮግራሞችም ተግባራዊ መደረግ የሚችል ነው፡፡

ቅድሚያ የሚሰጠው ምክረ-ሃሳብ

- መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ሌሎች ልማት ላይ ትኩረት አድርገው ከሚሰሩ ተቋማት ጋር በመተባበር ግብይቶች የሚከናወኑበትን ቦታና መጠን (የዝውውሮችን ቁጥርና የዝውውር የገንዘብ መጠን) በመለየት በልማት ድርጅቶች ምን ያህል ዋጋ ያለው የጥሬ ገንዘብ እንደተለቀቀ መለየት፣
- ከፋይናንስ ተቋማት፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ተሳታፊ ከሆኑ መንግስታዊ ተቋማት ጋር በመተባበር ደረጃ በደረጃ የሚከናወን የማህበራዊ ጥበቃና የሰብአዊ ድጋፍ ክፍያዎችን ዕቅድ ማውጣት፣

የዚህ ተግባር ስኬታማነት በተግባር 3 ውጤታማነት ማለትም የወኪል አገልግሎትን ለማስፋፋት የቢዝነስ ተሞክሮዎችን መከለስ፣ በተግባር 24 ውጤታማነት ላይ ይሄውም አዲሱን የወኪል አጠቃቀም መመሪያ ትግበራ መገምገም በሚለው ላይ እና በተግባር 27 ለፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ማህበረሰብ ጥበቃ ማድረግ በሚሉት ተግባራት ትግበራ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በተግባር 28 የተዘረዘረው የሳይበር ደህንነትን ማጠናከርም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የሲስተሞችን የሳይበር ደህንነት ማረጋገጥና የሚከናወኑ የማጭበርበር ድርጊቶች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን ማካሄድ፣ የወኪል ምልመላ ላይ ጥብቅ ማጣራት ማካሄድ፣ ከወጡ መመሪያዎች አንጻር ስራዎች በስምምነት መከናወናቸውን መቆጣጠር እና አጠራጣሪ ዝውውሮች ሲከናወኑ የዝውውሩን ሂደት መቆጣጠር አስፈላጊ ነው፡፡ በመጨረሻም የዚህ ድርጊት ስኬት በድርጊት 4 ውጤታማነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በድርጊት 4 የተቀመጠውም የቴሌኮሙኒኬሽን ተደራሽነትን በኔትወርክ ሽፋንና በመሣሪያ አቅርቦት ማሳደግ ነው፡፡

ተግባር 12፡ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የሚደረጉ ከቱሪዝም ጋር የተያያዙ ዝውውሮችን ዲጂታይዝ ማድረግ

በአገር-በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም አጀንዳ እንዲሁም በብሔራዊ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ ቱሪዝም በኢትዮጵያ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ዘርፎች ውስጥ ቀዳሚው ነው፡፡ ማንኛውም ቱሪስት ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ በኋላ በሚቆይበት ወቅት የያዘውን የውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ ገንዘብ ወይም ብር መቀየሩ የተለመደ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን በውጭ እንደ ቱሪስት በሚቆዩበት ጊዜ የባንክ ካርዳቸውን እንደማይጠቀሙ እሙን ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን በውጭ አገር ለሚኖራቸው ቆይታ የሚጠቀሙበትን የውጭ ምንዛሪ መጠን ደንበኛ ለሆኑበት ባንክ ጥያቄ በማቅረብ እስከ 3000 የአሜሪካ ዶላር ጣሪያ ድረስ በጥሬ ገንዘብ መውሰድ ይችላሉ[46]፡፡

የቱሪዝም ዘርፉን ዲጂታይዝ በማድረግ የዲጂታል ክፍያዎች እንዲለመዱና ስር እንዲሰዱ ማድረግ ከመቻሉም በላይ የውጭ ምንዛሪ መደበኛ በሆነው የፋይናንስ ዘርፉ አማካኝነት መሰብሰብ ይቻላል፡፡ ወደ ወጪ ሀገር ለሚጓዙ ኢትዮጵያዉያን በዉጪ ምንዛሬ የቅድመ ክፍያ ካርድ በባንኮች አማካኝነት ይዘጋጅላቸዋል፡፡ ይህም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር. FXD/49/2017 መሰረት የሚከናወን ይሆናል፡፡ ከውጭ የሚመጡ ቱሪስቶች ካርዶችን መጠቀም እንዲችሉ የክፍያ ነቁጦችና የክፍያ ማሽኖች በበቂ ሁኔታ መኖር አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ዓለም አቀፍ የክፍያ ሥርዓቶች አገር ውስጥ ካሉ የሞባይል ገንዘብ መተግበሪያዎች ጋር መናበብ መቻላቸው ለቱሪስቶች የበለጠ ምቾት ይፈጥራል[47]፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

ከውጭ ለሚመጡ ቱሪስቶች

- ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ ከቱሪዝም ኢትዮጵያ እና ከቱሪዝም ዘርፍ ዋና ተዋንያን ጋር በመሆን ዋነኛ የቱሪስት መዳረሻ የሆኑ ቦታዎችንና ማረፊያዎችን (የመኝታ አገልግሎት የሚሰጡ፣ ሬስቶራንቶች፣ መዝናኛዎች እና ባህላዊ ቦታዎች) መለየት፣
- ከባንኮች ጋር በመተባበር በተለዩ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችና ማረፊያዎች የክፍያ ነቁጥ ኔትወርክ መዘርጋት፣
- ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር በመተባበር ወደ ኢትዮጵያ ለሚመጡ ቱሪስቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን ማካሄድ፣

ከአገር ውጭ ለሚደረጉ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎች

- ከባንኮችና ከዓለም አቀፍ የክፍያ አማራጮች ጋር በመሆን በዉጪ ምንዛሬ የቅድሚያ ክፍያ ካርዶችን ማዘጋጀት፣

የዚህ ተግባር ስኬት የሚለካው ተግባር 1፣2 እና 16 በጋራ በሚያመጡት ስኬት ሲሆን ይህም ነጋዴዎች የዲጂታል ክፍያዎችን መቀበል ነው፡፡ ከዓለም አቀፍ የክፍያ አማራጮች ጋር በትብብር መስራትንም ይጠይቃል፡፡

ተግባር 13፡ በግብርና ዘርፍ ያሉ ክፍያዎችን ዲጂታይዝ ማድረግ

በኢትዮጵያ የግብርናው ዘርፍ 33 መቶ የአገሪቱን የሀገር ዉስጥ ምርት፣ 72 በመቶ የሚሆነውን የአምራች ኃይል እና 75 በመቶ የሚሆነውን የምርቶችን ኤክስፖርት ገቢ ይይዛል (UNDP)፡፡ ባለፉት አስርት ዓመታት አገሪቱ ያስመዘገበችው የኢኮኖሚ አፈጻጸም ከግብርና ምርት መጨመር ጋር በተለይም በስንዴና በበቆሎ (ከቡና፣ ከቅባት እህሎችና ከጫፍ ቀጥሎ ዋነኛ ምርቶች ናቸው) ጋር የተቆራኘነው (MInT 2020)፡፡ ነገር ግን ዘርፉ በቀጠናው ካሉ አገራት ጋር ሲነጻጸር በእጅጉ ወደ ኋላ የቀረ ነው፡፡ በአማካይ የሚገኘው ምርት ከሰሃራ በታች ካሉ አገራትም ያነሰ ነው (Tsan etal 2019)፡፡ በቀጠናው ያሉ አቻ አገራት የዲጂታል የክፍያ ሥርዓትን የግብርናውን ዘርፍ ለማሳደግ ተጠቅመውበታል፡፡ ለምሳሌ ስማርት መኒ የተሰኘው በታንዛንያና በኡጋንዳ የዲጂታል የክፍያ ሥርዓት አቅራቢ ድርጅት ሲሆን በአሁን ሰዓት በገጠር ወደ 200,000 የሚጠጉ ተገልጋዮችን እንዲሁም ከ2000 በላይ በከተማ የሚገኙ ነጋዴዎችን መድረስ ችሏል (ibid)፡፡ 20 በመቶ የሚሆኑት በገጠር የሚገኙ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች በየዕለት ተዕለት ህይወታቸው የዲጂታል ክፍያዎችን ይፈጽማሉ፣ እንዲሁም የግብርና ግብዓት ክፍያዎችን በስማርት መኒ በመክፈል አብዛኛው ማህበረሰብ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆኗል፡፡

አገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም አጀንዳ የኢትዮጵያ የግብርና ዘርፍን ለማዘመን አዲስ የቴክኖሎጂ አማራጮችን መጠቀም ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው በብሔራዊ የዲጂታል ስትራቴጂ ሰነድ ውስጥ የዘርፉን ዲጂታይዜሽን በማምጣት ረገድ መከተል ከሚገባው አራት መንገዶች/አማራጮች አንዱ በሚከተለው መልኩ ተቀምጧል "አማራጭ 1፡ ከግብርና የሚገኘውን እሴት አሟጦ መጠቀም"፡፡ ዲጂታል ክፍያዎች የግብርና ዘርፉን ለማዘመንና በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ውስጥ ትልቅ ሚና እንደሚጫወት ይታመናል፡፡ ግሎባል ፊንዴክስ ባወጣው ሪፖርት የግብርና ዘርፉን ክፍያ ዲጂታይዝ ማድረግ ግማሹንና ወይም ከዚያ በላይ የሚገመተውን ከባንክ አገልግሎት ውጪ ያለ ማህበረሰብ ጭምር ማካተት ነው (Demirguc-Kunt et al. 2018)፡፡ GSMA (2019b) የሞባይል ክፍያ አገልግሎት በግብርና ዘርፍ የተሰማራውን ማህበረሰብ ከፋይናንስ አገልግሎት ጋር ተያይዞ ያሉ የብድር ተደራሽነት፣ ቁጠባና ኢንሹራንስ ችግሮች የሚቀርፍ ነው፡፡ ይህ የብሄራዊ ዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ የግብርናዉን ዘርፍ ክፍያዎችን ዲጂታል በማድረግ መልካም አጋጣሚዎችን ይከፍታል፡፡ በግብርናው ዘርፍ የዲጂታል ክፍያውን ከየት መጀመር ይገባል የሚለውን ለመለየት ስትራቴጂያዊ መንገድ መከተልን ይገባል፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- ከግብርና ሚኒስቴርና ከግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ጋር በመተባበር ቅድሚያ የሚሰጣቸዉ የምርትና ዋጋ ሰንሰለትን በማስቀመጥ የዲጂታል ክፍያ መተግበሪያዎችን መተግበር፣

ተግባር 14፡ ድንበር ተሻጋሪ የሐዋላ አገልግሎትን ዲጂታይዝ ማድረግ

በባንክ ሂሳብ በኩል የሚላኩ ዓለም አቀፍ የሐዋላ አገልግሎትን ማስቀረት ወደ አገር ውስጥ በሚገባው የውጭ ምንዛሪ ፍሰት ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ እ.ኤ.አ. ከ2018-2019 ባለው የበጀት ዓመት ወደ ኢትዮጵያ በዉጭ ምንዛሬ የተላከዉ የግለሰብ ሐዋላ መጠን 5.7 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ነው፡፡ ይህ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ሲሆን የአገሪቱን የነፍስ ወከፍ ገቢ 6 በመቶ ይይዛል (UNDP)፡፡ ነገር ግን በአንዳንድ አካባቢዎች 78 በመቶ የሚሆነው ዓለም አቀፍ የዉጭ ምንዛሬ ሐዋላ የሚላከው መደበኛ ባልሆነ መንገድ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ (International Organization for Migration 2017)፡፡ ይህም አሰራር የሐዋላ አገልግሎቱ በኢኮኖሚ ውስጥ ሊጫወት የሚችለውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ የሚያስቀር ነው፡፡ በመደበኛ አማራጮች የሚላኩት አብዛኞቹ ሐዋላዎች ክፍያው የሚፈጸመው በጥሬ ገንዘብ ነው (World Bank Group 2020a)፡፡

ዓለም አቀፍ ተሞክሮ እንደሚያሳየው የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች በሐዋላ አገልግሎት ውስጥ ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው ነው፤ ነገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ይህ ሚናቸው የተገደበ ነው፡፡ ገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች አገልግሎታቸውን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጣቸው የፋይናንስ ተቋማት ጭምር መስጠት ያለባቸው ሲሆን አሁን ባለው አሰራር ግን ስርጭታቸው በባንኮች ቅርንጫፎችና በዋና ዋና ከተሞች ብቻ የተወሰነ ነው፡፡

ዓለም አቀፍ የሐዋላ አገልግሎትን በዲጂታል አማራጮች ማቅረብ በባንኮችና በሌሎች የዝውውር አማራጮች መጠቀምን የሚቀንስ ሲሆን መደበኛ የኢኮኖሚ አጠቃቀምን ለማጎልበት ያግዛል፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- ከፋይናንስና ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የዓለም አቀፍ ሐዋላ አገልግሎትን እንዴት ዲጂታይዝ ማድረግ እንደሚቻል ያሉ አማራጮችን መመልከት፣ አዳዲስ የአገልግሎት አቅራቢዎችና ቴክኖሎጂዎችን እንዲሁም ፈጣራዎችን ታሳቢ ማድረግ
- የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች ራሳቸውን ችለው የሚሰሩበትን አሰራር በመዘርጋትና የቁጥጥር ሥርዓትን በመፍጠር የተጣለባቸውን ገደብ ማንሳት አገልግሎቱን እንዲሰጡ ማድረግ ይገባል፡፡

ለ2.2.2 ማበረታቻዎች

በተለያዩ ኢንዱስትሪዎችና መስኮች ማበረታቻዎች አዲስ አስተሳሰብንና የቢዝነስ ሃሳብን እንዲሁም ለውጥን በመደገፍ ውስጥ ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡ የጥሬ ገንዘብ አጠቃቀም ወጪን በአገልግሎት ክፍያ መለወጥ በዲጂታል ክፍያ መተግበር ውስጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ለክፍያ ስርዓቱ ተዋናዮች የወጪ ማበረታቻ በመፍጠር መዋዕለንዋያቸዉን የዲጂታል አገልግሎት አቅርቦት ለማስፋፋትና ለማልማት ይጠቀሙበታል፡ ፡ በተጨማሪም በጊዜ ሂደት እነኚህ ማበረታቻዎች ተጠቃሚዎች የዲጂታል ክፍያን ከጥሬ ገንዘብ ይልቅ ምርጫቸዉ እንዲያደርጉ ያግዛሉ፡፡ .

በተጨማሪም የገቢዎች ባለስልጣን ለነጋዴዎች በዲጂታል አማራጮች ክፍያዎችን እንዲሰበስቡ የተለያዩ ማበረታቻዎችን በተለይም ከታክስ ክፍያ ተቀናሽ የሚደረግ ማበረታቻን በመተግበርና የኩባንያዎችን ጠቅላላ ኦፕሬሽናል ወጪ በመቀነስ ማበረታታት ይገባል፡፡ በሌሎች አካባቢዎች የታክስ ዕዳ ለንግድ ባንኮችና ለፈጠራ ሰዎች እንደ ተጨማሪ ማበረታቻ ይወሰዳል፡፡ የዲጂታል የክፍያ ሥርዓት አገልግሎት ስር እንዲሰድ በማድረግ ረገድ ያለውን ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ስንመለከት ማበረታቻዎች እንደ ቁልፍ የማነሳሻ መሳሪያ አገልግለዋል፡፡

ተግባር 15፡ ለፋይናንስ ተቋማት ጥሬ ገንዘብ አያያዝ ላይ ክፍያ መተግበር

በኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፉ በጥሬ ገንዘብ የሚያደርገው ግብይት ወጪ በመደበኛ መንገድ አልተቀመጠም፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከፋይናንስ ተቋማት ጥሬ ገንዘብ በመያዛቸው (cash-handling services) የሚሰበስበው የአገልግሎት ክፍያ የለም (dropping off and picking up banknotes)፡፡ የፋይናንስ ተቋማት ደንበኞች በጥሬ ገንዘብ ለሚያደርጉት ዝውውር የሚያስከፍሉት የተለየየ የክፍያ ሥርዓት የለም፡፡ በተጨማሪም በባንክ ቅርንጫፎች የሚደረጉ የጥሬ ገንዘብ ዝውውሮች ምንም ዓይነት የአገልግሎት ክፍያ የማይከፈልባቸው ሲሆን ነገር ግን ባንኮች በዲጂታል የክፍያ አማራጭ ለምሳሌ ለኤ.ቲ.ኤም የካርድ ክፍያ አገልግሎት ከደንበኞች ክፍያዎችን ይሰበስባሉ፡፡ አሁን ያለው አሰራር ነጋዴዎች ክፍያዎችን በጥሬ ገንዘብ ብቻ እንዲቀበሉ የሚያበረታታና ደንበኞች ለየዕለት ወጪ ማዋል የሚፈልጉትን ጥሬ ገንዘብ ለመያዝ ለአገልግሎት ወደ ባንኮች ቅርንጫፎች እንዲሄዱ የሚያደርግ ነው፡፡

በገንዘብ ተቋማት ላይ በማዕከላዊ ባንኮች ጥሬ ገንዘብ መያዝ ላይ ክፍያን መተግበር የገንዘባ ተቋማት የጥሬ ገንዘብን ወጪ እንዲረዱትና የጥሬ ገንዘብ ቅበላ እንዲቀንሱ፣ ደንበኞቻቸዉን የዲጂታል ክፍያ ዘዴዎችን እዲጠቀሙ እንዲያበረታቱ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ በጊዜ ሂደት የፋይናንስ ተቋማት በተለያዩ አማራጮች በሚደረጉ ውይይቶች የተለያዩ የክፍያ አማራጮች መዋቅሮችን በመተግበር በዲጂታል የክፍያ አማራጮች የሚደረጉ ዝውውሮችን የተሻለ ውጤታማ ማድረግ ይገባል፡፡ ዲጂታል የክፍያ ሥርዓት በረጅም ጊዜ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና ለፋይናንስ ተቋማት ተጨማሪ የገቢ አማራጭ የሚፈጥር ይሆናል፡፡

በአዉድ ላይ የተመሰረተ የጥሬ ገንዘብ አያያዝ የክፍያ መዋቅር መመስረት የገንዘብ ተቋማት ለቁልፍ ተዋናዮች የዲጂታል ክፍያዎችን እንዲያለሙ ጠቃሚ ማበረታቻ እንዲሰጡ ያስችላቸዋል፡፡ ይህን ተግባር ለመከወን ከጥሬ ገንዘብ ጥገኝነት ወደ ዉስን ጥሬ ገንዘብ ተጠቃሚ የኢኮኖሚ ሽግግር ማመቻቸትን ይጠይቃል፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- ለባንኮችና ለሌሎች የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርቡ የጥሬ ገንዘብ አገልግሎቶችን መለየት፣
- ዓለምአቀፍ መልካም ተሞክሮዎችን በመቃኘት መቼ የጥሬ ገንዘብ አገልግሎት ክፍያን መጀመር እንደሚያስፈልግ መወሰን፡፡

ተግባር 16፡ በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ግብይቶች ላይ ገደብ መጣል

በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ግብይቶች የማይለዩና ከየት ወደ የት እንደተዘዋወሩ ለማወቅ አስቸጋሪ ናቸው፡፡ ይህም ዝውውሩን ለመለየት አስቸጋሪ መሆን ቢዝነሶች ታክሳቸውን ለመሰወር ያግዛቸዋል፡፡ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት ስር እንዲሰድ ለማድረግ በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ዝውውሮች ላይ ገደብ መጣል አስፈላጊ ነው፡፡ከፍተኛ መጠን ያላቸው ክፍያዎችም መፈጸም ያለባቸው በዲጂታል አማራጮች መሆን አለበት (በካርድ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ የሚደረጉ ዝውውሮች)፡፡ የዲጂታል ክፍያ አማራጭ በመጠቀም የሚደረጉ ዝውውሮች በሌሎች አገራት ለአሸባሪዎች የሚደረግ የፋይናንስ ድጋፍ እንዲቀንስ፣ በወንጀል የተገኘን ሃብት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን በመቀነስ፣ የታክስ ስወራንና ድብቅ ኢኮኖሚን በመቀነስ ረገድ ትልቅ ድርሻ አለው (Global Legal Group 2019; Krishnan 2019)፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ዝውውሮች ላይ ገደብ ለማስቀመጥ የውስጥ

ዳሰሳዎችን እያደረገ ሲሆን ለዚህም ከክፍያ ነቁጥ ማሽኖች ተደራሽነት ጋር ተያይዞ ያሉ ቁልፍ ችግሮችን የመለየትና ኢ-መደበኛ በሆኑ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች በዲጂታል ክፍያ ውስጥ መካተትን በታክስ ሥርዓት ውስጥ ከመካተት ጋር በማያያዝ አገልግሎቱን ለመጠቀም አለመፈለጋቸው እንደ ተግዳሮች ተለይቷል፡፡ በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ዝውውሮች ላይ ገደብ ለማስቀመጥና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመተግበር መደበኛና ኢ-መደበኛ የሆኑ ገበያዎች ላይ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- ከፋይናንስ ተቋማትና ከኢት-ስዊች ጋር በመተባበር የገበያ ጥናት በማድረግ በገበያ ውስጥ የሚደረጉ የጥሬ ገንዘብ ዝውውሮችንና በየትኛው የብር ኖት ተደጋጋሚ ግብይቶች እንደሚካሄድ መለየት፣
- መደበኛና ኢ-መደበኛ የሆኑ ገበያዎችን በመለየት በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ዝውውሮች ላይ ገደብ በመጣል ውጤቱን መገምገም፣
- ከፋይናንስ ተቋማትና ከኢት-ስዊች ጋር በመሆን ዓለም አቀፍ መልካም ተሞክሮዎችን በመውሰድ የጥሬ ገንዘብ ዝውውር ላይ ገደብ የሚቀመጥበትን አውድ ዘርዝሮ ማቅረብ፣
- ከፋይናንስ ተቋማትና ከኢት-ስዊች ጋር በመሆን በጥሬ ገንዘብ ዝውውር ላይ የሚጣለውን ገደብ በጊዜ ማዕቀፍ ዘርዝሮ በማስቀመጥ መተግበር ናቸው፡፡

የዚህ ተግባር ስኬት የሚለካው በተግባር 2 የሚተገበሩት ተግባራት ናቸው፤ የክፍያ ማሽንና የክፍያ ነቁጥ የካርድ ክፍያን ማስፋፋት የሚለው ማለት ነው፡፡

ተግባር 17፡ ፡ታክስ የሚደረጉ በኤሌክትሮኒክስ ለሚከናወኑ ግብይቶች ማበረታቻዎችን ማድረግ

ነጋዴዎች ክፍያዎችን በዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ለመቀበል ማበረታቻ ያስፈልጋል የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ፡፡ የተናበበ ሥርዓት ባለመኖሩ በዲጂታል ሥርዓት ክፍያዎችን የሚቀበሉ ነጋዴዎች የተለያዩ የክፍያ ነቁጥ ካርድ መቀበያ ማሽኖችን በመክፈያ ቦታዎች ለማስቀመጥ ተገደዋል፡፡ ነጋዴዎች ክፍያዎችን በዲጂታል መንገድ ስለማይቀበሉ ተገልጋዮችም በሥርዓቱ ለመጠቀም የሚያገኙት ምንም ዓይነት ማበረታቻ የላቸውም፡፡ የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት የዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ስር እንዲሰድና እንዲለመድ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡

በኤሌክትሮኒክስ ለሚከፈል የግብር ማበረታቻ መፍጠር የዲጂታል ልምምድን በማበረታታት ድብቅ ኢኮኖሚን ይቀንሳል፡፡ .

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለነጋዴዎች የሚሰጡ የታክስ ማበረታቻዎችን መለየት (በግዢ ላይ የሽያጭ ታክስ ተመላሽ ማድረግ፣ ለታክስ የሚሰጡ ብድሮችን እንዲያገኙ ማድረግ)፡ ፡

የዚህ ተግባር ስኬት እውን ሊሆን የሚችለው በተግባር 1 ላይ የተቀመጠውን ከክፍያ ማሽንና ከክፍያ ነቁጥ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ቴክኒካዊ ጉዳዮችን መረዳት መነሻ ያደርጋል፡፡

ለ2.2.3 የግንዛቤ መፍጠሪያና ማስተማሪያ መርሃ-ግብሮች

የዲጂታል ፋይናንስ አዲስ ጽንሰ-ሃሳብ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዘርፉ ላይ ግንዛቤ መፍጠርና የዲጂታል ፋይናንስ ላይ የማስተማሪያ ይዘት በማስቀመጥ ተጠቃሚዎችን ማስተማርና ግንዛቤ መፍጠር ይገባል፡፡ የማስተማሪያ ይዘቱ ሁለት ነገሮችን ሊያካትት ይገባል፡፡ የመጀመሪያው የቴክኒካዊ ይዘት ሲሆን ከቴክኒክ ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ጉዳዮች ምላሽ የሚሰጥ ነው (ለምሳሌ የሞባይል ስልክ አጠቃቀም) እና ሁለተኛው ይዘት ደግሞ ከፋይናንስ ጋር ተያይዘው የሚነሱ መሰረታዊ የክፍያ ጽንሰ-ሃሳቦችን የሚያካትት ነው (ለምሳሌ ለግብይት የሚከፈሉ የአገልግሎት ክፍያዎች)፡፡

ብሔራዊ የፋይናንስ ማስተማሪያ ስትራቴጂ የብሔራዊ ባንክ የፋይናንስ አካታችነት ጽ/ቤት ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከፋይናንስ ሚኒስቴርና ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የፋይናንስ ማስተማሪያ መርሃ-ግብር ሰነድ አዘጋጅቷል፡፡ ፕሮግራሙ እ.ኤ.አ. በ2021 ወደ ትግበራ ይገባል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን በውስጡ ከተካተቱት በርካታ ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ የፋይናንስ አካታችነት ጥቅሞችና የተለያዩ ፋይናንስ አገልግሎቶች (ቁጠባ፣ ብድር፣ኢንሹራንስ) ተካተዋል፡፡

የተዘጋጀው የግንዛቤ መፍጠሪያና የማስተማሪያ መርሃ-ግብር ይዘት ቀደም ሲል ከተዘጋጁ የማስተማሪያ ፕሮግራሞች ጋር ተናበው እንዲሰሩና ድግግሞሽን ለማስቀረት ሲባል ትኩረት ይሰጠዋል፡፡

ተግባር 18፡ ዲጂታል የክፍያ አማራጮችን በተመለከተ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን መፍጠር

የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት ስር እንዲሰድና እንዲለመድ የዲጂታል ክፍያ አማራጮችንና ጥቅማቸውን በተመለከተ ግንዛቤ መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡ ተጠቃሚዎች እያደገ የመጣውን የዲጂታል ክፍያ አማራጮችንና መጠቀሚያዎችን በተመለከተ ግንዛቤያቸው እንዲያድግና የተሻለ እውቀት እንዲኖራቸው በእያንዳንዱ አማራጭ ያለውን የዝውውር አማራጭ ማለትም በክፍያ ነቁጥ፣ በክፍያ ማሽን፣ በሞባይልና በኢ-ባንኪንግ ማሳየት ይገባል፡፡ የሚካሄደው የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘመቻ በከተማና በገጠር ያለውን የተለያየ ህብረተሰብ ክፍል ባማከለ መልኩ የሚከተሉትን ነጥቦችንና ሌሎችን ባካተተ መልኩ መካሄድ ይኖርበታል፡፡

- ወጣቶች፡የዲጂታል ክፍያ አገልግሎትን በቀዳሚነት በመጠቀም አገልግሎቱ ስር እንዲሰድና እንዲለመድ ማድረግ፣
- ሴቶች፡ በጾታ ረገድ ያለውን ክፍተት ማጥበብ፣፣
- የገጠሩ አርሶ አደር (እና ቤተሰብ)፡ የፋይናንስ አካታችነትን በመጨመር በኩል በብዛት ግብርና ላይ ተሳታፊ የሆነውን የገጠሩ አርሶ አደር ማካተት፣

በተጨማሪም የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘመቻው የዲጂታል የክፍያ አማራጮች ያላቸውን ጥቅሞች ምሳሌዎችን በማንሳት የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል፡፡

- ምቹነት፡ ብቃትንና ክፍያ የሚፈጸምበትን ፍጥነት ያሳድጋል፣
- ግልጽነት፡ ተጠያቂነትን በማረጋገጥ ክፍያዎች ከየት ወደ የት እንደተከናወኑ ግልጽነትን ይፈጥራል፣
- ደህንነት፡ ዲጂታል አማራጮችን በማሳደግ የሚፈጸሙ የጥሬ ገንዘብ ስርቆቶችን በማስቀረት ደህንነቱ የተረጋገጠ አገልግሎት ለመስጠት ያግዛል፣

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- ከኢት-ስዊችና ከፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢ ተቋማት ጋር በመተባበር ብሔራዊ የግንዛቤ መፍጠሪያ መርሃ-ግብር በማዘጋጀት በፋይናንስ አገልገሎት ውስጥ የተካተቱትንና ያልተካተቱትን ለመድረስ የሚያስችል ፕሮግራም መንደፍ፡፡

ተግባር 19፡ የዲጂታል ክፍያ መጠቀሚያ ሁናቴን መሰረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን መቅረጽ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ ሰነድ የግንዛቤ መፍጠሪያና ማስተማሪያ መርሃ-ግብርንም አካቷል፡፡ ዲጂታል ክፍያን በተመለከተ ብቻ የግንዛቤ መፍጠሪያ መርሃ-ግብር በማዘጋጀት በሁለቱ ስትራቴጂዎች መካከል የተናበበ ፕሮግራም ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በክልሎችም ድግግሞሽን ለማስቀረት በፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ በታቀደው የማስተማሪያ መርሃ-ግብር ላይ መልካም ተሞክሮዎችን በማካተት ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች በዲጂታል ኢኮኖሚ ውስጥ ተሳታፊ ለሆኑት አካላት የሚሰጠው የስልጠና ፕሮግራም ክህሎትን መሰረት ማድረግ እንዳለበትና ትልቅ ድርሻ እንደሚኖረው ያሳያል (Asian Development Bank 2019)፡፡ ለተለዩ የዲጂታል ክፍያዎች የሚተገበረው የአቅም ግንባታ መርሃ-ግብር ተጨባጭ ሁኔታዎችን ከግምት ያስገባ መሆን አለበት፡፡ ይሄው ታዳሚውን መሰረት ያደረገ ክህሎት የማዳበር የስልጠና መርሃ-ግብር አካሄድ ለተለዩ ክህሎቶች የሚሆን የትምህርት መተግበሪያ በፈጠሩ እንደ Fundación Capital ባሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ማረጋገጫ የተሰጠው ነው፡፡ እያደገ የሚሄድ የዲጂታል ክፍያን አጠቃቀም በመፍጠር ውስጥ በትግበራው ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ ባለድርሻ አካላትን መነሻ አድርጎ የሚተገበር የአቅም ግንባታ መርሃ-ግብር መንደፍ አስፈላጊ ነው[48]፡፡ እነኚህ የአቅም ግንባታ መርሃ-ግብሮች የሚከተሉትን አራት ዋና ዋና ርዕሰ-ጉዳዮች አካታች መሆን ይኖርበቸዋል፡፡

- የሚተገበረው የዲጂታል ክፍያ አገልግሎትና መተግበሪያዉ ምን እንደሆነ፣
- የበለጸገውን የዲጂታል ክፍያና መተግበሪያ እንዴት ለመጠቀም ለሚያስችሉ ሁኔታዎች ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚቻል፣
- የዲጂታል ክፍያ ምርቶችን / አገልግሎቶችን/እና መተግበሪዎችን በመጠቀም ስለሚገኘዉ ፋይዳ ፣
- የዲጂታል የክፍያ አገልግሎቶችንና መተግበሪያዎችን ከመጠቀም ጋር ተያይዞ ስለሚነሱ የተገልጋይ ስጋቶችና የህግ ጥበቃዎች ማዕቀፍ ፡፡

ከዚህ ባሻገር በትግበራ ሂደት ውስጥ ትልቅ ክፍተት ሊኖርባቸው ይችላል ተብለው የሚታሰቡ የህብረተሰብ ክፍሎችን በተለይም ሴቶችን በተመለከተ የተለየ ይዘትን መፍጠር ይገባል (ዝርዝሩ በቀጣዩ ክፍል ይቀርባል)፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- የዲጂታል ክፍያ መጠቀሚያ ሁኔታዎችን በመለየትና የተወሰነ ይዘትና ተሳትፎ ያለዉ የአቅም ግንባታ መርሃ-ግብሮችን ለባለድርሻ አካላት መንደፍ (ለምሳሌ በአጭር ጽሁፍ የማሳወቂያ መልዕክቶችን መላክ፣ መተግበሪያዎችን ማበልጸግ፣ የስልጠና መርሃ-ግብሮችና ወዘተ)፡፡
- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተዘጋጀውን የማስተማሪያ መርሃ-ግብር ከዲጂታል ክፍያ መጠቀሚያ ሁኔታዎች መሰረት ባደረገ የአቅም ግንባታ መተግበር፡፡

ለ2.2.4 አካታችነት

በኢኮኖሚዉ ውስጥ የፋይናንስ አካታችነትን በማረጋገጥ በኩል የዲጂታል ክፍያ አገልግሎቶች ትልቅ ድርሻ አላቸዉ፡፡ የዓለም ባንክ ሪፖርት እንደሚያሳየው (World Bank 2020d) እ.ኤ.አ. ከ2011 እስከ 2017 ባለው ጊዜ በአፍሪካ የፋይናንስ ሂሳብ የጎልማሶች ድርሻ ከ23 በመቶ ወደ 43 በመቶ እንዳደገና ይህ እድገት በአብዛኛዉ በሞባይል ገንዘብ እድገት የመጣ ነዉ፡፡ የተስፋፋ ዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት አጠቃቀም የፋይናንስ ጥንካሬን በመጨመርና ድህነትን በመቀነስ ዜጎችን ከመደበኛ ኢኮኖሚ ተሳታፊ የሚያደርግ ስር የሰደደ የኢኮኖሚ እድገት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

የፋይናንስ አካታችነት ለኢትዮጵያ መንግስት ቅድሚያ የሚሰጠው ሲሆን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክም የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂን[49] በዉጤታማነት ለመተግበር በቁርጠኝነት እየሰራ ይገኛል፡፡ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ በአራት ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ i) መሠረተ ልማትን ማስፋፋት (የፋይናንስና ሌሎች) ii) በቂ የሆኑ የአገልግሎት አማራጮችን፣ አገልግሎቶችንና ተደራሽ የሆኑ አማራጮች መቅረባቸውን ማረጋገጥ iii) ጠንካራ የሆነ የፋይናንስ ተጠቃሚዎች ጥበቃ ማዕቀፍ መዘርጋቱን ማረጋገጥ እና iv) የፋይናንስ አቅም ደረጃን ማሻሻል- አተገባበሩም ከብሔራዊ ዲጂታል ክፍያ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነዉ፡፡ ይህም ቁርኝነት በመሰረተ ልማት ስትራቴጂክ ምሶሶ (የአገልግሎቶች ተናባቢነት፣ የቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌክትሪክ አገልግሎት እና ብሔራዊ የመለያ መታወቂያ) አማካኝነት ነዉ፡፡ በህግ ድንጋጌዎች ስትራቴጂክ ምሶሶዎች (ብድር መሰረተ ልማት እና የህግ ድንጋጌ) እና የመተግበር የስትራተጂክ ምሰሶ ወይም በፋይናንስ አካታችነት መረጃ ቋት ነዉ፡፡

በተጨማሪም ዋነኛው የፋይናንስ አካታችነት ማጠንጠኛ በጾታ መካከል ያለውን የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚነት ክፍተት ማጥበብ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃም ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገራት ጎልቶ የሚታይ በጾታ መካከል ያለ የአገልግሎት ተጠቃሚነት ክፍተት አለ፡፡ እ.ኤ.አ. በ2017 በወጣው የግሎባል ፊንዴክስ ሪፖርት የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚ ካልሆኑ ጎልማሶች መካከል 56 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች እንደሆኑ አስቀምጧል፡፡ በኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. በ2017 በወጣ ሪፖርት በጾታ መካከል ያለው የአገልግሎት ተጠቃሚነት ክፍተት እየሰፋ ነዉ፡፡ እ.ኤ.አ. በ2017 41 በመቶ ወንዶች እና 29 በመቶ ሴቶች የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ሲሆኑ እ.ኤ.አ 2014 ግን 23 በመቶ ወንዶች እና 21 በመቶ ሴቶች የፋይናንስ ተጠቃሚዎች ነበሩ (World Bank Group 2020d) ፡፡

ሴቶችን በፋይናንስ አገልግሎት ተካታች ማድረግ በኢኮኖሚ ውስጥ ተሳታፊ በመሆን ሰፊ አገራዊ ልማት ውስጥ ወሳኝ ሚና እንዲጫወቱ ያግዛል፡፡ በተጨማሪም ሴቶች በገጠራማ የአገሪቱ አካባቢ የቤተሰብን ግብይት በበላይነት ከማስተዳደር ካላቸው ድርሻ አንጻር የዲጂታል የክፍያ ሥርዓትን በማሳደግ ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ኢትዮጵያ ሴቶች በፋይናንስ ዘርፍ ውስጥ ለዲጂታል ክፍያ አስቻይ ሁኔታዎችን ከፋይናንስ አካታችነት ጥቅም ተቀባይነት አንፃር በፍጥነት ተሳታፊ እንዲሆኑ እዉቅና ሰጥታለች፡፡

እንደ the Better Than Cash Alliance (2020b) ሪፖርት በመንግስታትና በንግድ ተቋማት ሆን ተብሎ የሚደረግ ውስን የጾታ አካታችነት የሴቶች የፋይናንስ ተሳትፎ ውስን እንዲሆን ድርሻ አለው፡፡ ስለዚህ የተሻለ የሴቶችን የፋይናንስ አካታችነት ማሳደግ ያላሰለሰ ሁለንተናዊ ጥረት ማድረግን (ይህም አካታች የፋይናንስ ሥነ-ምህዳር ለሴቶች መፍጠርን) ፍላጎት ይጠይቃል፡፡ ይህም ከተለያዩ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ቡድኖች ጋር አብሮ መስራትን ይጠይቃል፡፡ ከዲጂታል ክፍያ ሥርዓት አንጻር ስንመለከተው ይህ ስትራቴጂ የተለያዩ የክፍያ አማራጮችን ማበልጸግን የሚጠይቅ ሲሆን ሴቶችን በፋይናንስ አገልግሎት ውስጥ የበለጠ ተካታች እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው፡፡

ተግባር 20፡ ፆታን መሰረት ያደረገ መረጃን በመሰብሰብ ሃላፊነት ያለባቸዉና ዓለምአቀፍ ዉሳኔ ሰጪ አካላትን ማሳወቅ

ፆታን መሰረት ያደረገ የመረጃ አሰባሰብን በማሳደግ ፖሊሲዎችና ምርቶችን በተሻለ መንገድ ማሳወቅ የፋይናንስ አካታችነትን ለማሳደግ ይረዳል፡፡ ከሁለቱም በኩል ማለትም ከፍላጎት በኩል (ከተጠቃሚዎች አንፃር) እና ከአቅርቦት በኩል (ከፋይናንስ ተቋማት አንፃር) የሚሰበሰቡ መረጃዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና የገንዘብ ሚኒስቴር ለፋይናንስ አካታችነት አናሳ መሆን አስተዋጽኦ ያደረጉ ምክንያቶችን ለመለየት ያስችላቸዋል፡፡

የሚሰበሰበው መረጃ ሴቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያደረጉ ምክንያቶችንና የፋይናንስ አገልግሎቶች አቅርቦቶችን፣ የፋይናንስ እውቀትንና የተጠቃሚዎች ጥበቃን በተመለከተ የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት ያግዛል፡፡ መረጃው በተጨማሪም ሴቶች የትኞቹን አገልግሎቶች እየተጠቀሙ እንደሚገኙና እንዴት ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ግንዛቤ ለማግኘት ይጠቅማል፡፡ ጾታን መሰረት አድርገው የሚሰበሰቡ መረጃዎች የሚከተሉትን የሚያካትቱ ናቸው፡-

- የፋይናንስ አገልግሎት ዓይነቶች፣
- የፋይናንስ አገልግሎቶች በቁጥር፣
- የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለማግኘት ያሉ ተግዳሮቶች፣
- የሂሳብ ዓይነቶች በቁጥር (ለምሳሌ ቼክ፣ የቁጠባ)፣
- የፋይናንስ አገልግሎቶች ዉስብስብነት፣ እና
- የብድር ሂሳቦች ዓይነቶች፡፡

መረጃዎች በየጊዜውና በተደጋጋሚ የሚሰበሰቡና የሚመዘገቡ ሲሆን የአገልግሎቱን ስኬትና የፖሊሲውን ውጤታማነት ለመገምገም ይረዳል፡፡ አሁን ያለዉ የመረጃ መሰብሰቢያ ቴምፕሌት ፆታን መሰረት ያደረገ መረጃን እንዲያካትት ይደረጋል፡፡ ደህንነቱ በተጠበቀ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎች ይከማቻሉ፡፡ በጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች በየወቅቱ የሚታተሙ ሲሆን የፋይናንስ ተቋማት፣ የሞባይል አገልግሎት አቅራቢዎችና በፋይናንስ ዘርፍ ተሳታፊ የሆኑ አካላት ለመረጃው ተደራሽነት ሊኖራቸው የሚገባ ሲሆን ለመጠየቅና መረጃውን አውርደው ለመጠቀም የሚችሉ መሆን አለበት፡፡

የተሰበሰበውን መረጃ በአግባቡ መጠቀም በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለመስጠት ያግዛል፡፡ ሜክሲኮ የመጀመሪያዉን ፆታን መሰረት ያደረገ የመረጃ አሰባሰብ ጥናት ከጀመረች ከሶስት አመት በኋላ የፋይናንስ አካታችነት 13 በመቶ እድገት አሳይታለች[50]፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክም የተሰበሰበዉን መረጃ በማሻሻልና በማዋቀር የፋይናንስ አካታችነትን በሚጨምሩ ዉሳኔዎችና ትግበራዎች ላይ ማዋል ይገባዋል፡፡ እነኚህ መረጃዎች ተሳታፊዎችንና ከፋይናንስ አገልግሎት የተገለሉትን አካላት ማዕከል ያደረገ የገበያ ዉሳኔዎችን እንዲያሳልፉና አዳዲስ አገልግሎቶችንና መተግበሪያዎችን እንዲጀምሩ አቅጣጫ ያሳያሉ[51]፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በመተባበር የመረጃ መሰብሰቢያ ቴምፕሌትን ፆታን መሰረት በማድረግ መረጃ እዲሰበሰብ በሚያስችል መልኩ መከለስ፣
- መረጃዎችን በመሰብሰብ መተንተንና ጥናቶችን የመረጃ መሰብሰብ ዑደቶችን ተከትሎ ማሳተም፡፡

የዚህ ተግባር ስኬት የሚመሰረተው በተግባር 21 ትግበራ (ከፋይናንስ አገልግሎቶች የተገለሉትን የህብረተሰብ ክፍሎችን ያማከለ አገልግሎቶችንና መፍትሔዎችን ማስጀመር) ላይ ነው፡፡

ተግባር 21፡ከፋይናንስ አገልግሎቶች የተገለሉትን የህብረተሰብ ክፍሎችን ያማከለ አገልግሎቶችንና መፍትሔዎችን ማስጀመር

የሴቶችን የፋይናንስ አካታችነት ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገር ፍላጎት በተለይም ለነሱ የሚሆን የፋይናንስ ውጤቶችን መቅረጽ ያስፈልጋል፡፡. እንደ the Global Partnership for Financial Inclusion የፋይናንስ አገልግሎቶች የሴቶችን ፍላጎቶች የማያካትቱ ከሆኑ የሴቶች አማራጮቹ ውስን እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ አገልግሎቶቹ የሴቶችን ፍላጎት፣ ወሳኝ የህይወት ኩነቶችንና ዑደቶችን ያካተቱ መሆን አለባቸው፡፡ የፋይናንስ ተቋማት ፆታን መሰረት ያደረገ መረጃን መሰረት በማድረግ ለሴቶች ፍላጎት ምቹ የሆኑ አገልግሎቶችን ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

ሴቶችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የዲጂታል ዝውውር አማራጮች ለምሳሌ ዴቢት ካርዶችና የሞባይል ዋሌቶች ተጠቃሚነታቸውን በመጨመር ያላቸውን ድርሻ በማየት ትኩረት ሰጥቶ መስራትን ይጠይቃል፡፡ ባንኮች የቤት ቁሳቁሶችን ከሚያቀርቡ ከተመረጡ ነጋዴዎች ጋር በመተባበር አገልግሎቱን ለሚጠቀሙ ሴቶች ቅናሽ መስጠት ይችላሉ፡፡

በኢትዮጵያ ሴቶች ብዙውን ጊዜ በአካባቢያቸው በፈጠሯቸው አማራጮችና በብድርና ቁጠባ ተቋማት አማካኝነት ገንዘብ ይቆጥባሉ፡፡ ዲጂታል ክፍያ መተግበሪያዎች በተለይም የህብረተሰብ ሂሳቦችን እንደ የጋራ የቁጠባ ሂሳብ እንዲኖር የሚያስችል ተደርጎ ማልማት የግለሰቦችን ፍላጎት በመጠበቅ ሴቶችን የዲጅታል ክፍያ እንዲጠቀሙ ለማበረታተት እንደ መሳሪያ ያገለግላል፡፡

እ.ኤ.አ. በ2017 UNCDF ባወጣው ጥናት ከወንዶች በበለጠ ሴቶች ለአገልግሎት መስጫ ቦታ ያላቸው ርቀት የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ በዋናነት እንቅፋት ሆኖ መጠቀሱን ጥናቱ ይፋ አድርጓል፡፡ የዲጂታል የክፍያ አማራጮች ያለውን ክፍተት የሚሞሉ ከመሆኑም በላይ የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆን የጎላ ሚና ይኖራቸዋል።

ይህ ተግባር ከፋይናንስ አገልግሎት ውጭ የሆኑ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችንም ለመድረስ ይረዳል።

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር እና ፆታን መሰረት ያደረገ መረጃን በመዳሰስ ለሴቶች የፋይናንስ ተደራሽነት ቁልፍ ተግዳሮቶችን መለየት እና ተግዳሮቶችን ለመፍታት የድርጊት መርሃ ግብር ማውጣት፣
- ልማት ላይ ትኩረት አድርገው ከሚሰሩ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ባንኮች ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን መሰረት አድርገው ሴቶችን ያማከሉ አገልግሎቶችን እንዲያጎለብቱ ማበረታታት፣
- ልማት ላይ ትኩረት አድርገው ከሚሰሩ ድርጅቶችና ከማይክሮ ፋይንስ ተቋማት ጋር በመሆን በሴቶች የሚመሩ የማይክሮ፣የጥቃቅንና መካከለኛ መጠን ያላቸውን ኢንተርፕራይዞች ያማከለ የፋይናንስ አገልግሎቶችን በማቅረብ ሴቶችን መደገፍ፡፡

የዚህ ተግባር ስኬት በተግባር 20 ትግበራ ላይ መሰረት ያደርጋል ፆታን መሰረት ያደረገ መረጃን በመሰብሰብ ሃላፊነት ያለባቸውና ዓለምአቀፍ ውሳኔ ሰጪ አካላትን ማሳወቅ፡፡

ተግባር 22፡ አገልግሎቶችን በበርካታ የቋንቋ አማራጮች ማቅረብን ማበረታታት

የዲጂታል ክፍያ አገልግሎት ሲቀረጽ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ተብለው የተለዩትን የህብረተሰብ ክፍሎች ምርጫዎችና ባህሪያት ከግምት ያስገባ መሆን እንዳለበት እ.ኤ.አ በ2019 Smart Campaign ያወጣው ሪፖርት በማስቀመጥ የተጠቃሚዎች ጥበቃ መርህ በማለትም "የዲጂታል ክፍያ አገልግሎቶች በደንበኛ መረጣ፣ ደንበኛን የአገልግሎት ተጠቃሚ በማድረግና አገልግሎቱን በመጠቀም ሂደት ምንም ዓይነት የሰው ጣልቃ ገብነት አለመኖሩ የአገልግሎቱ ንድፍ ሂደት የደንበኛን ጥበቃ በማረጋገጥ ረገድ ቁልፍ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት ተቆጣጣሪ ተቋማት የፋይናንስ አገልግሎት የተቀረጸበትን መንገድ (ዲዛይኑን) በመቆጣጠር ለተጠቃሚው የሚቀርበው የፋይናንስ አገልግሎት የደንበኞችን ፍላጎት የሚያሟላ መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡

የተለመደው የባንክ አገልግሎት በአሁን ሰዓት እየተሰጠ የሚገኘው በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ነው፡፡ ነገርግን በኢትዮጵያ ከ83 በላይ ቋንቋዎች የሚነገሩ ሲሆን ከ200 በላይ ዘዬዎች አሉ (Ethiopian Treasures 2020)፡፡ የሞባይል ዋሌት አገልግሎት አቅራቢዎች ተጨማሪ የአገልግሎት መስጫ ቋንቋዎችን በማካተት ላይ ይገኛሉ፡፡ በበርካታ ቋንቋዎች አገልግሎቱን ማቅረብን ማበረታታት የፋይናንስ አካታችነት አንዱ እርምጃ ነው፡፡ ሌሎች በርካታ ቋንቋ በሚነገርባቸው አገራት ኢኮኖሚ ለምሳሌ በህንድ የሚታየውም ይሄው ነው፡፡ በህንድ በኦፊሴል የሚነገሩ 22 ቋንቋዎች አሉ፡፡ እ.ኤ.አ በ2017 በህንድ የሚገኝ አንድ ትልቅ የግል ባንክ በ11 ቋንቋዎችና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰራ የሞባይል መተግበሪያ በገጠር ለሚገኙ ደንበኞቹ በስራ ላይ አውሏል፡፡ በተመሳሳይ ወቅት የህንድ መንግስት Bharat Interface for Money (BHIM) የተሰኘ በ9 የህንድ ቋንቋዎችና በእንግሊዝኛ ቋንቋ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችል የሞባይል መተግበሪያ አስተዋውቋል፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክረ-ሃሳቦች

- ከፌዴራልና ከክልል መንግስታት አስተዳደር ጋር በመተባበር ቅድሚያ አገልግሎት የሚሰጥባቸውን ክልሎችና ቋንቋዎች መለየት፣
- ከፋይናንስ አግልግሎት አቅራቢዎች ጋር በመተባበር በበርካታ ቋንቋዎች አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ይዘት እንደ ክልሎች ተጨባጭ ሁኔታ ማዘጋጀት፡፡

ለ2.3. ስትራቴጂያዊ ምሰሶ 3፡ ጠንካራና ወጥ የሆነ የሕግ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ መገንባት

መነሻና ቁልፍ ተግዳሮቶች

አዲሱ የዲጂታል ከባቢ ሁኔታ በኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ያልነበረ አዲስ የህግ ድንጋጌ ማዕቀፎች ይዞ መጥቷል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ወጥነተ ያለዉ፤ ሁሉን አቀፍና የተሟላ የህግ ድንጋጌ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት ሊመጡ የሚችሉ የገበያ ለዉጦችን ለማስተናገድ ቁርጠኛ ነዉ፡፡ የልማት አጋሮች ከ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር የፋይናንስ ዘርፍን ለማዘመንና ግርታዎችን በማስወገድ በፋይናንስ ዘርፍ ሪፎርም ሂደት ረገድ መንግስትን በመደገፍ ላይ ይገኛሉ (World Bank Group 2020a) ፡፡

በመሆኑም የቴክኖሎጂ ማደግን ተከትሎ ዲጂታል ክፍያ ስነምህዳሩ የሚያካልላቸውን አካባቢዎች በማስፋት አዳዲስ ተዋናዮችን፣ የአገልግሎት አይነቶችን እንዲካተቱ አድርጓል፡፡ በዚህ አግባብ

የደንበኞች/ሸማቾች/ ጥበቃ ድንጋጌዎችና የህግ ማዕቀፎች ዋና መሰረት መሆኑ በሁሉም አካላት ዘንድ እውቅና አግኝቷል፡፡ ዲጂታል የክፍያ ሥርዓት በተሳካ ሁኔታ መጠቀም እንዲቻል በአውቀት ላይ የተመሰረተ የህግ ድንጋጌ ሪፎረም በማድረግ በሚለዋወጥ ሥርዓት ውስጥ አብሮ መጓዝ እንዲቻል ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ይህም የደንበኞችን አመኔታና መተማመንን በማጎልበት ለዲጂታል ክፍያ ተዋናዮች የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

"የህግ ድንጋጌ ማዕቀፎች ለዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ማዕከላዊ ምሰሶ ሊሆኑ ይገባል"

በስትራቴጂዉ ዝግጅት ወቅት ከባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የተወሰደ

ይህን በማወቅ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሻለ የህግ ከባቢን ለመፍጠር የሚያስችሉ አራት አዳዲስ መመሪያዎችን በቅርቡ አውጥቷል፡፡ እነኚህ አራት መመሪያዎች በአነስተኛ ወጪ፣ አዳዲስ ተዋናዮችን እንደ ቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች እና ፊንቴኮችን በማሳተፍ የፋይናንስ አገልግሎት እንዲጎለብት ማድረግ ያስችላሉ፡፡

- የክፍያ መሳሪያ አቅራቢዎች/አውጪዎች/ መመሪያ፡ ይህ መመሪያ ባንክ ያልሆኑ የፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢዎች ፍቃድ እንዲያገኙ ለማስቻል እ፣ኤ.አ. በሚያዚያ 1፣2020 ሲወጣ፣ በተጨማሪም መመሪያው ሞባይል ኔትወርክ ኦፕሬተሮች፣ ፊንቴኮችና ሌሎችንም ያካትታል፡፡ መመሪያዉ እርከንን/tiered/ መሰረት ያደረገ ደንበኛህን እወቅ አሰራር በመደንገግ የፋይናንስ አገልግሎቶች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ለማስቻል እንዲሁም ውስን ጥቅም ያላቸዉ የክፍያ መሳሪያ የሚያቀርቡ አካላትን ፍቃድ መስጠትን ያጠቃልላል፡፡
- ወኪልን የመጠቀም መመሪያ፡ ይህ መመሪያ እ.ኤ.አ በሚያዚያ 1፣2020 የወጣ ሲሆን ወኪልን ለመጠቀምና ለማስተዳደር ሠፊ ምህዳር የፈጠረ ነው፡፡ መመሪያው ባንኮችና ባንክ ያልሆኑ ማለትም በብሔራዊ ባንክ የክፍያ መሳሪያዎች አውጪዎች መመሪያ መሰረት ፍቃድ የተሰጣቸው በሙሉ የፋይናንስ አገልግሎት ወኪል እዲኖራቸዉና እንዲያስተዳድሩ ይፈቅዳል፡ ፡ በተጨማሪም ይህ መመሪያ የፋይናንስ ተቋማት የወኪል አስተዳደራቸውንና የገበያ አገልግሎታቸውን ለሦስተኛ ወገን እንዲያስተላልፉና እንዲያሰሩ ይፈቅዳል፡፡
- የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተሮች መመሪያ፡ ባንክ ያልሆኑ ተቋማት የክፍያ ኦፕሬተር ስርዓትን እንዲቀላቀሉ ያስችላል፡፡ ይህም የክፍያ ጌትወይ ልማት የገንዘብ መክፈያ ማሽን እና የክፍያ ነቁጥ አሰራርን፣ ክልላዊ ስዊቾች አገልግሎት ልማት እዲሁም የኦንላይን ክፍያ ስነ ምህዳር የሚጠቀሱ ናቸው፡፡
- የደንበኞች ጥበቃ መመሪያ፡ ይህ መመሪያ የደንበኞችን ጥበቃ በፋይናንስ ሴክተር አውድ አግባብ የተዘጋጀ ነው፡፡

እነዚህ መመሪያዎች የፋይናንስ ሴክተሩ የአገልግሎት መዳረሻዎችን በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምር ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ ይጠበቃል፡፡ መመሪያዎቹ የታለመላቸውን አላማ ማሳካታቸውን ለማረጋገጥ የብሔራዊ ባንክ በዲጅታል ከባቢ ሁኔታ አተገባበር በቅርበት ለመከታተል የሚያስችል አሰራር መተግበር ይጠበቅበታል፡፡

ጠንካራ የደንበኞች ጥበቃ ህጎች መኖር የደንበኞችን እምነት ለማሳደግ ደህንነቱ የተጠበቀ አስተማማኝ እና ግልጽነትን የተላበሰ እንዲሆን ለማድረግ ያግዛል፡፡ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የደንበኞችን የግል መረጃ ሰፊ ትርጉም ባለው መልኩ የሚጠብቅ አንድ ህግ ብቻ ነው ያለው፡፡ ይህ ህግ ምንም እንኳን የደንበኞችን የግል መረጃ ለመጠበቅ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ያስቀመጠ ቢሆንም፣ የንግድ ድርጅቶች አሁንም መደበኛ ባልሆነ መንገድ ለሌላ ወገን መረጃዎችን ያስተላልፋሉ በዚህም ተጠያቂነት የለባቸውም፡፡ የደንበኞችን የግል መረጃ መጠበቅ እጅግ በጣም ጠቃሚ የሚሆነው በዲጅታል ክፍያ ጥቅም ላይ የሚውሉ የግል መረጃዎች ከብዛት፣ ከፍጥነት እና ከአይነት አንፃር ሲሆን ይህ መረጃ ደንበኞች የተለያዩ የአገልግሎት አይነቶችን ማግኘት እንዲችሉ እድል ይሰጣል(Better Than Cash Alliance 2016):: ደንበኞችን ከመጠበቅ አንጻር ተጨማሪ እርምጃዎችን ለመውሰድ የተቻለ ሲሆን ይህም በሁሉም ነጋዴዎችና የንግድ ተቋማት ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን በማድረግ ደንበኞች ሚዛናዊ በሆነ አግባብ

ለማስተናገድ ያስችላል፡፡ ይህም ሆኖ ግን የፋይናንስ ተቋማትን በሚመለከት ያለው ህግ፣ በተለይም ስጋትን ለመቀነስ የሚወሰዱ እርምጃዎች በባንኮች የሚያዙ የግል የፋይናንስ ጉዳዮችን በሚመለከት ጉድለቶች አሉበት፡፡ የግጭቶች መፍቻና ግጭቶችን የሚፈታ የተለየ አደረጃጀት በፋይናንስ ሴክተሩ አለመኖሩ በመደበኛው የፋይናንስ ሴክተር ውስጥ ያለውን የደንበኞች አመኔታ ይቀንሳል፡፡

ብሔራዊ ባንክና ሌሎች ተቆጣጣሪ ተቋማት አዲሱን የክፍያ ከባቢ ሁኔታ በቀጣይነት ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፎች ለማሻሻል ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ጸድቀው ወደ ትግበራ ከገቡት አራት መመሪያዎች በተጨማሪ አንድ መመሪያ በልማት አጋሮች አጋዥነት በክለሳና በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

- የባንክ ሴክተር ሳይበር ደህንነት መመሪያ፡ በባንክ ስራ አዋጅ (ኢ.ብባ እ.ኤ.አ2008) መሰረት ፍቃድ በተሰጣቸው ተቋማት ሊኖር የሚገባውን የሳይበር ደህንነት ማዕቀፍ ለመፍጠር በሚያስችል አግባብ እየተዘጋጀ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በረቂቅ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የገንዘብ ሚኒስቴር በክፍያ መሳሪያዎች አቅራቢዎች መመሪያ መሰረት የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ፍቃድ እንደገና በማደራጀት የሞባይል ኔትወርክ ኦፕሬተሮች በዲጂታል ክፍያ ከባቢ ሁኔታ ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና ለመወሰን እየተሰራ ነዉ፡፡

አለም አቀፍ መልካም ተሞክሮዎች

ዓለም አቀፍ የህግ ድንጋጌዎች ከአዲሱ የክፍያ ከባቢ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም አዳዲስ ተዋናዮችን በተገቢው መንገድ ለማካተት በሚያስችል አግባብ እየተቀየሩ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁለት መርሆዎች ታይተዋል፤

- አንድ ወጥ መመሪያ ለሁሉም ተዋናዮች አያገለግልም (one size does not fit all)፣ ውጤታማ የህግ ድንጋጌና ማዕቀፍ ሪፎርም ሂደቶች እንደየአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ሊታዩ ይገባል፡፡ በመሆኑም የሌሎች አገራት መልካም ተሞክሮ ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሊጣጣሙ ይገባል፡፡ የፋይናንስ ተቋማት ያልሆኑ ተዋናዮች (ቴሌኮሞች፤ፊንቴኮች) የተለያየ የተሣትፎ ደረጃ እንዲኖራቸዉ የሚያስችሉ አካሄዶች እስካሁን ዉጤታማ ነበሩ፡፡
- ከለውጥ ጋር መተግበር (adaption through change)፣ ውጤታማ የህግ ማዕቀፍ ሪፎርም ሂደቶች ለሚተገበሩ ለውጦች የገቢያውን ምላሽ መሰረት አድርገው የመቀየር አቅም እንዲኖራቸዉ ማድረግ፡፡

አንድ ወጥ መመሪያ ለሁሉም ተዋናዮች አያገለግልም (one size does not fit all)

በዓለም ደረጃ ለተለያዩ የዲጅታል ክፍያ ተሣታፊዎች የተለያየ አይነት አሰራሮች አሉ፡፡ አገራት የፋይናንስ ተቋማት፤ ሞባይል ኔትወርክ ኦፕሬተሮች እና ፊንቴኮች ለሚኖራቸው ሚና የተለያየ አይነት አቀራረብ ይከተላሉ፡፡ በዚህ የተለያየ የተዋናዮች ሚና በመነሳት በተለያየ መንገድ አሰራራቸውን ይመድባሉ፡፡ ከስር በምስል 14 እደሚታየው ምንም እንኳን በርካታ አሰራሮች ቢኖሩም ሦስት ዋና ዋና መስኮች አሉት፡፡ (i) ቴሊኮሙኒከሽን ኦፕሬተሮች መር (ii)የፋይናንስ ተቋማት መር (iii) ስነምህዳሮችና ሌሎች አሰራሮች መር ይገኛሉ፡፡

ምስል 14 የዲጂታል ክፍያ ሞዴሎች

ምንጭ: Better Than Cash Alliance; Bill & Melinda Gates Foundation (2009)’ Boston Consulting Group



በያንዳንዱ አሰራር የሚገኙ የደጂታል ክፍያን የመተግበር ውጤታማ ምሳሌዎች፣

1. ቴሌኮም መር፡ ኬንያ[52] አንደ ትልቅ የስኬት ሁኔታ የምትወሰድበት በተመሰረተ በሰባተኛዉ ወር 1 ሚሊዮን ተጠቃሚዎች ማግኘት የቻለውና በአሁኑ ሰዓት 73 ከመቶ የአገሪቱ ህዝብ የሚገለገልበት የኬኒያ የክፍያ ስርዓት ነው፡፡ በኬኒያ የሞባይል ክፍያ ከአገሪቱ ጠቅላላ ብሔራዊ ምርት 87 በመቶ ጋር እኩል ነው(Demirgüç-Kunt et al. 2018; Safaricom; Vodafone)::
2. ፋይናንስ ተቋማት መር፡ እንደ ዩናይትድ ኪንግደም፣ የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ የበለፀጉ አገራት ያደገ የፋይናንስ ሴክተራቸውን በመጠቀም ዲጅታል ክፍያ ሽፋናቸውን እንደ ቅደም ተከተላቸው 96 በመቶ እና 84 በመቶ ማድረስ ችለዋል፡፡ እዚህ ላይ የሞባይል ገንዘብ ተደራሽነት በነዚህ አገራት 2 በመቶ እና 21 በመቶ እንደ ቅደም ተከተላቸው በጣም ዝቅተኛ ነው(Demirgüç-Kunt et al. 2018; World Bank Group 2020f)፡
3. መሰረተ ልማት መር /ፊንቴክ መር/፡ በቻይና እ.ኤ አ. በ2017 ላይ 890 ሚሊዮን የሚገመቱ የሞባይል ክፍያ አገልግሎት ተጠቃሚዎች 17 ትሪሊዮን የአሜሪካ ዶላር አካባቢ የሚሆን አጠቃላይ ግብይት ፈጽመዋል(cgap 2019)፡፡ በቻይና ትላልቅ የቴክኖሎጂ ድርጅቶች እንደ አሊፔይ እና ዊቻት ፔይ የመሣሠሉት ከአገሪቱ የክፍያ ከባቢ ሁኔታ ተዋናዮች ጋር በመተባበር ይህንን አድርገዋል፡፡

ይህ የተለየየ አቀራረብ የሚያመላክተው የህግ ድንጋጌና ማዕቀፍ ሪፎርም ሥራዎች በክፍያ ከባቢ ሁኔታው አዳዲስ ተዋናዮችን በማካተት ከአገር ውስጥ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ተገናዝበው

ሊሠሩ ይገባል፡፡ የሪፎርም ሥራዎች ሙሉ ለሙሉ ከመተግበራቸው አስቀድሞ የመሠረተ ልማት ተደራሽነት ፤የፋይናንስና ቴሌኮሚኒኬሽን ሴክተሮች ወቅታዊ ሁኔታ፤ ያሉ የህግ ማዕቀፎች፤ ቅድሚያ የሚሠጣቸው አገራዊ ጉዳዮች ግምት ውስጥ ሊገቡ ያስፈልጋል፡፡ በኢትዮጵያ የሥራ ዕድል ፈጠራ እኩል ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን መሳብ የህግ ድንጋጌና ማዕቀፍ ሪፎረሙን የሚመራባቸው መርሆዎች ናቸው፡፡

ከለውጥ ጋር መተግበር

የህግ ማዕቀፍ ሪፎርም ቀጣይነት ያለው ሂደት ነው፡፡ ስኬታማ የክፍያ ከባቢ ሁኔታ የሚያብበው የተቆጣጣሪ አካላትና የቁጥጥር መንገድ ቀጣይነት ባለው መልኩ የህግ ማዕቀፎችን ለማጣጣም አቅም ሲኖራቸው ነው።

በቀጠናው የተለዩ የስኬት ተሞክሮዎች ታይተዋል። ጋና እ.ኤ.አ በ2008 ሪፎርም በማካሄድ ክፍያዎችን በሞባይል ገንዘብ አማካኝነት እንዲፈጸሙ ፈቅዳለች፡፡ ሆኖም ግን በዚህ የሞባይል ገንዘብ ሥነምህዳር የሚጠቀሙት በባንኮች ሲሆን፡ መሠረተ ልማቱን በባለቤትነት የያዙት የሞባይል ኔትዎርክ ኦፕሬተሮች ነበሩ፡፡ እነዚህ የሞባይል ኔትዎርክ ኦፕሬተሮች አገልግሎቱን እራሳቸው ስለማይሰጡ ተደራሽነቱን ለማስፋፋትም ሆነ ለማሳደግ የሚያበረታታቸው ነገር አልነበረም፡፡ ይህ ሁኔታ ውጤታማ ባልሆነ የውድድር ሥርዓት ወኪልን በብቸኝነት የመያዝ ጋር ተደማምሮ የሪፎርሙ ውጤታማነት ላይ ተጽዕኖ አሳይቷል፡፡ እ.ኤ.አ በ2015 ይህ የህግ ማዕቀፍ ተከልሶ የሞባይል ኔትዎርክ ኦፕሬተሮች የሞባይል ገንዘብ መተግበሪያቸውን በራሳቸው ይዘው እንዲያስተዳድሩ በመፍቀዱ የበለጠ በዘርፉ መዋዕለ ነዋይ እንዲያፈሱ ፈጠራ እንዲያጎለብቱ ወኪሎችን እንዲቀያይሩ አስችሏል(Mattern 2018; Ozyurt 2019)፡፡ ወኪሎች በብቸኝነት እንዲሠማሩ የሚያዘው ህግ በመቅረቱ አንድ ወኪል ለተለያዩ አካላት ወኪል እንዲሆን ተደራሽነትን ማስፋት በማስቻሉ የሞባይል ገንዘብ ሂሳቦች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምር አድርጓል፡፡

ስትራቴጂክ እርምጃዎች

ውጤታማ የህግ ድንጋጌና የቁጥጥር ማዕቀፍ ለመፍጠር እንዲያግዝ ባለ ሁለት ምድብ ስትራቴጂያዊ ተግባራት ተዘጋጅቷል፡፡ በሁለቱ ምድቦች ውስጥ ስድስት ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ የስትራቴጂ ተግባራት ተለይተዋል፡፡ ሁለቱ የስተራቴጂ ምድቦች፤

- ለአዲሱ የክፍያ ከባቢ ሁኔታ በሚመጥን አግባብ የቁጥጥር አቅምን መገንባት፣
- የህግ ድንጋጌዎችንና ማዕቀፎችን ሪፎርም በማድረግ አዳዲስ ተዋናዮችና የአገልግሎት መስጫ መንገዶችን መፍቀድ፡፡

እነዚህ በዝርዝር ተግባራት የተደገፉ ናቸው፦

የቁጥጥር/የህግ/ አቅም፡

ተግባር 23፡ የህግ ድንጋጌዎችን ማጠናከርና የቁጥጥር አቅምን ማጎልበት፡፡

የህግ ድንጋጌዎችና ማዕቀፎች ሪፎርም

ተግባር 24: አዲሱን የወኪል አጠቃቀም መመሪያን አተገባበር መከታተል፡፡

ተግባር 25፡ የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ባንክ ያልሆኑ የፋይናንስ ተቋማት ተሳትፎን መከታተል፡፡

ተግባር 26፡ አዲሱን የደንበኛህን እወቅ ህግ ተግባራዊነት መከታተል፡፡

ተግባር 27፡ የፋይናንስ ደንበኞችን ጥበቃ ማጠናከር፡፡

ተግባር 28፡ የሳይበር ደህንነትን ማጠናከር፡፡

ተግባር 29፡ ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኞችን በክፍያ ማረጋገጫነት መቀበል የሚያስችል ህግ ማውጣት

ለ2.3.1 የቁጥጥር አቅም

ዲጂታል ክፍያ በፍጥነት በማደግ ላይ የሚገኝ ዘርፍ ሲሆን የሚለዋወጡ ግንዛቤዎች፣ ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም ተዋናዮች አሉበት፡፡ ቀጣይነት ያለው መዋዕለንዋይ ይፈልጋል፡፡ በዚህም የኢትዮጵያ የክፍያ ከባቢ ሁኔታ ከልማዳዊ መሰናክሎች በላይ እንዲያድግና ኢትዮጵያውያን ባግባቡ የተረዱትና ጥበቃ ያላቸው እንዲሆኑ ለማስቻል ያግዛል፡፡

ተግባር 23፡ የህግ ድንጋጌዎችን ማጠናከርና የቁጥጥር አቅምን ማጎልበት

የዲጂታል ክፍያ ከባቢ ሁኔታ በፍጥነት የሚያድግና የሚለዋወጥ በመሆኑ ሥጋትን መሠረት ያደረገ ተለዋዋጭ አቀራረብ መጠቀም ውጤታማ መንገድ ነው፡፡ ይህን ለመፈጸም ከልማዳዊ ህግን ብቻ የተከተለ አቀራረብ የተሻለ ከፍተኛ የሆነ እውቀትና አቅም ይፈልጋል፡፡ በውይይትና ምክክር ላይ የተመሰረተ የቁጥጥር አሰራር ለክፍያ ሥርዓት እድገት ወሣኝ ነዉ፡፡ ለዚህም ተጨማሪ ክህሎት ሊኖር ይገባል፡፡

በተጨማሪም ዲጂታል የክፍያ አገልግሎቶች በከፍተኛ ሁኔታ ውስብስብና በስጋት የተሞሉ እየሆኑ መጥተዋል፡፡ በመሆኑም የተቆጣጣሪዎች አቅም በቀጣይነት የሚያድግበትን መንገድና ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ እነኚህ ተጨማሪ ክህሎቶች የስጋት ስራ አመራርና መመሪያዎች በክፍያ ስርዓቱ ውስጥ ለመገንባት ያግዛሉ፡፡

ከዚህ ቀደም የክፍያ ስርዓት ልማትና ቁጥጥር አገልግሎትን ለማሳደግ የተከናወኑ ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ብሔራዊ ባንክ የበለጠ ሊሻሻሉና ሊያድጉ የሚችሉበት ዕድሎች መኖራቸውን በመረዳት በአለም ባንክ የቴክኒክ ድጋፎች ፕሮግራም በመታገዝ እየሰራ ይገኛል፡፡ በሥራ ላይ ያሉ የህግ ማዕቀፎችን መከለስ፣ የህግ ማዕቀፍን ወቅታዊ ከማድረግና ከማሻሻል አንጻር የቀረቡ የውሳኔ ሃሳቦች፣ የብሔራዊ ባንክ የክፍያ ስርዓት ሰራተኞችን አቅም ከመገንባት፣ የክፍያ ስርዓት ልማትና ቁጥጥር የስራ ክፍል የአሰራር ስርዓት /procedure/ እንዲሁም ከክፍያ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚቀርቡ ሪፖርቶችን/off-site reports/እና ወደ ተቋማቱ በመሄድ የሚሠሩ የክትትል ሥራዎች/on-site/ ስራዎችን በክፍያ ስርዓት ልማትና ቁጥጥርን ከማሣደግ አንፃር ሊተኮርባቸዉ ከሚገቡ ጉዳዮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸዉ የዉሳኔ ሃሳቦች

- የክፍያ ስርዓት ክትትል የቴክኒክ ድጋፍ ፕሮግራም ከአለም ባንክ ጋር በመተባበርና በመተግበር ብሔራዊ የክፍያ ስርዓት ክትትል ማዕቀፍን ማሻሻል፡፡

ለ2.3.2 ሪፎርም

የህግ ድንጋጌዎችና ማዕቀፎችን ሪፎርም ማድረግና ዲጂታል ክፍያን ሙሉ አቅም ለመጠቀም ከባቢ ሁኔታው ቀደም ሲል ከተቀመጠለት ገደብ በበለጠ እንዲስፋፋ ማስቻል፡፡ እነዚህም:-

- በወኪሎች ላይ የተጣሉ እገዳዎችን በመቀነስ የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታዎች እንዲኖሩ ማድረግ፣
- በሞባይል ገንዘብ አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ ባንክ ያልሆኑ ተቋማትን የተሣትፎ ሁኔታ በመከለስ አዳዲስ ተዋናዮች እንዲካተቱ መፍቀድ፣
- የደንበኛህን እወቅ መስፈርቶችን በመከለስ አካታችነትን ማሳደግ፡፡

ነገር ግን ከአለምአቀፋዊ ተሞክሮዎች እንደታየው በድንገትና በአንድ ጊዜ የሚደረጉ ለውጦች በደንበኞች ላይ አደጋን ሊጋርጡ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም የህግ ድንጋጌ ሪፎርም ሥራዎች በዚህ ረገድ ጥምር ሚና ሊጫወቱ ይገባል፡፡ የደንበኞችን ጥበቃ ማስቻል የግል መረጃን እና ገንዘብ በቂ ጥበቃ እንዲኖር ማስቻል፡፡ በዚህም የደንበኞች ጥበቃ ፣ የሳይበር ደህንነት ህግን በማሻሻል በሃላፊነት የሚከወን አሠራር እንዲኖር ማስቻል ያስፈልጋል፡፡

ተግባር 24፡አዲሱን የወኪል አጠቃቀም መመሪያን አተገባበር መከታተል

በአዲሱ ከባቢ ሁኔታ የወኪል ስርጭቱ፣ የፋይናንስ ተደራሽነት ለማሳደግ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ አዲሱ የወኪል አጠቃቀም መመሪያ ቀደም ሲል የነበሩ ገደቦችን አንድ ወኪል ለተለያዩ ተቋማት እንዲሰራ በመፍቀድ ባንክ ያልሆኑ የፋይናንስ አገልግሎት ሰጪዎች ወኪሎችን እንዲያስፋፉ በማስቻል ባለ እርከን የወኪል መዋቅር (ዋና ወኪልና ንዑስ ወኪል) የመሳሰሉትን ጉዳዮች ፈቅዷል፡፡ ሆኖም ግን ከዋናው የኢትዮጵያ የፋይናንስ ማዕቀፍ የተነሳ የውጪ ተዋናዮች (ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ) ላይ የተቀመጠዉ ገደብ ባለበት የሚቀጥል ይሆናል፡፡

አዲሱ የወኪል መጠቀም መመሪያ ትግበራና አፈጻጸም ላይ ጥብቅ ክትትልና ግምገማ በማድረግ የወኪል ስርዓቱን፣ የፋይናንስ አገልግሎቶችና ተደራሽነትን ማሳደጉን ለማረጋገጥ ጥረት ይደረጋል፡፡ ብሔራዊ ባንክ በቀጣይነት አዲሱ መመሪያ ያመጣውን ለውጥ በመገምገም በሂደቱ ያጋጠሙ ችግሮችን ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር መፍታት፣ የወኪል ስርዓቶችን በማጎልበት የደንበኞችን ፍላጎት ከማርካት አንጻር ድንጋጌዎችን መቃኘት ያስፈልጋል፡፡

ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸዉ የዉሳኔ ሃሳቦች

- አዲሱን የወኪል መጠቀም መመሪያ ትግበራ ተከታታይ ግምገማና ክትትል በማድረግ የወኪል ስርዓት ተደራሽነትን መጨመር፣
- አንድ ወኪል ከተለያዩ አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር እንዲሰራ ለማስቻል የወጣውን ድንጋጌ በቅርበት በመከታተል ውጤታማ ውስጣዊ የአወሳሰን ሂደቶችን እና የክትትል አፈጻጸምን መተግበር፣
- አስፈላጊ ከሆነ ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በመተባበር የትግበራ ተግዳሮቶችን መፍታትና መመሪያዎችን መከለስ፣

የዚህ ተግባር ስኬት በተግባር 3 ላይ የተመሠረተ ነው የወኪል የንግድ ሁኔታን መከለስ፣

ተግባር 25፡ የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ባንክ ያልሆኑ የፋይናንስ ተቋማት ተሳትፎን መከታተል

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የኢትዮጵያ ዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት የህግ ማዕቀፍ፣ ባንክ መር ስርዓትን የተከተለ ነበረ፡፡ በዚህም ባንኮችና አነስተኛ የፋናንስ ተቋማት ብቻ ተቀማጭ ገንዘብ የመያዝ፤ የክፍያ አገልግሎት የመስጠት እንዲሁም የወኪል ስርጭት እንዲኖራቸዉ የሚፈቅድ ነበር፡፡ ሞባይል ኔትዎርክ ኦፕሬተሮችና ፊንቴኮች በተናጠል (በራሳቸዉ) የፋይናንስ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚፈቅድ አልነበረም፡፡ ይህ ሁኔታ በሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ከፍተኛ ቁጥር እዲኖር ያስቻለ ቢሆንም በአንፃሩ ተደራሽነቱ የአካታችነትን እድል የሚገድብ እንዲሁም የሥራ ዕድል ፈጠራን ከመጨመር አንጻር ውስንነቶች ነበሩት፡፡

በየኢትዮጵያ ወቅታዊና ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ታሣቢ በማድረግ የዚህ ሴክተር ቁልፍ ተዋናዮች የዚህን አሰራር /model/ በአስቸኳይ መቀየርና የሞባይል ኔትዎርክ ኦፕሬተሮችና ፊንቴኮች ተሳትፎን ማካተት አስፈላጊነት ተረድተዋል፡፡ የክፍያ መሣሪያዎች አቅራቢዎች መመሪያ መውጣት ይህንን ፍላጎት በማሟላት ሞባይል ኔትዎርክ ኦፕሬተሮች እና ፊንቴኮች የክፍያ መሣሪያዎች አቅራቢ በመሆን እንዲሰሩ ይፈቅዳል፡፡ ለዚህ ለውጥ በቁልፍ ምክኒያትነት የሚጠቀሰው አገራዊ አካታችና የብልጽግና ኢኮኖሚ ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት በማገዝ አገር በቀል ኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራምን ለማሳካት መንግስት የሚያደርገውን ጥረት ማገዝ ነው፡፡ ምስል 15 ሦስቱ የኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ አቅርቦት አሰራሮች ከአገራቀፍ ታሳቢዎች ጋር ያላቸዉ ስምምነት ያሳያል፡፡

ምስል 15: እያንዳነዱ ሞዴል ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ሁኔታ ጋር ያለዉ ቁርኝነት

ሀገራዊ እሳቤዎች	ቴሌኮም መር	ፋይናንስ ተቀም መር	መተግበሪያ መር
የተስተካከለ የፋይናንስ አካታችነት	✓	○	✓
ትረጉም ያለዉ የስራ ዕድል ፈጠራ	✓	○	○
ከቴልክም ሪፎርም የሚገኘዉን የዉጪ ምንዛሬ መጨመር*	✓	×	○
በፋይናንስ አገልግሎት ላይ የዉጪ ዜጎችን ተሳትፎ ያለመገደብ	○	✓	✓
በቴሌኮም ዘርፍ ያለዉን ዉድድር መጨመር	✓	×	○
በፋይናንስ ዘርፍ ያለዉን ዉድድር ማጎልበት	○	✓	○
ፈጣን አዘገጃጀት	○	✓	×
		በፊት የነበር የኢተዮጵያ አሰራር	

* ቴሌኮምን ወደ ግል በማዞርና ሁለት የቴሌኮም ፍቃድን በመሸጥ የሚገኝ ገቢ

ምንጭ: BTCA; BCG; BMGF

በቁጥር ያልታገዘ ግምገማ: ✓ ሙሉ ቁርኝነት ○ ትንሽ ቁርኝነት × የተገደበ ቁርኝነት

አዲሱ ቴሌኮም መር አሰራር በምስል 15 እደተቀመጠው ባንኮችና አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት፤ ሞባይል ኔትዎርክ ኦፕሬተሮች እና ፊንቴኮች በአዲሱ የክፍያ መሳሪዎች አቅራቢዎች መመሪያ መሰረት ኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ አቅርቦት ፍቃድ ያገኛሉ፡፡ እነዚህ ተቋማት በተጨማሪም በወኪል መጠቀም መመሪያ መሠረት የወኪል ኔትዎርክ እንዲኖራቸዉ ፍቃድ ይሰጣል፡፡ ነገር ግን ባንኮች እንደተቀማጭ ገንዘብ ያዥ በመሆን ያገለግላሉ ፤ ሞባይል ኔትዎርክ ኦፕሬተሮች የዋና ቴሌኮምኒኬሽን መሠረተ ልማት አቅራቢ መሆናቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በኢኮኖሚው ውስጥ የዲጂታል ክፍያን የበለጠ ለመቀበልና ተወዳዳሪና በትብብር የሚሰሩ እንዲሁም፣ የተለያዩ ተዋናዮች አንዳቸው የሌላውን ጥንካሬ እንዲጠቀሙ የሚያስችል ከባቢን ለመፍጠር ያግዛል፡፡

አሁን የተደረገው የህግ ድንጋጌዎች ክለሳ የውጪ ዜጎች ላይ የነበረውን ገደብ አላነሣም፡፡ አሁን ስራ ላይ ባለው ብሔራዊ አዋጅ[54] ምክንያት አገር በቀል ሞባይል ኔትዎርክ ኦፕሬተሮች እና ፊንቴኮች ብቻ[55] የክፍያ መሳሪያዎች ለማቅረብ ፍቃድ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

በቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ ሪፎርም ትግበራ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ኢትዮ ቴሌኮም በከፊል ወደ ግል ይዞታ ለማዛወርና ሁለት አዳዲስ የቴሌኮም ኦፕሬተሮች ፍቃድ የሚሰጠው ለውጥ አልሚዎች የመሆን እድል አለው፡፡ ለዚህም ብሔራዊ ባንክና ገንዘብ ሚኒሰቴር በስራ ላይ ያሉትን መመሪያዎች በመከለስ በከፊል ወይንም ሙሉ በሙሉ በዉጪ የግል ወይም የመንግስት ባለሀብቶች የተያዙ ተቋማት የክፍያ መሣሪያዎች አቅርቦት ፍቃድ መስጠት የሚቻልበትን አስመልክቶ ስትራቴጂዎችን ለመቅረጽ እቅድ ተይዟል፡፡

የሞባይል ገንዘብ አፈጻጸምና ትግበራን ለማረጋገጥ በዚህም ሚዛናዊ የሞባይል ገንዘብ ከባቢ ሁኔታና የገበያ ስርዓት በማረጋገጥ የዲጅታል ክፍያን ተደራሽነት ለማሳደግ ጥብቅ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች ይሰራሉ፡፡ የህግ ድንጋጌዎችን የመከለስ ሥራዎች በመካከለኛ ጊዜ በማከናወን በውጭ ባለሃብነት የተያዙ የንግድ ድርጅቶች በዚህ አገልግሎት እንዲሣተፉ ለማስቻል ታሥቧል፡፡

ቅድሚያ ትኩረት የሚሠጣቸዉ የዉሣኔ ሃሳቦች

- ከገንዘብ ሚኒሰቴርና ከቴሌኮሙኒኬሽን ባለስልጣን ጋር በመተባበር ሞባይል ኔትዎርክ አፕሬተሮች እና ፊንቴኮች በሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ላይ የሚያደርጉትን ተሳትፎ መከታተልና መገምገም፣
- ከገንዘብ ሚኒስቴርና ከቴሌኮሚኒኬሽን ባለስልጣን ጋር በመተባበር በትግበራ ወቅት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን መፍታት (ሲያስፈልግ)፣
- ከገንዘብ ሚኒሰቴርና ከቴሌኮሚኒኬሽን ባለስልጣን ጋር በመተባበር መመሪያዎችን ከገበያ ፍላጎትና ከኤሌክተሮኒክስ ገንዘብ አገልግሎት የውጭ የንግድ ተቋማትን ከማስፋት አንጻር መከለስና ማጣጣም፣

የዚህ ተግባር ስኬት በተግባር 30 ላይ የተመሰረተ ነዉ፡ የፊንቴኮች ተግባርና ሃላፊነትን ግልጽ ማድረግ፡፡

ተግባር 26፡ አዲሱን የደንበኛህን እወቅ ህግ ተግባራዊነት መከታተል

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የባንክ ወይም የሞባይል ገንዘብ ሂሳብ ለመክፈት ህጋዊ መታወቂያ ወረቀት ማቅረብ ያስፈልግ ነበረ፡፡ ህጋዊ መታወቂያ የሌላቸው ኢትዮጵያውያን ይህንን አገልግሎት ማግኘት አይችሉም፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ ተቋማት የመታወቂያ ኮፒን ማቅረብን እንደ ግዴታ ይጠይቃሉ፡፡ ይህም የፎቶ ኮፒ አገልግሎት በቅርበት ማግኘት ለማይችሉ ትልቅ እንቅፋት ይፈጥራል፡፡ የህጋዊ መታወቂያ ማቅረብ ግዴታ ከመኖሪያ አከባቢያቸው ርቀው ለሚገኙ ሴቶች በቀላሉ ማግኘት ስለማይችሉ ተጨማሪ ተግዳሮት ይሆንባቸዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ሁኔታ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ችግር ከመፍጠሩ ባሻገር በፋይናንስ አካታችነት ላይ የጾታ ልዩነትን የሚፈጥር ይሆናል፡፡

አዲሱ የክፍያ አቅራቢዎች መመሪያ በኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ሂሳቦች ባለ እርከን ደንበኛህን እወቅ አሰራርን በመፍቀድ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ተደራሽነት ለማሳደግ ይጠቅማል፡፡ መመሪያው የተለያየ ደረጃ ያላቸው የደንበኛን እወቅ በአነስተኛ የግብይት መጠን ተጠቃሚዎች እንዲሁም ሂሳብ ለመክፈት ቀላል መስፈርቶችን በማዘጋጀት በሂሳብ ገቢ የሚቀመጥ ገንዘብና ወጪ ማድረግ ላይ ገደቦችን ይጥላል፡፡ በዚህ መሰረት ደረጃ 1 ሂሳቦች (በጣም ቀላል የደንበኛህን እወቅ መስፈርት) መታወቂያ ሳይጠየቅ በሌላ መደበኛ መታወቂያ ባለው ሰው አስተዋዋቂነት ሊከፈቱ ይችላሉ፡፡ ተጨማሪ ባለ ዕርከን የባንክ አገልግሎቶችን ገደብ ያላቸው አገልግሎቶችንና የክፍያ መንገዶች ተጠቀሚነት ይጠቀሳሉ፡፡ የበለጠ ለማሳደግ ኤሌክትሮኒክስ የደንበኛን እወቅ መረጃዎችን፣ የዲጂታል ፊርማዎችን መቀበል ተደራሽነትን ለማሳደግና ከርቀት ሂሳብ በመክፈት በፋይናንስ አገልግሎቶችን ተደራሽነትን ቀላል ማድረግ ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን ይህንን ለመፈጸም የመሰረተ ልማቶች እድገት የተሟላ ሊሆን ይገባል፡፡

ባለ እርከን የደንበኛህን እወቅ ትግበራ ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ የፋይናንስ አካታችነትን፣ የዲጅታል ክፍያ ተጠቃሚነትን ማሳደግ እንዲቻል ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ የህግ ማዕቀፎቹ የታለመላቸውን ዓላማ ማሳካት መቻላቸውን ለማረጋገጥና የተሻሉ የደንበኛህን እወቅ እርምጃዎችን ለመውሰድ እንዲቻል የጊዜ ገደብ ለመወሰን ብሔራዊ ባንክ ተከታታይ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የህግ ማዕቀፎችን ማስተካከል አስፈላጊነትን ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡

ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸዉ የዉሳኔ ሃሳቦች

- ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የባለዕርከን የደንበኛህን ዕወቅ አሰራር ትግበራን ክትትልና ግምገማ ማድረግ፣
- ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ቀጣይነት ያለው የህግ ማዕቀፍና ድንጋጌዎችን የማሻሻል ሥራ በመሥራት ከሚለዋወጠው የክፍያ ከባቢ ሁኔታ ጋር ማጣጣም እና የተሻሻሉ የደንበኛህን እወቅ አሰራሮችን ማስጀመር፣

ይህን ተግባር ለማስፈጸም ከሠላም ሚኒስቴር ጋራ በቅንጅት መስራት ያስፈልጋል፡፡ ብሔራዊ ባንክ የብሔራዊ ዜግነት መታወቂያ ፕሮግራምን በሚከታተለው አብይ ኮሚቴ ውስጥ የሚሳተፍ ሲሆን በቀረጻና ትግበራ ሂደቱ ጉልህ ተሳትፎ ያደርጋል፡፡ ይህ ፕሮግራም ሙሉ ለሙሉ በሀገር አቀፍ ደረጃ በስድስት አመታት ውስጥ ለመተግበር ዕቅድ ተይዟል፡፡

ተግባር 27፡ የፋይናንስ ደንበኞችን ጥበቃ ማጠናከር

የተዋጣለት የፋይናንስ ደንበኞች ጥበቃ ማዕቀፍና የግጭት አፈታት ስልት ግልጸኝነትን በማስፈንና አመኔታን በማጎልበት የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳደግ ወሳኝ ነው(World Bank Group 2020a)፡፡

ግልጸኝነት እጅግ አስፈላጊ ሲሆን የሚያስገኛቸው ጥቅምም በዓለም አቀፍ አሰራሮችና ደረጃዎች እንዲሁም መርሆች መሠረት የመረጃ ጥበቃን በሚመለከት በስፋት ተተንትነዋል[56]፡፡ በተጨማሪም የፋይናንስ ግንዛቤ (እውቀት) ለማስረፅ እንደ ዋና መንገድ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በቅርብ የወጡ መረጃዎች የመረጃ አሠጣጥ የአገልግሎት ዋጋ አሰራርን ማሳወቅ፣ ማሳደግና ማስፈጸም ከፋይናንስ ትምህርት ፕሮግራሞች የበለጠ ውጤታማ ናቸዉ (Better Than Cash Alliance 2016)፡፡

የመረጃ አጠባበቅ ሥርዓት የደንበኞችን የግል ሚስጥር የሚከለክሉ መሆን አለባቸው፡፡ በርካታ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ አለማቀፍ መልካም ተሞክሮዎች፣ ደረጃዎች፣ እንዲሁም መርሆች የመረጃ ጥበቃን በተመለከተ በስፋት ተተንትነዋል[57]፡፡ በዲጅታል ከባቢ ሁኔታ የተጠቃሚዎችን መረጃ እንዴት መጠበቅ እንደሚቻል ካስቀመጡት መካከል፣ ከዲጅታል ክፍያ ጋራ የተያያዙ የደንበኞችን መረጃ ደህንነትና ሚስጥራዊነት ለማረጋገጥ መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች፣ ተቆጣጣሪ ተቋማትና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ለክትትል አላማ የደንበኞችን የግብይት መረጃ የሚያገኙበት አግባብ መረጃው የትም ቢቀመጥ እና ግልጽ የግብይት ሪከርዶች የኦዲት ማስታወሻዎች (audite trial) ለደንበኞችና ለተቆጣጣሪዎች ተደራሽነትን ያጠቃልላል፡፡

ለኢትዮጵያ የደንበኞች ጥበቃ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡ በአለም ባንክ ድጋፍ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የደንበኞች ጥበቃ መመሪያዎችን አዘጋጅቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በደንበኞችና በገንዘብ ተቋማት መካከል ለሚነሱ ግጭቶች ገለልተኛ ዳኝነት መስጠትን ያለመ የደንበኞች ጥበቃ ባለስልጣን ተቋም ማቋቋምን ጨምሮ ባንኩ ሌሎች አማራጮችንም በመመልከት ላይ ይገኛል ፡፡

ቅድሚያ የሚተገበሩ የዉሳኔ ሃሳቦች

- የፋይናንስ ደንበኞች ጥበቃ መመሪያዎችን በማውጣት የፋይናንስ ተቋማት ቁልፍ የእውነት መግለጫዎችን በሚሰጡት የባንክ አገልግሎቶች መተግበራቸውን ማረጋገጥ

ተግባር 28፡ የሳይበር ደህንነትን ማጠናከር

የሳይበር ደህንነት መመሪያዎችንና ደንቦችን ማጠናከር የሚከተሉትን የዲጅታል ፋይናንስ ስጋቶችን ለመቀነስ ያግዛል፡፡ የተዋጣለት የደንበኞችን ግለኝነት /ሚስጥር/ የሚጠብቅና አስፈላጊ የፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢዎችን የሚዳስስ የሳይበር ህግ ማዕቀፍ ያስፈልጋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ብሔራዊ ባንክ የሳይበር ደህንነት መመሪያዎን በማዘጋጀት ላይ ነዉ፡፡ የባንክ ዘርፍ የሳይበር ደህንነት መመሪያ በማውጣት የፋናንስ ዘርፉን የሳይበር ደህንነት ማዕቀፍ ለማጠናከር እየተሰራ ነው፡፡ የኢትዮጵያ መረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 808/2013[58] በተሰጠው ሃላፊነት መሰረት የብሔራዊ የሳይበር ደህንነትን ይከታተላል፡፡ ብሔራዊ ባንክ ደንህነቱ የተጠበቀ እና ግልጸኝነት የተላበሰ የዲጂታል ክፍያ ከባቢ ሁኔታን ለማረጋገጥ ከመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ጋር በቅንጅት በመስራት የተጀመሩ የመመሪያ ዝግጅት ሥራዎችን በማጠናቀቅ የተዋጣለት የፋይናንስ ሴክተር የሳይበር ደህንነት ማዕቀፍ እንዲኖር ያደርጋል፡፡

ቅድሚያ የሚተገበሩ የዉሳኔ ሃሳቦች

- ከመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር የባንክ ሴክተር የሳይበር ደህንነት መመሪያን ማውጣት፡፡
- ከመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር የመመሪያውን ትግበራ መከታተል፡፡
- አስፈላጊ ሲሆን ከመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር በትግበራ ወቅት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን መፍታት፡፡

ተግባር 29፡ ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኞችን በክፍያ ማረጋገጫነት መቀበል የሚያስችል ህግ ማውጣት

ደንበኞች ለፈፀሙት ግዥ ማረጋገጫ በነጋዴዎች የሚሰጥ ደረሰኝ የግብይት መረጃ ሠነድ ነው፡፡ ደረሰኞች ለኮርፖሬት ደንበኞች የሂሳብ አያያዝና ኦዲት አገልግሎት አስፈላጊ መረጃዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም በኮርፖሬትም ሆነ ሪግለሰብ ደንበኞች ሊፈጠሩ ለሚችሉ አለመግባባቶችና የክፍያ ቅሬታዎች በማስረጃነት ያገለግላሉ፡፡ ኤሌክትሮኒክ ደረሰኞች(e-receipt) ለዲጅታል ክፍያ መሰረታዊ አገልግሎት ናቸው ፡፡ ለምሳሌ ያህል፣-

- የባንክና የገንዘብ መክፈያ ማሽን ግብይቶች፡ ባንኮችና የገንዘብ መክፈያ ማሽኖች የወረቀት ደረሰኞችን በአጭር የሞባይል ስልክ መልዕክት (sms) ወይም በኢሜል አማራጮች ለሁለት አካላት ማረጋገጫነት ይልካሉ፣- አንደኛው ለደንበኛው ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ ለአቅራቢው ባንክ ነው፡፡
- የሞባይል ገንዘብ፡ በሞባይል ገንዘብ ለሚፈጸሙ ግብይቶች ማረጋገጫዎች በአውቶማቲክ አጭር የፁሁፍ መልዕክት አማካኝነት ይላካሉ፡፡
- ኦንላይን ትራንዛክሽን፡ በኦንላይን / ኢንተርኔት/ አማካኝነት ለሚከናወኑ ግብይቶች ኤሌክትሮኒክ ደረሰኞች ወዲያውኑ በኢሜል ይላካሉ፡፡
- በነጋዴዎችና ንግድ ቦታዎች የሚፈጸሙ ግብይቶች፡ የኢሜይል መልዕክት ወይንም አጭር የጹሁፍ መልዕክት በንግድ ቦታዎች ላይ ለሚፈጸሙ ግብይቶች ማረጋጋጫነት ይላካሉ፡፡

ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ደንበኞችንና ነጋዴዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡ ደረሰኞችን በእጅ በመጻፍ ወይንም በኮምፒውተር በማተም የሚባክን ጊዜን ይቆጥባሉ የደንበኞችን የግል መረጃዎችን ለመጠበቅ ያስችላሉ፡፡ በተጨማሪም የግዥ መረጃዎቻቸውን

በቋሚነት በራሳቸው የመረጃ ቋት ውስጥ እንዲቀመጡ በማድረግና በሚፈለጉ ጊዜ ለማግኘት የግዛሉ፡፡ ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኞች ለመደበቅ ወይም ለማጥፋት የማይቻሉ በመሆናቸው የገቢዎች ሚኒስቴር ለግብር አገልግሎት የሚሆኑ መረጃዎችን ከትክክለኛ ምንጭ እንዲያገኝ ያስችላል፡፡ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኞችን ጥቅም በበለጠ በማሳደግ ለገቢዎች ሚኒሰቴር በመረጃ ምንጭነት ለንግድ ተቋማት ግብር ለማሳወቅ ያግዛል፡፡

በኢትዮጵያ ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኞች ለግብር አገልግሎት እንደ ክፍያ ማረጋገጫነት አያገለግልም፡ ፡ በአሁኑ ሰዓት የህግ ድንጋጌዎችን የማዘጋጀት ስራዎች እየተሠሩ ሲሆን በዚህም ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኞች እንደ ክፍያ ማረጋገጫነት በመጠቀም የዲጅታል ክፍያን ለመተግበር ይጠቅማሉ፡፡

ቅድሚያ የሚተገበሩ የዉሳኔ ሃሳቦች

- ከገቢዎች ሚኒሰቴር ጋር በመተባበር የአሰራር መመሪያዎችን ፣ የአሰራር ሂደቶችን በማዘጋጀት ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ እንደ ክፍያ ማረጋገጫነት የሚያገለግልበትን አግባብ መፍጠር፣

ለ2.4 ስትራቴጂያዊ ምሰሶ 4፡ ለአዳዲስ ፈጠራ አስቻይ ከባቢ ሁኔታ መፍጠር

መነሻና ቁልፍ ተግዳሮቶች

በዲጂታል ፈጠራ መስፋፋት የክፍያ ከባቢ ሁኔታን ወደ ለውጥ እያመራው ይገኛል፡፡ ለፈጠራ አስቻይ ከባቢን ማመቻቸት የዲጅታል ስራ/ቢዝነስ/ ጉዳዮች እንዲስፋፉ የሚያግዝ ስኬታማ የዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ እንዲኖር ያስችላል፡፡

በኢትዮጵያ የክፍያ ከባቢ ሁኔታ አዳዲስ ፈጠራዎች እየተበራከቱ ይገኛሉ፡፡ የተለያዩ የስኬት ታሪኮች እንደሚያሳዩት አዳዲስ ፈጠራዎች ለዲጅታል ክፍያዎች እድገት አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ፡ ፡ ቀደም ሲል የተጠቀሰው የግብርና ሚነስቴር ምርታማነት ሴፍትኔት ፕሮግራም እና የኢትዮ ቴሌኮም የሞባይል አየር ሰዓት ይጠቀሳሉ፡፡ የፕሮዳክቲቭ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ሥራ ላይ የዋለው በግሉ ሴክተር ፈጠራ ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ሲሆን የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት በገጠሩ አካባቢ እንዲስፋፋ የራሱን ሚና ተጫውቷል፡ ፡ በአንጻሩ የኢትዮ ቴሌኮም የአየር ሠዓት ሽያጭ ዲጂታይዝ የማድረግ ሂደት ከባንኮች ጋር በመተባበር የሞባይል ገንዘብ በኢትዮጵያ እንዲጨምር አግዟል፡፡

የፊንቴክ ዘርፍ በኢትዮጵያ ገና በጅምር ላይ የሚገኝ ሲሆን በዋናነት የዲጅታል ክፍያ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ቤልካሽና ኤም ብር (ሁለቱም የዉጪ ኢንቨስትመንት ናቸዉ) በቀጥታ ከባንኮችና አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ጋር ይሰራሉ፡፡ በሌላ በኩል ራይድ እና የኔ ፔይ የራሳቸዉን አገልግሎት በሞባይል መተግበሪያ ወይም በድረ-ገፅ አማካኝነት በቀጥታ ለተጠቃሚዎች ያደርሳሉ ((World Bank Group 2020a)፡፡ በቅርቡ የወጡት ሁለት[59] መመሪያዎች በዲጅታል ክፍያ ከባቢ ሁኔታ ዉስጥ የፊንቴኮችን የተሳትፎ አድማስ እንደሚያሰፉ ይጠበቃል፡፡

ይህም ሆኖ ግን አዳዲስ ፈጠራዎች ለዲጅታል ክፍያ እድገት ከዚህ በበለጠ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የማያስችሉ ክፍተቶች አሉ፡፡ በዚህ ሴክተር አለምአቀፍ ተሣትፎ የተገደበ መሆኑ እጅግ በጣም ጥሩ የሚባሉ የፈጠራ ውጤቶችን እንዳይተገበሩ እንቅፋት የፈጠረ ሲሆን ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድጋፍ እንዳያገኝ አድርጓል፡፡ በኢትዮጵያ አዳዲስ ፈጠራዎች ቁጥጥር በሚደረግበት አካባቢ ለመሞከር የሚያስችል ማዕቀፍ የለም፡፡ ይህም ኢትዮጵያ ማዕበላዊ ለውጥ መቀጠል ከማስቻል አንፃር ጠቃሚ ነው፡፡ በዓለም ዙሪያ ተቆጣጣሪ ተቋማት እና ዲጂታል ገንዘቦችን (ክሪፐቶ ከረንሲ) የመሣሠሉ የላቀ የክፍያ አማራጮችን ለመጠቀም እያሰቡ ይገኛሉ፡፡

ዓለም አቀፍ መልካም ተሞክሮዎች

በዲጅታል አዳዲስ ፈጠራዎች ዓለምአቀፍ መልካም ተሞክሮዎች፣ ዓለም አቀፍ ሃብትና ብሄራዊ የሙከራ ማዕቀፎች ተለይተዋል፡፡

ዓለም አቀፍ ሃብቶች

በዓለም ላይ የፋይናንስ አገልግሎት አዳዲስ ፈጠራዎች ዲጅታል ክፍያዎች የሚመሩት በነባር ተዋናዮች (ባንኮችና የክፍያ መንገዶች) ብቻ ሳይሆን በአዳዲስ የቴክኖሎጂ የፈጠራ ተዋናዮች (ፊንቴኮች) ጭምር ነው፡፡ በተጨማሪም ዓለማአቀፋዊነት (በዓለምአቀፍ ንግድ የውጪ ቀጥተኛ መወዕለ ነዋይ፤ ዓለምአቀፍ የፈጠራ መብትን መጠቀም መልካም ተሞክሮዎችን መጋራት) አዲስ ፈጠራን እንዲያድግ አስችለዋል፡፡ እየጨመረ የመጣው ዓለምአቀፍ ውድድር ከአለምአቀፋዊነት ጋር ተደምሮ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመተግበር እና ለፈጠራ የሚደረገውን ማበረታቻ በማሳደግ ለዲጂታል አዲስ ፈጠራ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ዓለምአቀፍ የፊንቴክ ዘርፍ አስር አመታት በከፍተኛ ደረጃ መዋዕለነዋይ ወጥቶበታል ከዚህም መካከል አብዛኛው መጠን ድንበር ተሻጋሪ መዋዕለነዋይ ነው፤ አገራት ከዓለምአቀፍ የፊንቴክ ማህበረሰብ ጋር አብሮ መስራት የሚያስገኘው ጥቅም በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋ መጥቷል፡፡ እ.ኤ.አ በጃንዋሪ 2019 የዩናይትድ ኪንግደም የፋይናንሻል ኮንዳክት አውቶሪቲ (UK’s Financial Conduct Authority) ከሌሎች አባል አገራት ጋር በመተባበር ዓለምአቀፍ ፈጠራ ኔትወርክ መስርቷል፡፡ ይህ ትብብር ድንበር ተሻጋሪ የሃሳቦች ትብብርን ሃሳቦችን መሞከሪያ የህግ ማዕቀፍ (sandbox testing) እና የእውቀት ሽግግር ለማሳደግ መንገድ ይከፍታል፡፡

ብሔራዊ የሙከራ ማዕቀፍ

በቴክኖሎጂ የታገዙ የፋይናንስ አገልግሎቶች (ፊንቴኮች) ባለፉት አስር አመታት በፍጥነት አድገዋል፡፡ ከዚህም እደገት ጋር አብሮ ለመራመድ በፈጠራ አመንጪዎችና በህግ አውጪ አካላት መካከል ግልፅ ውይይት ለማስፈን የሚያግዝ ሥነ ምህዳር መፍጠርን ይፈልጋል፡፡ በዚህም ፈጠራ አገልግሎቶች ከትግበራ በፊት የሚሞከሩበት አሰራር መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ በዓለማችን ሦስት የአሰራር መንገዶች በግልፅ ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች በተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሀፊ አካታች ፋይናንስ ለእድገት በተደረገ ጥሪ ላይ እንደሚከተለው ገልፀዋቸዋል፡፡

- የፈጠራ ቢሮዎች ፡ ለአዲስ ፈጠራዎች አስቻይ ከባቢን ለመፍጠር የፈጠራ ቢሮዎችን ማቋቋም ቀዳሚ ተግባር ሊሆኑ ይገባል፡፡ የፈጠራ ቢሮዎች ፤የፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢዎች አዳዲስ የፈጠራ ምርቶች እና አገልግሎቶችን ለማቅረብ ሲፈልጉ የህግ ድንጋጌዎችና ማዕቀፎች ላይ ማብራሪያ በመስጠት ያግዛሉ፡፡
- የህግ መሞከሪያ ከባቢ ሁኔታ(Regulatory sandboxes)፡ የፋይናንስ አገልግሎቶች የስራ ጉዳዮችን ለተገልጋዮች በመስጠት ጥበቃና ክትትል እየተደረገ የሚሞከርበት መደበኛ ፕሮግራም ነው፡፡ የህግ መሞከሪያ ከባቢ ሁኔታ አካታች የፊንቴክ አገልግሎቶች እንዲኖሩ የሚያግዝ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ድንጋጌ ለማዘጋጀት እንዲሁም አገልግሎቱን የበለጠ ለመገንዘብ የሚረዳ ፕሮግራም ነው፡፡ ሆኖም ግን አገልግሎቱ ሲጀመር የሚከናወኑ የህግ መሞከሪያ የፊንቴክ አገልግሎት የማያስፈልግ ወይም በበቂ ሁኔታ የፋይናንስ አካታችነትን የማያረጋግጡ መሆናቸውን ያሳያሉ፡፡
- የቁጥጥር ቴክኖሎጂ (RegTech)፡ የተቀመጡ ህጎችና ድንጋጌዎችን የሚያከብሩ መሆናቸውን ለመከታተልና ለማስፈፀም በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ትኩረት ይደረጋል፡፡ የቁጥጥር ቴክኖሎጂዎች አዳዲስ የፋይናንስ ቴክኖሎጂ ፈጠራዎች በበለጠ ሃላፊነት ሥምሪት የሚሰጡበትን ሁኔታ በማገዝ የፋይናንስ አካታችነትን ለማጎልበት በጎ ተፅዕኖ ያሣድራል፡፡ በተጨማሪም ተቆጣጣሪዎች ለገበያ ለውጦች በፍጥነት ምላሽ እንዲሰጡ የተሻለ የደንበኞች ጥበቃ እና የተቋም ክትትልን ለማሳደግ እንዲችሉ ያግዛል፡፡ የተወሰነ ቢሆንም ከሂደቱ የሚገኙ ልምዶች ከተግዳሮቶች በመነሳት ውጤታማ መፍትሄ በማስቀመጥ ሰፊ ተቀባይነትን እንዲያገኝ ያስችላል፡፡

ስትራቴጂክ እርምጃዎች/ተግባራት

ለፈጠራ አስቻይ ከባቢ እንዲኖር ለማገዝ ሁለት ምድብ ስትራቴጂያዊ ተግባራት ተቀርፀዋል፡፡ በነዚህ ውስጥም ሦስት ስትራቴጂክ ተግባራት ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቷቸው ቀርበዋል፡፡ ሁለቱ ምድቦች:-

- አሣታፊነትን በማጎልበት በፈጠራ ቴክኖሎጂ ረገድ የአዳዲስ ተዋናዮችን ሙሉ አቅም መጠቀም፣
- ለፈጠራ ቴክኖሎጅ ልማት አስቻይ ማዕቀፍ መፍጠር፣

እነዚህም በሚከተሉት ቁልፍ ተግባራት ይታገዛሉ፣

አዳዲስ ተዋንያን

ተግባር 30፡ የፊንቴክን ተግባርና ሃላፊነት ግልፅ ማድረግ

ተግባር 31፡ የፊንቴክ ዓለምአቀፍ ሀብቶችን ተደራሽነት ማስፋት

ማዕቀፍ

ተግባር 32፡ ስጋቶችን በአግባቡ በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚያስችል የፈጠራና ቴክኖሎጂ ልማት ማዕቀፍ መፍጠር

ለ2.4.1 አዳዲስ ተዋንያን

በ20ኛው ክፍለ ዘመን የጥሬ ገንዘብና ሳንቲሞች ደህንነት የተጠበቀ እንዲሆን ባንኮች አገልግሎቱን ይሠጡ ነበር፡፡ የገንዘብ መክፈያ ማሽን፣ ኦንላይን ባንኪንግ እና የሞባይል ባንኪንግ መጀመር የባንክ አሰራር ሂደቶችን ብቻ ሣይሆን ባንክ ምንድነው የሚለውን ፅንሰ ሃሣብ ጭምር ቀይሮታል፡፡ ለበርካታ ደንበኞች ነባሩ ባንክ ሣይቀየር በአካል ወደ ቅርንጫፎች ሣይሄዱ የሚገለገሉበት ሆኗል፡፡ በክፍያ ማሽኖች በድረ ገፅ፣ በሞባይል መተግበሪያ በኩል በተደጋጋሚ አገልግሎቱን ማግኘት ይቻላል፡፡ ይህም ሁኔታ የባንክ ቅርንጫፎች እድገት መገታቱን በአንፃሩ የቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጫዎች መስፋፈታቸው የመረጃ አጠቃቀም ፍጥነትና ብዛት የባንክን ሁኔታና የፋይናንስ ምርቶችና አገልግሎቶችን ለደንበኞች የሚቀርቡበትን ሁኔታ ቀይሮታል፡ ፡ ቴክኖሎጂ በፋይንናስ አገልግሎት የተለዩ ፍላጎቶችን አስተዋውቋል፣ ከዚህ ቀደም ያልነበሩትን ጨምሮ የተለያዩ ተወዳዳሪዎች እንዲፈጠሩ አድርጓል፡፡ የዲጂታል ክፍያና ኤሌክትሮኒክስ ግብይት ከባቢ ሁኔታ ማደግ የባንክን ፅንሰ ሃሳብ ሙሉ ለሙሉ ቀይሮታል፡፡

ተግባር 30፡ የፊንቴክን ተግባርና ሃላፊነት ግልፅ ማድረግ

በክፍያ ከባቢ ሁኔታው የፊንቴኮች እንደ አዳዲስ ተዋንያኖች መምጣታቸው ተግባርና ሃላፊነታቸውን እንደ አዲስ ማስተካከልና ግልፅ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ግልፅነትን መፍጠር የፊንቴኮችን አስተዋፅኦ የማድረግ እድል ለማሳደግና ከነባር ተዋናዮች ጋር ሊፈጠር የሚችል የአገልግሎት አድማስ መጣረስ ለማስቀረት ይጠቅማል፡፡

እስካሁን ባለው ሁኔታ ፊንቴኮች ለ ፋ ይ ና ን ስ ተቋማት የሶፍትዌር አገልግሎት አቅራቢ በመሆን በማገልገል ላይ ተወስነው ቆይተዋል[60]፡፡ ፊንቴኮች አገልግሎታቸውን እያሰፉና እያደጉ መምጣታቸውን ተከትሎ ተግባራቸውን የመከለስና እንዴት በፋይናንስ ገበያው ውስጥ እንደሚሳተፉ በመወሰን በፈጠራ የታገዘ ቴክኖሎጂ ማቅረብ፣ ምርቶችን አገልግሎቶችንና ሂደቶችን ኢትዮጵያን በሚጠቅም አግባብ መከለስ ወሳኝ ነው፡፡ አዲሱ የክፍያ መሣሪያዎች አቅርቦት፣ የክፍያ ሲስተም ኦፕሬተርና የወኪል መጠቀም መመሪያዎች ፊንቴኮችን ቀደም ሲል የነበሩ የሚና መደናገሮችን በማጥራት የክፍያ መሣሪያዎችን እንዲያቀርቡ ፈቃድ በመስጠት የፋይናንስ ከባቢ ሁኔታው አካል እንዲሆኑ አስችሏል፡፡ ሦስቱ መመሪያዎች በጣምራ የሚከተሉትን ሁኔታዎች እንዲኖሩ ይፈቅዳሉ፡፡

- የኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ አገልግሎት በቀጥታ ለተጠቃሞዎች እንዲያቀርቡ፣
- የወኪል ኔትዎርክ እንዲያስተዳድሩ እንዲቀጥሩ፣ እንዲያሰለጥኑና እንዲቆጣጠሩ፣
- አገልግሎቶችንና ምርቶችን እንዲያስተዋውቁና ለገበያ እንዲያቀርቡ (እንዲሸጡ)፣
- የጥሪ ማዕከላት በማቋቋም ለደንበኞች እገዛ እንዲያደርጉ፡፡

አፈፃፀሙና ትግበራው በቅርበት ክትትልና ግምገማ ይደረግበታል፡፡

ቅድሚያ የሚሰጣቸው የውሣኔ ሃሣቦች

- ከፊንቴኮች ማህበር ጋር በመተባበር አዳዲሶቹ መመሪያዎች ፊንቴኮች በክፍያ ከባቢ ሁኔታ ውስጥ እንዲስፋፉ ከማስቻል አንፃር ያላቸውን ፋይዳ መከታተልና መገምገም፣
- ከፊንቴኮች ማህበር ጋር በመተባበር የፊንቴኮችን ተግባርና ሃላፊነት በማሻሻል ከሚለዋወጠው የክፍያ ከባቢ ሁኔታ ጋር ማዛመድ፡፡

ተግባር 31፡ የፊንቴክ ዓለምአቀፍ ሀብቶችን ተደራሽነትን ማስፋት

የቴክኖሎጂ እድገት ነባር ባልሆኑ የፋይንናስ ተቋማት የዕድገት እንቅስቃሴ፣ አዳዲስ ገበያዎች ላይ ከመሞከር፣ እንዲሁም አገራትና ባንኮች ዲጂታል ክፍያን ለማስፋፋት ከሚያደርጉት ለውጥ አንፃር በዓለማቀፍ የፋይናንስ ሴክተር ላይ እመርታዊ ለውጥ አምጥቷል፡፡ በአለም አቀፍ የቬንቸር ካፒታልና ክራውድ ፈንዲንግ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል፡፡ በንግድ ከሚሰበሰበው ሃብት ከፍተኛው መጠን በፊንቴኮች ጀማሪዎች ዘርፍ ፈሰስ የሚደረግ ነው፡፡ ዓለማቀፍ አዲስ ነገር ፈጣሪዎችና የፋይናንስ ተቋማት ከዚህ ለውጥ ጋር ለመስማማት ባለፉት 10 ዓመታት በዘርፉ ላይ ያለውን እውቀት ወደራሳቸው በማምጣት ፣ የምርቶች ፋይዳ ላይ እውቀት እንዲኖር ለማድረግ ጥረቶች ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡

ዓለማቀፍ ተሳትፎ በሳል ልምድና የላቀ ሃብት ያላቸው የፈጠራ ፕሮጀክቶች ጋር ትብብርን በመፍጠር የእውቀት ሽግግር እንዲኖር ያስችላል፡፡ ከዚህም የአገር ውስጥ ጀማሪ ተቋማት በዓለማቀፍ የቬንቸር ካፒታል አቅራቢዎች እና ክራውድ ፈንዲንግ የገንዘብ አቅርቦት እንዲያገኙ እድል ይፈጥራል፡፡ ይህም የኢንፎርሜሽንና ኮሙዩኒኬሽን (ICT) ድርጅቶች

ዓለማቀፍ የገንዘብ አቅርቦት ለማግኘት ባለው ጠንካራ የኢንቨስትመንት ፖሊሲና የትርፍ ድርሻን ይዞ ለመውጣት ያለው ተግዳሮት ይገታዋል፡፡ በኢትዮጵያ ብሔራዊ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጅ እንደተለየው በኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ዝቅተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት መጠን 200,000 የአሜሪካ ዶላር በሚል መቀመጡ፣ ይህም የገንዘብ መጠን ለICT ጀማሪ ድርጅቶች እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡

የክፍያ መሣሪያዎች አቅርቦት መመሪያ ከሌሎች አገራዊ ፖሊሲዎች አንፃር ተቃኝቶ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ በአዲሱ የባንክ ሥራ አዋጅ[61] እንደተደነገገው የውጭ ተዋናዮች በኢትዮጵያ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ መሣተፍ አይችሉም፡፡ ይህ ማለት በውጭ ባለሃብቶች የተያዙ ካምፓኒዎች በኢትዮጵያ የክፍያ መሣሪያዎች አቅርቦት ፈቃድ ማግኘት አይችሉም፡፡ ይሁንና ለፋይናንስ ተቋማት የቴክኖሎጂ አገልግሎት በማቅረብ መሥራት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ፈቃድ ከተሰጣቸው የፋይናንስ ተቋማት ጋር በመተባበር እንደ ሶስተኛ ወገን አገልግሎት አቅራቢ በመሆን መስራት ይችላሉ፡፡ የፋይናንስ ተቋማት የወኪል ሥርጭትና አስተዳደር እንዲሁም የሽያጭና ማስተዋወቅ ሥራዎቻቸውን ለነዚህ በውጭ ባለሃብቶች ለተያዙ ካምፓኒዎች በመስጠት ማሰራት ይችላሉ፡፡

የአዳዲሶቹ መመሪያዎች ትግበራና የፌንቴኮች ተሳትፎን በቅርበት በመከታተልና በመቆጣጠር ዲጂታል ክፍያን በከፍተኛ ሁኔታ ለመተግበር ይሠራል፡፡

ቅድሚያ የሚተገበሩ የውሣኔ ሃሣቦች

- ከገንዘብ ሚኒስቴርና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር አዳዲሶቹ መመሪያዎች ፊንቴኮችን በመጠቀም ዲጂታል ክፍያን በስፋት ለመተግበር በሚደረገው ጥረት ላይ ያመጡትን ለውጥ መቆጣጠርና መገምገም፡፡
- ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና የፊንቴኮች ማህበር ጋር በመተባበር ዲጂታል ክፍያንና የአካታችነት ፈጠራዎች ላይ ትኩረት የሚያደርጉትን የማቀፍና የማበረታታት ፕሮግራሞችን አፈፃፀም ማጎልበት፡፡
- ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፣ የውጭ አገራት የፊንቴክ ተዋናዮች ሊኖራቸው ስለሚችለው ተሳትፎ ዝርዝር ጥናት ማካሄድ እና ዝርዝርና የተሟላ የፊንቴክ ኢንቨስትሜንት ፖሊሲ ማዘጋጀት።

የዚህ ተግባር ስኬት በተግባር 25፣ ይኸውም በሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ውስጥ ባንክ ያልሆኑ የፋይናንስ ተሳታፊዎችን መቆጣጠር በሚለውና በተግባር 30፣ ይኸውም የፊንቴኮችን ሚና እና ኃላፊነት ግልጽ ማድረግ በሚለው ላይ የተመሰረተ ነው።

ለ.2.4.2 ማዕቀፍ

በፈጠራ ሥራና በቁጥጥር ከባቢ መካከል ከፍተኛ ቁርኝት አለ፡፡ በአንድ የህግ ማዕቀፍ ውስጥ የጠንካራና ገዳቢ ህጎችን ብዛትና መጠን የገዳቢነት ደረጃቸውን ወይንም የቆይታ ጊዜያቸውን መወሠን አይቻልም፡፡ ወጥ የሆነ በመረጃ ላይ የተመሠረተ መስፈርት አለመኖር የድንጋጌ ምእራፎችንና ክፍሎችን በጥልቀት መገምገምን አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡ ከዚህም መካከል ገበያን የመፍቀድ (የማዕደቅ) ሁኔታ የተረጋጋና ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ሊሆን ይገባል፡፡ አዳዲስ የምርት መንገዶችና ግብዓቶች ለማሳደግ (ለመቀየር) ዝግጁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በመሆኑም የአዲስ ነገር ፈጠራና የህግ ማዕቀፎች ማስተግበር ከያንዳንዱ አንጓ ተለይቶ ሊገመገም ይገባል፡፡ ይህንን መስተጋብር በሚገባ ለመገምገም የመሞከሪያ ምህዳር /sand Box/ የተሻለ እድል ይፈጥራል፡፡

ተግባር 32፡ ስጋቶችን በአግባቡ በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚያስችል የፈጠራና ቴክኖሎጂ ልማት ማዕቀፍ መፍጠር

በቴክኖሎጂ ፈጠራ ባለቤቶችና ተቆጣጣሪ ተቋማት መካከል በቁጥጥር ስር ባለ አካባቢ ውይይት ለመፍጠር የሚያስችል ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ አዳዲስ ምርቶች ከትግበራ በፊት የሚሞከሩበት አሠራር መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ በሌሎች አገራት የተወሰዱ መፍትሔዎች ለምሳሌ Sand boxes እና RegTech የዲጂታል ክፍያ ሲክተራቸው ባደገ አገራት የበለጠ ያገለግላል፡፡ ሆኖም ግን ኢትዮጵያ ከራሷ የገበያ እድገት ጋር የሚጣጣሙ የተወሰኑ መርሆችን በመውሰድ መጠቀም ትችላለች፡፡

የፈጠራ ባለቤቶችና ተቆጣጣሪ ተቋማት በሰጥቶ መቀበል ቁልፍ መርህ አግባብ በትብብር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት በመፍጠር አንዳቸው ከሌላኛው የሚማሩበትን እድል መፍጠር ይቻላል፡፡ የውይይት ወርክሾፖችን በማዘጋጀት የፈጠራ ባለቤቶች ያመጡትን አዲስ ፅንሰ ሃሣብ ለተቆጣጣሪዎች እንዲያቀርቡ ለማስቻል እድል ይፈጥራል፡፡ በዚህም ተቆጣጣሪዎች ያገኙትን መረጃ በመጠቀም ድንጋጌዎችና የህግ ማዕቀፎች እነዚህን ፅንሰ ሃሣቦችና አዲስ ፈጠራዎች የሚገድቡ ጉዳዮችን ለመለየት ያስችላል፡፡ የፈጠራ ባለቤቶች የፈጠራ ስራቸውን ካለው ህግ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ በሌላ በኩል ተቆጣጣሪ አካላት የቀረበውን ፅንሰ ሃሣብ በመጠቀም ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ህጎችን የት አካባቢ መሻሻል እንደሚገባቸው በመለየት በሁለቱም ወገን የሚደረግ መቻቻል ስኬት እንዲገኝ ያግዛል፡፡ ይህ ሰጥቶ የመቀበል ግንኙነት ህጎችና ድንጋጌዎች በሚለዋወጥ አካባቢና የቴክኒክ ሁኔታ ውስጥ መስማማት እንዲችሉ በማገዝ ዲጂታል ክፍያን የሚያጎለብቱ ምርቶች እንዲያድጉ ያስችላል፡፡

ይህን አይነት ከባቢ መፍጠር ዘመናዊና የተዋጣለት ዲጂታል የክፍያ መንገድ (ለምሳሌ ክሪፕቶከረንሲ) የመሣሠሉትን ለመሞከርና አንድምታቸውን ከመረዳት አንፃር ለተቆጣጣሪ ተቋማት እድል ይፈጥራል፡፡

ቅድሚያ የሚተገበሩ የውሣኔ ሃሣቦች

- ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና ፊንቴኮች ማህበር ጋር በመተባበር ተከታታይ ወርክሾፖችን ከፈጠራ ባለቤቶች ጋር ማዘጋጀት (ለምሳሌ በየስድስት ወሩ) ፈጠራን ለማበረታታት መከናወን የሚገባቸው ተግባራትን መለየት (ለምሳሌ ህጎችን እንዴት ማሻሻል እንደሚገባ)፡፡
- ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና የፊንቴኮች ማህበር ጋር በመተባበር በደንበኞች፣ በፋይናንስ ተቋማት እና ተቆጣጣሪ ተቋማት ሊተገበሩ የሚገባቸው ለውጦችን መለየት፡፡

ለ3. አስቻይ ሁኔታዎች

ስትራቴጂክ ምሶሶዎችን በመደገፍ ራዕዩን የሚያሳኩ አራት አስቻይ ሁኔታዎች ተለይተዋል፡፡ እነዚህ አስቻይ ሁኔታዎች ለብሔራዊ ዲጂታል ክፍያ ስትራቴጅ ስኬት መሠረት ናቸው፡፡

አስቻይ 1፡ ወጭ ቆጣቢ አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ የክፍያ ሥርዓት ለመገንባት ሊኖር የሚገባ ቁርጠኝነት፣

አስቸኳይ 2፡ በዲጂታል ክፍያ ከባቢ ሁኔታ ውስጥ ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶት የአቅም ግንባታ ስራዎች ላይ መዋዕለ ነዋይ ማፍሰስ፣

አስቸኳይ 3፡ ከአለምአቀፍ የልማት ሪፎርም እና ፖሊሲዎች ጋር ቀጣይነት ያለው ቅንጅት መፈጠሩን ማረጋገጥ፣

አስቸኳይ 4፡ የተሟላ የአስተዳደር የትግበራ እቅድ በማዘጋጀት ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያዎችን በመጠቀም ክንውንን መከታተል፡፡

አስቻይ 1፡ ወጭ ቆጣቢ አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ የክፍያ ሥርዓት ለመገንባት ሊኖር የሚገባ ቁርጠኝነት

ብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት የሚከተሉትን ያካትታል፡- (i) የክፍያ ትዕዛዞችን መላክ/መቀበልና መፈፀም (ii) የክፍያ መሣሪያዎችን ማቅረብና ማስተዳደር (iii) የክፍያ ማጣራትና ማወራረድ ሥርዓትና ተጓዳኝ አሠራሮች (iv) የክፍያ አገልግሎት አቅራቢዎች፣ ኦፕሬተሮች፣ ተሣታፊዎች፣ የክፍያ መሣሪያዎች አቅራቢዎችና ሌሎች በነሱ ስም የሚሠሩ ሦስተኛ ወገኖች (ኢ.ብባ 2011)፡፡ በብሔራዊ የክፍያ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 718/2011 በተሠጠው የቁጥጥር ፣ ክትትልና፣ ህግ የማውጣት ሃላፊነት መሠረት ኢ.ብባ ከፍተኛ መጠን ያላቸው ገንዘቦችን የማስተላለፊያ ስርዓት፣ የችርቻሮ (አነስተኛ መጠን ያላቸው) ገንዘብ የማስተላለፊያ ሥርዓት እንዲሁም የሴንትራል ሴኪዩሪቲ ዲፖዚተሪ ሥርዓቶችን ያካተተ የተቀናጀ የክፍያ ስርዓት የማቋቋም፣ በባለቤትነት የማስተዳደር፣ የማንቀሳቀስ የመሣተፍ፣ ህጎችን የማውጣት እና የመከታተል ተግባራት ያከናውናል፡፡

ኢ.ብባ በልማት አጋሮች አጋዥነት የኢትዮጵያ የፋይናንስ ሴክተር ማሻሻያ ፍኖተካርታ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል (World Bank)፡፡ በአለም ባንክ ግሩፕና በዩናይትድ ኪንግደም አለምአቀፍ ልማት ዲፓርትመንት እገዛ በመዘጋጀት ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ የፋይናንስ ሴክተር ሪፎርም ስትራቴጅ እንደተገለፀው ፍኖተካርታው የብሔራዊ የክፍያ ስርዓቱን ዋነኛ ክፍሎች ለማሻሻል የሚያግዙ የተለያዩ ጅምሮችን ያካትታል፣ ያብራራል፡፡ እነዚህም፡-

- ሚና እና ተልዕኮ፡ ለክፍያ ሥርዓቱ የተሻለ ዘመናዊ የክትትል ማዕቀፍ መፍጠር የአቅም ግንባታ፣ የአሠራር ሂደቶችን መወሠን፣ እንዲሁም የአሠራርና የሪፖርት አቀራረብ መንገዶችን መከለስን ያካትታል፡፡
- ህግ ማውጣት፡ ለክፍያዎች የህግና የቁጥጥር ማዕቀፎችን ማዘጋጀት - እየተዘጋጁና እየተከለሱ ካሉ ህጎችና ድንጋጌዎች፤ ኢ-ኮሜርስ ህግ ፤ ኢ-ፊርማ ህግ፤ የብሔራዊ ክፍያ አዋጅ ማሻሻል፤ እና የውጪ ዜጎችን ማሳተፍ ለማስቻል በሚያግዝ መልኩ የባንክ ስራ አዋጅን ማሻሻል ይገኙበታል፡፡
- መሰረተ ልማትና ቴክኖሎጂ፡ በብሔራዊ ባንክ ባለቤትነት የሚያዝ የክፍያ ስርዓት መሰረተ ልማትን ማልማት እና በሀገር ውስጥ በባንኮች መካከል ላለ ስዊች የረጅም ጊዜ የልማት እቅድና ስትራቴጂ ማሻሻል ኢትስዊችን ለሌሎች አገልግሎት አቅራቢዎች ማዕከል እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ የካርድ፤ የሞባይል እና የባንክ ሂሳቦች ተናባቢነት ሚናን በመወጣት ከሌሎች እንደ ቢል አግርጌተር፤ የክፍያ በር/ጌትወይ/ የመንግስት አገልግሎት መተላለፊያ/ ፖርታል/ እና ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ ደንበኛህን እወቅ ወይም የዲጅታል መታወቂያ ከመሳሰሉ ጋር ያገናኛል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የብሔራዊ ክፍያ ስርዓት ለብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂን በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን ወሳኝ ሚና ስላለው የበለጠ ወጪ ቆጣቢ፤ አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ ሆኖ እዲቀጥል ቁርጠኛ ነው፡፡

አስቻይ 2፡ በዲጅታል ክፍያ ከባቢ ላይ አቅም ለመገንባት ቅድሚያ መስጠት እና መዋዕለንዋይ ማስፈሰስ

ዲጅታል ክፍያ አዲስ እውቀትን መተግበር፤ በድጅታል ክፍያ ላይ መሰረት ያደረገ ሞያ እና የተለየ እውቀትን ይፈልጋል፡፡ ቴክኒካል /ብዙ እዉቀት ያለቸውን/ ባለሞያዎች መቅጠር እና ለአስፈላጊ እውቀትና ልምድ ላላቸዉ ሶስተኛ ወገን አካላት ማስተላለፍ ዲጅታል እውቀትን ለመተግበር ውጤታማ እድገት ኢንዲኖር ያደረጋል፡፡ በተጨማሪም የስልጠና ቦታዎችን በማቅረብ በዲጅታል ክፍያ ዙሪያ በአቅም እንዲሁም በቁጥር ብዙ የሰራተኛ ሀይል እዲኖር ያደርጋል፡፡

የፕሮጀክቱ ሰፊነት ስትራቴጂው የሚፈልገውን ለማሟላት የተለያየ እውቀት ያላቸው እና ብዙ የሰራተኛ ሀይል ያስፈልጋል፡፡ የስትራቴጂውን አተገባበር ለመከታተል እና ለመተግበር እንዲሁም ውጤታማ የሆነ ችሎታና በጊዜ ገደቡ መተግበሩን ለማረጋገጥ በሁሉም ባለድርሻ አካላት ዘንድ አቅም መገንባት ይኖርበታል፡፡ እነኚህ ባለድርሻ አካላት በዚህ ስትራቴጂ በሁለተኛ ምዕራፍ ተቀምጠዋል፡ - የትግበራ ማዕቀፍ፡፡ ይህ የብሔራዊ ድጅታል ስትራቴጂ በአገር አቀፍ ደረጃ በተለያዩ መስኮች ላይ ወደታች ወርዶ ለውጥ ያመጣል ተብሎ ተስፋ ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ ያህል፤ በሀገር ውስጥ ንግድ፤ ግንዛቤና ባሕሪ፤ እና የተለያዩ ከብሔራዊ ዲጂታል ስትራቴጂ ጋር አብሮ ሊሄዱ የሚችሉ ስትራቴጂዎችን ያጠቃልላል፡፡ ውጤታማ የትግበራ ዕይታን ለመያዝ አስፈላጊ እና የተለየ አቅም የስፈልጋል፡፡

በዲጅታል ከባቢ ውስጥ የሚያስፈልገውን አቅም ለመገንባት የኢትዮጵያ መንግስት አስፈላጊውን መዋዕለንዋይ ይመድባል፡፡ ምክኒያቱም የብሔራዊ ዲጅታል ስትራቴጂ ትግበራን ለማረጋገጥ በጣም ወሳኝ ድርሻ ስላለው፡፡

አስቻይ 3፡ ከብሔራዊ የልማት ሪፎርሞችና ፖሊሲዎች ጋር ንቁ እና ቀጣይት ያለው ትብብርን ማረጋገጥ

ኢትዮጵያ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ብሔራዊ ሪፎርሞች ውስጥ እያለፈች ትገኛለች፡፡ ይህም ድህነትን ለመቀነስ፤ የስራ ዕድልን መፍጠር እና አካታች እድገትን ለማምጣት የተያዘውን ብሔራዊ ግብ በተባበረ መልኩ እንድታሳካ ይረዳታል፡፡ የብሔራዊ ዲጅታል ስትራቴጂ ቀረጻና ትግበራ ከነኚህ በብሄራዊ ባንክ እና ከብሔራዊ ባንክ ውጪ ካሉ ሰፊ ሪፎርሞች ጋር መቆራኘት ይገባዋል፡፡

በብሔራዊ ባንክ ውስጥ ካሉ ሪፎርሞች ጋር ያለው ቁርኝነት

ብሔራዊ ባንክ በአሁኑ ሰዓት በፋይናንስ ስርአቱ ውስጥ የሚከናወኑ ሪፎርሞችን እየመራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ስትራጂ እና ነባር መመሪያዎች እየተከለሱ ይገኛሉ፡፡ ይህ የብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ለብሔራዊ የፋይናንስ ዘርፍ ሪፎርም እንደ ቁልፍ ምሰሶ፤ ለፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ እንደ አስቻይ እንዲሁም በመከለስ ላይ ላሉት መመሪያዎች አንደ አቅጣጫ ማሳያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

- የብሔራዊ የፋይናንስ ዘርፍ ሪፎርም ፕሮግራም በዓለም ባንክ ድጋፍ ወጪ ቆጣቢ፤ የተረጋጋ እና አካታች የፋይናንስ ዘርፍ እንዲኖር በሚያስችል መልኩ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ስትራቴጂ ለዘርፉ ሪፎርም ቁልፍ ምሰሶ ነው፣ እንዲሁም ከፋይናንስ ዘርፍ ሪፎርም ግምገማ ጋር ተመጋጋቢ ነው፡፡
- በቢልና ሚሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን አማካኝነት እየተከለሰ ያለው ብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ፤ ዲጅታል መተግበሪያዎችን በመጠቀም

አስገራሚ የፋይናንስ አካታችነት ጭማሪ እንዲኖር አልሟል፡፡ ይህ ስትራቴጂ ለዚህ ግብ መነሻ ይፈጥራል፡፡

- በመከለስ ላይ ያሉ መመሪያዎች- በዚህ ስትራቴጂ ስትራቴጂክ ምሰሶ 3 ላይ በ ጥልቀት ተቀምጧል- የዚህ ስትራቴጂ ግኝቶች ለነዚህ መመሪያዎች አመላካች ሆነዋል፡፡

ከብሄራዊ ባንክ ውጪ ካሉ ሪፎርሞች ጋር ያለው ቁርኝነት

ሰባት ቁልፍ ብሔራዊ ሪፎርሞች በሀገር ደረጃ እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ አንዳንዶቹ ለብሔራዊ የዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ወሳኝ አስቻይ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በከፍተኛ ሁኔታ ከብሔራዊ ድጅታል ስትራቴጂ ጋር የተቆራኙ ናቸዉ፡፡

ሁለት ሪፎርሞች ለብሄራዊ ዲጅታል ስትራቴጂ እንደ ዋና መሰረት ይታያሉ፣

- የብሔራዊ ዲጅታል ሽግግር / ትራንስፎርሜሽን/ ስትራቴጂ (እ.ኤ.አ ከ2020-2025) በቅርቡ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚነስቴር የተዘጋጀው ስትራቴጂ ለውጤታማነቱ ክፍያን እንደ አስፈላጊ አካል ለይቶታል፡፡ ስትራቴጂው መፈታት ያለባቸው የተለዩ ተግዳሮቶችን በክፍያ ምህዳር ላይ የለየ ሲሆን እነኚህም ተግዳሮቶች በባለፈው የስትራቴጂ ክፍል ውስጥ ተመላክተዋል፡፡ በዚህም ሁለት ፕሮጀክቶች ለብሔራዊ ባንክ ተለይተዋል፣ ፕሮጄክት 17 ለሞባይል ገንዘብ የህግ ድንጋጌዎችን ማውጣት እና ፕሮጄክት 18 ኤሌክትሮኒክ ግብይቶችን እና ዲጂታል ክፍያዎች እንዲጀመሩ የሚያስችል ግልጽ ድንጋጌዎችን፣ ፖሊሲዎችን፣ እና ስታንዳርዶችን ማውጣት፡፡ ይህ ስትራቴጂ እነኚህን ፕሮጄክቶች ወደ ፊት ለመውሰድ ጥልቀት ያለው የድርጊት መርሀ ግብር አስቀምጧል፡፡
- በልማትና እቅድ ኮሚሽን እየተዘጋጀ ያለዉ የአስር አመት ብሔራዊ መሪ/pro-spective/ እቅድ የዲጅታል ክፍያ ምህዳር እድገት ለታቀዱት እቅዶች ውጤታማነት እንደቅድመ ሁኔታ አስቀምጧል፡፡

በሌላ መልኩ በተለያዩ ተቋማት እየተመሩ ያሉ አምስት ሪፎርሞች ከብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ጋር ጥብቅ ቁርኝት አላቸዉ፡፡

- ሀገርበቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም አጀንዳ (እ.ኤ.አ2020-2023) የሀገሪቱን ብሔራዊ ግብ ለማሳካት የፋይናንስ ዘርፍ ሪፎርምን እንደ ቁልፍ አካል ይመለከተዋል፡ ፡ የብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ የቅርብ ክትትል የሚደረግበት ወሳኝ የፋይናንስ ዘርፍ ሪፎርም አካል ነው፡፡ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም አጀንዳ አሁን ያለውን የአስተዳደር አወቃቀር ለዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ለመጠቀም ይፈቅዳል (የበለጠ ማብራሪያ በአስቻይ 3 ቀርቧል)፡፡
- በገንዘብ ሚኒሰቴርና በኢትዩጵያ ኮሚኒኬሽን ባለስልጣን እየተመራ ያለው የቴሌኮሚኒኬሽን ዘርፍ ሪፎርም ለብሔራዊ ድጅታል ስትራቴጂ ስኬት ቁልፍ አስቻይ ነው፡፡ ሪፎርሙ በመንግስት ስር ያለውን ኢትዮ ቴሌኮምን በከፊል ወደ ግሉ ዘርፍ ማዞርን ጨምሮ ሁለት አዳዲስ የቴሌኮም ፍቃድን ለመስጠት አቅዷል፡፡ ሪፎርሙ ሲጠናቀቅ የሞባይል ኦፕሬተሮች በፋይናንስ ዘርፉ ውስጥ እንዲሳተፉ ለዲጂታል ክፍያ መሰረተ ልማት ማስፋፋት ላይ ለሚኖራቸው ሚና ብሔራዊ ባንክ ከቴሌኮሚኒኬሽን ባለስልጣን ጋር በቅርበት በመሆን አስፈላጊ የህግ ድንጋጌዎችና ማዕቀፎች መስራት አለበት፡፡
- በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተዘጋጀው ኤሌክትሮኒክስ ትራንዛክሽን አዋጅ ዲጅታል ክፍያን ወደፊት የሚያሸጋግር ነው፡፡ ብሔራዊ ባንክ የዚህን አዋጅ አፈጻጸም ከብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ጋር በማቆራኘት ይደግፋል፡፡
- በሠላም ሚኒሰቴር እየተመራ ያለዉ የዲጂታል መታወቂያ ፕሮግራም ዲጅታል

ክፍያን ለማሳደግ አስፈላጊ አስቻይን ይፈጥራል፡፡ ፕሮግራሙ በስድስት አመታት ዉስጥ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ልዩ ዲጂታል መታወቂያ እንዲኖራቸዉ ለማስቻል ያለመ ነው፡፡ የዚህ ፕሮግራም አተገባበር ፍጥነትና ስፋት በብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ትግበራ ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ከግንዛቤ ዉስጥ በማስገባት የስትራቴጂዉ ተግባራት በሙሉ ይህንን ታሳቢ ተደረጎ የተቀረጹ ናቸዉ ፡፡

- ብሔራዊ የዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ግንባር ቀደምነት ከጠቅላይ ሚኒሰቴር ቢሮ ጋር በመሆን እየተከናወነ ላለው ንግድን ለመስራት ቀላል ሁኔታን መፍጠር ሪፎርም/ Ease of Doing Business/ ትርጉም ያለው አስቻይ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ይህ Ease of Doing Business ሪፎርም ብዙ የክፍያ ቁርኝት የሚፈልጉ የዲጂታይዜሽን ፕሮግሞች አሉት፣ ለዚህም ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ውጤታማት የነዚህን ሪፎረሞች ውጤታማነት ትርጉም ባለው ሁኔታ ይጨምራል፡፡

ከነዚህ ሪፎርሞች በተጨማሪ ይህ ስትራቴጂ ከሌሎች የመንግስት ኢኒሼቲቮች እንደ የአቅም ግንባታ ጥረት በሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ጋር የሚከናወን ቁርኝነት አለው፡፡

የኢትዮጵ ብሔራዊ ባንክና ይህንን ስትራቴጂ ለመተግበር የሚኖረው መዋቅር፣ ከሀገራዊ የልማት ሪፎርምና ፖሊሲዎች ጋር ቀጣይነት ያለውና ንቁ መተባበር እንደሚኖር ዋስትና ይሰጣል፣ ምክንያቱም ለስተራቴጂው ትግበራ በጣም አስፈላጊ ግብዓት ስለሆነ፡፡

አስቻይ 4፡ የተሟላ የአስተዳደር የትግበራ እቅድ በማዘጋጀት ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያዎችን በመጠቀም ክንውንን መከታተል

የዚህን የብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ጥቅም እውን ለማድረግ የአተገባበር ዕቅድ፣ የተሟላ አስተዳደር መዋቀር እና የክትትል ዕቅድ ያለዉ የአተገባበር ማዕቀፍ መፍጠር ወሳኝ ነው፡፡

የትግበራ ዕቅዱ የድርጊት ምክረ ሃሳቦችን ወደ ሚተገበሩ እቅዶች ያሸጋግራቸዋል፡፡ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ድርጊቶች እንደየትግበራ ቅደም ተከተላቸው ተቀምጠዋል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትግበራ የሽግግር መሰረት ላይ ትኩረት ያደርጋል እነኚህም መሰረተ ልማት እና የህግ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ ሁለተኛው ደረጃ ትግበራ ደግሞ ዲጂታል ክፍያን ለመጠቀም ያሚያስችሉ ግብይቶችን /አገልግሎቶችን/ ማስፋትና ማፋጠን ላይ ትኩረት የደርጋል፡፡

ከሁሉም ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ያሉበት የስትራቴጂ አስተዳደር መዋቀር ለትብብር እና ቁልፍ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ ይረዳል፡፡ በመሆኑም ይህ ስትራቴጂ አራት የአስተዳደር መዋቅር እርከኖች አሉት፣

- ብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ካውንስል፡ ከፍተኛ የባለድርሻ ቡድን ሲሆን ሪፎርሞችን በማደራጀት አቅጣጫ ይሰጣል፡፡
- የዲጂታል ክፍያ ስቲሪንግ ኮሚቴ፡ በብሔራዊ ባንክ ውስጥ ከፍተኛ ቡድን ሲሆን የስትራቴጂዉን ትግበራ ይከታተላል፡ ፡
- የፕሮግራም አስተዳደር ክፍል፡ በብሔራዊ ባንክ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን የቀን ተቀን ትግበራን ይከታተላል ያስተዳድራል፡፡
- የትግበራ ቡድኖች፡ ቴክኒካል ቡድን ሲሆን ድረጊቶቹን የሚከውን ነዉ፡፡

ለለስትራቴጂው ትግበራ ስኬት የክትትል ዕቅድ ወሳኝ ነዉ፡፡ እያንዳንዱ ተግባር የራሱ የሆነ የታለመለትን ዉጤት የዲጅታል ትግበራን ማፋጠን እና የፋይናንስ አካታችነትን ማምጣቱን ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚለካበት ቁልፍ የአፈጻጸም መለኪያዎች አሉት፡

ሐ.

የትግበራ ማዕቀፍ

ሐ1. የትግበራ ዕቅድ

የብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ ትግበራ በሁለት ደረጃ ይከናወናል፤ ሽግግርን መመስረት እና ማፋጠን። የመጀመሪያዉ ደረጃ ትግበራ:- ሽግግርን መመስረት የሚያተኩረው ተገቢው የዲጅታል ክፍያ መዋቅር መኖሩን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህም እንከን የለሽ እና ተናባቢ መሰረተ ልማትን ማከናወን እና የዲጅታል ክፍያን ትግበራ እንዲኖር የሚያስችል የህግ ድንጋጌን ይጨምራል፡፡ ሁለተኛው ደረጃ ትግበራ:- ሽግግርን ማፋጠን የዲጂታል ክፍያን ለመጠቀም የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ስኬትና እድገት ማኖር ላይ ያተኩራል፡፡

የስትራቴጂክ ትግባራን አስፈላጊነት መሰረት በማድረግ ለሚመጡት ሶስት አመታት የሚተገበሩ እንደ አስፈላጊነታቸው ቅድሚያ በሚየስፈልጋቸው ትግበራ ተቀምጧል (ምስል 15 ተመልከት)፡፡ ለድርጊት ትግበራ ቅድሚያ መስጠት ሂደት ወቅት እና ለትግበራ አመቺ እና ተጽዕኖ ያላቸው እንዲሆኑ ከፍተኛ፤ መካከለኛ እና ዝቅተኛ በሚል በደረጃ ተቀምጠዋል፡፡ ምቹ የአተገባበር ስልት ማለት፡ (i) ቴክኒክና ውስብስብነት (የሂደትና አሰራር ለውጥ ይፈልጋል) ፤ (ii) የባለድርሻ ቁጥር (አንድ ተቋም ከአንድ በላይ ተቋማት ላይ መወሰን)፤ እና (iii) የትግበራ ሂደት (አንድ ድርጊት ከብዙ ደረጃዎች): : ተጽዕኖ ማድረግ ማለትም፡- (i) የዲጅታል ክፍያን አስፈላጊነት፤ (ii) የፋይናንስ አካታችነት ላይ ያለው ተጽዕኖ፤ እና (iii) የሚደረስበት የትራንዛክሽን መጠን ።

በምስል 16 እንሚታየው የትግበራ እቅድ የጊዜ ማዕቀፍ ለእያንዳንዱ የተለዩ ድርጊቶች እና የተገመተላቸው የመተግበሪያ ጊዜ ተቀምጧል፡ : በአፋጣኝ የሚተገበሩ፤ በከፍተኛ ቅድሚያ እና በረጅም ጊዜ የሚተገበሩ ከመካከለኛ ግዜ ከሚተገበሩ ድርጊቶች ቅድሚያ ይወስዳሉ፡፡

ለአተገባበር ምቹነት እና ለውጥ ለማምጣት የድርጊቶች አተገባበር በአምስት ደረጃዎች ተቀምጧል፡፡

በአፋጣኝ የሚተገበሩ፡ ከፍተኛ ተጽዕኖ እና ለአተገባበር ምቹነት፤- እነኚህ ድርጊቶች የድጂታል ክፍያን መተግበር የሚያፋጥኑ እና አነስተኛ ጥረትና በመከናወን ላይ ያሉ በመሆናቸው በጣም በአጭር ጊዜ የሚተገበሩ ይሆናሉ፡፡

ከፍተኛ ቅድሚያ የሚሰጣቸው፡ መካከለኛ ተጽዕኖ እና ከፍተኛ የአተገባበር ምቹነት፤- የዲጅታል ክፍያን የሚያስኬዱ /የሚያፋጥኑ/ ድርጊቶችን በቶሎ ማጠናቀቅ፡፡

በከፍተኛ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ግን በረጅም ጊዜ የሚተገበሩ፡ ከፍተኛ ተጽዕኖ እና ለአተገባበር መካከለኛ ምቹነት፤- የዲጅታል ክፍያ ትግበራን ለማፋጠን ወሳኝ የሆኑ ነገር ግን ከውስብስነትና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ስለሚያሳትፍ ረጅም የግዜ ሂደት የሚያስፈጋቸው ድርጊቶች ናቸው፡፡

አነስተኛ ቅድሚያ የሚሰጣቸው፡ አነስተኛ ወይም መካከለኛ ተጽዕኖ እና ለአተገባበሩ አነስተኛ ምቹነት፤- አነስተኛ ተጽዕኖ ያላቸው እና ተጨማሪ ጥረት ለአተገባበር የሚየስፈልጋቸው ናቸው፡፡

ምስል 16፡ የድረጊት መረሀግብር ቅድመ ተከተል

	ቅድሚያ የሚሰጣቸዉ	የመተግበሪያ ጊዜ
	በአፋጣኝ የሚተገበሩ ተግባራት	
5	ለኤሌክትሮኒክ የገንዘብ ዝውውር የሚያገለግል በቴክኖሎጂ የታገዘ የማጣሪያ መሰረተ ልማት /Automated Clearing House (ACH)/ ማቋቋም	6 ወር
20	ያታን መሰረት ያደረገ መረጃን በመሰብሰብ ሃላፊነት ያለባቸዉና ዓለምአቀፍ ዉሳኔ ሰጪ አካላትን ማሳወቅ	12 ወር
24	አዲሱን የወኪል አጠቃቀም መመሪያ ተግባራዊነት መከታተል	በሂደት ላይ ነዉ
25	የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ባንክ ያልሆኑ የፋይናንስ ተቋማት ተሳትፎ መከታተል	በሂደት ላይ ነዉ
26	አዲሱን የደንበኛህን እወቅ ህግ ተግባራዊነት መከታተል	በሂደት ላይ ነዉ
30	የፊንቴኮችን ተግባርና ሃላፊነት ግልጽ ማድረግ	12 ወር
	በከፍተኛ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጠዉ	
1	ከገንዘብ መክፈያ ማሽንና የክፍያ ነቁጥ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ቴክኒካዊ ችግሮችን መፍታት	12 ወር
3	የወኪል አገልግሎትን ለማስፋፋት የቢዝነስ ተሞክሮዎችን መከለስ	በሂደት ላይ ነዉ
18	ዲጂታል የክፍያ አማራጮችን በተመለከተ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን መፍጠር	በሂደት ላይ ነዉ
23	የህግ ድንጋጌዎችን ማጠናከርና የቁጥጥር አቅምን ማጎልበት	12 ወር
27	የፋይናንስ ደንበኞችን ጥበቃ ማጠናከር	በሂደት ላይ ነዉ
29	እልክትሮኒክስ ደረሰኞችን በክፍያ ማረጋገጫነት መቀበል የሚያስችል ህግ ማዉጣት	6 ወር
	ከፍተኛ ቅድሚያ የመሰጣቸዉ- በረጅም ገዜ የሚተገበር	
4	የቴሌኮም ተደራሽነትን በኔትወርክ ሽፋንና በአገልግሎት መሣሪያዎች አቅርቦት ረገድ ማሳደግ	በሂደት ላይ ነዉ
6	በሁሉም ተዋንያንና የክፍያ መንገዶች ተናባቢነትን ማሳደግ	24 ወር
10	የመንግስትና በመንግስት ስር ያሉ ኢንተርፕራይዞችን ክፍያና ገቢ መሰብሰቢያ አሰራር ዲጂታይዝ ማድረግ	በሂደት ላይ ነዉ
	መካከለኛ ትኩረት የሚሰጣቸዉ	
2	የገንዘብ መክፈያ ማሽንና የክፍያ ነቁጥ አገልግሎት መስጫዎችን ቁጥር ማሳደግ	በሂደት ላይ ነዉ
7	የክፍያ ጌትወይ ማበልጸግ	12 ወር
8	የሪልታይም /RTP/ ክፍያ አማራጭን መተግበር	9 ወር
11	የማህበራዊ ዋስትናና ሰብዓዊ ድጋፎችን ዲጂታይዝ ማድረግ	በሂደት ላይ ነዉ
12	በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የሚደረጉ ከቱሪዝም ጋር የተያያዙ ዝውውሮችን ዲጂታይዝ ማድረግ	በሂደት ላይ ነዉ
14	ድንበር ተሻጋሪ የሐዋላ ዝውውሮችን ዲጂታይዝ ማድረግ	በሂደት ላይ ነዉ
15	ለገንዘብ ተቋማት ጥሬ ገንዘብ ላይ ክፍያ መተግበር	12 ወር
16	በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ዝውውሮች ላይ ገደብ መጣል	12 ወር
21	ከፋይናንስ አገልግሎቶች የተገለሉትን የህብረተሰብ ክፍሎችን ያማከለ አገልግሎቶችንና መፍትሔዎችን ማስጀመር	በሂደት ላይ ነዉ
22	ባለብዙ ቋንቋ አገልግሎቶችን ማበረታታት	3 ወር
28	የሳይበር ደህንነትን ማጠናከር	6 ወር
31	የፊነቴክ ዓለምአቀፍ ሀብቶችን ተደራሽነትን ማስፋት	በሂደት ላይ ነዉ
	አነስተኛ ቅድሚያ የሚሰጣቸዉ	
9	የባንክ የክፍያ መሳሪያዎች ተመሳሳይና ወጥ እንዲሆኑ ማስቻል	በሂደት ላይ ነዉ
13	የግብርና ዘርፍን ዲጂታይዝ ማድረግ	በሂደት ላይ ነዉ
17	በኤሌክትሮኒክስ ክፍያ ለሚከናወኑ የግብር ማዘዋዎች ማበረታቻዎችን ማድረግ	6 ወር
19	የዲጂታል ክፍያ መጠቀሚያ ሁናቴን መሰረት የደረገ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን መቅረጽ	3 ወር
32	ስጋቶችን በአግባቡ በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚያስችል የፈጠራና ቴክኖሎጂ ልማት ማዕቀፍ መፍጠር	6 ወር

ምስል 17፡ የድርጊቶች መተግበሪያ የጊዜ ማዕቀፍ



ሐ2. አስተዳደራዊ መዋቅር

ጠንካራ የአስተዳደር ማዕቀፍ የስትራቴጂውን ትግበራ ሂደት በሶስት አመት ከግማሽ ጊዜ ውስጥ ለመከታተል ወሳኝ ነው፡፡ የአስተዳደር መዋቅሩ የብሔራዊ ዲጂታል ስትራቴጂን በተሳካ ሁኔታ ለመተግበር አላማ ያለዉ ውሳኔ፣ ተጠያቂነት፣ ቁርኝነት እና በባለድርሻ አካላት መካከል ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ማስቻል አለበት፡፡

በምስል 18 እንደሚታየው የአስተዳደር መዋቅሩ አራት እርከኖች አሉት፡

- ብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ካውንስል
- የዲጅታል ክፍያዎች ስቲሪንግ ኮሚቴ
- የፕሮግራም አስተዳደር
- የድርጊት ቡድኖች

ብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ካውንስል የተቋማት ስብጥር ሲሆን የዲጅታል ክፍያን የማሻሻል አላማ አለው፡፡ ስትራቴጂክ አቅጣጫ የመስጠት እና ከሌሎች ብሔራዊ ሪፎርሞች እና ፖሊሲዎች ጋር የማስተባበር አላማ አለው፡፡ አተገባበሩን በክልሎች መዋቅር ማውረድ እጅግ አስፈላጊ ነዉ፡፡ የካውንስሉ ሰብሳቢ የብሔራዊ ባንክ ገዥ ሲሆን ምክትል ሊኖረው ይችላል፡፡ ካውንስሉ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጸ/ቤት፣ ከሌሎች አስፈላጊ ሚኒስቴር መስሪያቤቶች እንደ ገንዘብ ሚኒሰቴር፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የገቢዎች ሚኒስቴር የግብርና ሚኒስቴር፣ የብሔራዊ መረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ፣ የኮሚኒኬሽን ባለስልጣን፣ ከግል ዘርፍ ደግሞ ከገንዘብ ተቋማት፣ ከሞባይል ኔትወርክ ኦፕሬተሮች፣ እና የፊንቴኮች ተወካዮች ይኖሩታል፡፡ ከካውንስሉ ዋና ሃላፊነቶች ለአተገባበሩ ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ድጋፍ ማስገኘት፣ ለቁልፍ ጥያቄዎች ስትራቴጂክ አቅጣጫዎችን ማሳየት፣ እና ለትግበራ እቅዱ የሚያስፈልጉ የብሔራዊ ፖሊሲ መከለስ እና መቀየር፡፡ በፕሮጄክት አስተዳደር ድጋፍ እና በስቲሪንግ ኮሚቴ አመቻችነት ካውንስሉ በየሶስት ወሩ እየተገናኘ ከፕሮጄክት አስተዳደር በሚገኘው የወር ሪፖርት የስትራጂውን አፈጻጸም ይገመግማል።

የዲጅታል ክፍያ ስትሪንግ ኮሚቴ በብሔራዊ ባንክ ውስጥ ሆኖ የስትራጂው መሪ አካል ነው፡፡ ሌሎች ተቋማት በግብዣ ስቲሪነግ ኮሚቴውን ሊቀላቀሉ ይችላሉ፡፡ የኮሚቴው አላማ

ምስል 18፡ የአተገባበር አስተዳደር መዋቅር

የብሔራዊ ዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ በጊዜና በስኬት መከናወኑን መከታተል ነው፡፡ የስትሪንግ ኮሚቴ ሰብሳቢ የፋይናንስ ተቋማት ሱፐርቪዥን ዘርፍ ምክትል ገዢ ሲሆን፣ የብሔራዊ ባንክ ዳይሬክቶሬቶች እና ሌሎች በአባልነት ይኖራሉ፡፡ ከብሔራዊ ባንክ የክፍያና ሒሳብ ማወራረጃ ዳይሬክቶሬት፣ ባንክ ሱፐርቪዥን ዳይሬክቶሬት፣ አነስተኛ የገንዘብ ተቋማት ሱፐርቪዥን ዳይሬክቶሬት፣ የፋይናንስ አካታችነት ጽ/ቤት የኢንፎርሜሽን ሲስተም ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሮች እና የክፍያ ስርዓት ልማትና ክትትል ፕሪንሲፓል ሲሆኑ ከሌሎች ተቋማት ደግሞ የባንኮች ማህበር ተወካይ፣ እና አማካሪዎችን ይይዛል፡፡ ስትሪንግ ኮሚቴው የስትራቴጂውን አተገባበር የመከታተል፣ አቅጣጫ የማሳየት፣ የድርጊት ቡድኖችን የአተገባበር መንገድ የማረጋገጥ ሃላፊነቶች አሉት፡፡ በተጨማሪም ስትሪንግ ኮሚቴው ከብሔራዊ ባንክ መዋቅር ጋር በመናበብ ፖሊሲ ለውጦችን ሳያካትት ምክረ ሀሳቦችን የማየት እና የማጽደቅ ስትራቴጂውን በተመለከተ መረጃዎችን ማሰራጨት እና የእውቀት ልውውጥ መርሀ ግብር ውስጥ መሳተፍ ሃላፊነት አለበት፡፡ በየአስራ አምስት ቀኑ መረጃን በማግኘት ይህ ስትሪንግ ኮሚቴ በየወሩ እየተሰበሰበ የስትራቴጂውን ትግበራን ይገመግማል፡፡

የስትራቴጂውን ትግበራ ለማስተዳደር የፕሮግራም አስተዳደር ክፍሉ አስፈላጊውን ሀብት በመያዝ በብሔራዊ ባንክ ክፍያና ማወራረጃ ሲስተም ውስጥ ይቋቋማል፡፡ የዚህ ክፍል አላማ መረጃን በመሰብሰብ እና በመተንተን ትብብርንና በተለያዩ የመዋቀር እርከን ላይ ለሚወሰን ውሳኔ ድጋፍ ማድረግ ነው፡፡ የፕሮግራም አስተዳደሩ ክፍል ሶስት ወይም አራት በላቀ ሽግግር ፣ በአስተዳደር ብቃት፣ በሀብት አስተዳደር ምደባ እና የክፍያና ሒሳብ ማወራረጃ ሞያተኛ የሆኑ ባለሞያዎች ይኖሩታል፡፡ ይህ ክፍል የስትራጂውን ጠቅላላ ትግበራ ያስተዳድራል፣ ጥልቅ የትግበራ ዕቅድ የዘጋጃል፣ መደላድሎችንና አቅርቦቶችን ይከታተላል፡፡ በተለያዩ የአስተዳደር እርከኖች መካከል ስብሰባዎችን ያመቻቻል እንዲሁም መረጃን ያከፋፍላል፣ መረጃን ይሰበስባል ይተነትናል እንዲሁም ይተረጉማል፣ እና ስጋትን ይከታተላል አስፈላጊ ከሆነም ወደ በላይ አካል ያቀርባል፡፡ በየአስራ አምስት ቀኑ ከተግባር ቡድኖች ጋር በመገናኘት መረጃን በመሰብሰብ ጥልቅ ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡ በተጨማሪም የፕሮግራም አስተዳደሩ የስቲሪነግ ከሚቴን እና የካውንስል ስብሰባዎችን ያመቻቻል፡፡

የተግባር ቡድኖች ከተግባሪ ተቋማት የሚወከሉበት የቴክኒካል አባላት አሉት፡፡ አላማቸው የተለዩ ድርጊቶችን ማከናወን፣ ስጋቶችን በመቀነስ ድርጊቶችን ይከውናል በተጨማሪም ለፕሮግራም አስተዳደር ክፍል መረጃዎችን ያቀርባል፡፡ እያንዳንዱ የተግባር ቡድን ለተለያዩ ተግባራት ተጠያቂ ነው፡፡ የትግበራ ቡድኖች አባላቱ በትግበራ ሊለያዩ ይችላሉ፡፡

ሐ3. የክትትል ዕቅድ

ለብሔራዊ ዲጂታል ስትራቴጂ ውጤታማነት የክትትል ዕቅድ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ የክትትል ዕቅድ የዲጅታል ክፍያ ስትራቴጂ የዲጅታል ክፍያን ልምምድ ማደግ እና የፋይናንስ አካታችነትን መጨመር ማሳካቱን ለመመዘን እንደ መሳሪያ ያገለግላል፡፡ ቁልፍ የውጤታማነት ማሳያዎች የስትራቴጂውን ተጽዕኖ በጊዜ ሂደት ያሳያሉ እንዲሁም የድርጊት ቡድኖች የአተገባበር መንገዳቸውን አስፈላጊ ከሆነ እንዲቀይሩ ይረዳቸዋል፡፡

የድርጊት ቡድኖች በየአስራ አምስት ቀኑ ለፕሮጄክት አስተደደር ስትራቴጂው አጠቃላይ የደረሰበትን ደረጃ መረጃ ይሰጣሉ፡፡ መረጃው ስትራቴጂው ያለበትን ጠቅላላ ደረጃ በአረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ወይም ቀይ ቀለም በማድረግ ይይዛል፣ በባለፉት ሁለት ሳምንት ያለቁ ተግባራት፣ ለሚመጡት ሁለት ሳምንታት የታቀዱ ስራዎችን ይይዛል፣ እንዲሁም ስጋቶችን የመቀነስ፣ መሰረቶችን ማደላደል እና ቁልፍ የውጤታማነትን ማሳያዎች የመሳሰሉ ጉዳዮችን ይይዛል፡፡

የቃላትና ሀረጎች ፍቺ

አውቶሜትድ ቴለር ማሽን : እራስ ሰር የሆነ የገንዘብ መክፈያ ማሽን

የክፍያ ነቁጥ፡ በግብይት ወይም በአገልግሎት መስጫ ስፍራ የሚቀመጥ ሆኖ ክፍያን በክፍያ ካርድ፣ በሞባይል ወይም በኤልክትሮኒክስ ዘዴ መክፈል የሚያስችል ማሽን

የሞባይል ክፍያ ነቁጥ፡ በሞባይል አማካኝነት በግብይት ስፍራ በኤልክትሮኒክስ ክፍያ አማራጮች (ዴቢት ካርድ፣ ክሬዲት ካርድ፤ ሞባይል ገንዘብ እና የመሳሰሉት) ያለንክኪ ክፍያን መፈጸም የሚያስችል ማሽን

አውቶሜትድ ክሊሪንግ ሀውስ፡ እራስ ሰር የሂሳብ ማጣሪያ ፤

ኢትስዊች፡ በሁሉም የፋይናንስ ተቋማት ባለቤትነት የሚተዳደር እና በፋይናንስ ስርዓት ውስጥ ለአነስተኛ ክፍያዎች የተነባቢነት እና የማዕከላዊ ስዊች አገልግሎት የሚሠጥ

ፊንቴክ፡ በቴክኖሎጂ አማካኝነት የፋይናንስ አገልግሎቶችን የሚሰጥ፤ የሚያሳልጥ እንዲሁም በቴክኖሎጂ አማካኝነት የፋይናንስ ተጠቃሚዎችን ከፋይናንስ ተቋማት ጋር የሚያገናኝ ተቋም

ሞባይል ዋሌት፡ የሞባይል ገንዘብ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ሂሳብ ውሥጥ የሚገኝ ገንዘብ ሆኖ በሞባይል የሚንቀሳቀስ

ዴቢት ካርድ፡ ከመደበኛ ቁጠባ ሂሳብ ጋር የሚገናኝ የክፍያ ካርድ

ክሬዲት ካርድ፡ ከብድር ሂሳብ ጋር የሚገናኝ የክፍያ ካርድ

የክፍያ ጌትወይ: በኢንተርኔት ወይም በሞባይል መተግበሪያ አማካኝነት ክፍያ እንዲከናወን የሚያስችል ስርዓት

ክላውድ ፈንዲንግ : ለአስፈላጊ ፕሮጀክቶች ከብዙ ሰው አስፈላጊውን ገንዘብ የማሰባሰብ ዘዴ

ወኪል እንደ ፋይናንስ ተቋም ሁኖ የፋናንስ አገልግሎት የሚሰጥ

ዲጅታል ክፍያ ክፍያን እንደ በክፍያ ካርድ፤ ኤልክትሮኒክ ገንዘብ፤ በአውተማቲክ ተለር ማሽን፣ በክፍያ ነቁጥ፤ ሞባይል ስልክ እና በመሳሰሉት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አማካኝነት ገንዘብን ማስተላለፍ

የዲጅታል ክፍያ መሳሪያዎች የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ሲሆኑ፣ ክፍያ በዲጅታል ለማስተላለፍ የሚረዱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ ኤቲኤም፣ የክፍያ ነቁጥ፣ ኮምፒውተር፣ ሞባይል ስልክ

ተናባቢነት አንድ የክፍያ ስርዓት ወይም የክፍያ ሰነድ ከሌላ የክፍያ ስርዓት ወይም የክፍያ ሰነድ ክፍዎች በቀላሉ እንዲተላለፉ የሚያስችል ስርዓት

የሞባይል ባንኪንግ: መደበኛ የባንክ ሂሳብን በሞባይል አማካኝነት ማንቀሳቀስ

የክፍያ መተግበሪያ: የኮምፒውተር ፕሮግራም ወይም ሶፍትዌር ሲሆን በሞባይል ስልክ አማካኝነት ከክፍያ አገልግሎት ሰጪዎች ጋር በመገናኘት ክፍያን መፈጸም ወይም የክፍያ መረጃን ማግኘት የሚያስችል መተግበሪያ

የክፍያ ሰነድ አውጪዎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፍቃድ ያላቸው የክፍያ ሰነድየሚያቀርቡ ተቋማት

የክፍያ ሰነዶች የሚታዩ (ዴቢት ካርድ፣ ክሬዲት ካርድ፣ ቮቸር የመሳሰሉት) እና የማይታዩ (ሞባይል ገንዘብ) አይነቶች ሲሆኑ ክፍያን ለመፈጸም የሚውሉ

ስዊች የክፍያ ከባቢ አካል ሲሆን ክፍያ ትዛዞችን በክፍያ ስርአቶችና ተዋናዮች መካከል የሚያስተላልፍ ስርዓት

ባለነጭ ምልክት የገንዘብ

መክፍያ ማሽኖች: በሶስተኛ ወገን የሚተዳደሩ እና በባለቤትነት የሚያዙ የክፍያ ማሽኖች ሲሆኑ የጥሬ ገንዘብ አቅርቦቱም በሶስተኛ ወገን የሚከናወን ነው

ባለቡናማ ምልክት

የገንዘብ መክፍያ ማሽኖች: በሶስተኛ ወገን የሚተዳደሩ እና በባለቤትነት የሚያዙ የክፍያ ማሽኖች ሲሆኑ የጥሬ ገንዘብ አቅርቦቱ በባንኮች በኩል የሚከናወንነዉ

ክሪፕቶ ከረንሲ የወረቀት ገንዘብ ያልሆነ ለመገበያያ የሚውል የዲጅታል ገንዘብ ነው

ማጣቀሻ

Aid & International Development Forum, 2016, Eight Principles for Digital Payments in Humanitarian Response, September 30, http://www.aidforum.org/topics/mobile-for-development/eight principlesfor-digital-payments-in-humanitarian-response/.

Alliance for Financial Inclusion, 2018, 'Innovative Cross-Border Remittance Services: Experiences from AFI Member Countries', Guideline Note, No. 30, Alliance for Financial Inclusion, Kuala Lumpur, https://www.afi-global.org/sites/default/files/publications/2018-09/AFI_DFS_cross border_AW_digital.pdf.

Alliance for Financial Inclusion, 2019, KYC Innovations, Financial Inclusion and Integrity in Selected AFI Member Countries, Alliance for Financial Inclusion, Kuala Lumpur, https://www.afiglobal.org/sites/default/files/publications/2019-03/KYC-Innovations-Financial Inclusion-IntegritySelected-AFI-Member-Countries.pdf.

Asian Development Bank, 2019, The Future of Work and Education for the Digital Age: The Need to Promote Digital Financial Literacy for the Digital Age, Asian Development Bank, Tokyo, https://financialcapability.gov.au/files/the-need-to-promote-digital-financial-literacy-for-the digitalage.pdf.

Banco do Brasil, 2020, https://www.bb.com.br/pbb/pagina-inicial. Bank for International Settlements, 2019, 'Proceeding with caution –a survey on central bank digital currency', BIS Papers 101, Bank for International Settlements, Basel, https://www.bis.org/publ/bppdf/bispap101.pdf.

Bank of Thailand, 2017, Payment Systems Report, Bank of Thailand, Bangkok.

Better Than Cash Alliance, 2016, Responsible Digital Payments Guidelines, Better Than Cash Alliance, New York, https://www.betterthancash.org/tools-research/case-studies/responsible-digital paymentsguidelines.

Better Than Cash Alliance, 2018, Igniting SDG progress through digital financial inclusion, Better Than Cash Alliance, New York, https://sustainabledevelopment.un.org/content/documents/2655SDG_Compendium_Digital_Financial_ Inclusion_ September_2018.pdf.

Better Than Cash Alliance, 2020a, Government Toolkit – Glossary, https://www.betterthancash.org/tools-research/toolkits/government/general resources/paymentsglossary/glossary.

Better Than Cash Alliance, 2020b, G20 Presentation: Advancing Women's Economic Participation, Better Than Cash Alliance, New York.

Boorstin, J., 2017, 'Going cashless to fight rising financial crime', CNBC, April 20, https://www.cnbc.com/2017/04/20/going-cashless-to-battle-financial-crimes-.html.

Central Bank of Kenya, 2020, Press Release: Emergency Measures to Facilitate Mobile Money Transactions, March 16, https://www.centralbank.go.ke/uploads/press_releases/2125980791_Press%20Release%20- %20Emergency%20 Measures%20to%20Facilitate%20Mobile%20Money%20Transactions.pdf.

CGAP, 2019, China: A Digital Payments Revolution, Consultative Group to Assist the Poor, Washington, D.C., https://www.cgap.org/research/publication/china-digital-payments-revolution.

Demirgüç-Kunt, A., Klapper, L., Singer, D., Ansar, S. & Hess, J., 2018, The Global Findex Database 2017: Measuring Financial Inclusion and the Fintech Revolution, World Bank Group, Washington, D.C., https://globalfindex.worldbank.org/sites/globalfindex/files/2018- 04/2017%20Findex%20full%20report_0.pdf.

Eschenbacher, S., & Irrera, A., 2019, 'Mexico pushes mobile payments to help unbanked consumers ditch cash', Reuters, February 19, https://www.reuters.com/article/us-mexico fintechunbanked/mexico-pushes-mobile-payments-to-help-unbanked-consumers-ditch-cash idUSKCN1Q80FN.

Ethiopian Treasures, 2020, Language, http://www.ethiopiantreasures.co.uk/pages/language.htm.

EthSwitch Steering Committee, 2019, Quarterly Transaction Bulletin, October–December.

Faz, X., & Dias, D., 2011, A Bold Move Toward Simplifying AML/CFT: Lessons from Mexico, Consultative Group to Assist the Poor, May 19, https://cgap.org/blog/bold-move-toward-simplifying-amlcft-lessonsmexico. Financial Action Task Force, 2020, Guidance on Digital ID, https://www.fatfgafi.org/publications/fatfrecommendations/documents/digital-identity guidance.html

Garcia Arabehety, P., Chen, G., Cook, W. & McKay, C., 2016, 'Digital Finance Interoperability & Financial Inclusion: A 20-Country Scan', Working Paper, Consultative Group to Assist the Poor, Washington, D.C., https://www.cgap.org/sites/default/files/researches/documents/interoperability.pdf.

Global Legal Group, 2019, Kenya: Anti Money Laundering 2019. Global Legal Group, London, https://iclg.com/practice-areas/anti-money-laundering-laws-and-regulations/kenya.

Global Partnership for Financial Inclusion, 2016, G20 High-Level Principles for Digital Financial Inclusion, https://www.gpfi.org/sites/gpfi/files/G20 High Level Principles for Digital Financial Inclusion.pdf.

Goodwin-Groen, R., 2020, Putting Digital Payments to Work in the Time of COVID-19, Better Than Cash Alliance, March 31, https://www.betterthancash.org/news/blogs-stories/putting-digital-payments-towork-in-the-time-of-covid-19.

Government of Ethiopia, 2019, Homegrown Economic Reform Agenda, Government of Ethiopia, Addis Ababa, https://pmo.gov.et/media/documents/Ethiopia 0509_Economic_Reform_Agenda.pptx.

Grupo Financiero Banorte, 2019, Annual Report 2018, Grupo Financiero Banorte, Monterrey, https://investors.banorte.com/~/media/Files/B/Banorte-IR/financial information/annualreports/en/2018/ANUALREPORT1BANORTE2018.pd.

GSMA, 2019a, Mobile money enabled cash aid delivery: Essential considerations for humanitarian practitioners, GSMA, Atlanta, GA, https://www.gsma.com/mobilefordevelopment/wpcontent/uploads/2019/04/Essential_Considerat ons_for_Using_Mobile_Money.pdf.

GSMA, 2019b, mAgri Webinar: How to prioritise agricultural value chains for digital interventions, GSMA, April 3, https://www.gsma.com/mobilefordevelopment/resources/magri-webinar-how-to-prioritiseagricultural-value-chains-for-digital-interventions/.

GSMA, 2020, Mobile subscription figures for 2019, GSMA, Atlanta, GA.

Gulati, V.P. & Srivastava, S., 2007, The Empowered Internet Payment Gateway, Computer Society of India, New Delhi, https://www.csi-sigegov.org/2/10_342_2.pdf.

HSBC UK Bank, 2019, Annual Report and Accounts 2018, HSBC UK Bank, London, https://www.hsbc.com/-/files/hsbc/investors/hsbc-results/2018/annual/hsbc-uk-bank-plc/190219- annual-report-and-accounts-2018.pdf/.

India Brand Equity Federation, 2011, RBI incentive to banks opening branches in rural areas, India Brand Equity Federation, July 18,
https://www.ibef.org/news/29360. International Monetary Fund, 2020, Financial Access Survey 2004–2018, https://data.imf.org/?sk=E5DCAB7E-A5CA-4892-A6EA-598B5463A34C.

International Organization for Migration, 2017, Scaling Up Formal Remittances to Ethiopia, International Organization for Migration, Brussels, https://www.iom.int/sites/default/files/press_release/file/iomethiopia-executive-summary-21.pdf.

International Telecommunications Union, 2020, Internet subscription figures for 2017, International Telecommunications Union, Geneva.

International Telecommunications Union Media Centre, 2019, Digital Financial Inclusion, https://www.itu.int/en/mediacentre/backgrounders/Pages/digital-financial-inclusion.aspx. Joy Online,
Bawumia launches Ghana and Africa's first universal QR Code, Joy Online, March 25, 2020, https://www.myjoyonline.com/business/bawumia-launches-ghana-and-africas-first-universal-qr-code/.

KCB Bank, 2019, 2018 Integrated Report and Financial Statements, KCB Bank, Nairobi, https://kcbgroup.com/wp-content/uploads/2019/05/KCB-Group-Integrated-Report-and-FinancialStatements-2018.pdf.

Knowledge@Wharton, 2018, Going cashless: What can we learn from Sweden's experience, Wharton School of the University of Pennsylvania, August 31, https://knowledge.wharton.upenn.edu/article/going-cashless-can-learn-swedens-experience/.

Krishnan, A., 2019, 'Demonetization Anniversary: Decoding the Effects of Indian Currency Notes Ban', The Economic Times, May 21, https://economictimes.indiatimes.com/tdmc/yourmoney/demonetization-anniversary-decoding-the-effects-of-indian-currency-notesban/articleshow/61579118.cms?from=mdr.

Lindsey, D., & Wilson, A., 2019, "Accessibility": How mobile operators can improve the accessibility of their services for women to help close the mobile gender gap, GSMA, March 25, https://www.gsma.com/mobilefordevelopment/blog/accessibility-how-mobile-operators-can-improvethe-accessibility-of-their-services-for-women-to-help-close-the-mobile-gender-gap/.

Mai, H., 2016, 'Cash, freedom and crime: Use and impact of cash in a world going digital', EU Monitor: Global financial markets, November 23, Deutsche Bank Research, Frankfurt am Main, https://www.dbresearch.com/PROD/RPS_ENPROD/PROD0000000000441785/Cash%2C_freedom_and_crime%3A_Use_and_impact_of_cash_in.pdf.

Manikandan, A., 2019, 'RBI announces new guidelines for "failed" ATM transactions', The Economic Times, September 20, https://economictimes.indiatimes.com/industry/banking/finance/banking/rbiannounces-new guidelines-for-failed-atm-transactions/articleshow/71224066.cms?from=mdr.

Massi, M., Sullivan, G., Strauß, M. & Khan, M., 2019, How Cashless Payments Help Economies Grow, Boston Consulting Group, May 28, https://www.bcg.com/publications/2019/cashless-payments-helpeconomies-grow.aspx.

MasterCard, 2016, Press Release: MasterCard to Expand Digital Aid Distribution Services, May 23, https://newsroom.mastercard.com/press-releases/mastercard-to-expand-digital-aid-distributionservices/.

Mattern, M., 2018, How Ghana Became One of Africa's Top Mobile Money Markets, CGAP, June 21, https://www.cgap.org/blog/how-ghana-became-one-africas-top-mobile-money-markets.

Mburu, J., 2018, Why is mobile money interoperability important for Kenya?, FSD Kenya, April 26, https://fsdkenya.org/blog/why-is-mobile-money-interoperability-important-for-kenya/.

MInT, 2020, Digital Ethiopia 2025 – A Strategy for Ethiopia Inclusive Prosperity (Draft), Ministry of Innovation and Technology, Addis Ababa.

Moneytrans, 2018, Digital Payments Triumph in Uruguay thanks to tax incentives, September 25, https://www.moneytrans.eu/moneytransblog/en/uruguay-digital-payments/.

NBE, 2008, Banking Business Proclamation No. 592/2008, National Bank of Ethiopia, Addis Ababa, https://nbebank.com/wp-content/uploads/2019/04/BANKING-BUSINESS-592.pdf.

NBE, 2011, National Payment System Proclamation No. 718/2011, National Bank of Ethiopia, Addis Ababa, https://nbebank.com/wp-content/uploads/2019/04/nationalpaymentsystem.pdf.

Niehaus, C. & Cook, W., 2018, Balancing the Economics of Interoperability in Digital Finance, CGAP, January 23, https://www.cgap.org/blog/balancing-economics-interoperability-digital-finance.Nkamgang Bemo, V., Aberra, D., Zimmerman, J.M., Lanzarone, A. & Lubinski, D., 2017, Enabling Digital Financial Services in Humanitarian Response: Four Priorities for Improving Payments, Bill & Melinda Gates Foundation, Seattle, WA, https://leveloneproject.org/wp-content/uploads/2017/02/EnablingDigital-Financial-Services-in-Humanitarian-Response-Four Priorities-for-Improving-Payments.pdf.

OECD, 2018, G20/OECD INFE Policy Guidance: Digitisation and Financial Literacy, Organisation for Economic Co-operation and Development, Paris, http://www.oecd.org/g20/G20-OECD-INFE PolicyGuidance-Digitalisation-and-Financial-Literacy.pdf.

Ozyurt, S., 2019, 'Ghana is now the fastest-growing mobile money market in Africa', Quartz Africa, July 9, https://qz.com/africa/1662059/ghana-is-africas-fastest-growing-mobile-money-market/.

Ryan, O., 2019, Harnessing the power of agents to drive female inclusion, GSMA, March 29, https://www.gsma.com/mobilefordevelopment/blog/harnessing-the-power-of-agents-to-drive-femalefinancial-inclusion/.

Remo, M.V., 2012, 'BSP ups incentives for rural banks' consolidation', Philippine Daily Inquirer, May 16, https://business.inquirer.net/59845/bsp-ups-incentives-for-rural-banks%E2%80%99-consolidation.

Siam Commercial Bank, 2019, Annual Report 2018, Siam Commercial Bank, Bangkok, https://www.scb.co.th/content/dam/scb/investor relations/documents/financialinformation/en/2018/annual-report/annual-report-en-2018.pdf

Smart Campaign, 2019, Handbook on Consumer Protection for Inclusive Finance, Center for Financial Inclusion, Washington, D.C., https://www.smartcampaign.org/tools-a-resources/1210-handbook-onconsumer-protection-for-financial-inclusion.

SmartPay, 2018, mPOS vs EFTPOS – How do they compare, https://www.smartpay.co.nz/blog/mpos-vseftpos-how-do-they-compare/. Square, 2018, mPOS – How to choose the right mobile POS system, https://squareup.com/au/en/townsquare/mpos-how-to-choose-the-right-mobile-pos-system.

State Bank of India, 2020, https://sbi.co.in/.

State Bank of Pakistan, 2007, 'Revised Branch Licencing Policy', BPRD Circular, No. 15 of 2007, http://www.sbp.org.pk/bprd/2007/C15.htm.

Tarazi, M. & Kumar, K., 2012, Platform-level Interconnection in Branchless Banking, CGAP, January 18, https://www.cgap.org/blog/platform-level-interconnection-branchless-banking.

Thakur, A., Sahoo, S., Barooah, P., Sivalingam, I. & Njoroge, G., 2016, How Female Agents Make a Difference, MicroSave Consulting, April 5, http://blog.microsave.net/2016/04/05/agency-banking-howfemale-agents-make-a-difference/.

Tsan, M., Totapally, S., Hailu, M. & Addom, B., 2019, The Digitalisation of African Agriculture Report, 2018–2019, CTA, Wageningen, The Netherlands, https://www.cta.int/en/digitalisation/all/issue/thedigitalisation-of-african-agriculture-report-2018-2019-sid0d88610e2-d24e-4d6a-8257-455b43cf5ed6.

UNCDF, 2017, PoWER Access and Agency Country Assessments: Ethiopia, United Nations Capital Development Fund, New York.

UNSGSA, 2019, Regulatory Sandboxes Not Always the Answer for Regulating Inclusive FinTech, Says New Report Commissioned by the UNSGSA, February 14, https://www.unsgsa.org/resources/news/regulatory-sandboxes-not-always-answer-regulatinginclusive/.

UNSGSA FinTech Working Group and CCAF, 2019, Early Lessons on Regulatory Innovations to Enable Inclusive FinTech: Innovation Offices, Regulatory Sandboxes, and RegTech, Office of the UNSGSA, New York, and CCAF, Cambridge, UK, https://www.unsgsa.org/files/2915/5016/4448/Early_Lessons_on_Regulatory_Innovations_to_Enable_I nclusive_FinTech.pdf.

WalletBuddy, 2017, 'POS Terminal Penetration in India – A closer look', Medium, May 9, https://medium.com/walletbuddy-insights/pos-terminal-penetration-in-india-a-closer- ook6b012e028285.

World Bank Group, 2012, Financial Inclusion Strategies – Reference Framework, World Bank Group, Washington, D.C., http://documents.worldbank.org/curated/en/801151468152092070/pdf/787610WP0P144500use0only0900A9RD899.pdf.

World Bank Group, 2019a, Mobile cellular subscriptions (per 100 people) – Kenya, India, Ethiopia, https://data.worldbank.org/indicator/IT.CEL.SETS.P2?locations=KE-IN-ET.

World Bank Group, 2019b, Commercial bank branches (per 100,000 adults) – Sub-Saharan Africa, Ethiopia, https://data.worldbank.org/indicator/FB.CBK.BRCH.P5?locations=ZG-ET.

World Bank Group, 2020a, Ethiopia's Financial Sector Reform Strategy, World Bank Group, Washington, D.C.

World Bank Group, 2020b, The World Bank In Ethiopia: Overview, https://www.worldbank.org/en/country/ethiopia/overview.

World Bank Group, 2020c, World Bank World Development Indicators 2017–2018, https://databank.worldbank.org/source/world-development-indicators.

World Bank Group, 2020d, The Global Findex Database, 2011–2017, https://globalfindex.worldbank.org/.

World Bank Group, 2020e, Global Indicators of Regulatory Governance: Data Visualization, https://rulemaking.worldbank.org/en/data/visualization.

World Bank Group, 2020f, G20 Financial Inclusion Indicators 2008–2019, http://datatopics.worldbank.org/g20fidata/.

World Bank, Better Than Cash Alliance & Bill & Melinda Gates Foundation for G20, 2014, The Opportunities of Digitizing Payments, World Bank Group, Washington, D.C., https://docs.gatesfoundation.org/documents/g20%20report_final.pdf.

Yoco, 2019, Unlocking digital merchant payments in Africa, https://www.yoco.co.za/blog/yocopulse/unlocking-digital-payments-in-africa/

የግርጌ ማስታወሻ

1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በአዋጅ ቁጥር 718/2003 እና 591/2000 በተሰጠው ስልጣንና ሃላፊነት መሰረት
2. ሀገር በቀል የሪፎርም አጀንዳ (ገንዘብ ሚኒስቴር), የ10አመት ሀገራዊ መሪ እቅድ (2020—2030) (PDC), ብሄራዊ ዲጅታል ትራንስፎረሜሽን ስትራቴጂ (ሚ.ኢ.ቴ), የተመቸ የንግድ አሰራር ሪፎርም (የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን), ብሔራዊ የዲጅታል መታወቂያ መራሀ ግብር (ሰላም ሚነሰቴር), የቴሌኮሚኒኬሽን ዘርፍ ሪፎርም (ገ.ሚ, የኢ.ቴ.ሚ, የኢ.ኮ.ባ).
3. የክፍያ መሳሪያ አዉጪዎች መመሪያ (ONPS/01/2020) (https://www.nbe.gov.et/wp-content/uploads/pdf/proclamation/oversight-thenational-payement-system.pdf) እና የወኪል አጠቃቀም መመሪያ (FIS/02/2020) (https://nbebank.com/wp-content/uploads/pdf/directives/bankingbusiness/use-of-agents.pdf).
4. ውጤታማነትን ለመለካት የምንጠቀምባቸዉ መንገዶች: የፋይናንስ አካታችነት "አጠቃላይ የህዝብ ብዛት ለባንክ ሒሳብ በማካፈል" ይለካል (World Bank Group 2020d); መሰረተ ልማት "በሞባይል ስልክ ስትጭት " ይለካል (World Bank Group 2019a); ትግበራ "በዲጅታል ክፍያ የላከ እና የተቀበለ ህዝብ ብዛት" ይለካል (World Bank Group 2020d); የህግ ማዕቀፍ በ "አለምአቀፍ የህግ አስተዳደር ማሳያዎች" ይለካል (World Bank Group 2020e); እና ፈጠራ "ለፊንቴክ የፈጠራ ከባቢን በማመቻቸት" ይለካል(UNSGSA 2019).
5. በኢ.ብ.ባ ግምት ከችርቻሮ ክፍያ ዉስጥ በጥሬ ገንዘብ የሚፈጸመዉ ክፍያ 90% ይሆናል.
6. የክፍያ መሳሪያ አዉጪዎች መመሪያ (ONPS/01/2020) (https://www.nbe.gov.et/wp-content/uploads/pdf/proclamation/oversight-thenational-payement-system.pdf) እና የወኪል አጠቃቀም መመሪያ (FIS/02/2020) (https://nbebank.com/wp-content/uploads/pdf/directives/bankingbusiness/use-of-agents.pdf).
7. https://pmo.gov.et/media/documents/Ethiopia-0509_Economic_Reform_Agenda.pptx. ተመልከት
8. በፕላኒንግ እና ዴቬሎፕመንት ኮሚሽን በመሰራት ላይ ያለ
9. ኤሌክትሮኒክስ ትራንዛክሽን አዋጅ ቁጥር 1205/2012
10. ውስን ጥሬ ገንዘብ መጠቀም ለሶስት አመት ስትራቴጂክ እቅድ ማድረግ በዉቀት ላይ የተመሰረተ ምርጫ ሲሆን ጥሬ ገንዘብ የማይጠቀም የሚለዉ እቅድ ግን የረጅም ጊዜ ማዕቀፍ ፍላጎት ነዉ። .
11. በፕላኒንግ እና ዴቬሎፕመንት ኮሚሽን በመሰራት ላይ ያለ
12. ምስሎች ከሳህራ በታች ባሉ ሀገራት ለ2019 ተገመተዉ የአከባቢዉን የ5 አመት አመታዊ እድገት ላይ ተመስረቶ ነዉ።.
13. በኢትዮጵያ ሞባይል ወኪል የተጀመረው በባንክ ወኪል ነዉ (የወኪል ክትትል የተፈቀደዉ ለባንክና አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ብቻ ነዉ).
14. በብሔራዊ የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ ምክክር
15. አዉቶሜትድ ክሊሪነግ /ማጣሪያ/ ሀዉስ/ማዓከል/
16. በብሔራዊ የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በተናጠል እንዲሁም በጋራ የተደረገ ምክክር
17. በብሔራዊ የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በተናጠል እንዲሁም በጋራ የተደረገ ምክክር
18. በብሔራዊ የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ ምክክር
19. ማንኛዉም ሰዉ ለማንኛዉም ሰዉ የባንክ ሂሳብ/የሞባይል ሂሳቡ የትኛዉም ተቋም ይገኝ ክፍያ እዲፈጽም ያስችለዋል። ይህ ሁለት ሰወች በዲጅታል አማካኝነት ገንዘብ እዲከፋፈሉ ከማስቻሉም በላይ ዲጅታል አጠቃቀምን ይጨምራል
20. https://www.nets.com.sg/ ተመልከት
21. የ2013 እና 2014 የወኪሎች መረጃ አልተገኘም
22. ዋና ዋና ችግሮች ብቻ- ቁጥሮች በመቶኛ አልተደመሩም

23. መረጃዎቹ ከኢትስዊች ስርአት ጋር የተሳሰሩና በሚሰሩ የመክፈያ ማሽኖች መሠረት የተደረገ ነው፡ እንደ ሀይል መቆራረጥ ምክያቶች አጠቃላይ መረጃውን ሊጎዳቸው ይችላል፡፡

24. በህንድ ለምሳሌ ማዕከላዊ ባንኩ ሁሉም የክፍያ ኦፐሬተሮች የተበላሹ የገንዘብ መክፈያ ማሽኖች፣ ሰዊች ማሽኖች፣ በአንድ ቀን እና ሌሎች የክፍያ ስርአት ጋር ተያይዞ የሚታዩትን ችግሮች በአምስት ቀናት እንዲፈቱ መመሪያ አስተላልፏ፡፡ (AEPS–see http://cashlessindia.gov.in/aeps.html) ለእያንዳንዱ ቀን መዘግየትም ከ 1.33 የአሜሪካ ዶላር ቅጣት ተጥሏል (Manikandan, 2019)፡፡

25. የኢብባ መረጃ 2020

26. ዓለምባንክ 2018

27. ኢትዮ ቴሌኮምን ጨምሮ ሁሉንም የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚያስተዳድር የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዋጅ በመረቀቅ ላይ ይገኛል፡፡ የህብረተሰብ አቀፍ ግዴታ ማዕቀፍ (የአዋጁ ቁልፍ አካል ነዉ) በመንግስት ወጪ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሁሉንም የግልም ይሁን የመንግስት የተወዳዳሪነት አዝማሚያ እንዲኖራቸዉ ያስችላል በተጨማሪም መንግስት ከሚያፈሰዉ መዋእለንዋይ በጥራትና በፍጥነት ፕሮጀክቶችን ይቀርጻል፡፡

28. ለልዩ ሞባይል ተጠቃሚዎች ተተኪ ተወስዷል

29. የኢትዮጵያ ቢዝነስ ፖርታል– https://www.eservices.gov.et/business/ ተመልከት .

30. በብሔራዊ ዲጂታል ስትራቴጂ ዝግጅት ወቅት ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ ምክክር

31. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መረጃ

32. የምርታማነት ሴፍቲኔት ፕሮግራም በገንዘብ ሚኒስቴር በቅርበት ክትትል የሚደረግበት ከለጋሶች የሚገኝ ገንዘብ ነዉ፡፡ አተገባበሩም በግብርና ሚኒስቴር አማካኝነት ነዉ

33. ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ ቃለምልልስ

34. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መረጃ 2020 (አዲስ አበባ ክፍያ መፈጸሚያ ስርጭት: የባንክ ቅርንጫፍ 34.7በመቶ, ኤ.ቲ.ኤም 46.9 በመቶ, እና የክፍያ ነቁጦች 77.0 በመቶ)

35. የኢትዮጵያ ብሔብዊ ባንክ የስትራቴጂ ማስቀመጫ ነዉ፡፡ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ አገር አቀፍ ስትራቴጂ ሲሆን በአገር አቀፍ ካዉንስል ዉስጥ የገንዘብ ሚኒስቴር፣የግብርና ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ብሔብዊ ባንክ፣ ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽንና የኢትዮጵያ ልማት ጥናት ኢንስቲትዩት ይገኙበታል፡፡

36. የ ቦስተን ኮንሰልቲንግ ግሩፕ ትንተና .

37. https://www.worldremit.com/en/mtn-mobile-money ይመልከቱ

38. https://verdant-cap.com/orange-launches-international-money-transfer-service-orange-money/ ይመልከቱ

39. https://bankinnovation.net/allposts/biz-lines/payments/worldremit-now-handles-75-of-mobile-remittances-looks-to-add-android-pay/ ይመልከቱ

40. https://www.xoom.com/ ይመልከቱ

41. https://transferwise.com/ ይመልከቱ

42. https://www.currencyfair.com/ ይመልከቱ

43. https://www.abra.com/technology/ ይመልከቱ

44. https://www.bitpesa.co/ ይመልከቱ

45. በብሔራዊ የዲጂታል ስትራቴጂ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ ዉይይት

46. በብሔራዊ የዲጂታል ስትራቴጂ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ ዉይይት

47. ሴንድ ዌቭ የአሜሪካ ዲጂታል ክፍያ መሳሪያዎች በኬኒያ ኤም-ፔሳ ጋር መዋሀድ ገንዘብ ቀጥታ ከ አሜሪካ ወደ ሀገር ዉስጥ ወደሚገኝ ኤም-ፔሳ ሒሳብ እዲተላለፍ አስችሏል፡፡,

48. https://www.fundacioncapital.org/home ተመልከት

49. ኢብባ የስትራቴጂ ማስቀመጫ ነዉ፡፡ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ አገር አቀፍ ስትራቴጂ ሲሆን በአገር አቀፍ ካዉንስል ዉስጥ የገንዘብ ሚኒስቴር፤የግብርና ሚኒስቴር፤ ኢብባ፤ ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽንና የኢትዮጵያ ልማት ጥናት ኢንስቲትዩት ይገኙበታል

50. እ.ኤ.አ2011 እና 2017 ባሉ አመታት የጾታ ልዩነት በ 8በመቶ ወርዷል

51. ተግባር 21፡ከፋይናንስ አገልግሎቶች የተገለሉትን የህብረተሰብ ክፍሎችን ያማከለ አገልግሎቶችንና መፍትሔዎችን ማስጀመር

52. እንደ እያንዳነዱ ሀገር ገበያ ደንበኛህን እወቅ በተቀማጭ ገንዘብ ሰብሳቢዎች ወይም በኤሌክትሮኒክ ገንዘብ አዉጪዎች ሊከናወን ይችላል፡፡

53. የኔትዎርክ ኦፕሬተሮች ኢ-ገንዘብን ለማግኘት የተለየ የህግ ተቋም በማቋቋም ፍቀድ ማግኘት አለባቸዉ

54. ብሔራዊ እይታ #3: licensesኢትዮ ቴሌኮምን ወደግል በማዞርነዘ ሁለት የቴሌኮም ፍቃድ በመስጠት የሚገኝ ገቢ

55. ሙሉ በሙሉ በመንግስት የተያዘ ተቋም ወይም ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያዉያን ወይም በትዉልደ ኢትዮጳያን የተያዘ ወይም በኢትዮጵያውያን እና በትውልደ ኢትዮጳያን በጋር የተያዘ ኩባንያ

55. የባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2008 ተመልከት (https://nbebank.com/wpcontent/uploads/2019/04/BANKING-BUSINESS-592.pdf) and Banking (Amended) Business Proclamation No. 1159/2019 (https://nbebank.com/wp-content/uploads/pdf/directives/bankingbusiness/banking-businessproclamation-1159-2019.pdf).

56. የ G20 መመሪያ በ ፋይናንስ ተጠቃሚዎች ጥበቃ በዲጅታል ዘመን፤ የ የፋይናንስ ጥበቃ ለአካታች ፋይናንስ ሀንድ ቡክ ስድስተኛዉ ምዕራፍ፤ ስማርት ካምፔይን ክሊያንት ፕሮትክሽን ፕሪነሲፕልስ ሶስተኛዉ መርህ፤ የጂ.ፒ.ኤፍ ሀይ ሌቭል ፕሪነስፐልስ ፎረ ዲጅታል ፋንንሻል ኢነክሉዥን አምሰተኛዉ መርህ፤ የጂኤስ ኤም ኤ የስነምግባር ደንብ መመሪያ 6.1.1፡ የፋናንስ አካታችነት ከክፍያ አኳያ ሪፖርት መመሪያ መርህ 2 እና 5

57. የጂ.ፒ.ኤፍ 2016 ሀይ ሌቭል ፕሪነስፐልስ ፎረ ዲጅታል ፋንንሻል ኢነክሉዥን : የ2016 አዉሮፓ ህብረት መረጃ ጥበቃ ህግ፡ የ ሲኤፍ አይ 2019 የፋይናንስ ጥበቃ ለአካታች ፋይናንስ ሀንድ ቡክ ዘጠነኛዉ ምዕራፍ - ግላዊነትና የደንበኞች መረጃ ደህንነት፡ በእ.ኤ.አ 2018 ዩናይትድ ኪንግደም የክፍያ ስረዓት ህግ በክፍያ ኢነደስተሪ ላይ የተደረገ የዉይይት ወረቀት ፡እ.ኤ.አ2013 OECD የግላዊነት ጥበቃና ድንበር ተሸጋሪ የግለሰብ መረጃ መመሪያ:የጂኤስ ኤም ኤ የስነምግባር ደንብ መመሪያ 8፡.

58. https://chilot.me/wp-content/uploads/2014/09/proclamation-no-808-2013-information-network-security-agency.pdf ተመልከት

59. የክፍያ መሳሪ አዎጪዎች መመሪያ (ONPS/01/2020) (https://www.nbe.gov.et/wp-content/uploads/pdf/proclamation/oversight-thenational-payement-system.pdf) and Use of Agents Directive (FIS/02/2020) (https://nbebank.com/wpcontent/uploads/pdf/directives/bankingbusiness/use-of-agents.pdf)

60. ፊነቴክ ድረጅቶች በተለምዶ በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚነሰስቴር ነዉ ፍቃድ ሚሰጣቸዉ ይህም ፍቃዱ ሚያመላክተዉ ለቴክኖሎጂ ነዉ እንጂ ለፋይናንስ አገልግሎት እዳልሆነ ያሳያል.

61. የባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር No. 592/2008 ተመልከት (https://nbebank.com/wpcontent/uploads/2019/04/BANKING-BUSINESS-592.pdf) and Banking (Amended) Business Proclamation No. 1159/2019 (https://nbebank.com/wp-content/uploads/pdf/directives/bankingbusiness/banking-businessproclamation-1159-2019.pdf).

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
ADDIS ABABA

P.O.Box: 5550
Tel: +251 115 517 430
Fax: +251 115 514 588
E-Mail: nbe.edpc@ethionet.et